
# ሐመር

ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

ሐመር ፲፫ኛ ዓመት ቁጥር ፯ መስከረም/ ጥቅምት ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.




©ማኅበረ ቅዱሳን 

# ከአንባብያን ለአንባብያን

## ስለ ሀገር ማዘንና መጸለይ ይገባል

ይህን አስተያየት ለመስጠት ያነሣሣኝ በሐምሌ/ነሐሴ 1997 ዓ.ም የሐመር መጽሔት እትም «ምርጫና ቤተ ክርስቲያን» በሚል ርእስ ከአንድ አንባቢ የተሰጠው ሐሳብ ነው:: በሀገራችን ግንቦት ሰባት ቀን 1997 ዓ.ም የተካኼደውን ሦስተኛውን ብሔራዊና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ እንዲሁም በተጓዳኝ የተፈጠሩ ነገሮችን በተመለከተ ቤተ ክርስቲያናችን በመገናኛ ብዙኀን የበኩሏን መግለጫዎች መስጠቷ ይታወሳል:: በዚህ ዙሪያ ተክሊት ኪዳኑ የተባሉ አንባቢ በሰጡት አስተያየት:- «እኛ ክርስቲያኖች ስለ ሃይማኖታችን እንጂ ስለ ዓለማዊ ፖለቲካ ምን አገባን?» ብለውናል:: እኔ የምለው÷ ጥንታዊቷና ታሪካዊቷ ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት ያቀናቻት ሀገር ጉዳይ አያገባት ምን? ጠባ ለኪዳን መሸ ለቍርባን የምትጸልየው ጸሎት የምታቀርበው መሥዋዕት በዓለም ሰላም እንዲወርድ አይደለምን? ሀገራችን እንኖርባት ዘንድ ከእግዚአብሔር የተሰጠችን ናት'ኮ:: አንድ ሰው መኖር፣ መጠራትና አምልኮተ እግዚአብሐርን መፈጸም የሚችለው ሀገር ሰላም ስትኾን ብቻ ነው:: በሀገር ላይ ችግር ከመጣሁላችንም የችግሩ ገፈት ቀማሾች ነን:: ስለዚህም አሁንም ኾነ ለምንጊዜውም እግዚአብሔር ኢትዮጵያችንን ከሚሰሙት፣ ከሚታዩት፣ ከሚገመቱት አስጨናቂ ነገሮች ሁሉ እንዲጠብቅልን፤ ለሁሉም እውነቱን ገልጦ መተማመንና መስማማትን እንዲሰጥልን መጸለይና ተቀባይነት ያለው የማቀራረብ ተቋማዊ ሚናዋን መጫወት የቤተ ክርስቲያናችን ታሪካዊና መንፈሳዊ ሓላፊነቷ ነው:: ይኸን ሲሆን ነው እኛ ልጆችዋ በየትኛውም ቦታና ጊዜ አንገታችንን ቀና አድርገን ስለ ማንነታችን በሙሉ እምነት ልንናገር የምንችለው እላለሁ::

*ዲ/ን ስንታየሁ ሥዩም*
*ወላይታ ሶዶ*

## መሥዋዕትነት ለእውነትና ለመተማመን

ይህን ደብዳቤ ለመጻፍ ያነሣሣኝ ለረዥም ጊዜ በውስጤ ሲመላለስና ሲረብሸኝ የቆየ ጉዳይ ነው:: እኔ ውስጥ ያለው ጭንቀት በእናንተም ኾነ በሌላው ክርስቲያን ውስጥ ላለመኖሩ ምንም ማረጋገጫ የለኝም:: በረከታቸው ይደርብን በቅርቡ ያረፉት ብፁዕ አቡነ ሰላማ የተናገሩትን መጥቀስ እሻለሁ:: «ልጆቼ÷ አባካችሁ እናንተ የምታስቡትን እኛም ሳናስበው የቀረን አይምሰላችሁ፤ ለዚህች አገርና ለሕዝብዋ ለምን መሥዋዕት አትኾኑም፤ ትሉናላችሁ? ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ማንም ተነሥቶ ቢሞት ከንቱ ሞት ነው፤ ሞቱም ቢፈልጉት አይቻልም፤ ከእግዚአብሔር ከታዘዘ ግን ማንም ወደ ኋላ ሊል አይችልም:: በአገራችንና በሕዝባችን ላይ የሚደርሰው መከራ ሳይሰማን ቀርቶ አይደለም:: ምነው÷ ከእርሱ ዘንድ መጥቶ እኔም በተሠዋሁ!!» ብለው ነበር:: አዎ÷ መሥዋዕትነት በየመልኩ ነው:: ዛሬ መናገር የሚገባቸው ሁሉ እውነቱ ይታወቅ ዘንድ መጠየቅ ባለባቸው ትክ ክለኛ ጊዜ ላይ እንገኛለን:: እውነቱ ይታወቅ ዘንድ ደግሞ ተቀራርቦ መነጋገር የግድ ነው:: መነጋገር ከቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር፤ መነጋገር ሀገርን እንመራለን ብለው ከሚወዳደሩ ወገኖች ጋር:: ማኅበረ ቅዱሳን ለዚህ በጎ ዓላማ የበኩሉን ድርሻ ሊወጣ ይገባል:: በኢትዮጵያችን ውስጥ ያንገቦ በበውን አደጋ ከመሸፋፈን ይልቅ በት ክክለኛ ገጽታው ተመልክቶ መፍትሔውን መሻቱ ለሁላችንም ይጠቅማል::

*የወንድ ወሰን ሰብስቤ*
*ለንደን*

## «በምን አለበት ክብር ቀረበት»

በቅርቡ በአዲስ አበባ የተለያዩ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በሠርክ ሰዓት በሚሰጡ የዐውደ ምሕረት ትምህርቶች ተገኝቼ ነበር:: በስብከተ ወንጌሉ ረገድ ያለው እንቅስቃሴ በጣም ደስ አሰኝቶኛል:: በሌላ በኩል ግን ፈሪሃ እግዚአብሔር ያነሰ ይመስለኛል:: ይኸውም ዐውደ ምሕረቱ ሴቶችና ወንዶች ሳይለያዩ የሚቀመጡበት መኾኑ ነው:: የእኅቶቻችን አለባበስ ቅጡን አጥቷል:: ሁኔታቸው ማንንም ይፈትናል፤ አጋነንክ ባትሉኝ መረን የለቀቀም ይመስለኛል:: ምናልባት እኅቶቻችን «ምን አለበት፤ መብታችን ነው፤ ምርጫችን ይከበር» ሊሉ ይችሉ ይሆናል:: ይህ ዓይነቱ የግዴ ለሽነት መልስ ግን ለሰው ኅሊና አለመጠንቀቅና ራስ ወዳድነት ነው:: ጉዳዩን ልናስብበት ይገባል:: «በምን አለበት ክብር ቀረበት...» እንዲሉ::

*መ/ር ገብረ ሥላሴ*
*ቡሬ*

## ማስተካከያ

ባለፈው የሐመር መጽሔት እትማችን ከመጽሔቱ የጀርባ ሽፋን ላይ ዜና መጻሕፍት በሚል ርዕስ በወጣው ማስታወቂያ ለተከሰተው የአድራሻ ስሕተት ይቅርታ እየጠየቅን ትክክለኛው አድራሻ እንደ ሚከተለው ነው:-

**ስልክ (09) 63-63-93 ወይም 20-04-38**
**E:mail: yakobzz@yahoo.com**
**P.O.Box 1243 መሆኑን እንገልጻለን**

በ13ኛ ዓመት ቁጥር አራት ሐምሌ/ነሐሴ 1997 ዓ.ም ሐመር መጽሔት እትም ላይ የታዩትን ግድፈቶች በሚከተሉት ማረሚያዎች እንድታነቧቸው ከይቅርታ ጋር እንጠይቃለን::

- «ኅሡ ሰላመ ወዴግንዋ፤ ሰላምን ሿት÷ ተከተሏትም» /የሽፋን የውጭ ገጽ/ የሚለውን «ኅሡ ሰላመ ወዴግኑ፤ ሰላምን ሹ÷ ተከተሉም::»
- ዲያቆን ታደሰ አያሌው፣ ዲያቆን የማነ ኃይሉ፣ ▪ዲያቆን ዳንኤል ገብረ መድኅን /ገጽ 21-22/ የሚሉትን መ/ር ታደሰ አያሌው፤ አቶ የማነ ኃይሉ፣ አቶ ዳንኤል ገብረ መድኅን
- እ6ቤታችን ያፈችው ጥር 21 ቀን 1950 ዓ.ም ነው:: /ገጽ 16/ የሚለውን▪ እመቤታችን ያረፈችው ጥር 21 ቀን 50 ዓ.ም ነው::
- ንቡረ እድ አባ ገብረ ማርቆስ የሚለውን ንቡረ እድ አባ ወልደ ማርቆስ

**የሐመር መጽሔትና የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ደንበኛ ይሁኑ**

| | ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ | | ሐመር መጽሔት | |
|---|---|---|---|---|
| | የ6 እትም | 12 እትም | የ6 እትም | 12 እትም |
| ለአዲስ አበባ | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| ለክፍለ ሀገር | 12.00 | 24.00 | 25.00 | 50.00 |
| አፍሪካ | 9 ዶላር | 18 ዶላር | 12 ዶላር | 24 ዶላር |
| አውሮፓና መካከለኛው ምሥ | 12 ዶላር | 24 ዶላር | 15 ዶላር | 30 ዶላር |
| አሜሪካና ሩቅ ምሥራቅ | 15 ዶላር | 30 ዶላር | 18 ዶላር | 36 ዶላር |

ለማኅበረ ቅዱሳን ልማት ተቋማት የባንክ ሂሣብ ቁጥር 81164 ሥላሴ ቅርንጫፍ
Mahibere kidusan Lemate Tequamat
አድራሻዎንና የከፈሉበትን ደረሰኝ ኮፒ በመልእክት ሣጥን ቁጥር 80078 ይላኩልን
ወይም በ E-mail Mk_distribution @ Yahoo.com

መዓርገ ጵጵስና ሐላፊነቱ ከባድ፣ ሥርዓቱም በራሱ በባለቤቱ የተሰናዳ ሰማያዊ ነው:: ይህንንም ጌታችን በፈጸመውና ከላይ በመጠኑ ከተተረከው ሥርዓተ ሢመት እንረዳለን:: ሐላፊነቱ ከባድ ነው ስንል «እሺ፣ ይደረግልኝ» ብሎ ከመቀበል በፊት ከጉባኤ ጉባኤ ተዟዙሮ፣ ከሊቃውንት እግር ሥር ውሎና አድሮ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን መርምሮ ሰፊ የነገረ ሃይማኖት፣ የሥርዓተ እምነትና የታሪክ እንዲሁም የክርስቲያዊ ትውፊት ዕውቀትን ይዞ መገኘት ይጠይቃልና::

## የማኅበሩ መልእክት

ጌታ ለእኛ ስለ ተቀበለው መከራ ወንጌላውያን የጻፉትን መሠረት አድርገን ስንመለከተው መከራው የሚጀምረው ከጌቴ ሴማኒ ነው:: ማር.14÷32–49:: ጌቴ ሴማኒ የቃሉ ትርጉም የዘይት መጭመቂያ ማለት ነው:: አካባቢው በወይራ ዛፍ የተሞላ እንደ ነበር ነው የሚተረከው:: ንጉሥ ዳዊት ተራራውን ሁሉ የወይራ ዛፍ አስተክሎበት ነበር:: እንዲያውም ጌታ በሥጋው ወራት በምድር ይመላለስ በነበረበት ጊዜ የነበሩ መሆናቸው የሚነገርላቸው ስምንት የወይራ ዛፎች ዙሪያቸው በድንጋይ ተደግፈው ይታያሉ::

## ከሰሞኑ በረከት

ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን መንፈሳዊ ትምህርት ቤትን ጥር 14 ቀን 1965 ዓ.ም መርቀው ሲከፍቱ:- «ለመተዳደርያው በጀት (ርዳታ) ይፈቅ ዱልኛል» የሚል ተስፋ ነበራቸው:: ይህንንም በምረቃው ዕለት ባደረጉት ሰፊ ንግግር እንደሚከተለው ገልጠውት ነበር:- «ግርማዊ ሆይ÷ልዑል እግዚአብሔር አባታችን አዳምን÷አካሉን አሣ ምሮ ውበቱ እንደ አበባ የሚያሽበርቅ፣እንደ ፀሐይ የሚያንጸባርቅ፣ይህ ቀረኸ የማይባል ውብና መልክ መልካም አድርጎ ፈጠረው፤ በኋላ በአፍንጫው የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት፤ የሚንቀሳቀስም ሕያው ፍጥረት ኾነ:: ይህም ትምህርት ቤት አሁን የሚታየው አካሉ÷መልኩና ውበቱ ብቻ ነው:: ሕይወት ኖሮት እንዲንቀሳቀስ፣ሕያው ትምህርት ቤት እንዲኾን የግርማዊነትዎን የሕይወት እስትንፋስ ይፈልጋል:: ግርማዊነትዎ እፍ እንዲሉበት ይማፀናል::»

## እናስተዋውቃችሁ

ዋና አዘጋጅ - ዲ.መርሻ አለኸኝ
ም/ዋና አዘጋጅ- አሉላ ጥላሁን
ከፍተኛ ሪፖርተር - መ/ር ኃይለ ማርያም ላቀው
ሪፖርተር - ዲ/ን ፋሲል አስረስ
ኮምፒዩተር ዲዛይን - ወይንሸት ወጉ
ኮምፒዩተር ጸሐፊ - ፍቅርተ ኃይሌ
ስልክ 556328
ፖስታ 80078
አዲስ አበባ
E -mail:Hamer@EOTC-Mkidusan.org
Website: – www.EOTC-Mkidusan.org

«ማኅበረ ቅዱሳን»

እግዚአብሔር ያከበራቸው የነቢያት፣የሐዋርያት፣የጻድቃን፣ የሰማዕታት በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ትሩፋትና አማላጅነት የሚዘከርበት በመሆኑ ይህን ስያሜውን አግኝቷል::

ሐመር
፲፫ኛ ዓመት ቁጥር ፭
መስከረም/ጥቅምት ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

# ይዘት

**የማኅበሩ መልእክት**
- ብዙ ከተሰጠው ከእርሱ አብዝተው ይሹበታል ........ ፪

**ደብዳቤዎች** ........ ፬

**ከሰሞኑ በረከት**
- የመስቀሉ መስቀላዊ ጉዞ ........ ፯

**ትምህርተ ሃይማኖት**
- ያዕቆብ ዘሥሩግ ሕይወቱ፣ ትምህርቱ ........ ፱
- ነገረ ድኅነት በመጽሐፈ ቅዳሴ ........ ፲፪

**ጥያቄዎቻችሁ**
- የቅዱሳን መሰወር ........ ፲፭

**ኪነ ጥበብ**
- ምንደኛዋ ........ ፲፱

**እናስተዋውቃችሁ**
- ኮከብ እማእከለ ከዋክብት ........ ፳፩
- ቅዱስ ቆስጠንጢኖስ ........ ፳፬

**ዓምደ ወራዙት**
- የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ........ ፳፯

**ሐመረ ሕይወት**
- የጠባይ ለውጥ እንዴት? ........ ፴

**ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ**
- በየጥቂቱ ማደግ ........ ፴፪

**ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ**
- ሥርዓተ ማሕሌት ........ ፴፭

**ወቅታዊ ጉዳዮች**
- «ዘመን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጠው የመኖሪያ ፈቃድ ... ነው::» ........ ፴፯

**እቡጊዳ - የግእዝ ቋንቋ ትምህርት**
- ካልአይ አንቀጽ ........ ፵

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የኅትመት ዝግጅት ማስተባበርያ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ::

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የማኅበሩ መልእክት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ::

## «ብዙ ከተሰጠው ሰው ሁሉ ከእርሱ ብዙ ይፈለግበታል ÷ ከእርሱ አብዝተው ይሹበታል::»

« ... ወነገሮሙ በእንተ መንግሥተ እግዚአብሔር ወበእንተ ተስፋሁ ለአብ ወባረኮሙ በሣ
ወረሰዮሙ አማልክተ÷ስለ አብ ተስፋና ስለ እግዚአብሔር መንግሥትም ነገራቸው፤ እጁንም በመጫ
ማቸው፤ መምህራንም አደረጋቸው:: ...» /መዝገበ ሃይማኖት፣ ገጽ 20/::
ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን ስለማዳን በአባቱ ፈቃድ፣ በራሱና በመን
ወርዶ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም በመንፈስ ቅዱስ ያለ ዘርዐ ብእሲ ድንግልናዋ ሳይለወጥ ሰው
ደርሳ ለአዳም በደል ቤዛ ይሆን ዘንድ በመስቀል ላይ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶ በምስጋና ወደ አባቱ አ
ተቀመጠባት ጊዜ ድረስ፤ በለበሰው ሥጋ በመካከላችን በተመላለሰባቸው ዓመታት ሦስት መሠረ
በቃልና በትእዛዝ ብዙ ተኣምራትን አድርጓል፤ የመንግሥቱን ወንጌል አስተምሯል፤ በደሙ
ክርስቲያን ትተዳደርባቸው ዘንድ በርከት ያሉ ሥርዓቶችን ሠርቷል::
ጌታችን ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ደኅንነት፣ ስለ አገልግሎቷ ሥምረትና ስ
የደነገጋቸውንና የሠራቸውን ሥርዓቶች ስንመለከት ደግሞ የማዳን ሥራውን በመስቀል ላይ ከፈ
በኋላ የሠራቸው ሆነው እናገኛቸዋለን:: «ወሤመ ሐዲሰ ሕገ፤ ለሐዲስ ሕግ ÷ ለአዲስ ሕዝብ አዲ
የማዳን ሥራውን የሲያልን ግድግዳ በማፍረስ፣ ሰይጣንን በማሰር፣ ሞትንም በመስቀሉ ኃይል ወ
እንደ መሆኑ አዳምን ከልጆቹ ጋር በደሙ አጥምቆ ካዳነው፣ ነጻም ካወጣው፤ ወደ ርሱም ካቀረበወ
ውስጥ ደግሞ አንዱና ዋነኛው ሥርዓተ ሢመተ ጵጵስና ነው::
ጌታችን በደሙ ዋጅቶ የመሠረታት፣ አሁንም ራሷ ሆኖ በቅዱስ መንፈሱ እያበረታታ የ
ቤተ ክርስቲያኑ፤ በቅዱስ ቃሉ እንደ ተነገረ በመቅረዝ ላይ ያለች መብራት ሆና በጨለማ ይ
እንድትሆን /ማቴ.5÷14/ በፈጻሚነትም በአስፈጻሚነትም ያገለግሉ ዘንድ ለመጀመሪያ ጊዜ ደቀ
ሾሟቸዋል:: በቅዱሳት መጻሕፍት እማኝነት መሠረት ጌታችንን ይህን ሥርዓት የሠራው ከትንሣ
ተሰብስበው በተቀመጡበት ቤት ተገልጦ ነው:: /ዮሐ.21÷14/:: «ወበአርብዓ ዕለት እምትንሣኤሁ
ወናሁ ሣልሱ ዝንቱ ዘአስተርአዮሙ፤ አኮ በምትሐት፤ ወአኮ በሕልም፤ አላ ገሃደ ወብሩሃ ጥዩቀ
በልብ፤ ወበአእምሮ÷ ከትንሣኤው በኋላ በአርባ ቀን ታያቸው፤ ሲታያቸውም አሁን ይህ ሦስተኛው
ውም በሕልምና በምትሐት አይደለም፤ በአእምሮ በልብ በነፍስ፤ በሥጋ የነቃ ሆኖ ግልጥና ብሩህ
እንዲል:: /መዝገበ ሃይማኖት፣ ገጽ 19/::
መዓርገ ጵጵስና ሓላፊነቱ ከባድ፣ ሥርዓቱም በራሱ በባለቤቱ የተሰናዳ ሰማያዊ ነው:: ይ
ከላይ በመጠኑ ከተተረከው ሥርዓተ ሢመት እንረዳለን:: ሓላፊነቱ ከባድ ነው ስንል «እሺ፤ ይደረግ
ከጉባኤ ጉባኤ ተዟዙሮ፣ ከሊቃውንት እግር ሥር ውሎና አድሮ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን መርና
የሥርዓተ እምነትና የታሪክ እንዲሁም የክርስቲያዊ ትውፊት ዕውቀትን ይዞ መገኘት ይጠይቃል
ጌታችን በኪደተ እግሩ ሲዟዟር አብረው የተዟዟሩትን፣ ሲራብ አብረው የተራቡትን፣ ሲጠማ
መዛሙርቱን ጳጳሳት አድርጐ ከመሾሙ በፊት፤ ምንም እንኳን አብረውት በመቆየት ከቃልም
ተአምር ብዙ እንደ ተማሩ ቢያውቅም እንደ ገና መሠረታዊ የነገረ ሃይማኖት ትምህርት አስተ
ሥልጣንም ይሁን የሚቀመጡበት ወንበር ቤተ ክርስቲያንን በብቃት መምራትን የሚጠይቅ ነውና
ሌላው የዚህ ሥርዓት ከባድነት መገለጫ ደግሞ እሱ ራሱ በሐዋርያቱ ላይ እጁን ጭኖ
ነው:: በመግቢያነት ከተቀመጠው ኃይለ ቃል እንደ ምንረዳው ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ተገል
የሚያስችላቸውን ዕውቀት ካስጨበጣቸው በኋላ ሥልጣኑን በእያንዳንዳቸው ላይ እጁን በመጫን ሰ
ሥርዓተ ሢመተ ጵጵስና ጌታችን የማዳን ሥራውን ጨርሶ ወደ ጥንት አነዋወሩ ከመሄዱ
ሠራው ሥርዓት ነው:: «ጳጳስነትም ሾማቸው፤ መምህራንም አደረጋቸው» ካለ በኋላ «ወዐርገ በስብ
ዘትካት ህላዌሁ በሥጋ ወበነፍስ...÷ በምስጋናም ወደ አባቱ ዐረገ፤ በሥጋና በነፍስ በአጥንትና
በፀጉርና በጽሕም እንዳለ በጥንት አነዋወሩ ተቀመጠ» ይላልና:: በመሆኑም ይህ ሥርዓት ከላይ ከተ
እጓለ መሕያው ክርስቶስ የማዳን ሥራው ሁሉ ማጠቃለያ ያደረገው በመሆኑ ሓላፊነቱ ከባድ÷ ሥ
ሐዋርያዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስተያን በአምላካችን ተመ
አስተላላፊነት የመጣውን ይህን ሥርዓት ተቀብላ ከብርሃናዊው የጉዞ ጅማሬዋ አንሥቶ እስከ ዛሬ
መርጣ በጵጵስና እየሾመች አገልግሎቷን ስትፈጽም ቆይታለች:: በዚህም መሠረት ባለፈው
የተሾሙትን 17 ብፁዓን አበው ጨምሮ እስከ አሁን በአጠቃላይ ከ220 በላይ ብፁዓን አበውን ሾማ
መቶ ዘጠኙ ኢትዮጵያውያን ለራሳቸው ከራሳቸው ወገን አይሹሙ» በተባሉ ጊዜ ከግብፅ
ግብፃውያን አበው ናቸው:: የቀሩት ግን በእግዚአብሔር ፈቃድና አበርቺነት፣ በኢትዮጵያውያን
መንበር ኢትዮጵያውያን መያዝ ከጀመሩበት ጊዜ ወዲህ እየተሾሙ አገልግለው ያለፉና በማገልገ
ብፁዓን አበው ናቸው::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የብፁዓን አበው መሾም ለቤተ ክርስቲያን ሁሉን ዐቀፍ አገልግሎት መፋጠን መሠረታዊ ነገር ነው:: በመሆኑም እግዚአብሔር ፈቅዶ በቅርቡ በተደረገው የኤጲስ ቆጶሳት ምርጫ አልፈው ሥልጣኑን ከሐላፊነቱ ጋር የተቀበሉት አበውም ይሁኑ ቀደም ሲል ተቀብለው ሲያገለግሉ ከቆዩትና በማገልገል ላይ ካሉት አባቶቻችን ወቅቱ የሚጠይቃቸውና በአስቸኳይ እንዲከናወኑ የሚገባቸው በርካታ ሥራዎች እንዳሉባቸው እናያለን::

የመጀመሪያው የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዐቢይ ዓላማ የሆነው ስብከተ ወንጌልን የሚመለከት ነው:: እኛም ሆን ማንኛውም የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን የአገልግሎት ስፋት የሚመኝ ሁሉ እንደ ሚለው ዛሬ በሀገር ውስጥም ይሁን ከሀገር ውጭ የቤተ ክርስቲያናችንን ድምፅ በእጅጉ የሚናፍቁ ሕዝቦች በርካታ ናቸው:: ወደ ሀገራችን ሲመጡም ሆነ በዚያው በያሉበት ሆነው በልዩ ልዩ መንገድ ከሚያስሟቸው ድምፆች ለመገንዘብ እንደ ምንችለው ለበርካታ ጥቁር ሕዝቦች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የማንነታቸው መገለጫ፣ በምድርም ይሁን በሰማይ ተስፋ መመኪያቸው ናት:: በሀገር ውስጥም ቢሆን ከመሐሉ ጀምረን ወደ ጠረፍ ወጣ እያልን በሄድን ቁጥር በአረማውያንና በመናፍቃን ተውጠው፤ የቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ድምፅ የሚናፍቁ አያሌ ወገኖቻችን አሉ:: በመሆኑም በእግዚአብሔር ፈቃድ በቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ የአመራር ወንበር ላይ የተቀመጡት ብፁዓን አባቶቻችን ለዚህ መሠረታዊ ተግባር ቅድሚያ በመስጠት እነዚህን ወገኖች በማስተማርና በማጥመቅ ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አንድነት እንደሚያገቡልን ተስፋ እናደርጋለን::

ዛሬ ቤተ ክርስቲያናችን ዘርፈ ብዙ ችግሮች አሉባት:: የትምህርተ ሃይማኖት፣ የሥርዓተ እምነት፣ የታሪክ፣ የባሕልና የትውፊት ማኅደር ሆነው ለአያሌ ዘመናት ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ሲያገለግሉ የነበሩ ገዳማት እየተፈቱ ነው፤ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንም ችግር ቢጸናባቸው ዕውቀት ለማግኘት ከወንበሮቻቸው ሥር የፈሰሱ ተማሪዎቻቸውን በትነው እየተሰደዱ ነው:: ይህ ትልቅ በቤተ ክርስቲያን የተጋረጠ አደጋ ደግሞ ነገ እንደ ዛሬዎቹ ብፁዓን አበው የቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ የአስተዳደር ወንበር የሚረከቡ አባቶችን እንድናጣ፣ የቤተ ክርስቲያን ነባር ትምህርትና ሥርዓት ለመበረዝ የሚነሣን መናፍቅ ባካበቱት የደለበ ዕውቀት በቃልም በመጽሐፍም አሳፍረው የሚመልሱ ሊቃውንትን እንድናጣ ያደርገናል:: በመሆኑም አባቶቻችን እነዚህ ኹነኛ የቤተ ክርስቲያናችን ህልውና ምንጮች ለሆኑ ገዳማትና አድባራት እንዲሁም አብነት ት/ቤቶች መጠናከር ጊዜ ሳይሰጡ መፍትሔዎችን እንደሚሰጡ ተስፋ እናደርጋለን::

ቤተ ክርስቲያናችን ለሀገሪቱ ሁሉን ዐቀፍ ዕድገት ያደረገችው አስተዋፅኦ ተዘንግቶ ትንሽም ይሁን ትልቅ ሥልጣን አለኝ የሚል ሁሉ ቤተ ክርስቲያንን በየአደባባዩ ለሀገሪቱ ድህነት ተጠያቂ እያደረገ ሲከስና ሲወነጅል እናያለን፤ ትላንት በልዩ ልዩ ዘዴ ተጠቅመው ወደ ሀገራችን የገቡት መናፍቃን ነባሯንና ጥንታዊቷን ቤተ ክርስቲያን ሲጋፉ እናያለን፤ እንሰማለን:: ቀርቦ ለተመለከተም በየሰበካ ጉባኤው በርካታ ችግሮች ይስተዋላሉ:: በመሆኑም ቤተ ክርስቲያንን የመምራት ሓላፊነት የተቀበሉ አባቶቻችን በየአህጉረ ስብከታቸው በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚሰነዘረውን ወቀሳና ዘለፋ እንዲሁም የመናፍቃን የቅሰጣ እንቅስቃሴ በቅርበት እየተከታተሉ በቃልም በተግባርም ጠንካራ መልስ በመስጠት የአባቶቻቸውን ተግባር እየደገሙ እንዲጓዙ አደራ እንላለን::

የብፁዓን አበው መብዛት ስለ ቤተ ክርስቲያ ደኅንነት፣ ስለ አገልግሎቷ ስፋት የሚጸልዩ፣ ተቀምጠውም ስለምእመናን ወቅታዊ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው እየመከሩ መፍትሔ የሚሰጡ አበው መብዛት ነው:: ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ «ይህ ወገን በጸሎትና በጦም ካልሆነ በምንም ሊወጣ አይችልም» እንዳለ /ማር.9÷29/ ዛሬ በጥንተ ጠላት ዲያብሎስ ቆስቋሽነት በሀገራችንም ይሁን በዓለም ዙሪያ ለሚታዩ ችግሮች መቀረፍ አምርረው የሚያለቅሱ፣ የእግዚአብሔርን ምሕረት የሚጠይቁ አበው በዚህ ዘመን እንዲበዙ ያስፈልጋል:: ስለዚህ ብፁዓን አባቶቻችን እኛ የመንፈስ ልጆቻቸው በሥጋም ይሁን በነፍስ እየጐዱን ካሉት ችግሮች ተላቀን የመንግሥቱ ወራ ሾች ለመሆን እንድንበቃ ወደ አምላክ የሚቀርብ ጸሎታቸውን አጥብቀን እንሻለን:: ከዚህም በተጨማሪ ከትምህርተ ሃይ ማኖቱና ሥርዓተ እምነቱ በመለስ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆች መልስ የምንፈልግላቸው በርካታ ማኅበራዊ ችግሮችና ጥያቄዎች አሉን:: በመሆኑም የምእመናንን ማኅበራዊ ጥያቄዎች በማድመጥ መልስ የመስጠት ሥልጣንና ሐላፊነት ያለበት የአባቶቻችን የአንድነት ጉባኤ /ቅዱስ ሲኖዶስ/ በግልም ይሁን በቤተሰብ ደረጃ አልፎም በማኅበራዊ ኑሮ የሚያጋጥሙትንና የቅዱስ ሲኖዶስ ድንጋጌና ትእዛዝ ለሚያስፈልጋቸው ጥያቄዎች ግልጽና የማያሻሙ መልሶች እንደሚሰጥ ተስፋ እናደርጋለን::

አጠቃላይ ሂደቶችን በጥንቃቄ ላስተዋለ ቤተ ክርስቲያናችን ያላት ቁሳዊ ሀብት ከራሷ አልፎ ለሌላው ይበቃል:: ነገር ግን ይህ ሀብት በአያያዝ ጉድለትና ግልጽ የአጠቃቀም ሥርዓት ካለመኖሩ የተነሣ እየባከነ ቤተ ክርስቲያም ከዕለት ወደ ዕለት ችግሯ እየበዛ፤ ይባስ ብሎም እርሷ ደኸይታ ሀገር ያደኸየች» እስከ መባል ደርሳለች:: በመሆኑም ነባሩን የቤተ ክርስቲያን ዕውቀት ከዘመናዊው ጋር አገናዝበው የያዙ አባቶቻችን እዚህም እዚያም በየቦታው የሚባክነው የቤተ ክርስቲያናችን ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብት እንዲሰበሰብና ለቤተ ክርስቲያ ኹነኛ አገልግሎት እንዲውል ያደርጋሉ የሚል ተስፋ አለን:: ለዚህም ከላይ ጀምሮ እስከታችኛው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር ድረስ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው የሀብት አሰባሰብና አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል እንላለን::

በቤተ ክርስቲያናችን በአላስፈላጊ ሁኔታ ሲባክኑ ከምናያቸው ሀብቶች መካከል አንዱ የሰው ኃይል ነው:: ቤተ ክርስቲያን ከራሷ አልፎ ሀገር ሊመራ የሚችል የተማረ የሰው ኃይል አላት:: ይህም ባለፈው ታሪኳ ሀገርን በመምራት ያደረገችው ሓፊነት የተመላበትና ውጤታማ እንቅስቃሴ የተመሰከረ ነው:: ዛሬም ቢሆን ከዚያ ያልተናነሰ የሰው ኃይል አለ:: ይህን የሰው ኃይል በተገቢው መስመር በማሠማራት ቤተ ክርስቲያ መሥራት ያለባትን እንድትሠራ የማድረግ ድርሻው ደግሞ የአባቶቻችን ሓላፊነት ነው:: ይኸው ድርሻቸው ደግሞ በየሀገረ ስብከታቸው ተገቢውን ሰው በተገቢው ቦታ ከመመደብ ይጀምራል::

አባቶቻችን ይህን ሁሉ ተፈላጊ ሥራ የሚያከናውኑት አስቀድሞ ለዚህ ሓላፊነት የመረጣቸው አምላክ በመንፈሱ በቅዱስ ሲኖዶስ አድሮ ወደ መራቸው ቦታ /ሀገረ ስብከት/ በሙሉ ደስታና ፍላጐት ሲሄዱ ነው:: የተቀበሉት ሓላፊነት የእግዚአብሔርን ቃል ለመዝራት በሚቻልበት ቦታ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቸርነት፣ የቅዱሳንን ምልጃና ተራዳኢነት አጋዥ በማድረግ በቆራጥነት እንዲጓዙ የሚጠይቅ ነውና:: ከሄዱም በኋላ በሀገረ ስብከታቸው በቂ ጊዜ ተሰጥቷቸው ከአካባቢውና ሕዝቡ ጋር በመላመድ ነባራዊ ሁኔታዎችን ያገናዘቡ ሥራዎችን እንዲሠሩ ሊፈቀድላቸው ይገባል:: በተሰማሩበት የሥራ ዘርፍ ውጤት ለማስመዝገብ ከሚያስፈልጉ ነገሮች አንዱ ሥራው በሚሠራበት ቦታ በቂ ጊዜ እንዲያገኝ ማድረግ ነው:: በመሆኑም ብፁዓን አባቶች በሀገረ ስብከታቸው ፍሬ እስኪያስገኙ ድረስ መቆየት እንዳለባቸው እናምናለን:: /ዘኒቂያ÷ትእዛዝ 77፤ አብጥሊስ÷ቀኖና 13/

በነፍሳችን ተጠያቂ ለመሆን ከላይ በዝርዝር ያቀረብናቸውም ይሁኑ ሌሎች በርካታ ሓላፊነቶቻቸውን እንዲወጡ ደግሞ መላው ምእመናንና የቅርብ ረዳቶቻቸው ሁሉ ትእዛዛቸውን በመቀበል፣ ባሠማሩን ቦታዎች ሁሉ በትጋት በመሥራት ልንተባበራቸው ይገባል እንላለን:: የቤተ ክርስቲያናችን አምላክ ለአባቶቻችን የሥራ ፍሬዎችን የሚያስመዘግቡበት፣ የቤተ ክርስቲያንን ሁሉን ዐቀፍ ሕይወት የሚጠብቁበት ረጅም ዕድሜ ይስጥልን:: አሜን::

## ቅዱስጌዮ /ቅዱስጌ/

በሐመር መጽሔት 13ኛ ዓመት ቁጥር ሦስት የሐመር መጽሔት እትም ትምህርተ ሃይማኖት ዓምድ ላይ «ገድላተ ክርስቶስ ሠምራ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር» በሚል ርእስ በቀረበው ጽሑፍ ከልቤ ተደስቼአለሁ:: ከገድለ ክርስቶስ ሠምራ እንዳነበብኩት÷በአካባቢው ተወልጄ ያደግኹ እንደ መኾኔም መጠን እንደማውቀው÷ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ የተወለደችበት ሥፍራ ልዩ ስሙ «ቅዱስጌዮ /ቅዱስጌ/» በመባል ነው የሚታወቀው:: አሁንም ቢሆን ቀበሌው ዱስጌ ተብሎ ይጠራል:: በጽሑፉ ግን «ጌዮ» ተብሎ ቀርቧል:: ይህ ቢታረም መልካም ነው::

*ወጋየሁ አየለ*
*አዋሽ ሰባት ኪሎ*

## «የልሳነ ግእዝ ወዳጆች ማኅበር»

በሐመር መጽሔት «አቡጊዳ- የግእዝ ቋንቋ ትምህርት» ዓምድ በተከታታይ የሚቀርበውን ትምህርት እየተከታተልኩ ነው:: አቀራረቡ በሚረዳ መልክ የኾነና ግልጽ ነው:: በዚሁ እንዲቀጥል አደራ እላለሁ:: በማያያዝም በአ.አ.ዩ በሚያዝያ ወር 1997 ዓ.ም «የልሳነ ግእዝ ወዳጆች ማኅበር» መመሥረቱ ታላቅ ርምጃ ነው:: በአንጻሩም የቋንቋውን ክፉ ለሚመኙ መርዶ ነው:: ለግእዝ ቋንቋ ወዳጆች ግን ዐቢይ የምሥራች ነው::

*መ/ር ወንድሙ ታዴዎስ*
*ወላይታ ሶዶ*

<u>ከአዘጋጁ:-</u>«የልሳነ ግእዝ ወዳጆች ማኅበርን» ማግኘት ለምትሹ በሚከተሉት አድራሻዎች መጠቀም ትችላላችሁ::

ስልክ:- 254-22-62
55 63 28
09-24 65 80
ኢ-ሜይል:- geez aau@yahoo.Co.uk
አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ማዕከል
መ.ሣ.ቁ. 1176 ወይም
20077
አ.አ

## ዘመናዊነትና ሥልጣኔ

በሐመር መጽሔት 13ኛ ዓመት ቁጥር ሦስት እትም በዓምደ ወራዙት ላይ:- «ዘመናዊነትና ሥልጣኔ» በሚል ርእስ ማወያየት የጀመራችሁበት ጽሑፍ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ተያይዘው ለሚነሡ ጥያቄዎች ሚዛናዊ እይታን የሚያጎናጽፍ ነው:: ይሁንና በተከታዩ እትም ላይ ተቋርጧል:: ዝግጅቱ አሳታፊ በኾነ መልኩ ቀጥሎ ደኅና መቋጫ ላይ መድረስ ይኖርበታል::

*በዛብህ መኮንን*
*ደሴ*

## ሰነፎቹን ይገሥጻል...

በ13ኛ ዓመት ቁጥር ሦስት እና አራት የሐመር መጽሔት እትሞች በወቅታዊ ጉዳዮች ዓምድ ላይ:- ቤተ ክርስቲያናችን በትምህርት ተቋማት ግንባታ ረገድ የምታርደገውን እንቅስቃሴ በተመለከተ በአርአያነት ሊጠቀሱ የሚችሉትን ነቅሳችሁ አስነብባችሁናል:: ከሁሉም በላይ ምእመናን በገንዘብና በጉልበት ያደረጉት አስተዋፅዖ ታላቅ መልእክት አለው:: ይኸውም በአንድ በኩል ቤተ ክርስቲያናችን የጥበብ ምንጭ የሥራ ማዕከል መኾኗን ያስረግጣል:: በሌላ በኩል በዚህ ረገድ ሀብቱ ችሎታው እያላቸው ቸል ያሉቱን ይገሥጻል:: ስኬቱ በአዲስ አበባና በአህጉረ ስብከት ደረጃ ሳሉቱም መስፋፋት ይኖርበታል::

*የደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት*
*ቤተ ክርስቲያን*
*ሰንበት ት/ቤት*
*ግንኙነት ክፍል*
*ብቻና*

## ተምረንበታል

በሐመር መጽሔት 13ኛ ዓመት ቁጥር ሦስት «መነኩሴ ንብረት ርስት ጉልት አይደለም የሚያከማቸው፤ ዕውቀት ነው» ብለው አባ ወልደ ትንሣኤ ጫኔ በተናገሩት ነጥብ እስማማለሁ:: በየዕድሜ እርከኑ ላሉት አገልጋይ ካህናትም አስተማሪነቱ የጎላ ነው:: አጠቃላይ ሕይወታቸውም በቤተ ክርስቲያን ትምህርት የበለጠ እንድበረታ አድርጎኛል:: አባ ወልደ ትንሣኤን «ይበርቱ» በሉልኝ::

*ዲ.ን ተመስገን ዘገየ*
*ወረታ ግ/ቴ/ማ/ግቢ ጉባኤ*

## ድርሻችንን ያወቅንበት አቋም «ኅሡ ሰላመ ወዴግኑ፤ ሰላምን ሹ÷ ተከተሉም»

በሐመር መጽሔት 13ኛ ዓመት ቁጥር አራት እትም «ሰላምን ሹ÷ ተከተሉም» በሚል ርእስ ማኅበሩ ያስተላለፈው መልእክት ወገንተኛ ያል ኾነ፣ ሰላምን የሚሰብክ፣ የእያንዳንዱን ክፍል ድርሻ የጠቆመ ነበር:: በተለይም ክርስቲያን ወገኖች «ሰላም በኢትዮጵያ ላይ ይሁን» ብለን የሰላም ባለቤት ወደ ኾነው አምላካችን እጃችንን እንድናነሣ የሚያነቃቃን ነው:: ሰላመ እግዚአብሔር ይብዛልን::

*አሸናፊ ስለሺ*
*ደብረ ሮሃ-ላሊበላ*

## ቅዱስ ጋብቻን ማበረታታት

በሐመር መጽሔት መጋቢት/ሚያዝያ 13ኛ ዓመት ቁጥር ሁለት እትም «የጠባይ ለውጥ እንዴት?» በሚል ርእስ የቀረበው ጽሑፍ ወጣቱ ራሱን እንዲጠብቅ፣ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዲበረታ፣ ለልማትና ለመልካም ሥራ እንዲነሣሣ ግንዛቤን ይሰጣል:: በተለይም ትዳር ለመመሥረት የሚያስቡና የወሰኑ ወጣቶች ንጽሕ ጠብቀው ለቅዱስ ጋብቻ እንዲበቁ ያበረታታል:: መሰል ጽሑፎች ቀጣይነት ቢኖራቸው መልካም ነው:: በዚህ አጋጣሚ በዚሁ እትም ደብዳቤዎች ዓምድ ላይ «መዝሙርም ወረት ኾነን?» በሚል ርእስ ለቀረበው አስተያየት «ቄስ ሰሎሞን ታዬ» የተባለው «መ/ር ሰሎሞን ታዬ» ተብሎ እንዲታረምልኝ እጠይቃለሁ::

*መ/ር ሰሎሞን ታዬ*
*ባሌ ሠዌና ወረዳ*
*ሚጫ*

ስማችሁ ከዚህ በታች የተዘረዘረው አንባብያን ደብዳቤዎቻችሁ ደርሰውናል:: ሐመርን አንብቡ፤ ለሐመር ጻፉ፤ በተሳትፏችሁ ቀጥሉ::

አቶ መዝገቡ አያሌው/ሸኖ/፣ ብሥራተ ገብርኤል /ባሕር ዳር/፣ ኃይለ ኢየሱስ ነጋሲ /ወንጂ/፣ ወልደ ገብርኤል/ ምዕ. ወለጋ/፣ ገብረ ማርያም ገብረ ሥላሴ/አዋሳ/፣ ተማሪ ተሾመ ጋሺ /ጅማ/፣ መሐመድ አልጋፍሊ /የተባበሩት ዐረብ ኤምሬቶች/፣ በላይ ምሕረተ አብ/ጅማ ዩኒቨርስቲ/፣ እኅተ ሚካኤል /ጊዶሌ/፣ አበበ ፋንታ/ ባሌ-ጃራ ከተማ/፣ መልአከ ገነት ብርሃን ዓለማየሁ /ነቀምት/፣ መ/ር ጫላ አበራ /ባሌ ዶዶላ/፣ ዓለምነሽ ፈቃደ/ባሕሬን/፣ በለጡ ኪዳኖ /ሊባኖስ/፣ዮርዳኖስ ሚደቅሳ/ድሬዳዋ/ ደመወዝ አሰፋ፣ ኪዳነ ሰንበት፣ ተማሪ አዱኛ ፀሐይ፣ ዐጸደ ማርያም፣ ፣ ታሪኩ ብላቴ /አ.አ/::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ቅርሶቻችን ይመለሱ ወይስ ለደኅንነታቸው ሲባል በዚያው ይቆዩ?

## «ወርቆቻችን» ይመለሱልን የምንደምቅባቸው ብቻ ሳይሆን የምንጸድቅባቸው ጭምር ናቸውና።

ከመገኛ አገራቸው በተለያየ መልክ ተወስደው በባዕዳን ዘንድ የሚገኙቱ ቅርሶቻችን «ወርቆቻችን» ስለሆኑ ይመለሱልን። እኒህ «ወርቆቻችን» የምንደምቅባቸው ብቻ ሳይሆኑ የምንጸድቅባቸው ጭምር ናቸው። መንግሥትና የተለያዩ ወገኖች ለአክሱም ሐውልት መመለስ ላደረገት ጥረት ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ይሁንና ተመሳሳይ የኾነ ትብብርና ትጋት ለሌሎቹም ቅርሶቻችን መመለስ መደረግ ይኖርበታል። ባዕዳን ላይደምቁባቸው የወሰዱብንን ቅርሶቻችንን «አይመለሱ» የማለት ትርፉ የታሪክ ወቀሳ ብቻ ነው።

*ዳንኤል ሐጎስ*
*ማይጨው-ትግራይ*

## «ቅርሶቹ ያለ ኢትዮጵያ አይደምቁም»

ኢትዮጵያውያን ቅርሶቻችንን አደጋ ላይ የምንጥል፣ የምናስቀምጥበት ሥፍራ የቸገረን ያህል ተደርጎ መነገሩ አሳዛኝ ነገር ነው። እነርሱ የሚሉት ዓይነት እክል እንደ ሌለብን ከአክሱም ሐውልት አመላለስ፣አቀባበል መረዳት ይገባቸዋል። በእኛም በኩል ይህ ችግር አለብን የሚል ነገር የቀረበ አይመስለኝም። «የኢትዮጵያውያን ለቅርሶች ክብር የመስጠት ጉዳይ አጠያያቂ ነው» ማለት «ልጅ ለእናትዋ ምጥ አስተማረች» እንደ ማለት ይቆጠራል። በሌላ በኩል ቅርሶቹ ያለ ኢትዮጵያ አይደምቁም። ኢትዮጵያና ቅርሶችዋ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። ባላገሩ የኢትዮጵያ ሕዝብና ዓለም አቀፍ አጋሮችም ኢትዮጵያና ቅርሶችዋን ለማገናኘት መተባበር ይኖርባቸዋል። ቤተ ክርስቲያናችንም ከጉዳዩ አኳያ ያሉባትን የአመራር፣ የአሠራርና የአደረጃጀት ክፍተቶች ማሻሻል ይገባታል። ቅርሶቹ በሚመለሱበት ወቅት ደግሞ መቀመጥ ያለባቸው ቀደም ሲል በተወሰዱበት ቦታ መኾን ይገባዋል።

*ገበየሁ አባተ*
*ደሴ*
*ጌታሁን ተከተል*

*ሚቶ*

## «የቅርሶቻችን መወሰድ ትልቅ መንፈሳዊ ምሥጢር ሊኖረው ይችላል»

በቅድሚያ «የተዘረፉ ቅርሶቻችን» ስለሚለው ሓሳብ አስተያየቴን ለመስጠት እወዳለሁ። በእኔ እምነት የቅርሶቻችን ወደ ባሕር ማዶ መወሰድ ትልቅ መንፈሳዊ ምሥጢር ያለውና ፈቃደ እግዚአብሔር ሊኾን ይችላል። በተለይም ቅርሶቻችን በባዕድ አገር በአገባቡ ከተያዙ የሚያስመሰግን ነው። ባለንበት ዘመን ቅርሶች ዓለም አቀፋዊ ይዘትና ባሕርይ ብሎም የሰው ልጆች ሁሉ ሀብት እየኾኑ መጥተዋል። ቅርሶችን ከሚያጠፉትና ከሚያወድሙት የሚዘርፉትና በነበራቸው መልክ የሚያቆዩቱ የተሻሉ ናቸው። ለምን ቢባል አንድም፦ የእግዚአብሔርን ድንቅ ጥበብ አይተውባቸዋል፤ በሌላ በኩል እኛም ዛሬ አምጡ ለማለት የቻልነው እነርሱ ይዘው በመገኘታቸው ነው። ትልቁ ቁም ነገር ዛሬ ቅርሶቻችን ያሉበትን ሁኔታ ማወቅ ነው። የት ነው የሚገኙት? ምን ምን ናቸው? ብዛታቸው ምን ያህል ነው? መቼና እንዴት ከሀገር ሊወጡ ቻሉ? አሁን ያሉበት ሁኔታ ምን ይመስላል? በመጀመሪያ እኒህ መረጃዎች መጠናቀር አለባቸው።

ይልቁንም እኔን የሚያሳስበኝ በውጭ ያሉቱን ለማስመለስ ከማሰብ ይልቅ ዛሬ በተለያየ መንገድ ከአገር የሚወጡቱን የመከላከሉ ጉዳይ ነው። በእጃችን ያሉት የቤተ ክርስተያናችን ቅርሶች ዝርዝራቸው ታውቆ ሞያዊ በኾነ መልኩ ተመዝግበው ይቀመጡ። ለሁሉም እግዚአብሔር አስተዋይ ልቡናን ይስጠን። አሜን።

*ፈቃዱ ሙሉነህ*
*አ.አ*

## «ቅድመ ዝግጅት ይደረግ፤ ቅርሶቻችንም ይመለሱ።»

ቅርሶቻችን በዝርፊያም ኾነ በሌላ መንገድ ከመወሰዳቸው በፊት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ዘመኑ የፈቀደው የአኗኗርና የአጠባበቅ ዘዴ ነበራቸው። አቅማቸው በፈቀደ መጠን በፍጹም ክብካቤ ይዘዋቸው እንደ ነበር የማይታበል ሐቅ ነው። በኋላ ዘመን ቅርሶቻችንን ያጣናቸውም በንጥቂያ፣ በወረራና በዘረፋ ነው። ዛሬ ቤተ ክርስቲያናችን በሥጋዊውም በመንፈሳዊውም ረገድ የሠለጠነ የሰው ኃይል አላት። ስለሆነም ለቅርሶቹ አያያዝ መዘጋጀት ስላለበት ቅድመ ሁኔታ የአቅም ችግር የለብንም። ሕዝባችን በእናት አገሩ የሚጠየቀውን በማሟላት ረገድ ደግሞ የሚታማ አይደለም። ቅርሶቻችን መንፈሳዊ ዋጋና በረከት የሚኖራቸው በእኛ በባለቤቶቹ ዘንድ ሲኾኑ ነው። ስለዚህ የምክንያት ድሪቶ ማብዛት አያስፈልግም። የቅርሶቻችን መመለሻ ጊዜ አሁን ነው። ለኢትዮጵያ ልዩ አስተያየት ያላቸው ወገኖችና በባሕር ማዶ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በስፋት መንቀሳቀስ አለባቸው። በተለይም፦

1. መንግሥት፦
   - የጀመረውን ዲፕሎማስያዊ ጥረት አጠናክሮ መቀጠል፤
   - በባለሞያዎች የሚደረጉ ጥናቶችን ማበረታታትና መደገፍ፤
   - ከቤተ ክርስቲያናችን ጋር አብሮ መሥራት ይገባዋል።
2. ቤተ ክርስቲያን፦
   - የቤተ ክርስቲያንን ማንነት የሚያንጸባርቅ ዘመኑ የሚጠይቀውን የቅርስ ጥበቃና አያያዝ ሥነ ዘዴ ነድፉ ተግባራዊ ማድረግ፤
   - በአገልግሎትና በአስተዳደር ተቋሞቿ ውስጥ ላሉ አገልጋዮቿ ሥልጠና መስጠት፤ ምእመናንም ተግባራዊ ድጋፍና ትብብር እንዲያደርጉ ማስተባበር፤ ለዚህም ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤
   - ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልኾኑ ተቋማት ጋር ሊሠሩ የሚገባቸውን ተግባራት ለመለየት አፈጻጸሙን የሚከታተል አካል ማቋቋም ይገባታል።

በአጠቃላይ ከቤተ ክርስቲያን፣ ከመንግሥትና ከሕዝቡ መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች እንዳሉ ኾነው ቅርሶቻችን ግን መመለስ አለባቸው እላለሁ። «የሰው ወርቅ አያደምቅ» ነውና።


*ይመስላል ዓምባቸው*
*ወሎ-ወልድያ*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የመስቀሉ መስቀላዊ ጉዞ

መ/ር ብርሃኑ ጎበና



ጌታችን መስቀሉን ተሸክሞ በአይሁድ እየተገረፈ ሲሔድ ለሦስተኛ ጊዜ የወደቀበት ቦታ /ቦታው 9ኛው ምዕራፍ በመባል ይታወቃል/ - ማቴ. 26 ÷ 39

ልዑለ ባሕርይ አምላክ የሰው ልጆችን ለማዳን ባደረገው አምላካዊ ጉዞ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከተወለደበት ከቤተ ልሔም÷ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ለቅዱሳን ሐዋርያት እስካደለበት እስከ ጽርሐ ጽዮን ያሉት በኪደተ እግሩ የባረካቸው ስፍራዎች ሁሉ ሳይቀሩ በተከታዮቹ በክርስቲያኖች ዘንድ ልዩ ክብር አላቸው:: በዕለተ ዐርብ አይሁድ ጌታን እያዳፉ በጲላጦስ አደባባይ ካቀረቡበት ቦታ ወደ መቃብር እስከ ወረደበት ድረስ የተቀበለውን መከራና ስቃይ በማዘከር ክርስቲያኖች የስቅለት ዕለትና በየሳምንቱ በዕለተ ዐ ርብ የጲላጦስ አደባባይ ከነበረበት እስከ ጌታ መቃብር ጎልጎታ ድረስ መስቀል ተሸክመው ዕለተ ዐርብን የሚያዘክር የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ በየምዕራፎቹ እያነበቡና እየጸለዩ ጉዞ ያደርጋሉ:: በላቲን «ቪያ ዶሎሮዛ» በግእዝ «ፍኖተ መስቀል» ይባላል:: የመከራ÷ የሥቃይ መንገድ ማለት ነው:: ዐሥራ አራት ምዕራፎች አሉት:: ርዝመቱ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ይሆናል:: ከጥንት ዘመን ጀምሮ ጌታ በዕለተ ዓ ርብ መስቀሉን ተሸክሞ ሲወድቅ ሲነሣ የነበረባቸውን ቦታዎች የሚመለከት ነገር በጥንት ክርስቲያኖች ዘንድ ነበር:: ኾኖም ዐሥራ አራቱ የመስቀል ምዕራ ፎች በውል ተለይተው የታወቁት (Standardized የሆኑት) በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፍራንሲስካውያን መሆኑ ይነገራል:: ሁልጊዜ ዐርብ ዐርብ ፍራሲ ስካውያን ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ጀምረው መስቀል በመያዝ ዛሬ «አመርያ» ተብሎ ከተሰየመው ጥንት ግን «ሊትስጥ» (ሊቶስጥራ) ወይም በዕብራይስጥ «ገበታ» ይባል ከነበረው ጀምሮ እስከ ጎልጎታ ድረስ ጉዞ ያደርጋሉ:: የስቅለት ዕለት ደግሞ ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት በየተራ መስቀል ተሸክመው÷ በየምዕራ ፎቹ ጸሎት እያደረጉ÷ በቦታው ላይ ስለ ተፈጸመው ድርጊት እያወሱ ጉዞ ያደርጋሉ::

ጌታ ለእኛ ስለ ተቀበለው መከራ ወንጌላውያን የጻፉትን መ ሠረት አድርገን ስንመለከተው መከራ ው የሚጀምረው ከጌቴ ሴማኒ ነው:: ማር.14÷32–49:: ጌቴ ሴማኒ የቃሉ ትርጉም የዘይት መጭመቂያ ማለት ነው:: አካባቢው በወይራ ዛፍ የተሞላ እንደ ነበር ነው የሚተረከው:: ንጉሥ ዳዊት ተራራውን ሁሉ የወይራ ዛፍ አስተክሎበት ነበር:: እንዲያውም ጌታ በሥጋው ወራት በምድር ይመላለስ በነበረበት ጊዜ የነበሩ መሆናቸው የሚነገርላቸው ስምንት የወይራ ዛፎች ዙሪያቸው በድንጋይ ተደግፈው ይታያሉ:: አሁንም ቢሆን ልምላሜ ያቸው ከእነርሱ አልተለየም:: የወይራ ዛፍ ከሦስት ሺህ ዓመት በላይ በልምላሜ እንደሚኖር የዘርፉ ተመራ ማሪዎች ይናገራሉ::

የእናትና አባትዋ የሐና እና የኢያቄም እንዲሁም የእመቤታችን የ ራስዋ፣የአገልጋይዋ የዮሴፍ መቃብር ያለው በዚሁ በጌቴ ሴማኒ ነው:: ጌታችን በሥጋው ወራት በምድር ተገልጦ ይመላለስ በነበረበት ጊዜ ብዙውን ጊዜ ከሚያዘወትራቸው ስፍ ራዎች መካከል ጌቴ ሴማኒ አንዱ ነበር:: ለጸሎት ወደዚህ የአትክልት ቦታ ይመጣ ነበር:: ዐርብ ሊሰቀል ኀሙስ ምሽት በአልዓዛር ቤት የተዘጋጀውን ፋሲካ በልተው ከጨረሱ በኋላ አመስግነው÷ ዘምረው ወደ ደብረ ዘይት ወጡ:: ከዚያም ደቀ መዛሙርቱን አስከትሎ ወደ ጌቴ ሴ ማኒ አመራ:: ማር.14÷26–32::

ጌቴ ሴማኒን እንደሚያዘወትር የሚያውቀው ይሁዳ ለ30 ብር ተገዝቷልና የካህናት አለቆችን፣ ጻፎችንና የሕዝብ ሽማግሌዎችን እየመ ራ÷ ሰይፍና ጎመድ በያዙ ሰዎች ታጅቦ ጌታ ወዳለበት ቦታ መጣ:: «መምህር ሆይ» በማለት ጌታን ስሞ አሳልፎ ሰጠው:: ወዲያው ሰይፍና ጎመድ የያዙት ጭፍሮች ተረባረቡበት:: እየገፈተሩ እያዳፉትም ወደ ሊቀ ካህናቱ ግቢ ወሰዱት:: በ ማግሥቱ ማልደው ጌታን ከሊቀ ካህናቱ ግቢ እያዳፉ ወደ ጲላጦስ ፊት ሊያስፈርዱበት አቀረቡት:: የፍኖተ መስቀል መጀመሪያ ይህ ቦታ ነው::

ከላይ እንደ ተገለጸው ፍኖተ መስቀል ዐሥራ አራት ምዕራፎች አሉት:: ዘጠኙ ከጎልጎታ ውጭ ሲሆኑ አምስቱ ግን በጎልጎታ ውስጥ ነው የሚገኙት:: ሁሉንም ቀጥለን በዝርዝር እናያቸዋለን::

<u>አንደኛው ምዕራፍ</u> :–በጲላጦስ ፊት ተከሶ የቆመበት::

«በወዲያውም ማለዳ፤ የካህናት አለቆች ከሽማግሌዎችና ከጻፎች ከሸንጎውም ሁሉ ጋራ ከተማከሩ በኋላ ኢየሱስን አሳስረው ወሰዱትና ለጲላጦስ አሳልፈው ሰጡት::» ማር.15÷1::

በዕብራይስጥ «ገበታ» በግሪክ «ሊቶስጥራ» ማለትም «በተራ የተነጠ ፈ ድንጋይ÷ ከፍተኛ ቦታ» በሚሉት ፍርድ ቤት ጲላጦስ ተሠይሞ ሳለ ጌታን ወደ እርሱ ዘንድ አመጡት:: መስፍኑ ጲላጦስ በጌታ ላይ ፈርዶ÷ ጌታም ተፈርዶበት ሲሄድ የወረደበት ደረጃ ቁጥር 28 ነበር:: ንግሥት እሌኒ በ327 ዓ.ም. ወደ ኢየሩሳሌም በመጣች ጊዜ 28ቱን ደረጃዎች ሮማ ወስዳ በወርቅና በዕንቊ አስለብጣ «ሳንታ እስካለ» የሚባል ቤተ ክርስቲያን አሠርታ በክብር አስቀምጣዋለች:: በትርጉሙም «ቅዱስ ደረጃ» ማለት ነው::

በጥንት ጊዜ የአይሁድ ካህናት ፍርድ ቤት እንደ ነበር የሚነገርለት ይህ ቦታ ኋላ ላይ ትልቁ ሄሮድስ አዳ ራሽና ምሽግ አሠርቶበት ነበር:: በሮ ማውያን ጊዜ ፕራይቶርዮም ፍርድ ቤት ተብሏል:: በቱርክ ጊዜ ደግሞ «ሸርእያ» ይባል ነበር:: ዛሬ የዐረቦች ትምህርት ቤት ሆኗል:: ይህ «አመርያ» የሚባለው ትምህርት ቤት



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ያለበት ቦታ ጌታ ጲላጦስ ፊት ለፍርድ የቀረበበት ሲሆን አንደኛው ምዕራፍ ነው::

<u>ሁለተኛው ምዕራፍ</u> :– *ከለሜዳ አልብሰው፣የእሾህ አክሊል ደፍተው÷ መስቀሉን ያሸከሙበት ቦታ ነው::*

«በዚያን ጊዜም ጲላጦስ ኢየሱስን ይዞ ገረፈው:: ወታደሮቹም የእሾኽ አክሊል ጎንጉነው በራሱ ላይ አኖሩ፤ ልብስም አለበሱት፤ እየቀረቡም «የአይሁድ ንጉሥ ሆይ÷ ሰላም ለአንተ ይሁን» ይሉት ነበር:: በጥፊም ይመቱት ነበር:: ጲላጦስም ደግሞ ወደ ውጭ ወጥቶ:– እነሆ÷ አንዲት በደል ስንኳ እንዳላገኘሁበት ታውቁ ዘንድ እርሱን ወደ ውጭ አወጣላችኋለሁ አላቸው:: ኢየሱስም የእሾኽ አክሊል ደፍቶ÷ ቀይ ልብስም ለብሶ ወደ ውጭ ወጣ፤ ጲላጦስም:– እነሆ ሰውየው አላቸው::» ዮሐ.19÷1–5::

«እነሆ ይህ ሰው» (Ecce Home) ተብሎ የተሰየመው ይህ ቦታ ሁለተኛው ምዕራፍ ሲሆን ጌታ የሚሰቀልበትን መስቀል ያሸከሙት ከዚህ ስፍራ ነው::

<u>ሦስተኛው ምዕራፍ:</u>– *ለመጀመሪያ ጊዜ መስቀሉን ተሸክሞ የወደቀበት*

የጌታ መስቀል በግራና በቀኝ እንዲሰቀሉ ከተፈረደባቸው ወንበዴዎች መስቀል በተለየ ሁኔታ በጣም ከባድ ነበር:: ይህም የሆነበት ምክንያት በርባን በኢየሩሳሌም ከተማ ውስጥ የሮማውያንን አገዛዝ ለመቃወም አድማ አሥነስቶ በነበረ ጊዜ ብዙ ሕዝቦች አልቀው ነበር:: ከሟቾቹ ውስጥ በኢየሩሳሌም ይኖር የነበረ አንድ የአናጢ ልጅ ይገኝበት ነበር:: አባትየው በርባን ባሥነሳው ዐመፅ ምክንያት አንድ ልጁን አጥቷልና ልቡ በሐዘን ተወግቶ ይኖር ነበር:: በርባንን ለመበቀል አቅሙ ቢያንስም በርባን ተይዞ ሞት የተፈረደበት በመሆኑ እየተቆጨ ይኖር ነበር:: በልጁ ሞት ያዘነው አባት÷ በርባን በስቅላት እንደሚቀጣ ርግጠኛ ሆኖ ነበርና ወደ ሮማውያን ወታደሮች ሄዶ ሁለቱ ወንበዴዎችና በርባን የሚሰቀሉበትን መስቀል እንዲሠራ እንዲፈቀድለት እጅ መንሻ የሚሆን የወይን ጠጅና ሌላም ስጦታ ስለ ሰጣቸው መስቀሉን እንዲሠራ ፈቀዱለት:: ይህ አናጢ መስቀሎቹን ሲሠራ:– «በርባን የሚሰቀልበትን መስቀል ራሱ ተሸክሞ ጎልጎታ ድረስ መሄዱ የማይቀር ነው» ብሎ ከመስቀሉ ክብደት የተነሣ እንዲሠቃይ ብሎ «በርባን ይሰቀልበታል» ብሎ ያሰበውን በጣም ክብደት እንዲኖረው አድርጎ ሠርቶት ነበር:: ዳሩ ግን ይሁዳ ከአይሁድ ከተቀበለው ሠላሳ ብር በተጨማሪ የሚስቱ ዘመድ የሆነው በርባን እንዲፈታ ጥያቄ እንዲያቀርቡ አምሎአቸው ነበር:: በአይሁድ ውትወታ ዐመፀኛው በርባን ተለቆ ንጹሐ ባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ በበርባን ፈንታ የስቅላት ሞት ተፈረደበትና ለበርባን ታስቦ የተሠራውን መስቀል እርሱ ተሸከመ:: «የእኛን ሞት ተቀብሎ የእርሱን ሕይወት ለእኛ ሰጠን» እንደ ተባለ:: ስለ በርባን እርሱ መከራ ተቀበለ::

ጌታ ከመስቀሉ ክብደት የተነሣ እየተንገዳገደ መስቀሉን ተሸክሞ ሲጓዝ ሳለ ከመስቀሉ ክብደት የተነሣ ለመጀመሪያ ጊዜ የወደቀበት ቦታ ሦስተኛው ምዕራፍ ነው:: በኃጢአት የወደቅነውን እኛን ለማንሣት እርሱ ስለ እኛ ወደቀ:: በሦስተኛው ምዕራፍ ላይ የአርመን ካቶሊኮች መቅደስ ይገኛል::

<u>አራተኛው ምዕራፍ:</u>– *እመቤታችን ከልጅዋ ጋር ዐይን ለዐይን የተያየችበት ምዕራፍ ነው::*

ምንም እንኳን መድኃኔዓለም ክርስቶስ የመጣው ስለ ሰዎች ልጆች በደል መከራ ተቀብሎ የሰው ልጆችን ከዘላለም ሞት ለማዳን መሆኑን ብታውቅም ወልዳ ያስገኘች አዝላ የተሰደደች ናትና መያዙን ከሰማችበት ሰዓት ጀምሮ ልብዋ በሐዘን ተመቷል:: ሉቃ.2÷35፤ዮሐ.19÷25–27 እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም «ይሙት በቃ» ተፈርዶበት በቀራንዮ ኮረብታ ላይ ሊሰቅሉት መስቀሉን አሸክመው እያዳፉ ወደ መስቀያው ቦታ እየወሰዱት መሆኑን ስትሰማ ወደ ልጅዋ ዘንድ እንዳትቀርብ በጠባቂ አስከልክለዋት ነበር:: ኾኖም በለቀቅዋት ጊዜ እየወደቀች እየተነሣች ስትሄድ በአራተኛው ምዕራፍ ላይ ከተሸከመው መስቀል ክብደት፣ ከደረሰበት ድብደባ የተነሣ ደክሞ ፊቱ ላይ በሚጎርፈው ደሙ ተጋርዶ ስታየው ልብዋ በመሪር ሐዘን ተነካ:: «በአንቺም በልብሽ ሰይፍ ያልፋል» (ሉቃ.2÷35) ያላት የአረጋዊውና ካህኑ ስምዖን ትንቢት ደረሰ፤ ተፈጸመ:: በልብዋ ላይ መሪር የሐዘን ፍላጻ ገባ:: የእንባ ጎርፍ በሚያጎርፈው ዐይንዋ ደም ከጋረደው የልጅዋ ዐይን ጋር ተያዩ::

የአርመን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እመቤታችን የልጅዋን ሥቃይ ባየችበትና ልብዋ በሐዘን ፍላጻ በተወጋበት በዚህ ቦታ ላይ «የድንግል ሥቃይ» በሚል ስያሜ የሚጠራ ቤተ ክርስቲያን አላቸው::

<u>አምስተኛው ምዕራፍ:</u>:– *ስምዖንን የጌታን መስቀል እንዲሸከም ያስገደዱበት*

«በወሰዱትም ጊዜ ስምዖን የተባለ የቀሬናን ሰው ከገጠር ሲመጣ ይዘው ከኢየሱስ በኋላ መስቀሉን እንዲሸከም ጫኑበት::» ሉቃ.23÷26::

ከገጠር ሲመጣ ሳያስበው የመስቀሉ በረከት የደረሰው የቀሬናን ወይም የአሁንዋ ሊቢያ ተወላጅ የሆነው ስምዖን በዚህ ቦታ ላይ መስቀሉን እንዲሸከም ተደርጓል:: በመኾኑም የመስቀሉ በረከት ለፍጹም ቅድስና አብቅቶት ከቅዱሳን ማኅበር ሊቀላቀል በቅቷል:: በዚህ የተነሣ በቦታው ላይ በስሙ ቤተ ክርስቲያን ታንጿል:: «የስምዖን ቀሬናን ቤተ ክርስቲያን» የሚል በአምስተኛው ምዕራፍ ከነበረ ቦታ ጋር ተገጣጥሞ ያለው ቤት የባዕለ ጸጋው የነዌ ቤት እንደ ነበር ይነገራል::

<u>ስድስተኛው ምዕራፍ:</u>– *ቬሮኒካ ፊቱን እንዲያብስበት ሻሽዋን የሰጠችበት::*

የጌታ ፊቱ በላብ ተጠምቆ÷ ዐይኑ በደም ተሸፍኖ አየችው:: ፊቱን እንዲጠርግበት ሻሽዋን አውልቃ ሰጥተዋለች:: እርሱም ፊቱን ጠርጎ ሲመልስለት ከሻሽዋ ላይ ገጹ ተሥሎ ተገኝቷል:: የጌታ እውነተኛ መልኩ የታተመበት ቀጸላ ርእስ ወይም የሻሽ ጨርቅ (Veronica's Veil) በሮማ ባለው በቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን ይገኛል:: የእርሷም ስም «ቬሮኒካ» የተባለው በሻሽዋ ጨርቅ ላይ የጌታ መልክ ተሥሎ ከተገኘ በኋላ ነው:: «ቬሮ ኢኮን» ማለት በላቲን ቋንቋ «የእውነት መልክ÷ የእውነት ሥዕል» ማለት ነው::. ስድስተኛው ምዕራፍ የዚህች ሴት ቤት የነበረው ነው:: ቬሮኒካ ቁጥርዋ ከሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት ነው::

<u>ሰባተኛው ምዕራፍ:</u>– *ጌታ ለሁለተኛ ጊዜ መስቀሉን እንደ ተሸከመ የወደቀበት «የፍርድ በር» እየተባለ* ይጠራ የነበረው ሥፍራ የከተማው መጨረሻ መውጫ በር ነበር:: ጎልጎታ የዚያን ጊዜ ከከተማው ቅጥር ውጭ ነበር:: እንደ ዛሬው በከተማው ቅጥር ውስጥ አልገባም ነበር:: ዳሩ ግን ቀራንዮ (ጌታ የተሰቀለበት ኮረብታ) ለከተማው ቅርብ (Suburb)እንደ ነበር ዮሐንስ ወንጌላዊ ገልጾታል:: ዮሐ.19÷20::

በዚህ ቦታ ከመንገዱ ርቀት፣ ከመስቀሉ ክብደት፣ከመከራው ጽናት የተነሣ ለሁለተኛ ጊዜ ጌታ መስቀሉን እንደ ተሸከመ ወድቋል:: ይህ ቦታ ሰባተኛው ምዕራፍ ነው::

ይህ ቦታ በዚያን ጊዜ የመጨረሻው በር ስለ ነበር በደማስቆ በር ወደ ኸሊልና ወደ ደብረ ጽዮን (ጽርሐ ጽዮን) የሚተላለፈው ሕዝብ እንዲያነበው የጌታ የፍርድ ደብዳቤ ከበሩ ላይ ተሰቅሎ ነበር ይባላል:: የቦታው ስም እስከ አሁን ድረስ «የፍርድ በር» ተብሎ ይጠራል::

<u>ስምንተኛው ምዕራፍ</u>:– *«እናንተ የእሥራኤል ልጆች÷ ለእኔ አታልቅሱ» ያለበት::*

«ዋይ ዋይ ከሚሉና ሙሾ ከሚያወጡ ሴቶችና ከሕዝቡ እጅግ ብዙዎች ተከተሉት:: ኢየሱስ ግን ወደ እነርሱ ዘወር ብሎ እንዲህ አለ:– እናንተ የኢየሩሳሌም ልጆች÷ ለእኔስ አታልቅሱልኝ፤ ዳሩ ግን መካኖችና ያልወለዱ ማኅፀኖች ያላጠቡ ጡ



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

-ቶችም ብፁዓን ናቸው የሚባሉበት ጊዜ እነሆ ይመጣልና ለራሳችሁና ለልጆቻችሁ አልቅሱ።» ሉቃ.23፥28።

ይህ ቦታ የኢትዮጵያ ገዳም ንብረት የሆኑ ሕንፃዎች የሚገኙበት ነው። ወደ መንበረ ጵጵስናውም የሚኬደው በዚሁ ስምንተኛው ምዕራፍ ባለበት ነው። አካባቢው የኢትዮጵያ ገዳም ቦታ ነው።

*<u>ዘጠነኛው ምዕራፍ፡-</u> ለሦስተኛ ጊዜ ጌታ መስቀሉን እንደ ተሸከመ የወደቀበት።*

ዴር ሡልጣን የተባለው የኢትዮጵያውያን የጥንት ርስት የሆነው ገዳም ትልቁ በር ያለበት ቦታ፡- ዘጠነኛው ምዕራፍ ነው። ጌታ ከዚህ ቦታ ሲደርስ ከመንገዱ ርቀት፥ ከተሸከመው መስቀል ክብደት፥ ከሚያደርሱበት የመከራ ጽናት የተነሣ ለሦስተኛ ጊዜ ወድቋል።

ቀሪዎች አምስቱ ምዕራፎች የሚገኙት እሌኒ ንግሥት በ325 ዓ.ም. በሠራችውና ኋላ ላይ በ614 ዓ.ም. ፋርሶች ባፈረሱት እንደገናም በ1099 ዓ.ም. በ«መስቀላውያን» (crusaders)አማካይነት ተጠግኖ በአዲስ መልክ በተሠራው «ቅዱስ የመቃብር ቤተ ክርስቲያን» (The Church of Holy Sepulchre) በተባለው የጎልጎታ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው። «ጎልጎታ» የቃሉ ትርጉም «የራስ ቅል» ማለት ነው። የመጀመሪያው ሰው የአዳም ዐፅም (የራስ ቅሉ) የተቀበረው በዚህ ቦታ በመሆኑ የራስ ቅል ተብሏል። በሌላም በኩል «ኮረብታው የሰው የራስ ቅል ይመስል ስለነበር ነው» የሚሉም አሉ። በጎልጎታ ውስጥ የሚገኙት አምስቱ ምዕራፎች የሚከተሉት ናቸው።

*<u>ዐሥረኛው ምዕራፍ</u> ፡- የጌታን ልብሱን የገፈፉበትና እርቃን ያደረጉበት ቦታ*

*<u>ዐሥራ አንደኛው ምዕራፍ፡-</u> በመሬት ላይ አስተኝተው በመስቀሉ ላይ የቸነከሩበት ቦታ*

*<u>ዐሥራ ሁለተኛው ምዕራፍ፡-</u> መስቀሉ የተተከለበት ማዕከለ ምድር የተባለው ቀራንዮ*

ጌታን በመሬት ላይ ጥለው መስቀሉ ላይ ከቸነከሩት በኋላ በአዳም መቃብር (የራስ ቅል) ላይ የበቀለ ትልቅ ዛፍ ነበር። ያን ከመካከሉ ቆርጠው፥ እንደ ሙቀጫ ፈልፍለው የጌታን መስቀል አሹለው፥ ከተፈለፈለው ውስጥ በማስገባት በብረት አያይዘው በዚያ ላይ ቸንክረውታል። መስቀሉ የተተከለበት ስፍራ የአዳም ዐፅም የተቀበረበት ሲሆን የምድራችን ማዕከል ነው፤ «በምድር መካከል መድኃኒትን አደረገ» ተብሎ አስቀድሞ በነቢዩ ዳዊት አንደበት እንደ ተነገረ። በአስነገረው ትንቢት መሠረት በማዕከለ ምድር በቀራንዮ ተሰቀለ። ይህ ቦታ ከፍ ያለ ነው። «ከመሬት ከፍ ባልኩ ጊዜ ሁሉን ወደ እኔ በምሕረት እስበዋለሁ» እንዳለ ሁሉ፥ መላ የሰው ዘርን በምሕረቱ ይጎበኝ ዘንድ ከፍ ባለው ቦታ ተሰቀለ። በዚህ ቦታ ሥጋውን ቆረሰ፤ ደሙን አፈሰሰ። ቅድስት ነፍሱን ከክቡር ሥጋው በገዛ ፈቃዱ ለየ።

በአሁኑ ጊዜ ጌታ በተሰቀለበት በቀራንዮ በጉልጉታ ቤተ መቅደስ የጌታ የሥነ ስቅለት ሥዕል አለ። በሥነ ስቅለቱ ባለው በእግሩ ትይዩ ክብ ጉድጓድ አለ። ጉድጓዱ የጌታ መስቀል እስከ ተተከለበት የአዳም መቃብር ይደርሳል። ከጌታ ከቀኝ ጎኑ፥ከእግሩና ከእጆቹ የፈሰሰው ደሙ በአዳም ዐፅም ላይ ፈሷል። የመጣው አዳምንና ልጆቹን በደሙ ለማንጻትና ለመቀደስ ነውና።

*<u>ዐሥራ ሦስተኛው ምዕራፍ፡-</u> ከመስቀል አውርደው የገነዙበት ቦታ*

ወደ ጎልጎታ በዋናው በር ሲገቡ ከፊት ለፊት ባለ አራት ማእዘን የተቀረጸ ደንጊያ ከመሬት ላይ ሆኖ ይታያሉ። ከበላዩ ብርሃናቸውን ቀንና ሌሊት የሚሰጡ ቀንዲሎች ይታያሉ። ይህ ቦታ የአርማትያሱ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ጌታን ከመስቀል አውርደው የገነዙበት የግንዘቱ ቦታ ነው።

*<u>ዐሥራ አራተኛው ምዕራፍ፡-</u> ጌታ ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት በመቃብር ያደረበት ሥፍራ ጎልጎታ (የመቃብሩ ቦታ)* ጌታ የተቀበረበት ቦታ ነው። በቀድሞ ዘመን የአትክልት ቦታ ነበር። ይህ ስፍራ የአርማትያሱ ዮሴፍ ርስት የነበረ ነው። ማንም ሰው ያልተቀበረበት፥ ዮሴፍ ለራሱ መቃበሪያ ያዘጋጀው አዲስ መቃብር ነበረበት። ዮሴፍና ኒቆዲሞስ ጌታን በእናቱ ርስት እንዳይቀብሩት ሰንበት ሊገባባቸው ስለሆነ ሰንበት ሳይገባ ተፋጥነው ዮሴፍ ለራሱ ባዘጋጀው አዲስ መቃብር ይቀብሩት ዘንድ ሁኔታው አስገደዳቸው። ሉቃ.23፥54። ከጲላጦስ አደባባይ (የፍርድ ስፍራ) እስከ ጎልጎታ ጌታ ያደረገው የመከራና የስቃይ ጉዞ የሚታወስባቸው ዐሥራ አራቱ ፍኖተ መስቀል (ምዕራፈ መስቀል) የተባሉት እነዚህ ናቸው።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
ወለወላዲቱ ድንግል ወለ መስቀሉ
ክቡር። አሜን።

<u>ምንጭ፡-</u>

1.አማከለ ገበየሁ፥ቅድስት ሀገር፥ 1996 ዓ.ም.
2. አባ ገብረ ሥላሴ ተስፋ፥ በቅድስት ሀገረ ኢየሩሳሌም ከ15 ዓመት በላይ የኖሩ የቃል አስረጂ.
3. ISRAEL (The Golden Book), 2004.
4. VIA DOLOROSA (Pictorial Map and Illustrated Guide).

# የቆስጠንጢኖስ ...

*/ ከገጽ ፳፩ የዞረ/*

4. ከክርስቲያኖች ወገን በሕይወቱም ሆነ በሞቱ «ንብረቴን ለቤተ ክርስቲያን አወርሳለሁ» የሚል ምእመን ቢኖር ቤተ ክርስቲያን ኑዛዜ የመቀበል፤ ውርስ የመውረስ መብት አላት።
5. በ321 ዓ.ም. በክርስቲያኖች መካከል አንዳንድ አለመግባባት ቢፈጠር ወንጀል ነክ ላልሆነ ጉዳይ ለኤጲስ ቆጶሳት የዳኝነት ሥልጣን ሰጥቷቸዋል።

በጠቅላላውም ቤተ ክርስቲያን የወንጌልን የመዳን መልእክት እያወጀች ሐዋርያዊ ጉዞዋን እንድትቀጥል ያልተቆጠበ ጥረት ትና ርዳታ ያደረገላት መፍቀሬ ሃይማኖት ወፍትሕ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ወልደ እሌኒ ነው።

ቆስጠንጢኖስ ከዚህ በላይ የተዘረዘረው ሕጋዊ የቤተ ክርስቲያን መብት በሕገ መንግሥቱ እንዲሠፍርና ክርስትናም የመንግሥቱ ብሔራዊ ሃይማኖት (state religion) እንዲሆን ዐወጀ። ቆስጠንጢኖስ እናቱ እሌኒ ክርስቲያን ስለነበረች የክርስ ትናን ትምህርት በመሠረቱ ይቀበለው እንጂ በይፋ ተጠምቆ ወደ ቤተ ክርስ ቲያን የገባውና ክርስቲያን የተባለው ለሞት በቀረበበት ጊዜ ነበር። ያጠመቀ ውም የኒቆሚዲያ ኤጲስ ቆጶስ አውሳብዮስ ነው።

ቆስጠንጢኖስ በሕይወቱ ፍጻሜ የተጠመቀበት ሁለት ምክንያቶች አሉ። እነርሱም፡- አባ ጎርጎርዮስ «የቤተ ክርስ ቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ» በሚለው መጽሐፍ እንዳሰፈሩት አንዱ ምክንያት፡ - ቆስጠንጢኖስ ከአረማዊ አባት የተወለደና በዲዮቅልጥያኖስ ቤተ መንግሥት ያደገ በመሆኑ፤ ኋላም የነገሠው በአረማውያን ላይ ስለነበረ በሕዝቡ ዘንድ ተቃውሞ እንዳይነሣበት ነው።

ሁለተኛው ምክንያት ከቤተ ክርስ ቲያንና ከምእመናን ሕይወት እንደ ምንረዳው የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ማለት እስከ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖች፡- «ኃጢአት በጥምቀት ከተሰረየ በኋላ ሁለተኛ ኃጢ አት ደግመው ቢሠሩ አይሰረይም» የሚል እምነትና ትምህርት ስለነበራቸው፤ ከተጠመቁና ክርስቲያን ከተባሉ በኋላ ኃጢአት እንዳይሠሩ፥ ወደ ኃጢአት እንዳይመለሱ በመፍራት ይጠመቁ የነበሩት ካረጁና ካፈጁ በኋላ እንዲያውም በሞት ጻዕር ላይ በሚገኙበት ቅጽበት ነበር። ቆስጠንጢኖስም ጥምቀቱን ያዘገየው በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም።

*/ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል/*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ ሕይወቱ ትምህርቱ

*ዲያቆን ስሎሞን ወንድሙ*

## ልደቱ ለያዕቆብ ዘሥሩግ

የሥሩግ ኤጲስ ቆጳስ የነበረው ቅዱስ ያዕቆብ ኤፍራጥስ በተባለች መንደር በ451 ዓ.ም ተወለደ:: አባቱ የሶርያ ሊቀ ካህናት ነው:: ከእርሱ በቀር ልጅ አልነበረውም:: በሦስት ዓመቱ እናቱ ይዛው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደች:: በዕርገተ ቁርባን ጊዜ ከእናቱ ተለይቶ ወደ ቤተ መቅደስ ገባ:: ሊቀ ጳጳሱ ጸጋ እግዚአብሔር እንደ ጠራችው ዐውቆ በጽዋው ሦስት ጊዜ ከደሙ አጠጣው:: ብላቴናው ያዕቆብም በሕዝቡ ፊት፡- «ሦስት ነገሮች ያስፈሩኛል፤» በማለት ማልቀስ ጀመረ:: የሚያስፈሩት ነገሮችም፡- 1ኛ/ የነፍስ ከሥጋ መለየት፤ 2ኛ/ በጌታ ፊት በአካለ ነፍስ መቅረብ፤ 3ኛ/ ከጌታ «ወደ ገነት ወይም ወደ ሲኦል ሂድ» የሚለውን ፍርድ መስማት ናቸው::

ሕዝቡና ካህናቱ ይህን ሲሰሙ፡- «እግዚአብሔር በሕፃኑ አድሮ ገሠጸን» በማለት ማልቀስ ጀመሩ:: ቅዱስ ያዕቆብ የተማረው በኤዴሳ ነው:: ኤዴሳ የዛሬዋ ቱርክ ከተማ ነበረች:: የዛሬን አያድርገውና ጥንተ ክርስትና የተሰበከባት የክርስትና ማዕከል ነበረች:: ኤዴሳ በቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ደግሞ «ሮሐ» በሚል ስያሜ ትታወቃለች:: ዛሬ ግን ኡርፋ በመባል ትጠራለች::

ቅዱስ ያዕቆብ በሰባት ዓመቱ የብሉያትና ሐዲሳት መጻሕፍትን አጥንቷል:: በዐሥራ ሁለት ዓመቱ ድርሰት መድረስ ችሏል:: አንድ ቀን አምስት ያህል ጳጳሳት መጥተው ቅዱስ ያዕቆብን፡- «ከፊታችን ቆመህ እኛ እየሰማንህ አዲስ ድርሰት ድረስልን::» አሉት:: ቅዱስ ያዕቆብም ትሕትና ልማዱ ስለሆነ፡- «አባቶቼ በእናንተ ፊት እንኳን እንግዳ ድርሰት መድረስ ያጠናሁትን ቀለም አክናውኖ መናገር አይቻለኝም::» አላቸው:: «እንግዲያስ በቤተ ክርስቲያን ያለውን ሥዕለ አርባዕቱ እንስሳን ተርጉምልን» አሉት:: በሥዕለ አርባዕቱ እንስሳ ሕዝቅኤል በፈለገ ኮባር /በኮባር ወንዝ/ እንዳያቸው ሁነው አንገታቸውን ዘንበል አድርገው ተሥለዋል:: ቅዱስ ያዕቆብ «እሺ» ብሎ፡- «ሁለቱን ክንፋቸውን ወደ ታች ማድረጋቸው ደኀራዊነቱን ይመረምሩታል÷ ያጡታል:: ሁለቱን ክንፋቸውን ወደ ላይ ማድረጋቸው ቀዳማዊነቱን ይመረምሩታል÷ ያጡታል:: በሁለት ክንፋቸው ከዳርቻ ዳርቻ ይበራሉ÷ ሁለቱን ክንፋቸውን ወዲያና ወዲህ ማድረጋቸው ምልዓቱን፣ ስፋቱን ይመረምራሉ÷ ያጡታል፤ የማይመረመር ስለሆነ:: ስለዚህ ዕፁብ÷ ዕፁብ÷ ዕፁብ ይላሉ::» ብሎ ተርጉሞላቸዋል::

ቅዱስ ያዕቆብ ለረጅም ዓመታት አነስተኛ የኾኑችውን የሥሩግ ሀገረ ስብከት ኤጲስ ቆጳስን በመጐብኘት ያገለግል ነበር:: በ519 ዓ.ም በባትናም ኤጲስ ቆጳስነት ተሹሞ ሁለት ዓመት ከመንፈቅ አገልግሎ ዐርፏል:: ዕረፍቱ በሰኔ 27 ቀን ነው:: ገድል ተጽፎለታል፤ ጽሌ ተቀርጾለታል:: ቅዱስ ያዕቆብ በሶርያ ቋንቋ በመቶዎች የሚቆጠሩ በግጥም መልክ የተዘጋጁ ድርሳናትን በመጻፉ፡- *«ዕንዚራ መንፈስ ቅዱስ»* (The Flute of the Holy Spirit) የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል:: በሶርያ ቤተ ክርስቲያንና በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት በስፋት ጥቅም ላይ የዋለ ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በግጥም የተዘጋጀ ድርሰት ደርሷል:: በስሙ የሚታወቅ ቅዳሴም ደርሷል:: በሀገራችን በቅዱሳን መላእክት በዓላትና በነገረ ምጽአት መታሰቢያ ዕለት ቅዳሴው ይቀደሳል::

✥ ✥ ✥

ቅዱስ ያዕቆብ ስለ ነገረ ድኅነት ሰፊ ትምህርት አስተምሯል:: በትምህርቱም፡- አባታችን አዳም ጥንተ ተፈጥሮው በወልደ እግዚአብሔር አምሳል ነው ይላል:: አዳምና ሔዋንም ዔደን ገነትን ይከባከቧትና ይጠብቋት ዘንድ በዚያ ነበሩ:: ዔደን ገነትም ለሰው ዘር መኖሪያ ትሆን ዘንድ የተገባች ነበረች::

አዳም በጥንተ ጠላት ዲያብሎስ በመሸነፉ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የጥል ግድግዳ ተገነባ:: አዳም ከገነት ተባረረ:: ተመልሶ እንዳይ ገባባትም በሚገለባበጥ እሳት ተከባ በኪሩቤል ሰይፍ ትጠበቅ ነበር:: የሰው ልጅ በምድረ ፋይድ (በመከራ ምድር) ሲኖር በኃጢአት ቀንበር ወድቆ፣ አምልኮ ባዕድን ጀመረ:: በዚህም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ልዩነት በጣም እየሰፋ መጣ:: ስሕተትን ያጠፋ ዘንድ እውነትን በመጀመሪያ በሲና ተራራ፣ ከዚያም በነቢያት ትንቢትና ምሳሌ በብዙ ኅብረ አምሳል ገለጠ:: ጌታ በሥጋ ማርያም እስኪገለጥ ድረስ የሰው ልጅ ታሪክ በእውነትና በስሕተት፣ በብር ሃንና በጨለማ ትግል ውስጥ ነበረ:: እግዚአብሔር በአርአያውና በምሳሌው የፈጠረውን የሰው ልጅ ያድን ዘንድ፣ የጠላት ኃይልንም ያጠፋ ዘንድ አንድ ልጁን ላከ:: በማይመረመር ረቂቅ ምሥጢር በኀቱም ድንግልና በማኅፀነ ማርያም ተፀነሰ:: ስለዚህም ድንግል ማርያም «ምሥጢር የተሞላች÷ የታተመች ደብዳቤ» ሆነች:: በድንቅ መገለጥ ረቂቅ መለኮት ሥጋን ተዋሕዶ በግልጽ ታየ፤ የተሰወረው ተገለጠ:: ጌታ አምላክነቱን በእጁ ተአምራትና በቃሉ ትምህርት በመግለጥ የሰው ዘርንም ወደ አባቱ አቀረበ:: በመልዕልተ መስቀልም ካህናተ አይሁድ ዕሩቅ ብእሲን የሰቀሉ እንዲመስላቸው ለአጽድቆተ ትስብእት፣ ለአብነትና ለአቅርቦተ ሰይጣን በተናገራቸው ሰባት ቃላት አሞኛቸው:: በክብርት ሞቱም ኅበዝ ዋናተኛ የጠፋውን ዕንቍ ለማውጣት ወደ ጥልቁ ባሕር እንደሚገባ አባታችን አዳምን ከገባበት ያወጣ ዘንድ በአካለ ሥጋ ወደ መቃብር በነፍሱ ወደ ሲኦል ወርዶ በብርሃኑ ሲኦልን በዘበዛት፤ ነፍሳትንም ከግዞት ነጻ አወጣቸው፤ ወደ ገነት መለሳቸው:: የሰው ልጅም በሐዲስ ተፈጥሮ ተፈጠረ:: በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የተገነባው የጥል ግድግዳ ፈረሰ፤ የሰው ልጅ በሐዲስ ሰውነት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ቻለ:: የእግዚአብሔር ቃል በማኅፀነ ማርያም እንዳደረ ፍጹም ቃሉ በምእመናን ንጹሕ ኅሊና አደረ::

ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ የመለኮትና ፣ ትስብእትን ፍጹም ተዋሕዶ በማስተማሩ *«የተዋሕዶ ጠበቃ»* ተብሏል:: በትምህርቱ «ወልደ እግዚአብሔር እንበለ ውላጤ /ያለመለወጥ/ ሰው ሆኗል:: በእርሱም አንዲት ፈቃድና አንዲት ግብር አለች፤ በተዐቅቦ የመለኮት ግብር የትስብእት /የሥጋ/ ግብር፣ የትስብእት /የሥጋ/ ግብርም የመለኮት ግብር ሆኗል:: ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ባሕርይ፣ አንድ አካል ነው::» በማለት የንስጥሮስንና ኬልቄዶናውያንን የምንታዌ ትምህርት ይቃወማል::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ድርሳነ ያዕቆብ ዘሥሩግ

ቅዱስ ያዕቆብ÷ ዘሥሩግ አባታችን አብርሃም አንድ ልጁን ይስሐቅን ለመሥዋዕትነት እንዴት እንዳቀ ረበውና ይስሐቅም በበጉ መሥዋዕትነት እንደዳነ የተጻፈውን ታሪክ በሰፊው አመሥጥሮታል÷ ምሳሌውንም አብራርቶ ገልጦታል:: ጸሎቱና በረከቱ ለዘለዓለም በእኛ ላይ ይደርብንና በሥሩግ ኤጲስ ቆጶስነትን የተሾመው የቅዱስ ያዕቆብ ድርሳን ይህ ነው::

«የእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ሆይ! ልቡናዬ ምሥጢርን ሊያውቅ፣ ለሌሎችም ይገልጥ ዘንድ ይሻል:: ሕማምህና ሞትህ በተነገረ ጊዜ ልብ ይለያል፣ ኅሊናም ይመታል፣ ነፍስም ትንቀጠቀጣለች:: አቤቱ÷ ሕማምህንና ሞትህን እናገር ዘንድ ማስተዋልን ስጠኝ፣ እንደቤቴንም ክፈት:: አብርሃም የአንተን ቀን ሊያይ እንደ ወደደና አይቶም ደስ እንዳለው /ዮሐ.8÷56/ እኔም የሕማምህንና የሞትህን ነገር መናገር እሻለሁ:: አብርሃም የሞትህ ምሳሌ ስለ ተገለጸለት በቸርነትህ ስጦታ ደስ አለው:: ወልደ እግዚአብሔር ሆይ÷ ከአንተ የተገኘው ምሥጢር ታላቅ ነው:: በይስሐቅ ፈንታ የተሠዋው በግ የታሰረበት ዕፀ ሳቤቅ እንዲፈታ ባደረገ ጊዜ ድንቅ ምሥጢር ተገለጠ::

አረጋዊ አብርሃም የእግዚአብሔርን ቀን ለማየት ወዷልና÷ የጌታችን መድኃኒትነት እንደምን እንደሚገለጽለት ማወቅን ልቤ በወደደ ጊዜ መልካም ምሥጢር ተገለጸ:: እንግዲህ እንዲህ እላለሁ:- አብርሃም እንዴትና በምን ሁኔታ ይህን ቀን አየ? እንዴትስ ደስ አለው? የይስሐቅ ለመሥዋዕትነት መቅረብ በጌታ ሕማምና ሞት ግልጽ ምሳሌ በመሆኑ ከመናገር መከልከል አይቻልም:: ሊነገር የሚገባውን መሥዋዕትነት ገልጬ ልናገር፤ ፍጻሜውንም እነግርሃለሁ:: አሁንስ ስለ አብርሃም የወልድን ነገር መናገር ተገለጠ:: እግዚአብሔር አብራምን «አብርሃም» ብሎ ጠራው:: አብርሃምም:- «ጌታዬ÷ እነሆ አለሁ» አለ:: ያን ጊዜ «አንድ ልጅህን ወስደህ እኔ በማመለክትህ ተራራ ላይ ሠዋልኝ» አለው:: እግዚአብሔር ይህን ያለው የይስሐቅን መሥዋዕትነት ሽቶ ሳይሆን ለወልደ እግዚአብሔር መሥዋዕትነት ምሳሌ ይሆነው ዘንድ ነው:: የይስሐቅን ታዛዥነትና ሞት ለጌታ ሕማምና ሞት ምሳሌ መሆኑን ሳልገልጽ መተው አይቻለኝም:: የይስሐቅ ምሳሌነት ለጌታ አማናዊ ሕማምና ሞት ነውና::

ዳግመኛም ይስሐቅ÷ አብርሃም በሽምግልናው ወራት ያገኘው አንድ ልጁ ሲሆን «ልጅህን ሠዋልኝ» በተባለ ጊዜ ታላቅ ምሥጢር ባይኖን ኖሮ «አይሆንም» ባለ ነበር:: ይስሐቅም «እሺ» ብሎ ለመሠዋት ባልተዘጋጀም ነበር:: አስቀድሞ ለወልደ እግዚአብሔር መሥዋዕትነት ምሳሌ ይሆን ዘንድ አብርሃም ፈጣሪውን «እሺ» ብሎ ልጁን ለሞት አቀረበ፤ ይስሐቅም አባቱን «እሺ» ብሎ ራሱን ለሞት አቀረበ:: እግዚአብሔር አብርሃምን ሊፈትነው ይህን እንዳደረገ መጻሕፍት ይናገራሉ:: ይህን ታሪክ የምታስተምር አስቀድመህ ይህን ጥልቅ ምሥጢር ለመረዳት ሞክር:: እግዚአብሔር የአብርሃምን ደግነት ስለ ሚያውቅ ወዳጅ አደረገው፤ ፍቅሩንም ለመፈተን የልጁን መሥዋዕትነት የፈለገው ረቂቅ ምሥጢርን ለመግለጽ ስለ ወደደ ነው:: አብርሃም የወልደ እግዚአብሔርን ዕለተ ሞት ሊያይ ይወድ ነበርና ይስሐቅ በአብ አንድ ልጅ ምሳሌ ሞትን ታገሠ:: አብርሃም የጌታን ምሳሌ አይቶ ደስ አለው:: በዚህም በፍጻሜው ጌታ የሚያደርገውን ድንቅ ምሥጢር ለማወቅ በቃ::

አብርሃም ልጁን እንዲሠዋ ሲጠየቅ:- «በዚህ ልጅ ዘርህ ይበዛል ብለህ ሰጥተኸኝ አልነበረምን? ከሠዋሁት በምን ይበዛል? ቃል ኪዳንህም ፈረሰ::» ማለት ሲችል ከመታዘዝ በቀር መልስ አልሰጠም:: ዳግመኛም <ዘርህ እንደ ሰማይ ከዋክብት፣ እንደ ባሕር አሸዋ ይበዛል ሃል> ብለህ ተስፋ ሰጥተኸኛል:: ታድያ አባት ልጁን ሠውቶ ዘሩ የበዛለት በየትኛው ዘመን ነው?» በማለት መጠየቅ ሲችል ፈጣሪውን በመውደዱና በማመኑ «እሺ» በማለት ታዘዘ እንጂ አልተከራከረም:: ይስሐቅም የጌታ ምሳሌ ነውና «እሺ» በማለት ለሞት ታዘዘ::

እግዚአብሔር አብም:- «ይስሐቅ ለረቂቅ ምሥጢር ምሳሌ ነውና ለልጅህ አትዘንለት፤ እኔም ለምወደው ልጄ አላዘንለትምና፤ ልጅህን ሠዋው» አለው:: ዳግመኛም «ልጅህን ለመሥዋዕት ባቀረብህ ጊዜ፣ ቢላዋውንም በአንገቱ ላይ ባሳረፍህ ጊዜ የክርስቶስን ምሳሌነት እንዳይጉድል ልብህ እንዳይሸበር፣ እንዳትጠራጠር፤ ልጅህን በመሠዋትህ ልቡናህ እንዳያዝን ተጠንቀቅ» አለው:: ስለዚህም አብርሃም በደስታ ልጁን ፈጥኖ ሊሠዋው ወደ ተራራው ወሰደው:: ይስሐቅን ሊሠዋው ሲወስደው ሚስቱ ሣራ በስተ እርጅና ያገኘችው ልጅዋ ስለሆነ ሳስታ ያሰበውን እንዳይፈጽም እንዳታሰናክለው አልነገራትም፤ በእርሱና በፈጣሪው መካከል ያለውን ምሥጢር ለማንም አልገለጠም:: ሁለት ሎሌዎቹን አስከትሎ ለመሥዋዕት ማቅረቢያ የሚሆነውን እንጨት አሸክሞ፣ የመሠዊያውን ቢላዋ ራሱ ይዞ ወደ ተራራው ወጣ:: ለሎሌዎቹ ወደ ተራራው ለምን እንደሚሄዱ አልገለጠላቸውም፤ በመንገዱ በመቸኮሉ የአምላክ ምሥጢር ይታየው ነበር፤ የልጁም ትንሣኤ ሐዘኑን ያርቅለት ነበር:: ይስሐቅም አባቱ ሊሠዋው እንደሚወስደው ባለማወቁ ያለ ፍርሃት ከአባቱ ጋር እየተነጋገረ ይኼድ ነበር:: «የመሥዋዕቱ በግ ወደ የት አለ?» በማለት ጠየቀ እንጂ «ወደ የት እንሄዳለን?» አላለም:: አብርሃም ግን መልስ አልሰጠውም:: ከሦስት ቀን መንገድ በኋላም እግዚአብሔር አብርሃምን:- «ድኅነተ ዓለም ወደሚፈጸምበት ተራራ ውጣ፤ በመሠዊያውም ላይ ያለ መጥባሕት ሕያውና ምዉት ሆኖ የቀረበ ንጹሕ መሥዋዕትና ቍርባን ተመልከት:: ድኅነት የሚሰጥ ባትን ዕለት ተመልከት፤ አንተም ዛሬ ልጅህን በመሠዋት ግለጣት፤ ቀርበህም ተረዳት፤ በዚህም የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌነት ትፈጸማለች:: የመንገድህ ፍጻሜ ይህ ነው:: በዚህ ቦታ የጌታ ንጹሕ ደም ይፈስበታል::» አለው:: ይህ ቦታ ጎልጎታ ነው:: ይስሐቅ ለመሥዋዕትነት በታሰረበት ቦታ የጌታ መስቀል ተተክሏል፤ ይስሐቅ በታሰረበት ወልደ እግዚአብሔር እጁንና እግሩን ተቸንክሮበታል:: ለይስሐቅ መሠዊያ ወቅለምት /ካራ/ በተሣለበት ቦታ ለጌታ መውጊያ ቀኖት ተስሎበታል:: ሎሌ ቀድሞ ለጌታው መንገድ እንደሚጠርግ ይስሐቅ መሥዋዕትነቱን ሳያውቅ ወደ ተራራው ወጣ:: የጌታ መምጣት ለመሥዋዕትነት ነውና ወደ ተራራው ወጣ:: አብርሃም በተራራው ላይ ምሥጢር እንደሚፈጸምበት ዐወቀ:: እግዚአብሔር ልጅህን በማሳይህ ተራራ ላይ ሠዋው አለው እንጂ ተራራውን በስም አልነገረውም:: ስለዚህም ይስሐቅን በጎልጎታ ይሠዋው ዘንድ ክርስቶስ በመሠዊያው ከመስቀሉ አስቀድሞ አብርሃም ለሦስት ቀናት በተስፋ ተጓዘ:: በሦስት ቀን ጉዞውም ክርስቶስ በከርሠ መቃብር የሚያድርበትን ሦስት መዓልትና ሌሊት ምሳሌ ፈጸመ:: ጌታ በሦስተኛው ቀን ሞትን ድል አድርጎ እንደ ተነሣ ይስሐቅም በሦስተኛው ቀን ተሠዋ፤ የጌታ ትንሣኤ ምሳሌ ይፈጸም ዘንድ ይህ ምልክት ታየ::

አብርሃም ሎሌዎቹን:- «በተራራው እግር ሥር ቆዩኝ፤ እኔና ልጄ ከተራራው ላይ ጸሎት አድርገን እንመለሳለን::» አላቸው:: አብርሃም ልጁን ሊሠዋው እየወሰደው ለሎሌዎቹ «እንመለሳለን» ማለቱ ልጁን ለመሠዋት ተጠራጥሮ ይሆን? ወይስ ትንቢት መናገሩ? ወይስ ይስሐቅ እንዳይፈራ ማረጋጋቱ? ወይስ የተሠዋውን ልጅ እግዚአብሔር ያስነሣልኛል ብሎ በማመኑ? እንዴት ከይስሐቅ ጋር መመ ለሱን ዐውቆ እንዲህ አለ? «ሎሌዎቹም ለምን ወደ ተራራ እንዳን ወጣ ከለ ከለን? ለእግዚአብሔር የሚሰግድስ ከሆነ ለምን የጸሎት ልብሱን አለበሰም? መሥዋዕት ለማቅረብ ከሆነስ ለምን የመሥዋዕቱን በግ አልያዘም?» ይሉ ነበር:: አብርሃም ግን በጎልጎታ በተገለጠለት ምሥጢር አእምሮው ተይዞ ነበር፤ መስቀልም በእጁ መካከል ይታየው ነበር:: ያን ምሥጢር ብቻውን ያይ ዘንድም ሎሌዎቹን በእግረ ተራራ እንዲቆዩ አዘዛቸው:: ይስሐቅን በኅሊናው ሲሠዋው እንደ ሚድን ተስፋ ያደርግ ነበር:: ነገር ግን በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚድን አላወቀም::

አብርሃም ለመሥዋዕት የሚሆነውን እሳቱንና መጥባሕቱን /ካራውን/



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ይዞ÷ይስሐቅ ደግሞ የወልደ እግዚአብሔርን መስቀል ተሸክሞ ወደ ተራራ መውጣቱን ለማጠየቅ ለመሥዋዕት ማቅረቢያ የሚሆነውን እንጨት ተሸክሞ ወጣ:: አብርሃም ከሎሌዎቹ አንዱን:- «እንጨቱን ከተራራው ላይ አድርሰህ ተመለስ» ማለት ይቻለው ነበር:: ነገር ግን ይስሐቅ የጌታ ምሳሌ ሆኖ መስቀሉን ተሸክሞ ይሔድ ዘንድ ሎሌውን እንዲይዝ አልፈቀደለትም:: ለጌታ መሥዋዕትነት ምሳሌ ይሆን ዘንድ ይስሐቅ አስቀድሞ መሥዋዕት ሆኖ ቀረበ::

ይስሐቅ:- «አባቱን ለመሥዋዕት ማቅረቢያ የሚሆነው እንጨት፣ መጥባሕት /ካራ/ እንዲሁም እሳት በዚህ አለ:: ነገር ግን የሚጨሰው መሥዋዕት ወደ የት አለ? አንተ መሥዋዕቱን በሚያቀርበው ካህን አምሳል ተዘጋጅ ተሃል÷ የምትሠዋው መሥዋዕት ግን የለም:: እኔን መሥዋዕት አድርገህ ልታቀርበኝ ፈቅደህ ነውን?» በማለት ጠየቀው:: አብርሃም የልጁን የሚያሳዝን አነጋገር ሲሰማ ልቡ ያሰበ ውን ለማድረግ አልራራም፤ ፈጽሞም አላዘነም:: ይልቁንም ለልጁ:- «ለመሥዋዕት የሚሆነው በግ ወደ የት እንዳለ እግዚአብሔር ያውቃል::» በማለት ነገረው እንጂ:: ይስሐቅ አባቱን የጠየቀው ሁሉ÷ ወልድ ሥጋ ብእሲን በመዋሐዱ አባቱን አብን የጠየቀው ጥያቄ ነው:: ይስሐቅ:- «የመሥዋዕቱ በግ ወደ የት አለ?» በማለት እንደ ጠየቀው፤ ወልድም አባቱን «አባት ሆይ÷ ቢቻልህስ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ::» በማለት ጠይቋል::

አብርሃም ልጁን ይዞ ከተራራው ራስ በደረሰ ጊዜ:- «ከዚህ ቁም÷ መሥዋዕቱን የምታቀርበው ከዚህ ነው» የሚል ምልክት ታየው:: ስለዚህም ምልክቱን ወዳየበት ቦታ ቀርቦ መሥ ዋዕት ለማቅረብ የሚመቸውን ቦታ ተመለከተ:: ጎልጎታ ምሥጢር ይፈጸም ዘንድ የመሠዊያውን መሠረት አዘ ጋጀ:: ይኸውም ወልድ በፈቃዱ ለመሞቱ ምሳሌ ነው:: የመሠዊያው ቦታ እንደ ተዘጋጀ እንጨቱን ረበረበ:: ይስሐቅም አባቱ ሊሠዋው እንደ ተዘጋጀ ባወቀ ጊዜ ሸሽቶ መሄድ ሲቻለው:- «አባቴ ሆይ÷ ልትሠዋኝ ከፈቀድክ እነሆ የፈቀድከውን አድርግ÷ ከፈቃድህ አልወጣም::» በማለት ራሱን አጎንብሶ እጆቹን የኋሊት ታስሮ ለመሠዋት ተጋደመ:: የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ በመሆኑ በፈቃዱ ታሰረ:: አብርሃም የአንድ ልጁን መሥዋዕትነት ደስ ብሎት ባይቀበል ኖሮ ምሳሌውን ለማየት ባልበቃም ነበር:: ይስሐቅም መሠዋቱን ዐውቆ ባይታገሥ የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ ለመሆን ባልቻለ ነበር:: የጌታ ምሳሌነት ትዕግሥት ሰጥቶት ሁሉን ታገሠ እንጂ:: ጌታ አባቱን: - «የእኔ ፈቃድና የአንተ ፈቃድ አንዲት በመሆኗ እንደ ፈቃድህ ይሁን እላለሁ እንጂ እንደ እኔ ፈቃድ ይሁን አልልም::» በማለት እንደ ተናገረው ይስሐቅም:- «እንደ ፈቃድህ አድርግ» በማለት በፈቃዱ እጆቹን ታሰረ:: አብርሃምም በደስታ ልጁን ለመሠዋት ባቀረበ ጊዜ:- «ልጄ ሆይ÷ አንተ ቀድመህ ሂድና በዚያ ቆየኝ:: እኔ የምልክህ ወደ ንጉሠ ሰማይ ወምድር ፈጣሪዬ ነው:: በዚያ ያለው ሀብት ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ አታውቅም:: ስለዚህ ደስ ይበልህ::» አለው:: ይስሐቅም:- የሚያስደስተው ብዙ ትርፍ የሚገኝበት ሀብት እንጂ ሞት መራራ መሆኑን ሰምቻለሁ:: ነገር ግን አሁን የምቀበለው ሞት መዓዛው የሚጣፍጥ፣ ጣዕሙ የሚያስደስት ነው:: በመሠዋቴ አዲስ ሕይወት የማገኝ ስለሆነ የሞት ሐዘን አይሰማኝም:: በዚህም ታላቅ ትምህርት ተገልጾልኛልና የቀረ በልኝን ከመቀበል ወደ ኋላ አልልም:: ስለዚህም የታዘዝከውን ፈጽም» አለው::

አብርሃም በኅሊናው አስቀድሞ የልጁን ደም በማፍሰስ ሠውቶታል:: ዳግመኛም መጥባሕቱን (ካራውን) አንሥቶ በይስሐቅ አንገት ላይ አሳርፎ እስባለሁ ባለ ጊዜ:- «ተው እንዳታደርገው::» የሚል ድምፅ ሰማ:: መልአከ እግዚአብሔርም: - «... ታላቅ ምሥጢር ፈጽመሃልና ልጄን እሠዋለሁ አት በል:: ዓለም በይስሐቅ መሥዋዕትነት አይድንምና ሰይፉን ከአንገቱ ላይ አንሣው:: ይስሐቅንም ከታሰረበት ፍታውና ይሂድ፤ በዚህ የምትታይ ምሥጢር አለችና ቀርበህ ተመልከት፤ እውነተኛውንም ምሳሌ ተመልከት:: እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- <አንተ ዛሬ ለልጅህ እንዳልራራህ ለአንድ ልጄ አላዝንለትም:: ለዓለም ቤዛ አሳልፌ እሰጠዋለሁ:: አሁን አይተህ ደስ ይልህ ዘንድ ምሳሌውን ገለጥኩልህ:: ይህን እስከ መጨረሻ ጠብቀው:: ይስሐቅ ቢሠዋ ሲዖልን ሊማርክ÷ በሮቿንም ሊከፍት÷ ነፍሳትን ነጻ ሊያወጣ÷ ሞትን ድል ሊነሳ አይችልም:: ጽኑዕ ሥልጣን ያለው ልጄ ግን አጋንንትን ድል ነስቶ ነፍሳትን ነጻ ያወጣል:: ይስሐቅ መሥዋዕት ቢኾን በሲዖል ወደአሉ ነፍሳትም ቢሄድ አይጠቅማቸውም፤ መሥዋዕትነቱም ለራሱም ለማንም አይጠቅምምና ተወው::» አለው:: አብርሃም የወልደ እግዚአብሔርን ምሳሌነት በማየቱ በጣም ደስ አለው:: የስቅለቱን ነገር እንደምን ይሆን? መቼ ይሆን? እያለ ሲያወጣ ሲያወርድ በግ በእንጨት ላይ ታስሮ፤ በበግ አምሳል የጌታ የስቅለቱና የሞቱ የትንሣኤው ምሥጢር ተገለጠለት:: አብር ሃም ይስሐቅን ፈታና:- «የክርስቶስን ነገር ልትረዳ ከፈቀድህ መረዳት የም ትችል በት ጊዜው አሁን ነውና አይተህ ደስ ይበልህ፤ የሚፈጸምበትን ቀን ለማየት ከወደድክ ሁሉም ከፊትህ አለልህ::» አለው::

የይስሐቅ ከታሰረበት መፈታት÷ ጌታ አምልኮተ ጣዖትን ከሰው ልጅ የመለየቱና የማጥፋቱ ምሳሌ ሆነ:: ጌታ እንበለ ሩካቤ፣ እንበለ ዘር፣ እንበለ ሰስሎተ ድንግልና ከእመቤታችን ተወለደ፤ የሰውን ዘር ከማዕሰረ ኃጢአት እስኪፈታ ድረስ ሁሉም በኃጢአት ተይዞ ነበርና:: አብርሃም ለዚህ ምሥጢር ምሳሌ የሚሆነውን በግ ሠዋ:: በበጉም መሠዋዕትነት አንድ ልጁ ስለዳነለት ደስ አለው:: ዳግመኛም አምላካችን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተመሰገነ ነው:: ደስታን ለሚሰጥ፣ ሐዘንን ለሚያርቅ ለእርሱ ለዘለዓለሙ ክብር ምስጋና ይሁን:: አሜን::

# የቆስጠንጢኖስ ...

/ ከገጽ ፰ የዞረ/

ታላቁ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በበራንጥያ ታላቅ ከተማ ሠርቶ በስሙ «ቁስጥንጥንያንኸ (constantinople) ብሎ ሰይሟቷል:: በዚያም ቤተ ክርስቲያን አሳንጿል:: ለቤተ ክርስቲያን ብዙ ውለታ ውሏል:: ቤተ ክርስርቲያንም ስለ ብዙ ውለታው ስታስታውሰው ትኖራለች:: ቆስጠንጢኖስ መነኮሳት በአክናፈ እሳት ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ሲያርጉ አይቶ አባ ብሶይን በአካለ ነፍስ ሄዶ: «ሰላም ለክሙ፤ አ ብፁዓን መነኮሳት» ብሎታል:: አባ ብሶይም «አንተም እንጂ ብፁዕ ነህ፤ በዘመንህ ቀርነ ሃይማኖት ቆሟልና» አለው:: ቆስጠንጢኖስ «የመነኮሳትስ ክብራችሁ እንዲህ እንደሆነ ባውቅ: - መንግሥቴን ለቅቄ÷ ዳባ ታጥቄ÷ ዳዋ ጥሼ÷ ጤዛ ልሼ÷ ደንጊያ ተንተርሼ ዘመኔን ዘመን ሳልለው በኖርሁ ነበር» ብሎታል:: ከሄደ በኋላ አርድእቱ (የአባ ብሶይ ተማሪዎች÷ የመንፈስ ልጆች) መጥተው «እባታችን ከማን ጋር ስትነጋገር ነበር» አሉት:: «ቆስጠንጢኖስ በአካለ ነፍስ መጥቶ እንዲህ አለኝ፤ እኔም እንዲህ አልሁት» ብሏቸዋል:: (የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች ንባቡና ትርጓሜው):: ቆስጠንጢኖስ ለቤተ ክርስቲያን ከሠራቸው የማይረሱ ውለታዎች ውስጥ÷ የሚላኖው ውል፣ ኋላም በአርዮስ ምክንያት በተነሣው የቤተ ክርስቲያን የውስጥ ብጥብጥ፤ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ሠርታ ቀጥተኛውን የሃይማኖት ትምህርት ከሌላው ለይታ እንድታስታውቅ ጉባኤው እንዲሰበሰብ አድርጓል:: እንዲያውም በእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን የአርዮስ መርዝ መነዛቱ፤ ይህም ሁኔታ ቀስ በቀስ እየተባባሰ መሄዱ በእስክንድርያ ብቻ ሳይሆን በቆስጠንጢኖስ ቤተ መንግሥትም ስጋት ማሳደሩ አልቀረም:: በዚህም ምክንያት ነገሩን ለመረዳትና ተጨባጭ መፍትሔ እንዲገኝለት በማሰብ፤ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ የመጀመሪያውን መልእክተኛ ታማኝና ወዳጁ የነበረውን የእስጳኝ ጳጳስ ኦስዮስ /ሆስዮስን/ ወደ እስክንድርያ ላከው:: ኤጲስ ቆጶስ ሆስዮስም ከእለ እስክንድሮስና ከሌሎች ኤጲስ ቆጶሳት ጋር ሲወያይ ሰንብቶ ወደ ንጉሡ ተመለሰ:: ጉዳዩም በሽምግልና መፈታት እንደማይችል ለንጉሡ አስረዳው:: «ጠቡና ግዝቱ የሃይማኖት እንጂ የአስተዳደር ስላልሆነ በጉባኤ መታየት አለበት» ብሎ ለንጉሡ አማከረው:: ንጉሥ ቆስጠንጢኖስም የሃይማኖት ወዝግቡን ለማስወገድ ጉባኤ በኒቂያ እንዲደረግ ዐዋጅ አስነገረ::

አንዳንድ የታሪክ ጸሐፊዎች: - «የጉባኤው ሊቀ መንበር ራሱ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ነበር» ይላሉ:: ከሚያዝያ 21 እስከ መስከረም 21 ድረስ አባቶች ከያሉበት ተሰባስ
በው ኅዳር 9 /ወደ ገጽ ፲፬ ዞሯል/



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ነገረ ድኅነት በመጽሐፈ ቅዳሴ

መምህር ደጀኔ ሽፈራው

*ባለፈው እትም በሚፈጸመው ጸሎት ተለውጦ ሥጋ መለኰት ስለሚሆነው ኅብስትና ደመ መለኰት ስለሚሆነው ወይን አዘገጃጀት ያቀረቡልን መ/ር ደጀኔ በዚህ እትም ደግሞ ከግብዓተ መንጦላዕት ጀምሮ ያለውን የቅዳሴ ሥርዓት ማብራራት ይጀምራሉ፡፡*

/ካለፈው የቀጠለ/

## 5. ሥርዓተ ቅዳሴ

ይህ ክፍል የሚያካትተው ባለፈው በተከታታይ እንደ ተመለከትነው ከግብዓተ መንጦላዕት ጀምሮ ያለውን ነው፡፡ የሚዘልቀውም እስከ ምንባበ ወንጌል ነው፡፡ ይኸውም በአራት ምዕራፎች የተከፈለ ነው፡፡ ከእነዚህም በንዋያተ ቅድሳት ላይ ስለሚደረገው ጸሎት፥የንዋያተ ቅድሳትን ምሥጢር፥ የሥጋ ወደሙን ዝግጅትና እንዴት ከቤተ ልሔም ወደ ቤተ መቅደስ በክብር እንደሚገባ በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ የተቀረውን ደግሞ እንደ ሚከተለው እናያለን፡፡

ተራዳኢው ቄስና ዲያቆናቱ በቤተ ልሔም የተዘጋጀውን ኅብስትና ወይን አክብረው የቀራንዮ ምሳሌ ወደ ሆነው ቤተ መቅደስ በሚያስገቡበት ጊዜ ዋናው ቄስ እጆቹን ተናጽቶ ሳይቆይ ከመድረቁ በፊት ከተዘጋጁት ኅብስቶች አንዱን መርጦ ላዩን ይመዘምዘዋል /ይወለውለዋል/፡፡ ከዚህ በኋላ ቊርባኑ ሙቀት ሳይለየው ለምእመናኑ ማቊረብ እንዲችል ጊዜ ሳያባክን ነቅቶ ተግቶ ይቀድሳል፡፤ ዛሬስ እነ እገሌ መጥተዋልና «ድምጤን ይስሙልኝ፥ ቃሌን ይዩልኝ» ብሎ በማቀማጠል በማደላደል የሚቀድስ ከሆነ ግን የተዘጋጀውን ቊርባን ሙቀት ይለየዋል፡፡ ይህም የሥርዓቱን የሃይማኖት ምሥጢር ያፋልስበታል፡፡ ምክንያቱም ሙቀት ሳይለየው መቊረባችን «የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መለኰት አልተለየውም» ማለታችን ነውና፡፡

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ድኅነተ ምእመናንን በመስቀል ላይ በፈጸመ ጊዜ ቅድስት ነፍሱ ከክብርት ሥጋው ተለይታለች፡፡ «ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ፡- ተፈጸመ አለ፥ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ፡፡» እንዲል፡፡ ዮሐ.19፥30፡፡ መለኰት ግን ከነፍስም ከሥጋም አልተለየም፡፡ ይኸንን በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ፡- «ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን /ወደ መለኰታዊ ክብሩ ወደ አምላካዊ ጸጋው ሊያቀርበን/ እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዐመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት /ስለ ኃጢአተኞች ተላልፎ/ ሞተ፤ /ነፍሱ ከሥጋው ተለየች/፤ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ፤ /ሕያው መለኰት ከሥጋም ከነፍስም አልተለየም/፤» ብሏል፡፡ 1ኛጴጥ. 3፥18፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በመስቀል ላይ የፈሰሰውን የክርስቶስን ደም፥ «የእግዚአብሔር ደም» ያለው መለኰት ከክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ጋር በተዋሕዶ ስላለ ነው፡፡ ግብ.ሐዋ.20፥28፡፡ ስለዚህ «መለኰት ከክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም አልተለየም» ለማለት ሙቀት ሳይለየው ማቊረብ ይገባል፡፡ የክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ነፍስ የተለየው እሳተ መለኰት ያልተለየው ነውና፡፡

ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ለመቀበል የተሰበሰቡ ምእመናንም ነገረ እግዚአብሔር ወንጌልን አንድም ነገረ እግዚአብሔር ቅዳሴውን ለመስማት መከራ መስቀሉንም ለማሰብ በጸጥታ መቆም አለባቸው፡፡ ዋዛ ፈዛዛ የሚናገር፥ የሚስቅ፥ የሚሳለቅ መኖር የለበትም፡፡ እንዲህ ማድረግ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የፈጸመውን ቤዛነት ማቃለል ነው፡፡ ይኸንን በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡- «ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶች ሆነው ይመላለሳሉና /በመስቀል ላይ የተፈጸመውን ቤዛነት ያቃልላሉና/፤» ብሏል፡፡ ፊልጵ.3፥18፡፡

በቅዳሴ ጊዜ የሚስቅ ካህን ቅጣቱ አንድ ሱባዔ ነው፡፡ ቅጣቱን ፈጽሞ የማይመለስ ከሆነ ግን ክርስቶስን በመስቀል ላይ በመስቀላቸው እንደ ተደሰቱ አይሁድ ይቆጠራል፡፡ ምእመን ከሆነ ግን ወዲያው ከቤተ ክርስቲያን እንዲወጣ በዕለቱም ሥጋ ወደሙን እንዳይቀበል ይደረጋል፡፡ ይህም ፍርድ ለማበላለጥ አይደለም፡፡ ምክንያቱም /ካህን የሚቆመው ከውስጥ/፡- ስለሆነ የሚያየው የለም፡፡ ስለዚህ በዕለቱ ቆርቦ ከወጣ በኋላ ቅጣቱን ይቀበላል፡፡ አንድም «ቅዳሴውን አቋርጦ ይውጣ» የተባለ እንደ ሆነ ምእመናን ስለሚሰናከሉበት ነው፡፡ ምእመኑን ግን ሲስቅ ሲሳለቅ ሁሉ ያዩታል፤ ያዝኑበታልም፡፡ በዚህን ጊዜ ወዲያውኑ ከቤተ ክርስቲያን ያስወጡት እንደ ሆነ ሌሎች ከእርሱ ይማሩበታል፡፡ መቀጣጫ ያደርጉታል፡፡ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን የጸሎት፥ የሐዘን ቦታ ናትና፡፡ «ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የሚሆን የጸሎት ቤት ይባላልና የሚቃጠለውን መሥዋዕታቸውንና ሌላ መሥዋዕታቸውን በመሠዊያዬ ላይ እቀበላለሁ፡፡» እንዲል፡፡ ኢሳ.56፥7፤ ማቴ.21፥13፡፡ ነቢዩ ኤርምያስም፡- «ይህስ ስሜ የተጠራበት ቤት በዐይናችሁ የሌቦች ዋሻ ሆኖአልን? እነሆ፥ እኔ አይቻለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር፡፡» ብሏል፡፡ ኤር.7፥11፡፡

ሣቅ፥ አለማመንን ሊያመለክት ይችላል፡፡ «እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው፡- ካረጀሁ በኋላ በውኑ እወልዳለሁን? ስትል ሣራ ለምን ሳቀች? በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?» እንዲል፡፡ ዘፍ.18፥13፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ነቀፌታንም ያመለክታል፡፡ «በሰማይ የሚኖር እርሱ ይሥቃል፥ ጌታም ይሣለቅባቸዋል፡፡ በዚያን ጊዜ በቁጣው ይናገራቸዋል፥ በመዓቱም ያውካቸዋል፡፡» እንዲል፡፡ መዝ.2፥4፡፡ በትንቢተ ኤርምያስ ላይም፡- «አቤቱ፥ አታለልኸኝ እኔም ተታለልሁ፥ ከእኔም በረታህ አሸነፍህም፤ ቀኑን ሁሉ መሣቂያ ሆኛለሁ፤» የሚል አለ፡፡ ኤር.20፥7፡፡

ካህናትም ሆኑ ምእመናን በቅድስናው ስፍራ በምንቆምበት ጊዜ፡- 1ኛ/ እንደ አዳም፥ እንደ ዳዊት፥ እንደ ስምዖን ጴጥሮስ የራሳችንን ኃጢአት እያሰብን፤ 2ኛ/ እንደ ነቢዩ ሳሙኤል የወገኖቻችንን በኃጢአት መውደቅ እያሰብን፤ 3ኛ/ በዚህ ዓለም ዕለት ዕለት የሚፈጸመውን ግፍ እያሰብን፤ 4ኛ/ እንደ ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ መከራ መስቀሉን እያሰብን ማዘንና ማልቀስ ይገባናል፡፡ ይኸንን ካሰብን የምንደሰትበት ሰውነት፥ የምንስቅበት ጥርስ አይኖረንም፡፡ ሣቃችን ወደ ሐዘን፥ ደስታችን ወደ ትካዜ ይለወጣል፡፡ «እናንተ ኃጢአተኞች፥ እጆቻችሁን አንጹ፤ ሁለት አሳብም ያላችሁ እናንተ፥ ልባችሁን አጥሩ፡፡ ተጨነቁና እዘኑ አልቅሱም፤ ሣቃችሁ ወደ ሐዘን ደስታችሁም ወደ ትካዜ ይለወጥ፡፡ በጌታ ፊት ራሳችሁን አዋርዱ ከፍ ከፍም ያደርጋችኋል፡፡» እንዲል፡፡ ያዕ.4፥8-10፡፡



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

እንግዲህ ማንም ቢሆን በዋዛ በፈዛዛ፥ በሣቅ በሥላቅ በእግዚአብሔር ቤት እንዳይቆም:- ካህኑ ድምፁን ከፍ አድርጎ:- «ይህች ቀን ምን ያህል የምታስፈራ ናት፤ ይህችስ ሰዓት ምን ያህል የምታስጨንቅ ናት፤ መንፈስ ቅዱስ ከሰማየ ሰማያት የሚወርድባት፥ ይህን መሥዋዕት የሚሰውርባትና የሚያከብርባት። በጽሙናና በመፍራት ቁሙ፥ የእግዚአብሔር ሰላም ከእኔና ከእናንተ ጋር ይሆን ዘንድ ጸልዩ።» የሚለውን አሰምቶ ይናገራል። ምክንያቱም የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነውና። ምሳ.9፥10፤ መክ.12፥13። እንዲህ ዓይነት ፈሪሃ እግዚአብሔር በራሱ ጸጋ እግዚአብሔር ነው። « ለእነርሱም ከእነርሱም በኋላ ለልጆቻቸው መልካም ይሆንላቸው ዘንድ ለዘላለሙ እንዲፈሩኝ አንድ ልብና አንድ መንገድ እሰጣቸዋለሁ። ለእነርሱም ከማደርገው በጎነት አልመለስም ስል፥ ከእነርሱ ጋር የዘላለምን ቃል ኪዳን እገባለሁ፤ ከእኔም ዘንድ ፈቀቅ እንዳይሉ መፍራቴን በልቡናቸው ውስጥ አኖራለሁ።» እንዲል። ኤር. 32፥39-40።

ልኡካኑ ደግሞ ከዋናው ቄስ በማስከተል:- «ሃሌ ሉያ በቅዳሴ ጊዜ ከምእመናን ወገን ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባ ቢኖር ቅዱሳት መጻሕፍትን ሰምቶ የቅዳሴውን ጸሎት እስኪጨርሱ ባይታገሥ፥ ከቊርባንም ባይቀበል ከቤተ ክርስቲያን ይለይ፤ የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሷልና፥ የነፍስና የሥጋ ንጉሥ በሚሆን በሰማያዊ ንጉሥ ፊት መቆምንም አቃሏልና። ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው እንዲህ አስተማሩን።» የሚለውን በዜማ ያሰማሉ። ነገር ግን ትእዛዝ ስለሆነ በንባብም ማሰማት ይችላሉ።

## 5.1 ዑደት

ካህኑ መሥዋዕቱን ይዞ መንበሩን ሲዞር:- «ተዘከር እግዚኦ እለ አቅረቡ ለከ ዘንተ ቊርባነ፥ ወእለሂ አምጽኡ በእንቲአሆሙ ሀቦሙ ለኵሎሙ ዐስቦሙ ዘበሰማያት፤ አቤቱ ይህን ቊርባን ያቀረቡልህን አስብ፤ ስለነሱ ያመጡትንም ለሁሉም በሰማያት የሚገኝ ዋጋቸውን ስጣቸው።» እያለ ይጸልያል። በዚህ ጸሎት ውስጥ:- «የጻድቁን የአቤልን ቊርባን የአባታችንን የአብርሃምን መሥዋዕት፥ የድኻይቱንም ሁለት መሐለቅ እንደ ተቀበልህ የእኛንም ተቀበል፤» እያለ ያሳስባል።

አቤል ከበጎቹ በኵራት:- ቀንዱ ያልከረከረውን፥ ጠጉሩ ያላረረውን፥ ጥፍሩ ያልዘረዘረውን ነውር የሌለበት ጠቦት መሥዋዕት አድርጎ በየዋህ ልቡና፥ በትሑት ሰብእና አቅርቧል። እግዚአብሐርም ተቀብሎታል። አቤል ያቀረበው ነውር የሌለበት ንጹሕ የበግ ጠቦት በባሕርዩ ንጹሕ ለሆነ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። ዘፍ.4፥4። «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ፤» እንዲል። ዮሐ.1፥29። አባታችን አብርሃምም መሠዊያ እየሠራ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ያቀርብ ነበር። ዘፍ.12፥6-8፤ 13፥18። ሌላው ቀርቶ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት ልጁን እንኳ መሥዋዕት አድርጎ ለማቅረብ በመሠዊያ ላይ አጋድሞታል። «አብርሃምም የመሥዋዕቱን እንጨት አንሥቶ ለልጁ ለይስሐቅ አሸከመው፤ እርሱም እሳቱንና ቢላዋውን በእጁ ያዘ፥ ሁለተም አብረው ሄዱ። ይስሐቅም አባቱን አብርሃምን ተናገረው:- አባቴ ሆይ አለ። እርሱም:- እነሆኝ ልጄ አለው። እሳቱና እንጨቱ ይኸው አለ፤ የመሥዋዕቱ በግ ግን ወዴት ነው? አለ። አብርሃምም:- ልጄ ሆይ፥ የመሥዋዕቱን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል አለው።» አብርሃም ይኸንን እምነቱን ይዞ መሠዊያ በመሥራት ልጁን በመሠዊያ ላይ አጋደመው። እግዚአብሔርም ስለ ልጁ ስለ ይስሐቅ ፈንታ የሚሠዋው በግ ሰጠው። «አብርሃምም ዐይኑን አነሣ፤ በኋላውም እነሆ አንድ በግ በዱር ውስጥ ቀንዶቹ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ አየ፤ አብርሃምም ሄደ በጉንም ወሰደው፥ በልጁም ፈንታ መሥዋዕት አድርጎ ሠዋው።» ይላል። ዘፍ.22፥6-13። አብርሃም ስለ ይስሐቅ ፈንታ የሠዋው በግ ስለ አዳም ፈንታ በዕፀ መስቀል ላይ ለተሠዋው ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። በአዲስ ኪዳን ደግሞ:- «ኢየሱስም በመዝገብ /በሙዳየ ምጽዋት/ አንጻር ተቀምጦ ሕዝቡ በመዝገቡ ውስጥ ገንዘብ እንዴት እንደሚጥሉ ያይ ነበር፤ ብዙ ባለጠጎችም ብዙ ይጥሉ ነበር፤ አንዲትም ድሀ መበለት መጥታ አንድ ሳንቲም የሚያህሉ ሁለት ናስ ጣለች፤ ደቀ መዛሙርቱንም ጠርቶ እውነት እላችኋለሁ፥ በመዝገብ ውስጥ ከሚጥሉት ሁሉ ይልቅ ይህች ድኻ መበለት አብልጣ ጣለች፤ ሁሉ ከትርፋቸው ጥለዋልና፥ ይህች ግን ከጉድለትዋ የነበራትን ሁሉ ትዳርዋን /ሕይወቷን/ ሁሉ ጣለች አላቸው።» የሚል አለ። ማር.12፥41-44። ጌታችንም ሕይወቱን በመስቀል ላይ ሰጥቶናል። ለዚህ ነው ካህኑ አቤልን፥ አብርሃምንና ደኻዋን ሴት እየጠቀሰ የሚያሳስበው። ጌታችን በደኻ ሴት የተመሰለው ባዕለ ጸጋ ሲሆን ለእኛ ሲል ራሱን ደኻ ማድረጉን ለማጠየቅ ነው። ይኸንን በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ:- «የጌታችንን ቸር ስጦታ ዐውቃችኋልና፤ ሀብታም ሲሆን፥ እናንተ በእርሱ ድህነት ባዕለ ጸጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ደኻ ሆነ፤» ብሏል። 2ኛቆሮ. 8፥9።

የተቀኑት አገልጋዮች ደግሞ:- «አንቲ ውእቱ መሶበ ወርቅ ንጹሕ እንተ ውስቴታ መና ኅቡዕ፥ ኅብስት ዘወረደ እምሰማያት ወሃቤ ሕይወት ለኵሉ ዓለም፤ ከሰማያት የወረደ ኅብስት፥ ለዓለሙ ሁሉ ድኅነትን የሚሰጥ በውስጧ የተሰወረ መና የነበረባት ንጹሕ የወርቅ መሶብ አንቺ ነሽ።» እያሉ አብረው ዑደት ያደርጋሉ። መሶበ ወርቅ የእመቤታችን፥ መና ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌዎች ናቸው። ዋናው ካህን ዑደት የሚያደርገው በመሶበ ወርቁ ላይ እጁን ረቦ /እጁን ከፍ አድርጎ ዘርግቶ/ ነው። ይህም ኅብስቱ ምድራዊ ያይደለ ሰማያዊ መሆኑን ለማጠየቅ ነው። ምክንያቱም ተለውጦ ሥጋ መለኮት የሚሆን ነውና። «ከሰማይ የወረደ የሕይወት ኅብስት እኔ ነኝ፤» እንዲል። ዮሐ.6፥51።

ዋናው ካህን ዑደቱን ከጨረሰ በኋላ አንዱን ኅብስት አንሥቶ:- «ነሢሥኩ ገጸከ፥ ገጸ ዚአከ አንሥሥ እግዚኦ፥ ወኢትሚጥ ገጸከ እምኔየ። ወኢትትገኃስ እምገብርከ ተምዒዐከ፥ ረዳኤ ኩነኒ ወኢትግድፈኒ፤ ወኢትትሀየየኒ አምላኪየ ወመድኃንየ። ፊትህን ሻሁ፥ አቤቱ ያንተን ፊት እሻለሁ፥ ፊትህን ከእኔ አትመልስ። ተቆጥተህ ከባርያህ አትለይ፥ ረዳት ሁነኝ፥ አትጣለኝ፤ አምላኬ መድኃኒቴ ቸል አትበለኝ።» እያለ ይማፀናል። ይኸውም ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኮት የሚሆንለት፥ እግዚአብሔር በረድኤት ሲቀርበው ገጸ ምሕረቱን /የምሕረት ፊቱን/ ወደ እርሱ ሲያዞርለት መሆኑን ስለሚያውቅ ነው። ሦስት ጊዜ ደጋግሞ « ፊትህን» ማለቱም በመለኮት አንድ የሆኑ ሥላሴ በስም በአካል በግብር ሦስት መሆናቸውን ለማጠየቅ ነው። «ለአብ ፍጽም ገጽ፥ ፍጹም መልክ፥ ፍጹም አካል አለው፤ ለወልድም ፍጹም ገጽ፥ ፍጹም መልክ፥ ፍጹም አካል አለው፤ ለመንፈስ ቅዱስም ፍጹም ገጽ፥ ፍጹም መልክ፥ ፍጹም አካል አለው፤» እንዲል። ካህኑ ኅብስቱን በክብር አንሥቶ «ነሠሥኩ ገጸከ» እያለ ላዩንም ታቹንም የሚወለውለው በርጥብ እጁ ነው። ይኸውም ጌታ በቅዱስ ዮሐንስ እጅ መጠመቁን ለማጠየቅ ነው። ከዚህም አያይዞ በጣቶቹ ትእምርተ መስቀል ሠርቶ እያተመ:- «በእውነት አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀኝህ እተብ፥ በእጅህም ባርክ፥ በኃይልህም አክብር፥ በመንፈስህም አጽና፤ ይህ ኅብስት የሕዝብህ የኃጢአት ማስተስረያ ይሆን ዘንድ አሜን።» እያለ ይማልዳል። በዚህ የምልጃ ጸሎት መጀመሪያ ላይ:- «የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት አውሎግዮስ፥ ጌርዮስ፥ ማንጦን፥ ፓንዋማንጦን፥ አላቲኖን ነው፥ አሜን።» የሚል አለ። አውሎግዮስ ማለት ክቡር፥ ጌርዮስ ማለት ክብር የሚገባው አረጋዊ ብሉየ መዋዕል፥ አግዮስ ማለት ቅዱስ፥ ማንጦን ማለት ቅዱስ ቅዱሳን፥ ፓንዋንማጦን ማለት አምላከ አማልክት፥ አላቲኖን በእውነት የሚታመን ማለት ነው።

ንፍቁ ቄስ ደግሞ ኅብስቱን በማኅፈድ ይቀበለውና:- «የካህናት አለቃ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፥ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ በበፍታ እንዲገንዙህ እንደ ወደድህላቸው እንዲሁ ውደድልን።» የሚለውን ጸሎት እየጸለየ በመንበሩ ውስጥ ለውስጥ መልሶ ለዋናው ቄስ ይሰጠዋል። እርሱም:- «ከእግዚአብሔር



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

አብ የተገኘ የኃጢአት ማስተስረያ የሚሆን የሚያከብሩት፥ የሚለውጡት፥ የሚቀበሉት የሚያቀብሉት ይህ ኅብስት ነው:: ኃይል /መንፈሳዊ ኃይል/፥ በረከት /በረከተ ሥጋና በረከተ ነፍስ/፥ ደገኛ ብርሃን /ደገኛ ዕውቀት/ ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ክብር /ለምእመናን መክበሪያ/ ይሁን::» እያለ ይቀበለዋል:: ከእግዚአብሔር አብ የተገኘ ማለቱም ተቀዳሚና ተከታይ የሌለውን አንድ የባሕርይ ልጁን ለቤዛ ዓለም እንደ ሰጠን ለማጠየቅ ነው:: «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና::» እንዲል:: ዮሐ.3፥16::

ከዚህ በኋላ ዋናው ቄስ ኅብስቱን በማኅፈድ እንደ ያዘ:- መብራት የያዘውን ዲያቆን ከፊት አስቀድሞ፥ መስቀል የያዘውን ደግሞ ከኋላ አስከትሎ አንድ ጊዜ መንበረ ታቦቱን ይዞራል:: «አምላካችን እግዚአብሔር በምድረ በዳ የአቤልን ቊርባን፥ የኖኅን በመርከብ ውስጥ፥ የአብርሃምንም በተራራ ላይ፥ የዳዊትንም የኢያቡስ ወገን በምትሆን በኦርና አደባባይ፥ የድኻይቱንም መሐለቅ በቤተ መቅደስ የተቀበልህ:- ለቅዱስ ስምህ የቀረበውን የኃጥእ ባርያህን መባና ቊርባን እንደርሱ ተቀበል::» የሚለውንም ይጸልያል:: መብራት ይዞ ከፊት ከፊት የሚሄደው ዲያቆን ከጌታ በፊት መንገድ ጠራጊ ሆኖ ለመጣው ለመጥምቁ ዮሐንስ ምሳሌ ነው:: ምክንያቱም ጌታችን ዮሐንስን:- «እርሱ የሚነድና የሚያበራ መብራት ነበረ፤» ብሎታልና ነው:: ዮሐ.5፥35:: ቄሱ የጌታ ምሳሌ ሲሆን መስቀል ይዞ የሚከተለው ደግሞ የቅዱስ እስጢፋኖስ ምሳሌ ነው:: ከኋላ የመከተሉም ምሥጢር:- ቅዱስ እስጢፋኖስ ከጌታ በኋላ ከሐዋርያት ቀድሞ መከራ መቀበሉን ለማጠየቅ ነው:: የሐዋ.7፥54-60:: በመጨረሻም ካህኑ ቊርባኑን በጻሕሉ ላይ ያኖረዋል:: ዲያቆኑ ደግሞ ጽዋውን ይዞ:- «እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፤ የሚያሳጣኝም የለም::» የሚለውን የዳዊት መዝሙር እየጸለየ ሦስት ጊዜ መንበረ ታቦቱን ይዞራል:: ዑደቱን ሲጨርስም ንፍቁ ቄስ ተቀብሎት ከኅብስቱ አጠገብ ያኖረዋል::

በአጠቃላይ አገላለጥ:- ኅብስቱ ከቤተ ልሔም ተነሥቶ ወደ ቤተ መቅደስ መሄዱ፥ ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን:- «እነሆ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፥ በዚያም የሰው ልጅ /ወልደ ዕጓለ መሕያው ክርስቶስ/ በአይሁድ እጅ ይወድቃል::» ብሏቸው ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄዱ ምሳሌ ነው:: አንደኛ:- ኅብስቱን ከፊት አስቀድሞ ቄሱ እጁን ረቦ ከኋላ ሆኖ አንድ ጊዜ ይዞራሉ:: ሁለተኛ ቄሱ ቆሞበት ከነበረው ሲደርሱ ዲያቆኑ ዙሮ ይቆማል:: ንፍቁ ቄስ ማኅፈዱን ይገልጽለትና ዋናው ቄስ «ኀሠሥኩ ገጸከ፤» እያለ አትሞ ኅብስቱን ይዞ ይዞራል:: ሦስተኛ:- ቄሱ ከተቀበለበት ቦታ ሲደርስ በመንበሩ የሰሜን ደጅ ንፍቁ ቄስ በማኅፈድ ውስጥ ለውስጥ ይቀበለዋል:: ዋናው ቄስ ደግሞ ከንፍቁ ቄስ በጀርባው በኩል አልፎ በመንበሩ የደቡብ ደጅ ውስጥ ለውስጥ ይቀበለውና የታዘዘውን ጸሎት እየደገመ መንበሩን አዙሮ በጻሕሉ ላይ ያስቀምጠዋል::

ቄሱ ለሁለተኛ ጊዜ መንበሩን መዞሩ ጌታ በተያዘባት ሌሊት በርተዘግቶባቸው ከዳር እስከ ሐና ቦታ የመዞራቸው ምሳሌ ነው:: በመጀመሪያ ቄሱ ኅብስቱን የሚቀበልበት ቦታ የጌቴሴማኒ ምሳሌ፥ ቄሱ ለንፍቁ የሚሰጥበት ቦታ ለጲላጦስ ቤት ምሳሌዎች ናቸው:: ጻሕል ደግሞ የመስቀል ምሳሌ ነው:: ካህኑ ኅብስቱን በጻሕሉ ላይ ማኖሩ ጌታ ነገረ ሕማሙን በመስቀል ላይ ለመፈጸሙ ምሳሌ ነው:: ዲያቆኑም:- «እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፤» የሚለውን እየደገመ መንበሩን መዞሩም ጌታ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ዞሮ ለማስተማሩ ምሳሌ ነው:: ነገረ ድኅነቱን አምነን እንድንኖር የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን:: አሜን::

## ተቀጸል ጽጌ

የተቀጸል ጽጌን በዓል ደነገገ የሚባለው ዐፄ ገብረ መስቀል /536-570 ዓ.ም/ ነው:: በዓሉ የሚከበረው አንደ ኢትዮጵያ አየር ንብረት ሁናቴ በክረምት ማለቂያና የመፀው መጀመሪያ ላይ (መስከረም 25 ቀን) ነበር:: በዚህ ቀን ካህናት ልብሰ ተክህኖ ለብሰው የአበባ ጉንጉን ይዘው «ተቀጸል ጽጌ ገብረ መስቀል ዐፄጌ» እያሉ ግስ ይገሳሉ፤ የአበባ ጉንጉን ያበረክታሉ፤ የልምላሜ ወቅት መምጣቱን በዚህ ሁናቴ ያበሥራሉ:: የኋላ ሊቃውንት የመስቀል በዓል የሚከበርበትን መስከረም 10 ቀን ሲወስኑ የተቀጸል ጽጌን በዓል ወዲህ (ከመስከረም 25 ቀን ወደ መስከረም 10 ቀን) አሸጋሸገውታል::»

ምንጭ:- Sergew Hable Sellasse, Ancient and Medieval Ethiopian History to 1270 (Addis Ababa)

## የቆስጠንጢኖስ...

/ገጽ ከገጽ ፲፩ የዞረ/

ቀን ጉባኤው ሲጀመር፤ ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ እንዲህ በማለት ነበር በንግግር የከፈተው:- «አባቶቼ ከማንኛውም የውጭ ጦርነት ይልቅ በእግዚአብሔር ቤት፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረገው የእርስ በርስ ጦርነት የከፋ ነው:: በውጭ ከሚደረገው ጦርነት ይልቅ እጅግ የመረረ ነው:: አዲስ ችግር በመካከላችሁ መፈጠሩን ስለ ሰማሁ በነገሩ ብትወያዩበት አይከፋም በማለት ያለምንም መዘግየት እንድትሰበሰቡ አደረግሁ:: የእግዚአብሔር አገልጋዮች÷ አባቶቼ ሆይ! መለያየትን ለማጥፋት ዛሬ ነገ አትበሉ፤ ለዚህም አደራዬ ጥብቅ ነው::» የሚል ነበር:: 318 ቅዱሳን አበውም እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ በመሆን አርዮስንና ትምህርቱን አውግዘው ለይተዋል:: ቆስጠንጢኖስ በጉባኤው ለተሰበሰቡት አባቶች ያሳየው ክርስቲያናዊ ጠባይና ትሕትና ተጠቃሽ ነው:: /የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት፣ ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት፤ ገጽ 19/::

ከዚህም ሌላ የክርስቲያኖችን ቅዱሳት መካናት ክብርና ታሪክ ለመጠበቅ ቀና መንፈስ ነበረው:: ስለዚህም በኢየሩሳሌም አካባቢ÷ «ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት በቤተ ልሔም÷ ሦስት መዓልት ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ በተነሣበት በጎልጎታ፣ ምሳሌ የማይገኝላቸው አብያተ ክርስቲያናትን በዘመኑ አሠርቷል:: ቤተ ክርስርቲያንም ስለ ብዙ ውለታው ስታስታውሰው ትኖራለች::

በዘመነ ቆስጠንጢኖስ እናቱ ቅድስት እሌኒ በ327 ዓ.ም ወደ ኢየሩሳሌም ሄዳ የጌታን መስቀል ከተቀበረበት ሥፍራ አውጥታለች:: ንግሥት እሌኒ መስቀሉን በክብር አስይዛ በጎልጎታ ቤተ መቅደስ አሠርታ በዚያ አስቀመጠችው:: ለዚህ ትልቅ ዕድል የበቃችው ቅድስት እሌኒም መስቀሉን ባወጣች በዓመቱ ግንቦት ዘጠኝ ቀን በ328 ዓ.ም ዐርፋለች:: አባ ጎርጎርዮስ «የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ» በሚለው መጽሐፍ እንዳሰፈሩት: - «ታላቁ ቆስጠንጢኖስ በ337 ዓ.ም ግንቦት 22 ቀን የጰራቅሊጦስ ዕለት እሑድ በ54 ዓመቱ የንጉሠ ነገሥትነቱ ሥልጣን በያዘ በ31 ዓመቱ ዐረፈ::» ቆስጠንጢኖስና እናቱ ቅድስት እሌኒ በሠሩት ክርስቲያናዊና ሐዋርያዊ ተግባር ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በታሪኳ ስታስታውሳቸው ትኖራለች:: በረከታቸው ይደርብን:: ልመናቸው ይደረግልን:: አሜን::



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የቅዱሳን መሰወር (ኅብአተ ቅዱሳን) ምንድን ነው?

*በቅዱሳት የታሪክ መጻሕፍት አንዳንድ ቅዱሳን በተጋድሎአቸው ፍጻሜ ላይ ሞት እንዳላገኛቸውና እንደ ተሰወሩ እናነባለን:: በክብረ በዓላት ወቅት በምንሂድባቸው ቅዱሳት መካናትም እስካለንበት ዘመን ድረስ በስውር ስለሚኖሩ ኅቡአን ቅዱሳን ታሪክ እንሰማለን:: ለመሆኑ ኅብአት (መሰወር) ምንድን ነው? የተሰወሩ ቅዱሳን መጨረሻስ ምን ይሆን?*

*ገላጋይ አበበ*
*አ.አ*

*ውድ አንባቢያችን :- አሳጥረን ለማቅረብ የምከርነውና በማብራሪያ የታገዘው ጥያቄዎ ከበርካታ አንባብያን ዘንድ የሚደርሰን ነው:: በመኾኑም የጥያቄውን መልስ ትምህርታዊ መልክ ባለው አቀራረብ በማዘጋጀት በጉዳዩ ላይ ሰፋ ያለ ግንዛቤ ለማስጨበጥ አስበናል:: ጽሑፉን ያቀናበረልን መምህር ይልማ ደፌሳ ነው:: መልካም ንባብ*

የሰው ልጆች ወደ እግዚአብሔር በመንፈሳዊ አገልግሎት ባዘነበሉ መጠን ቸርነት የባሕርዩ የኾነ እግዚአብሔር ደግሞ የተለያየ መንፈሳዊ ብቃትን ይሰጣቸዋል፤ ሰማያዊ ምሥጢርን ይገልጥላቸዋል:: ቅዱሳን በሥጋቸው በምድር ለጸሎት ቆመው ነፍሳቸው በተመስጦ ገነት መንግሥተ ሰማያት ተነጥቃ ሄዳ ከቅዱሳን መላእክት ጋር ታመሰግናለች:: እንዲሁም በአካል እንደ ነቢያቱ ሔኖክና ኤልያስ በመወሰድ እስከ ጌታችን ዳግም ምጽአት መዳረሻ ቀን በመሰወር እንደ ሚኖሩ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዱናል::

ከላይ በጥያቄው በተነሣው ጉዳይ መሠረትነት በዚህ ዝግጅት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ከሚሰጠው ብቃት መካከል የመሰወርን መንፈሳዊ/ሃይማኖታዊ/ ምንነት ለመዳሰስ እንሞክራለን:: «መሰወር» የሚለው ቃል የግእዝ ግሱ «ኀብአ»: - «ሰወረ፥ መሰወር»፤ «ተኀብአ»: - ተደበቀ፣ ተሰወረ፣ ራቀ፣ ረቀቀ ማለት ሲሆን በጥቅሉ ለዐይን እንዳይታይ እንዳይገኝ ሆነ፤ ለምሥጢርም ከሆነ ለአእምሮ ረቀቀ ማለት ነው::

ርእሰ ጉዳዩ መንፈሳዊ እንደ መሆኑ መጠን የሚሰወሩት ነገሮች ዕውቀትን፣ ምሥጢርን፣ ሰውን፣ ቦታን፣ ወዘተ ሊያካትት ይችላል:: የሚሰወሩበት የጊዜ መጠን ለአጭር ጊዜ፣ ለረጅም ጊዜ፣ እስከ ምጽአት፣ ለዘለዓለምም ሊሆን ይችላል:: የመሰወር ምሥጢርንም በሰው ልጆች ዘንድ መረዳቱ እኩል መሆን አይችልም:: ለሁሉም አንድ ዓይነት ትርጉምና ስሜት ሊሰጥ ይችላል ተብሎም አይታሰብም:: በማወቅ ደረጃም ተመሳሳይነት ሊኖረው አይችልም፤ እያንዳንዱ ሰው እንደ መንፈሳዊ አገልግሎቱና ፍቅሩ፥ እግዚአብሔር እንደ ገለጠለትም መጠን ያውቃል እንጂ:: እንግዲህም ለአንዱ የተሰወረው ምስጢር ለሌላው ሊገለጥ ይችላል:: ለአንዱ የረቀቀበት ሁኔታና ዕውቀት ለሌላው ጎልቶ ሊታይ ይችላል:: አንዱ በአካል ማየት ያልቻለውን ሌላው ሊያየው ይችላል:: አንዱ መስማት ያልቻለውን ድምፅ ሌላው ሊሰማው ይችላል:: ስለዚህ እያንዳንዱ እንደ ተሰጠው ጸጋ በከፊልም ሆነ በሙሉ ያውቃል፣ ያያል፣ ይሰማል፣ ይተረጉማል፤ እንደ ብቃቱም በአካል እስካለመታየት /እስከ መሰወር/ ይደርሳል::

«መሰወርን» የምንዳስስበት ሃይማኖታዊ ጠገግ ወይም አድማስ በሥጋ ለባሽነት የኖሩትን የሰው ልጆችን በ ጽድቅና በቅድስና መሰወር የሚያካትት ነው:: በዚህም መሠረት ከሰው ልጆች ወገን:- በቅድስናቸው ብቃት፥ እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ እስከ ምጽአት ድረስ በሥጋቸው በብሔረ ሕያዋን እንዲሰወሩ፤ ከሰው ልጆች ዐይን ለጊዜው ለአስፈላጊ ሁኔታ እንዲሰወሩ፤ ከመደበኛ መልካቸው ለጊዜው ሌላ ሰው በመምሰል እንዲሰወሩ፤ መከራ እንዳያገኛቸው የሰወራቸውና ከሞቱ በኋላ ቅዱስ ሥጋቸውን የሰው ልጆች እንዳይቀብሯቸው የተሰወሩት ወዘተ ይገኙባቸዋል::

እዚህ ላይ አንዳንድ ሰዎች «ያለመረጃ ምንም ነገር አይታመንም» ከማለት አኳያ፥ መንፈሳዊውን ምስጢር በሥጋዊ ዐይን ለማየት ከመሻት፥ ይልቁንም ሳይንስ «የተሻለ መረጃ» እንዳለው በማመን የእግዚአብሔርን ሥራ ሊንቁ፥ ሊያቃልሉ ይችላሉ:: በመሠረቱ መንፈሳዊው ዓለም ያለው መረጃ ከሳይንስ ይልቅ ይረቃል፥ ይመጥቃል፤ ለመረዳትም እምነትና ተአምኖ ያስፈልገዋል:: ስለዚህ ጥልቅ ምሥጢሩን በመንፈሳዊ የምርምር መንገድ:- በጾም፣ በጸሎት፣ በመልካም ሥነ ምግባር፣ በየዋህነትና ራስን ለእግዚአብሔር አሳልፎ በመስጠት ቢመረምሩት ቸርነትና ይቅርታ የባሕርዩ የኾነ እግዚአብሔር እንደ ፈቃዱ ይገልጥላቸዋል:: በዚህ ምርምር የሄዱ ቅዱሳን የተሰወረውንና የተገለጠውን ዓለም በዐይናቸው ፊት ለመመልከት አያዳግታቸውም:: እንዲያውም በመንፈስም በአካልም ደርሰው ተመላልሰውበታል:: በደስታውም ሰጥመውበታል:: በብርሃኑ ዋኝተውበታል:: በምስጢሩም ረክተውበታል:: ዓለም ግን መንገዱ የሥጋ ስለሆነ ከሕዋው ብዙ ሳይርቅ እዚሁ ይዳክራል:: በጥረቱም አልረካበትም:: እንዲያውም ብዙ ጠበብቶቹ በሕዋው ላይ የውኃ ሽታ ሆነውበታል::

ከሁሉ አስቀድሞ የሰው ልጆች ሊያውቁት የሚገባው ነገር የእግዚአብሔርን ማንነት ነው:: የእግዚአብሔርን ማንነት መረዳት ሥራውንና ጥልቅ ምስጢሩን ለማወቅ ያስችላል:: ይህም ደግሞ ልብ ለእግዚአብሔር በእውነት እንዲንበረከክ ያደርጋል:: እግረ ልቡና በእውነተኛ ተመስጦ ከተንበረከከ የሰማይ ምስጢራት ይከሰቱለታል:: በዚህም መንፈሳዊ ምርምሩን በጥቂት በጥቂት መጀመሩን ይገነዘባል::

የምርምሩ ዘዴ የማይመረመረውን እግዚአብሔርን አያካትትም፤ እኛ በርእሱ እንደ ገለጽነው መንፈሳውያን አባቶች እስከ መሰወር የደረሱበትን፥ ለፍጡራኑ የተሰጠውን መንፈሳዊ ብቃት እንጂ:: አምላክ ሊመረመር ቀርቶ የሠራው ፍጡር እንኳን ተመርምሮ አይደረስበትም:: ሢራክ በመጽሐፉ «የእግዚአብሔር ስሙ ልውጥ፥ ምስጢሩም ከሰው የተሰወረ ነውና::» /11፥4/ እንዳለ:: በተጨማሪም ታላቁ የትዕግሥት ሰው ኢዮብ:- «የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ልትመረምር ትችላለህን? ወይስ ሁሉን የሚችል አምላክን ፈጽመህ ልትመረምር ትችላለህን?» /11፥8-10/ በማለት የእግዚአብሔር መኖር ከሰው አእምሮ በላይ እንደ ሆነ በፈቃዱ በምሳሌ ራሱን ካልገለጠ በቀር በሰው ምርምራ ሊደርስበት የማይችል እንደ ሆነ እንረዳለን:: እንዲያውም የሰው ልጅ እንኳን እግዚአብሔርን ቀርቶ የሠራውን ሥራ እስከ ዓለም ፍጻሜና እስከ ዘለዓለም መርምሮ እንደማይዘልቀው የታወቀ ነው:: ይህም የሰው ልጅ አፈጣጠሩ ራሱ በአቅሙ እንዲያስብ፥ ለጤናማ ምርምሩ ገደቡን እንዳያልፍ የተሠራ ነው:: ለዚህም ጠቢቡ ሰሎሞን በመጽሐፉ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

መክብብ:- «... እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ እስከ ፍጻሜ ድረስ የሠራውን ሥራ ሰው መርምሮ እንዳያገኝ ዘለዓለምነትን ሰጠው::» /3÷10-11/ እንዲል:: ስለዚህ የሰው ልጅ መንፈሳዊ ዕውቀትን በእግዚአብሔር ስጦታና ፈቃድ አገኘ እንጂ በራሱ ሥጋዊ ምርምር እስከ አሁን ያመጣው አዲስ ነገር÷ ወደ ፊትም በራሱ ሊያመጣ የሚችለው እንደሌለ ከመንፈሳዊው ዓለም እንረዳለን::

በተጨማሪም የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት ሰውና ሥጋዊው ሰው እኩል የመንፈሳዊ ምርምር ችሎታ የላቸውም:: በሥጋዊ ሐሳብ ኾነው ስለ መንፈሳዊነትና መንፈሳውያን የሚሰጠውም አስተያየት የተሳሳተና ግምታዊ ሊሆን ይችላል:: ምክንያቱም የሥጋዊ ሐሳብ ብቃት መንፈሳዊውን ምስጢር ሊመዝን አይችልም:: ለመንፈሳዊ ሰው ምስጢርን የሚገልጥ መንፈስ ቅዱስ ነውና ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ እንደ ጻፈው ጌታችን:- «... ከናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም ዓለም የማያውቀው ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ::» ሲል ተናግሯል:: ዮሐ.14÷16-17:: እንዲሁም ሥጋዊ ሰው መንፈሳዊ ሰውን ሊመረምረው አይችልም:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ: - «መንፈሳዊው ሰው ግን ሁሉን ይመረምራል፤ ራሱ ግን በማንም አይመረመርም» /1ቆሮ.2÷15/ እንዳለ:: ይህም መንፈሳዊ ሰው ከጥበብ ባለቤት በተቀበለው መንፈሳዊ ስጦታ የተነሣ የዕውቀትና የጥበብ ባለቤት በመሆኑ ከሥጋዊ ሰው ጥበብ በላይ ነው:: በሥጋዊ ሰው የግምት ዐይን ሊመረመር አይችልም::

የመሰወር ብቃት ደረጃ ላይ የደረሱ ሰዎችም መንፈሳዊ ምርምርን በተገቢ መንገድ ያደረጉ ናቸው:: የብቃቱም መንገድ የተለያዩ ደረጃዎች አሉት:: በአንድ ጊዜ ወደ መሰወር ደረጃም አይደረስም:: ለምሳሌ በዓለማዊ ኑሮ የተለያዩ የብቃት ደረጃዎች አሉ የትምህርት፣ የሀብት፣ የኪነ ጥበብ ወዘተ:: የትምህርት ደረጃ ብቃት ብናይ ፊደል መቁጠር፣ አንደኛ ደረጃ፣ ሁለተኛ ደረጃ፣ ዲፕሎማ፣ ዲግሪውም በየዘርፉ ይደረስበታል:: እንዲሁም በክርስትና ሕይወትም ጉዳዩ ብሎ ለያዘው መንፈሳዊ ሰው የተለያዩ የብቃት ደረጃዎች አሉት:: እዚህ ላይ ግን ልናስታውለው የሚገባን የቅዱሳንን መሰወርና ብቃታቸውን ስናይ በቅዱሳት መጻሕፍት የተጠቀሱትን ዋቢ በማድረግ በዐቅማችን ለማስታወስ ያህል እንጂ በጥልቀት እናውቃለን በማለት የቅዱሳን ሰዎችን ሕይወት መርምረን እንደርስበታለን ለማለት አይደለም::

በዚህም መሠረት እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት አንድ ሰው ለመሰወር የተለያዩ የብቃት ደረጃዎች ላይ መድረስ አለበት:: ደረጃዎቹም ሊገኙ የሚችሉት ሃይማኖትን ከምግባር ጋር በማጽናት፣ በጾም፣ በጸሎትና በትሩፋት ማጌጥን ይጠይቃል:: የብቃት መዓርጋቱም በሦስት ዐበይት መዓርጋትና በዐሥር ንዑሳን ደረጃዎች ይከፈላሉ:: የመጀመሪያው ዐቢይ መዓርግ ንጽሐ ሥጋ ይባላል:: በውስጡም ጽማዌ፣ ልባዌና ጣዕመ ዝማሬን ያጠቃልላል:: «ጽማዌ»: - ከአንደበት ከሚወጣ ኃጢአት መቆጠብና ንግግር አለማብዛት፣ «ልባዌ»:- ፍጹም መንፈሳዊና እውነት የሆነውን ነገር በሚገባ ማስተዋል፤ «ጣዕመ ዝማሬ»:- የእግዚአብሔርን ምሥጢር በንቃትና በተመስጦ ኾኖ በዜማ ሳህይ በማመስገን መትጋት ነው::

ሁለተኛው ዐበይት የብቃት መዓርግ ንጽሐ ነፍስ ነው:: ቅዱሳን ወደዚህ መዓርግ የሚደርሱት የመጀመሪያውን ሲያልፉ ነው:: በውስጡም አንብእ፣ ኩነኔ: - ፍቅርና ሁሰትን ያጠቃልላል:: «አንብእ» ከመንፈሳዊ ተመሥጦ የተነሣ እንደ ምንጭ /ሰን ውኃ/ ከቅዱሳን ዐይን እንባ የሚፈስበት ደረጃ ነው:: «ኩነኔ» ፈቃደ ሥጋን ለፈቃደ ነፍስ በመንፈሳዊ ጥበብ የማስገዛት ደረጃ ነው:: «ፍቅር»:- በቅዱሳኑ ዘንድ የሰው ልጆችን ዘር ሁሉ እኩል የመውደድ ደረጃ ነው:: «ሁሰት»:- በዚህ ደረጃ ቅዱሳኑ በቅርብም በሩቅም ማንኛውንም ክንውን በዐይነ ሥጋ ሳይሆን በዐይነ መንፈስ ማየት ነው:: ይህም የቅዱሳን መላእክትን እንቅስቃሴ /ተልእኮ/ እስከ ማወቅ ያደርሳቸዋል::

ሦስተኛው ዐቢይ የብቃት መዓርግ ንጽሐ ልቡና ነው:: ይህ የመጨረሻው የፍጹምነት ደረጃ ነው:: በውስጡም ንጻሬ መላእክት፣ ተሰጥሞ ብርሃን፣ ከዊነ እሳት ይገኙበታል:: «ንጻሬ መላእክት»:- በዐይነ ሥጋ ቅዱሳን መላእክትን በያሉበት ዓለማት መመልከት ነው:: «ተሰጥሞ ብርሃን»:- በእግዚአብሔር ልዩ የባሕርዩ ብርሃን መመሠጥ ሲሆን «ከዊነ እሳት» ደግሞ ቅዱሳን ሰዎች በእሳታዊነት ጸጋ ከነ ጽሮተ ሥሉስ ቅዱስ የሚደርሱበት ደረጃ ነው::

ከላይ እንዳየነው በእነዚህ የብቃት መዓርጋት ውስጥ ያሉ ቅዱሳን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ከሚሰጧቸው ጸጋዎች አንዱ መሰወር ነው:: የመሰወር ጸጋውም የተለያዩ ሁኔታዎች አሉት:: እንደ ሚከተለው እንመለከተዋለን::

## 1. በሕይወተ ሥጋ ሳሉ ለጊዜው መሰወር

ይህ የመሰወር ጸጋ በዓለመ ሥጋ መካከል ሳሉ አስፈላጊ ለሆነ ሁኔታ አብረው ካሉት ሰው ለጊዜውም ቢሆን አለመታየት ነው:: ይህን ዓይነት መሰወር በጾም በጸሎት ተወስነው÷ በብሕትውና ያሉ ቅዱሳን ከፈቃደ እግዚአብሔር ውጪ ሊያዩዋቸው የሚመጡትን ሰዎችና በክፉ የሚመጡባቸው ሰዎች እንዳያገኟቸው የተሰጣቸው የመሰወር ጸጋ ነው:: ይህንም እውነታ ለቅዱሳኑ ማድረግ እንደ ሚቻላቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዱናል:: ለዚህም አብነት የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: በግእዙ «ወዘንተ ብሂሎ እግዚእ ኢየሱስ ሖረ ወተኀብአሙ»፤ ትርጉሙም:- «ኢየሱስ ይህን ተናግሮ ሄደና ተሰወረባቸው::» /ዮሐ.12÷36፤ ሉቃ.24÷31/:: ከላይ ያለውን ንባብ ስንመረምር ጌታችን ሲያስተምር በጊዜው በጉባኤው ላይ የተገኙት አይሁድ ትምህርቱን በመቃወም ሊገድሉት ፈልገው÷ ሊይዙት ነበር:: ጌታችን ግን ራሱን አሳልፎ የሚሰጥበት ጊዜ ስላልደረሰ ከአጠገባቸው እያለ ተሰወረባቸው:: በአጠገባቸው አልፎ በመካከላቸው ሲሄድ ማየት እንዲሳናቸው አደረጋቸው::

ለቅዱሳኑም ይህን ጸጋ ሰጥቷቸዋል:: በእነርሱ አድሮባቸው ይኖራልና ይሰወራሉ:: «እውነት እውነት እላችኋለሁ÷በእኔ የማያምን እኔ ያማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል::» /ዮሐ.14÷12/:: በግብረ ሐዋርያት መጽሐፍ ላይ ይህን ታላቅ ተአምር በተግባር እናየዋለን:: ሄሮድስ በቤተ ክርስቲያን ላይ መከራ ባጸናባት ዘመን የዮሐንስ ወንድም ቅዱስ ያዕቆብን በሰይፍ በማስገደል፤ አይሁድን ይበልጥ ደስ ለማሰኘት ቅዱስ ጴጥሮስን ከፋሲካ በኋላ ሊያወጣላቸው ሌሊትና ቀን ቆመው በሚጠብቁት ወታደሮች አስከበበው:: ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ አጥብቆ ይጸለይ ነበረ:: ሄሮድስ ቅዱስ ጴጥሮስ እንዳያመልጥ ፈጽሞ ስለ ፈለገ በሁለት ሠንሠለት ታስሮ በሁለት ወታደሮች መካከል እንዲተኛ ተደረገ:: በተጨማሪም በሩ እንዳይከፈት ጠባቂዎችም በደጁ ፊት ሆነው በተጠንቀቅ ይጠብቁ ነበር:: ቅዱስ ጴጥሮስን ሊያወጣው በመጣው የእግዚአብሔር መልአክ አማካይነት ተቀስቅሶ ከሁለቱ ጠባቂዎች መካከል ሲነሣ ያየው ጠባቂ የለም:: ሠንሠለቶቹ ከእጆቹ ሲወልቁና ሲወድቁ ያስተዋለው አልነበረም:: በተለይ የሚገርመው በሩን በተጠንቀቅ ደጁ ላይ ሆነው ይጠብቁ የነበሩ ጠባቂዎች በሩ ተከፍቶ ቅዱስ ጴጥሮስ ሲወጣ ሊያዩት አልቻሉም:: ምክንያቱም ከርሱ ጋር ያለች የእግዚአብሔር የመሰወሪያው ጸጋ ጠብቃዋለችና ነው:: የእግዚአብሔር መልአክ ባለበት የእግዚአብሔር ቸርነት አለና:: ሲነጋም ወታደሮቹ ቅዱስ ጴጥሮስን «ምን ነካው? ወዴት ጠፋ?» ብለው ታወኩ:: ምክንያቱም በሩ ሳይከፈትለት÷ በቁልፉ እንደ ተቆለፈ ሆኖ ወታደሮች በተጠንቀቅ ሳሉ ወዴት ሄደ ይበሉ? እነርሱ አላወቁም እንጂ ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔርን በጸሎት ትማፀን ስለነበር የእግዚአብሔር መልአክ ለሞት ከጠበቁት ወታደሮች ዐይን ሰውሮ አውጥቶታል:: ወዲያውም ወደ ማርቆስ እናት ቤት በመሄድ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ነግሮአቸዋል:: ከዚህም እግዚአብሔር በፈለገ ጊዜ እንደ ወደደ ቅዱሳኑን ለጊዜውም ቢሆን የመሰወር ብቃት እንደ ሚሰጣቸው እንረዳለን:: /የሐዋ.12÷6-19/::

## 2. የመገለጥ ጊዜ እስኪደርስ ሌላ ሰው በመምሰል መሰወር:-

ለዚህም ምሳሌ የምናደርገው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: በትንሣኤው ዕለት በመቃብሩ የተገኘችው መግደላዊት ማርያም ዘወር ብላ ጌታችንን አይታው ነበር:: ነገር ግን አላወቀችውም:: እንደውም የአትክልት ጠባቂ መስሏት ነበር:: ፈቃዱ እስኪሆንም ልታውቀው አልቻለችም:



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ከጭንቀቷ የተነሣ:- «ወዴት እንዳኖርከው ንገረኝ» በማለት ራሱን ትጠይቀው ነበር:: ፈቃዱ በሆነ ሰዓት «ማርያም» ብሎ በመጥራት እንድታውቀው አደረጋት:: /ዮሐ.2÷11-17/::

የኤማሁስ ሰዎችም ታሪክ ተመሳሳይ ሁኔታን የያዘ ነው:: ስድሳ ምዕራፍ ቀኑን ሙሉ እስከ ምሽት ቃሉን እየሰሙ ፊቱን እያዩ ቢጓዙ በፈቃዱ እርሱን ለማየት እንዲበቁ እንጀራ ቆርሶ እስኪሰጣቸው ሊያውቁት አልቻሉም:: በዐይናቸው ፊት እያዩት ሳለ እርሱ መሆኑ ተሰውሮባቸው ነበር:: «ቆርሶ ሲሰጣቸው ዐይናቸው ተከፈተ:: ዐውቁትም:: ወዲያውም ከዐይናቸው ተሰወረ::» /ሉቃ.24÷13-35/:: ጌታ ለወደደው በወደደው ጊዜ ይገለጣል፤ ለሌላው ይሰወራል:: በአንድ ጊዜና እይታ ሳሉም የሰዎችን የተሰወረውን የማወቅን ብቃት ይለያያል:: ይህንንም በጥብርያዶስ ባሕር ዓሣ በማጥመድ ላይ ያደሩ ሐዋርያት ታሪክ በሚገባ ያስረዳናል:: ሲነጋም:- «ጌታ እኮ ነው» በማለት ለቅዱስ ጴጥሮስ ሲነግረው ሊረዳ ችሏል:: በኋላም በየደረጃው ሁሉም ሐዋርያት ሊያውቁት ችለዋል:: /ዮሐ.21÷4-14፤1ኛሳሙ.3÷1-14/::

ለሰው ልጆችም እንደ ብቃታቸው መጠን ይህች ጸጋ ተሰጥታቸዋለች:: ነቢዩ ኤልሳዕ ከሩቅ በሶርያ ቤተ መንግሥት የሚደረገውን በጸጋ እግዚአብሔር የማወቅ ደረጃ ደርሶ ነበረና የሶርያ ንጉሥ የመከረውንና ያቀደውን እያወቀ ለእስራኤል ንጉሥ ይነግረውና እስራኤልን ከአደጋ ይጠብቅ ነበር:: የሶርያ ንጉሥ ይህን ባወቀ ጊዜ ጭፍሮቹን ልኮ ነቢዩ ኤልሳዕን እንዲይዙት አስከበበው:: ነቢዩ ኤልሳዕም ወደ እግዚአብሔር የሶርያ ጭፍሮች ዐይኖች እርሱ ያለበትን ቦታ እንዳያውቁት÷ ዐይነ ስውርም እንዲሆኑ ጸለየ:: እግዚአብሔርም የነቢዩ ኤልሳዕን ጸሎት ሰማ:: ነቢዩ ኤልሳዕም እንደሌላ ሰው እንዲመስላቸው አደረገ:: ነቢዩ ኤልሳዕም እንደ ሌላ ሰው ሆኖ ኤልሳዕ ያለበትን ቦታ ላሳያችሁ» ብሎ ወደ ሰማርያ ወሰዳቸው:: እንደገናም «ዐይኖቻቸውንም ግለጥ» በማለት ጸለየና በሰማርያ መካከል መሆናቸውንና መርቶ ያመጣቸው ነቢዩ ኤልሳዕ መሆኑን እንዲለዩ አደረጋቸው:: እዚህ ላይ ነቢዩ ኤልሳዕ የበቃ ሰው በመሆኑ በጸሎቱ የሶርያ ወታደሮችን እየመራቸው ሲመጣ እርሱ እንደ ሆነ እንዳያውቁት÷ ያለበትንም ቦታ እንዳይለዩ አደረጋቸው:: ይህም የእርሱ ማንነት እንዲሰወራቸው በመኾኑ ነው::

እንደዚሁም ጻድቁ ገብረ ክርስቶስ ከሙሽርነቱ ቦታ በእግዚአብሔር ተጠርቶ ከቤተሰቦቹ በተለየ ጊዜ የአባቱ ጭፍሮች እርሱን በፍለጋ እንዳያገኙ ሰውነቱ እንዲለወጥ ጸለየ:: እግዚአብሔር እርሱ እንደ ሆነ እንዳይታወቅ በቁስል ሸፈነው:: በዚህም ሁለት ነገር እንዲያገኝበት አድርጉታል:: አንደኛው ከቤተሰቦቹ እንዲሰወር ሁለተኛው በመከራው ዋጋ እንዲያገኝበት የእግዚአብሔር ሙሽራው ሆኗልና:: ዐሥራ አምስት ዓመት በሰው አገር፣ ዐሥራ አምስት ዓመት በአባቱ ደጅ ሲተኛ ያወቀው የለም:: እዚህ ላይ መረዳት ያለብን ምንም እንኳ በቁስል ቢመታ በአንድ ምልክት ቤተሰቦቹ ሊያገኙት ይችሉ ነበር:: የእግዚአብሔር ጸጋው ሸፍናዋለችና ይህን ያህል ዓመት በደጃቸው ሆኖ ተሰውሯቸው ኖሯል::

## 3. ልዩ መሰወር

እስራኤላውያን እግዚአብሔርን በመበደላቸውና ከኃጢአታቸው አል መለስ በማለታቸው፣ ለባቢሎናውያን አሳልፎ ሰጣቸው:: በመካከላቸው ግን ከነቢዩ ኤርምያስ ጋር ለእስራኤል ሕዝብ መልካም ያደርጉና ለእግዚአብሔር ታዛዦች የሆኑ «የኢየሩሳሌምን ጥፋት አታሳየን» ይሉ የነበሩ ነቢዩ ባሮክና ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክን ከመከራና ከግዞት እግዚአብሔር እንደ ሰወራቸው እንመለከታለን:: ይህ እንዲሆን ነቢዩ ኤርምያስ ወደ እግዚአብሔር ስለ ሦስት ነገር በጸሎቱ አመለከተ:: በመጀመሪያ ስለ ንዋያተ ቅድሳቱ መሰወር እንዲህ ብሏል:: «አቤቱ ጌታዬ÷ ይህቺን አገር በጠላት እጅ አሳልፈህ እንድትሰጣት የባቢሎን ወገኖች እንዲይዟት እነሆ ዛሬ ዐወቅሁ::... ስለምናገለግልበት ንዋያተ ቅድሳት ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ? ጌታም:- እነርሱን ወስደህ በምድር በቤተ መቅደስ አደራ ስጣት፤ አንቺ ምድር በውሆች ላይ የፈጠረሽ የስገነት ክፍልም የከፈለሽ የፈጣሪሽ÷ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተሽ÷ ጌጥሽን ተቀበይ፤ ዘሩባቤል እስኪመጣ ድረስ ገንዘብሽን አደራ ጠብቂ» በላት አለው:: ባሮክና ኤርምያስ ወደ ቤተ መቅደስ ገቡ፤ የሚያገለግሉበትን ዕቃ ሁሉ ጌታ እንዳዘዛቸው ለምድር ሰጧት:: ምድርም ያን ጊዜ አደራ ተቀብላ ዋጠች::» ይህም ምድር የቤተ መቅደሱን ንዋያተ ቅዱሳት መሰወሯን÷ መደበቋንና መሸሸጓን ያመለክታል::

ሁለተኛም:- «... ለኢትዮጵያዊ ሰው ለአቤሜሌክ የማደርገውን ግለጥልኝ፤ ... እርሱ ከረግረግ ጉድጓድ ውስጥ አወጣኝ፤ እንዳያዝን የአገሪቱን ጥፋት ያይ ዘንድ አልወድለትም» በማለት ጸለየ:: «ጌታም ለኤርምያስ ወደ አግሪጳ የወይን ቦታ በዚህ ተራራ ጉዳና አቤሜሌክን ላከው፤ ሕዝቡን ወደ አገራቸው እስክመልሳቸው ድረስ እኔ እሰውረዋለሁ::» አለ:: በነጋውም ኤርምያስ እግዚአብሔር እንዳዘዘው አቤሜሌክን እንዲህ ብሎ አዘዘው: - «ወደ አግሪጳ የወይን ቦታ ለታመሙ ወገኖች ትንሽ በለስን አምጣ ብሎ ላከው:: ... አቤሜሌክም ኤርምያስ ከላከው ቦታ በቀትር ጊዜ በለሱን አመጣ፤ ጽፍቅ ያለች ዱርንም አገኘ፤ ጥቂትም ያርፍ ዘንድ በጥላዋ ሥር ተቀመጠ፤ በለስ ያለባትንም ሙዳይ ተንተርሶ ስድሳ ስድስት ዓመት ተኛ:: ሲነቃም ገና ራሴን ይከብደኛል፤ እንቅልፌን አልጨረስኩምና ዳግመኛ ጥቂት ብተኛ በጎ ነገር ነው» አለ:: ያን ጊዜም በለስ ያለበትን ሙዳይ ከፈተ:: በለሶችም በሙዳዩ ውስጥ አዲስ ሆነው ወተታቸውም ሲፈስ አገኘ:: «ተመልሼ እንዳልተኛ እንዳልዘገይም አባቴ ኤርምያስ እንዳይነቅፈኝ እፈራለሁ» አለ:: ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ ቢገባ አገሩን ሊያውቀው አልቻለም:: በስድሳ ስድስቱ ዘመን ዛፎች በቅለው ደን ሆኖ ነበርና::

ሦስተኛም እግዚአብሔር ለነቢዩ ኤርምያስ:- «ባሮክን ግን በኢየሩሳሌም ተወው አለው:: ባሮክም ስድሳ ስድስቱን ዘመን በመቃብሩ ሥፍራ ባለው የመቃብር ቤት ተሰውሮ አሳለፈ:: ዘመኑም ከተፈጸመ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ አቤሜሌክን ወደ ባሮክ መርቶ ወሰደው:: ባሮክም በመቃብር ቤት ተቀምጦ ነበር::» 38÷7-16፤ ትንቢተ ኤርምያስ 39÷15-18፤ ተረፈ ኤር.ቁ.8፣9፣10/ በማለት የእግዚአብሔር ቃል ይነግረናል:: ከአቤሜሌክ ተአምራዊ እንቅልፍ ምን እንረዳለን? «እግዚአብሔር እሰውረዋለሁ» እንዳለ ከጠላቶች ሰውሮታል:: የሚገርመው ነገር አቤሜሌክ ራሱ ከራሱ ተሰውሮበታል:: 66 ዘመን እንደ ጥቂት ደቂቃ አሳልፎ በመነሣቱ ከ66ቱ ዘመንም /ከጊዜ/ ተሰውሯል:: የተኛው ጫካ ውስጥ ነበር፤ ከአውሬ፣ ከዝናም፣ ከብርድ፣ ከፀሐይ ወዘተ ተሰውሯል:: በላዩ ላይ ሣር በቅሎበት አልጠፋም:: የእግዚአብሔር ተኣምራዊ ጸጋው ከጥፋት ሰውራዋለች:: «ወሰወረኒ በምኅባአ ኀሳሎተ:፤ በድንኳኑም መሸሸጊያ ሾሸኙኛልና» እንዳለ ቅዱስ ዳዊት:: መዝ.26÷5::

4. <u>ብሔረ ብፁዓን:-</u> ከኻያው ዓለማት ውስጥ የኾነች /ከመሬት ወገን የምትመደብ/ ስውር ምድር ብሔረ ብፁዓን ናት:: እንደ ገድለ ዞሲማስ አገላለጽና ሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት÷ በዚህች ቦታ ተሰውረው የሚኖሩ ሰዎች ራሳቸውን ለፈቃደ እግዚአብሔር ያስገዙ ናቸው:: በውስጧም ቅዱስ ጋብቻን መፈጸም የሚችሉና ዘርን ለማስቀረት ለመተካት ልጅን መውለድ ይችላሉ:: ለኃጥአን ያልተፈቀደች የማትገባም ቦታ ናት::

5. <u>ደብር ቅዱስ:-</u> ከምድር ወገን ሆና የተለየች ሥፍራ ናት:: አዳም በበደለና ከገነት በወጣ ጊዜ ገነትን በማየት ይጸጸት ዘንድ በዚህች ሥፍራ አኑሮታል:: መጽሐፍ ቅዱስ /ብሉይ ኪዳን/ ይህችን ቦታ *«ደብር ቅዱስ፣ ከፍ ያለች ሥፍራ»* በማለት ይጠራታል:: /ሔኖክ 4÷71/:: አዳም ከአቤል ሞት በኋላ የተወለደለት ሴት ከነ ልጆቹ ይኖር እንደ ነበርና በኋላም በኖኅ ዘመን የቃየንን ሴቶች ልጆች በማየት ስተው መውረዳቸውን በዘፍጥረት ትርጓሜ እንረዳለን:: «የእግዚአብሔር ልጆችም /በደብር ቅዱስ/ የሚኖሩ የሴት ልጆች/ የሰውን ሴቶች ልጆች /የቃየንን ልጆች/ መልካሞች እንደ ሆኑ አዩ፤ ከመረጡአቸውም ሁሉ ሚስቶችን ለራሳቸው ወሰዱ::» /ዘፍ.6÷2/ ይላል:: እነዚህ የቃየንን ሴቶች ልጆች በኃጢአት ተመኝተው ቅዱስ ሥፍራቸውን ጥለው በመውረድ የወለዷቸው ልጆች ኃያላን ነፍስ ገዳዮች÷ ለእግዚአብሔር የማይታዘዙ ሆኑ:: እግዚአብሔር ምድርን በእነርሱ ምክንያት አጠፋት::

ጻድቁ ሔኖክም ስለ እነርሱ መሳትና ስለ ደብር ቅዱስ ቅድስና እንዲህ ይላል:- «ከፍ ያለ ደብር ቅዱስን ዘለዓለም ጸንቶ የሚኖር መንግሥተ ሰማያትን ስለምን ተዋችሁት» /ሔኖክ 4÷21/፤ «ቀድሞ የንጽሕና መሠረት የነበሩ እነዚ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ህም በዚህ ዓለም ክፉ ልጆች ይሆናሉ:: ክፉ ልጆች ይባላሉ»/ ሔኖክ 4÷83/ ብሎአቸዋል:: በተጨማሪም መልካም ሥራ ን በመልካም ቦታ እንዲሁም ጸሎትን መ ጸለይ የተውትን የሴት ልጆች እንዲህ ይላቸዋል፡- «እናንተ ለሰው ልትለምኑ ይገባችሁ ነበር:: ሰው ግን ለእናንተ ሊ ለምንላችሁ አይገባችሁም ነበር» በማለት የሴት ልጆች ሳይስቱ በደብር ቅዱስ ቢቆዩ ኖሮ ለሰው ልጆች እየጸለዩ እንደሚኖሩ ገልጿል:: ነቢዩ ሔኖክ በብሔረ ብፁዓን ይኖሩ የነበሩትን ከብሔረ ሕያዋን ሄዶ የነገራቸው፥ ለሰው ልጆች ሁሉ የሚራራ እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ጥፋት አይወድምና የሴት ልጆች ከነበሩበት ቦታ የሚያስወጣ ምኞት ተጸናውቷቸው በነበረ ጊዜ ምን አልባት ይመለሱ እንደሆን ያስተምራቸውና ይመክራቸው ዘንድ ነው:: እግዚአብሔር ትእዛዙን ለነቢዩ ሔኖክ የገለጸለት በቅዱሳን መላእክቱ በኩል ነበር:: /መጽ.ሔኖክ 4÷6-7፣ 26/::

6 **ብሔረ ሕያዋን፡-** በዚህ ቦታ የሚኖሩ ቅዱሳን ሰዎች በዘመናቸው መልካም ሥራን በማድረግ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኙ ሰዎች ናቸው:: ከእነዚህም በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ ከሚታወቁ ት መካከል ዋነኞቹ ነቢዩ ሔኖክና ነቢዩ ኤልያስ ናቸው:: ስለ ነቢዩ ሔኖክ በመ ጽሐፈ ሢራክ ላይ፡- «ሔኖክ እግዚአብሔ ርን ደስ አሰኘው፤ እግዚአብሔርም እርሱን ከሞት ሰወረው፤ ንስሐ ለሚገቡ ሰዎች አብነት ሆኑ» /ሢራክ 44÷16/ በተሰወረ ጊ ዜም ከሰው ልጆች ያወቀ የለም:: እርሱም በብሔረ ሕያዋን ለመግባት የመጀመርያው ሰው ነበር:: መጽሐፍም «ከነገር ሁሉ አስቀድሞ ሔኖክ ተሰወረ፤ ከሰውም ልጆች በተሰወረበት ቦታ ሳለ የሚያውቀው አልነበረም:: ይሙት ይዳንም የሚያውቅ የለም» /ሔኖክ 4÷1-2/ እንዲል:: /ዕ ብ.11÷5-6፤ ዘፍ.5÷22-24/::

ነቢዩ ሔኖክ ከመሰወሩ በፊት በአናኗሩ እግዚአብሔርን የሚያውቅና የሰ ማያት ምስጢር የተገለጠለት ከእግዚ አብሔር የተማረ ነበር:: በመጽሐፈ ኩፋሌ «ስሙን ሔኖክ አሉት፤ እርሱ አስቀድሞ በዚህ ዓለም ከተፈጠሩ ሰዎች ይልቅ መጻሕፍትንና ትምህርትን ጥበብንም ተ ማረ፤ የዘመኑን ጊዜ ያውቅ ዘንድ እንደ ወ ራቸው ሥርዓት የሰማይን ምልክት በመ ጽሐፍ ጻፈ::» /ኩፋሌ 5÷22-23፤ ይሁዳ ቁ. 1÷14-15/ በማለት ይገልጸዋል::

በተጨማሪም ቅዱሳን መላእክት የሰማይን ምስጢር እያስጎበኙ ገልጠ ውለታል:: እርሱም ከምድር ወደ ሰማይ በመነጠቅ በተመሥጦ ተረድቶታል:: «ከነዚያ ወራት በኋላ በነፋስ ሠረገላ ተነጥቄ ነበርና መላእክትም ወደ ምዕራብ ወስደውኝ ነበርና:: በዚያ ቦታ የተሰወሩትን ራእዮች አየሁ» /ሔኖክ 14÷1/ በማለት ይገልጸዋል::

ነቢዩ ኤልያስም ከደቀ መዝሙሩ ነቢዩ ኤልሳዕ ጋር ሳለ እግዚአብሔር በእሳት ሠረገላ ወስዶታል:: ከመወሰዱ በፊት ሙት በማንሣት፣ ሰማይ ዝናም እንዳይሰጥ በመለጉም፣ እንደገናም ዝናምን በጸሎቱ በማዝነብ ወዘተ ተአምራት በ ማድረግ ለአምላኩ ቀናዒ መሆኑ ተመስክሮለታል:: /1ነገ.18÷16-46፤ 2ነገ.2/::ከርሱ ቀድሞ የተሰወረ ጻድቁ ሔ ኖክ ስለ ኤልያስ በመጽሐፉ እንዲህ ሲል ገልጿል፡- «የእስራኤል ጌታ እግዚአብሔ ር የእስራኤልን ጸባዖት ነቢያት ጠርቶ አስተምሩ ብሎ ላካቸው፤ እስራኤል ይገድሏቸው ጀመር:: ከነቢያት አንዱ ኤልያስ ከሞት ዳነ፤ ሞት አላገኘውም፤ ፈጥኖ ሄደ፤ በእስራኤል ከተማ አስተ ማረ:: እስራኤል ሊገድሉት ወደዱ:: የእስራኤል ገገር እግዚአብሔር ከእስራ ኤል እጅ አዳነው:: ወደ እኔም አምጥቶ አኖረው::» ይላል::

እንግዲህ በብሔረ ሕያዋን የሚ ኖሩ፡- በብሉይ ኪዳን እንደነ ነቢዩ ሔ ኖክና ነቢዩ ኤልያስ ያሉት ናቸው:: በሐ ዲስ ኪዳንም በወንጌሉ የተነገረላቸውና ከእነርሱም በኋላ ብዙ ቅዱሳን እንዳሉ መጻሕፍት ያስረዳሉ::ከዐሥራ ሁለቱ ሐ ዋርያት መካከል ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐ ንስ በወንጌላቱ ገጸ ንባብ ስሙ ሳይጠቀስ በምልክት፥ በትርጓሜ ወንጌል ላይ ደግሞ በስሙ ተጠቅሶ ወደ ስውራኑ መኖርያ ወደ ብሔረ ሕያዋን እንደ ተነጠቀ ይገልጽልናል:: ለዚህም ቅዱስ ሉቃስ፡- «እውነት እላችኋለሁ፥ በዚህ ከሚቆሙት ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት እስኪያዩ ድረስ ሞትን የ ማይቀምሱ አንዳንድ አሉ» /ሉቃ.9÷27/ በማለት ሲጠቅስ ቅዱስ ዮሐንስ ደግሞ ስለ ራሱ፡- «ጴጥሮስም ዘወር ብሎ ኢ የሱስ ይወደው የነበረውን ደቀ መዝሙር ሲከተለው አየ፤ እርሱ ደግሞ በእራት ጊ ዜ በደረቱ ተጠግቶ ጌታ ሆይ፥ አሳልፎ የሚሰጥህ ማን ነው? ያለው ነበር:: ጴጥሮስም ይህን አይቶ ኢየሱስን፡- ጌታ ሆይ፥ ይህስ እንዴት ይሆናል? አለው:: ኢየሱስም እስከ መጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ ምን አግዶህ? አንተ ተከተለኝ አለው:: ስለዚህ ያ ደቀ መዝሙር አይሞትም የሚለው ይህ ነገር ወደ ወንድሞች ወጣ፤ ነገር ግን ኢየሱስ እስከመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ ምን አግዶህ? አለው እንጂ አይሞትም አላለውም::» /ዮሐ.20÷23/ በማለት ይገ ልጻል:: በትርጓሜውም፣ በገድሉም፣ በስ ንክሳሩም ይህን መነሻ አድርገን ቅዱስ ዮሐንስ ከነሔኖክና ኤልያስ ጋር በብሔ ረ ሕያዋን እንደሚኖር እናረጋግጣለን::

እነዚህ በብሔረ ሕያዋን ተሰውረው የሚኖሩ ቅዱሳን በአንዳንዶች ዘንድ «እዚያ ምን ይሠራሉ?» የሚል ጥያቄ ሊያሥነሳ ይችላል:: በመጽሐፈ ሔ ኖክ ከመላእክት ጋር በቅዳሴ እንደ ሚያመሰግኑ እንደ ሚከተለው ተገልጿል:: «ሥራውም ሁሉ በተሰወረበት ወራት በቅዳሴያቸው ከሚተጉ ቅዱሳን መላእክት ጋርና ከቅዱሳኑ ጋር ነበር::» በተጨማሪም «እኔም ሔኖክ ገናና ጌታን በአራቱ ማእዝነ ዓለም የነገሠ እግዚአብሔ ርን አመሰግነው ጀመር» /ሔኖክ 4÷34/ በማለት ከተግባሩ አንዱ ምስጋና እንደ ሆነ ይገልጽልናል:: እንዲሁም ቅዱሳኑ ከመላእክት ጋር ስለ ሰዎች ልጆች ድኅነት እንደ ሚነጋገሩና ነቢ ዩ ሔኖክ ወደ ደብር ቅዱስ ይሄድ ዘንድ በመላእክት እንደ ተነገረው እርሱ ከጻፈው መጽሐፍ እንረዳለን:: «... ለቅዳሴያቸው የሚተጉ መላእክት እነሆ ይጠሩኛል:: ...ለኃጢአት ለሚተጉ ሰማ ያዊ መዓርጋቸውን መንግሥተ ሰማያትን አጥተው ከሴቶችም ጋራ ለጠፉ የቃየን ልጆችም እንደ ሚያደርጉ ሳደረጉ ለደ ቂቀ ሴት ሄደህ ንገር አለኝ...» /ሔኖክ 4÷6-7/ በማለት ቅዱሳን መላእክት ወደ ብሔረ ሕያዋን በመምጣት ሔኖክ ወደ ደቂቀ ሴት ከጥፋታቸው እንዲመለሱ እንዲነግራቸው ከእግዚአብሔር ተልከው ነግረውታል:: እርሱም የተላከውን መል እክት ሊያስተላልፍ ወደ ደቂቀ ሴት እንደ ሄደና እንደ ነገራቸው፡- «እውነት ነገር ያለበት ይህን ቃል እናገር ዘንድ በደብር ቅዱስም ለነበሩ በኃጢአታቸው ለሚተጉ ለደቂቀ ሴትም አስተምር ዘንድ ጀመርሁ» /ሔኖክ 4÷26/ በማለት በዚ ያም ያለውን የቃለ እግዚአብሔር የማስ ተማር ተልእኮውን ይገልጽልናል::

በአጠቃላይም በብሔረ ሕያዋን ምስጋና፣ ቅዳሴ፣ ቃለ እግዚአብሔርን መነጋገር፣ ከቅዱሳን መላእክት ጋር መነ ጋገር፣ መጸለይ፣ ስለ ሰው ልጆች ድኅ ነት ማሰብ ወዘተ እንዳለ እንረዳለን::

በተጨማሪም በብሔረ ሕያዋን በሚኖሩ ቅዱሳን መካከል ጌታችን መድ ኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ታቦር ግርማ መለኮቱን በገለጸ ጊዜ ነቢ ዩ ኤልያስ ከሊቀ ነቢያት ሙሴ ጋር እንደ ተገለጠ ከወንጌሉ እንረዳለን:: /ሉቃ.9÷28-36፤ ማቴ.17÷1-8፤ ማር.9÷2 -8/:: ይህም በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ነቢ ዩ ኤልያስ በሥጋው እንዳረገ ስለሚያ ውቁ ከጌታችን ወደዚህ መምጣት ጋር ተጋጭቶባቸው የጌታችንን አምላክነት እንዳይክዱ ለሐዋርያቱ ከነቢያት አንዱ ኤልያስን ከመሰወሪያው ከብሔረ ሕያዋን በማምጣት እንዲያዩት አድርጓቸዋል:: ይህንም በማየት ቅዱስ ጴጥሮስ «እኔ ማን ነኝ?» ለሚለው ጥያቄ ጌታችን አም ላክ ኤልያስ እንጂ ነቢዩ ኤልያስ እንዳልሆነ፡- «አንተ የሕያው የእግዚ አብሔር ልጅ ነህ» በማለት አረጋግጧል::

ስውራን ቅዱሳን /ኀቡአን ቅዱ ሳን/ በፍጻሜ ዘመን ወዳለንበት ምድር መጥተው እንደ ሚገለጡና ስለ እግዚ አብሔር መንግሥት መስክረው በአው ሬው /ሐሳዌ መሲሕ/ ሰማዕትነትን እንደ ሚቀበሉ መጻሕፍት ያስረዱናል:: በዮሐ ንስ ወንጌል እንደ ተጻፈው ቅዱስ ዮሐ ንስን ጌታችን «እስከመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ ምን አግዶህ?» ብሎታል:: ይህም ማለት በብሔረ ሕያዋን እስከ ም ጽአት መዳረሻ /ጌታ መዳረሻ እስከ ሚመጣበት ቀን ድረስ/ ሳይሞት ይኖር ዘንድ እንደ ፈቀደለት እንጂ ጭራሹኑ አይሞትም አላለውም:: /ዮሐ.21÷22 -23/:: በሐሳዌ መሲሕ ዘመን በእውነተኛ ምስክርነቱ ሰማዕትነትን እንደ ሚቀበል፣ ነፍሱ ከሥጋው እንደ ሚለይ ያስረዳናል:: ስለ ነቢያቱ ሔኖክና ኤልያስም ዮሐንስ በራእዩ፡- «ሁለቱ ወይራዎችና ሁለቱ መቅረዞች» በማለት የሐሳዌውን መሲሕ ክሕደት በመቃወም ምስክርነታቸውን እንደሚሰጡ፥ በምድር ላይ ያሉትን ሕ ዝቦች እንደሚያስተምሩና ታላላቅ ተአም ራትን እንደሚያደርጉ ከትርጓሜ ራእየ ዮሐንስ እንረዳለን:: ዮሐ.ራእ.11÷4-13::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «ምንደኛዋ»

/ትዕግሥት ታፈረ/

«አንቺ ደብሬ÷ ደብሬቱ...» የእማማ ጉትጎታ ከእንቅልፌ አነቃኝ:: ዐይኔን እያሻሸሁ ስጨናበስ «ተነሽ እንጂ ÷ እኛ እዚሁ ተኝተን ነጋ እኮ» ሲሉ እሑድ መሆኑንና ቅዳሴ እንደ ምንሄድ አስታወስኩ:: ተመኝታዬ ተስፈንጥሬ ተነሣሁና ቤቱን ከእማማ ጋር ባንድነት አስተካከለን÷ ሁላችንም ነጠላችንን አጣፍተን ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ወጣን:: አዲስ አበባ ከመጣሁ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን የተሳለምኩበትን ቀን መቼም አልዘነጋውም:: እንደ ዛሬው እማማ በሌሊት ሲቀሰቅሱኝ የወፎቹን ጫጫታ በመስማቴ መንጋቱ ታወቀኝ:: እማማ ÷ ቀሚስና ነጠላ ሳንድያዬ ሰጥተውኝ ሽክ ብያለሁ:: የመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንን ደጅ ስንሳለም ለአመል ያህል በከንፈሬ መዝጊያውን ነካኹት እንጂ ከልቤ አልነበርኹም:: አሻግሬ እያየሁ ተመሥጫለሁ:: አይ የሕንጣው ማማር! ደብሩን ታገሬ ደብር ጋር ሳመሳስለው ይኼኛው ቤተ መንግሥት መሰለኝ::

በምናቤ÷ ከደባርቅ ወረዳ አለፍ ብሎ በእግር ሦስት ሰዓት የሚፈጀውን መንገድ በእፍታ ደርሼ የምንዲገብሳን አሞራ ስቀል ማርያም ደብር ቃኘሁት:: በሣር የተሠራችው ጎጆ ጉስቁልናዋ መጣብኝና ከተሜዎቹን ታዘብኳቸው:: ምናለ ያገሬን ደብርም ቢያስቧት?!

ከሐሳቤ የተመለስኹት በእማማ ውትወታ ነበር:: ከቅዱስ ገብርኤል ሸቅብ ስንወጣ ደግሞ ዐይኔ ሌላ ተኣምር አየ:: በጎንና በጎናችን እንደ መልካም ጎፈሬ ተስተካክሎ የተከረከመውን ጥድ ሳደንቅ እማማ የገዙልኝን ሸራ ጫማ እንዳወልቅ ነገሩኝ:: ጫማዬን አውልቄ ቀና ስል መግቢያው ላይ ያሉት አንበሶች ነፍስ ያላቸው መስሎኝ ነፍሴ የተመነጠቀች እስቲመስለኝ ደንግጬ ነበር:: ወደ ውስጥ ዘልቄ ከእማማ ጋር ቆምኩ:: ዐይኔ ጉድ አዬ:: ዕፁብ ድንቅ ነበር:: ፊት ለፊታችን የሥነ ስቅለት ሥዕል ይታያል:: አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያኑ የውስጥ ክፍል በቅዱሳን ሥዕል ተሞልቷል:: ተኛ ሀገር ደብር ጋር ሳወዳድረው ልዩነቱ የትየለሌ ሆነብኝ:: በእኛ ደብር ከዐሥር የማይበልጡ የአምላክና የቅድስት ድንግል ማርያም እንዲሁም የቅዱሳን ሥዕሎች ከግድግዳው ላይ በተገኘው ሚስማር አለፍ አለፍ ተደርገው ይሰቀላሉ:: ወለሉንም በሐሳቤ ሥዬ ለሀገሬ ደብር ተቆጨሁ:: ያለቀ ሠሌንና ሳጠራ ቢነጠፍበትም አቧራ አላጣውም:: ልቀመጥ ቢሉ ልብስ ያበላሻል:: ይኼማ ምቾቱ ሌላም አ'ደል እንዴ? የካህናቱ ወዝስ ቢሆን ወዴት ተገናኝቶ?! ኧረ ምኑ ቅጡ! ያገሬ ወተት የመሰለ ኩታም÷ ዐይንን ይማርካል:: ማማራቸው መቼም ሌላ ነው::

ያን ቀን ለእማማ ሥራ አብዝቼባቸው መዋሌ አሁን አሁን ነው በደንብ የታወቀኝ:: የቅዳሴ ልምድ ስላልነበረኝ ወንጌል እየተነበበ ቁጭ እላለሁ:: ስገዱ ሲባል እቆማለሁ:: ዛሬም ያለፈውን ሳወጣ ሳወርድ ነው ከደብሩ የደረስነው:: አሁን አለማውቄ ሁሉ በአሠሪዬ ብርታት ተሻሽሎ ሳስቀድስ «ቁሚ ÷ ቁጭ በይ» የሚለኝ የለም:: ይኼንን ክብር ካገኘሁ ዓመት ከመንፈቅ ሆኖኛል:: በፊቱ ÷ እንድቆም የወደደ÷ ከትቢያ ያነሣኝን እግዚአብሔርን የማመሰግንበት ቃል ያንሰኛል:: የሆነውንና ያለፈውን ማስታወሴ የምስጋናዬ ምንጭ ነው::

ከትውልድ መንደሬ ያላቻ ጋብቻውን ሸሽቼ ከአንዲት ዘመዴ ጋር ኮብልዬ ተወጣሁ በኋላ አዲስ አበባ ተያዥ ሆና ሰው ቤት አስቀጠረችኝ:: የገጠሬ ኑሮ እንደ ከተሜው ባለመሆኑ ሥራውን በቶሎ አለመድኹትም:: አለማወቄ ለመከራ ዳረገኝ፤ አሠሪዬ ቁጡ ናት:: አንድ ጊዜ እንደ ተለመደው ሌት ከእንቅልፌ ተነሥቼ ወደ ሥራዬ ገባሁ:: አስታውሳለሁ÷ እንደ ዛሬው ሰንበት ቀን ነበር:: ሰዓቱን አየሁት:: ከጠዋቱ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ሊሆን ግማሽ ያህል ደቂቃ ቀርቶቷል:: መርገጫዬ አሁንም የወለል ማሻውን በርኖስ ጨምድዶ ይዟል:: ወገቤን በሁለት እጆቼ ደገፍ አድርጌ ያዝኹዋቸው:: እግሮቼም ጽናት ጉድሏቸው ይብረከረካሉ:: ረኀቡ ደረቴን ይፍቀኛል:: ምሬት አእምሮዬን ተቆጣጥሮት እንባዬ ዐይኔን መቆጥቆጥ ሲጀምር የመኝታ ቤቱ በር ድንገት ተከፈተ:: እግሮቼ በማላውቀው ኃይል ፈጥነው ወለሉን ማሸት ጀመሩ:: እድል ግን ከኔ ጋር አልነበረችም፤ እትዬ ቆሜ እንደ ነበር አይተዋላ::

«ወገብሽን ይዘሽ ተገተርሽሳ? እስከ አሁን እንዴት ቤቱን አጽድተሽ አልጨረስሽም?» በጥያቄ አጣደፉኝ:: ቀና ብዬ ላያቸው አልደፈርኩም:: ድምጣቸው ቁጣቸውን ስለ ነገረኝ ፈርቻለሁ::

«ተናገሪ እንጂ ምን ይዘጋሻል:: ልሳንሽን ይዝጋው:: ተኝተሽ አርፍደሽ ነዋ?» አሉ ንዴታቸው እየጨመረ::

«ኧረ አይደለም እትዬ» አልኩ በእግሮቼ ጣት ቆንጥጬ በያዝኹት ማሻ ወለሉ ላይ እየተሯሯጥኩ:: ረፈድ ያሉት ግን ገርሞኛል:: ዐሥራ ሁለት ሰዓት እንኳን አልሞላም'ኮ::

«አትክልቶቹ ውኃ ጠጡ?»

«አይ÷ ቤቱን ልጨርስና አጠጣቸዋለሁ::»

«አፈር ያጠጣሽና÷ እነርሱ የደረቁ ቀን ነፍስ ሥጋሽን ነው የማደርቀው::» አሉኝ:: ተቆናጥረው ወደ በሩ እያመሩ:- «አንቺ ገልቱ÷ ተቀብዬ ስመጣ መበሳጨት አልፈልግም:: ሁሉ ነገር ተስተካክሎ ይጠብቀኝ! ገባሽ?» ሲሉ «አዎ» ብዬ መለስኩ:: በሩን ዘጋሁት እሪ ብለሽ ጩኺ የሚል ስሜት መጣብኝ:: እትዬ ÷ ሲበዛ ክፉ ናቸው:: ክፋታቸውን ልቋቋመው አልቻልኩም:: «እየዬም ሲደላ ነው» እንዲሉ የቤቱ ትልቅ ልጅ ዔዶም ደግሞ ተነሣች:: ዘወትር ጠዋት እትዬ ቤተ ክርስቲያን እንደ ሄዱ እርሷ ተተክታ ትሙኸብኛለች::

«አንቺ ገጠሬ ÷ የዋና ልብሴን የት አባሽ ጣልሽው?»

«ነይ ÷ ከአልጋው ሥር ጫማ አውጭልኝ»

«ይኼንን ሻንጣ አውርጂ... ያንን ሱሪ አጥበሽ ተኩሰሽ አስቀምጭ...» ሌላም ሌላም:: ትእዛዟን ከስድብና አንጓጓዶም ከጥፊ ጋር አስተናግዳለሁ:: የኾነውን ሁሉ ችዬ ነበር:: ዳሩ ግን የእርሷን ፈቃድ ስሞላ እትዬ ያዘዙኝ ሥራ ይታጐልብኛል:: እርሳቸውም የልጃቸውን ጠባይ እያወቁ አያዝኑልኝም:: ሕይወት ጣዕም አልባ ሆነችብኝ:: ከአገሬ ከወጣሁ ጀምሮ ጠግቤ በልቼ አላውቅም:: እትዬ የምሠራው ሁሉ አያረካቸውም:: ቢያረካቸው እንኳን መልካም ቃል ከአፋቸው እንዳይወጣ የማሉ ይመስላሉ:: አካላቴ ዕረፍት የሚያገኘው እኩለ ሌሊት ካለፈ በኋላ ነው:: የሚሠራ ቢያጡ እንኳን «ድንጋይ ፍለጭ» ይሉ እንደሆን እንጂ ዐርፌ ማየት አይዋጥላቸውም:: አንድ ዕለት የቤቱን ሥራ በሌሊት ጨራርሼ ሙሉ ቀን ልብስ ሳጥብ ዋልኩና ወገቤ እየተንቀጠቀጠ አፌ እንደ ኩበት ደርቆ በተቀመጥኩበት እንቅልፍ ሲያንገላጀጀኝ እትዬ ደረሱ:: አቤት ቁጣቸው÷ መዐቱን አወረዱት:: የእኔ ደግሞ ድንጋጤዬ... ጠዋት ቁራሽ ዳቦ የተጣለለት ሆዴ ረኀቡን ትቶ ፍርሃቱን ማስተናገድ ጀመረ:: እየተውረገረጉ የስድብ ናዳ አወረዱብኝ:: «የ'ኔ እመቤት አስተኝቼ ልቀልብሽ እኮ አላመጣሁሽም::» ሲሉ:: «መቀለቡ ቀርቶ እንደ ወጉ ምሳዬን በሰጡኝ::» አልኩ በሆዴ:: መኝታ ቤታቸው የሚቀልፉበትን የእንጀራ ሞሰብና ወጥ የተሠራባቸውን ድስቶች በስስት በዐይነ ኅሊናዬ እየሣልኩ::

ዝምታዬ ንዴታቸውን አጦፈው መሰለኝ ተንደርድረው በጥፊ አጮሉኝ:: ከረኀቡና ከድካሙ ጋር የማየው ሁሉ ተሽከረከረብኝ:: እንደምንም ራሴን ሳረጋጋ «ምን ዓይነት ገልቱ ባላገር ገጠመችኝ...» እያሉ የተሰጣውን ልብስ አንድ በአንድ እያዟዟሩ ያያሉ:: እንባዬ በጉንጮቼ ላይ መውረድ ከጀመረ ቆይቷል::

«ነይ አትነፋረቂ÷ ነካ ነካ አድርገሽ የተውሽውን ልብስ እጠቢ፤ የማይመቱት ልጅ ሲቆጡት ያለቅሳል::» ሲሉኝ እንደ ሁልጊዜው አጥቤ ያሰጣሁትን ልብስ ሊያስደግሙኝ መሆኑን ሳውቅ ሐሞቴ ፈሰሰ:: ምርጫ ግን አልነበረኝም:: ቅጣቱ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በዚህ ቢያበቃ መልካም:: ራትም ተነፈገኝ:: አንዳንዴ የሚያሠሩኝ ቢያጡ ቤት ውስጥ ያለ የዐሥር ሳንቲም ፌስታል ይለቅሙና ቆመው ያሳጥቡኛል:: ወገቤን ሣር ፍራሼ ላይ ሳሳርፍ ሰውነቴ ድቅቅ እንዳለ ቢሰማኝም ረኀቡ በልጦ አንስፈሰፈኝ:: ሰመመን እንጂ እንቅልፍ ሲያምረኝ ቀረ:: እትዬ ሁልጊዜም የግፍ በትራቸውን እኔ ላይ ለማሳረፍ ባይሰንፉም እንደዚያች ሌሊት ግን መፈጠሬን የረገምኹበት ጊዜ የለም:: አዳሩን እንደምንም አድሬ ማልጄ ተነሥቼ ከቀዬ ወዳመጣችኝ ዘመዴ ሄድኩ:: ችግሬን ብነግራትም ልትረዳኝ ቀርቶ ልትሰማኝ ፈቃደኛ አልሆነችም:: በወር በወር እየመጣች ደሞዜን ስትወስድ «ጠርቀም ሲልልሽ ትወስጂዋለሽ» ብትለኝም የገንዘቤን ነገር ሣነሳ ዐይኔን ግንባር ያ'ርገው አለች:: ከእርሷ ቤት ማረፍ እንኳ ለእኔ አደጋ ሆነ:: ሴትዬዋ ቤት ተመልሰሽ ካልገባሽ «ሰርቃ ነው የወጣች» ብለን እናስይዝሻለን ስትለኝ ሹልክ ብዬ ወጥቼ እግሬ ወደ መራኝ ነጎድኩ:: ጦም ያደረው ሆዴ አካላቴን ሁሉ ሲያርደው መንገድ ዳር ቁጭ ብዬ የማይንጥፈውን እንባዬን ከዐይኔ ላይ ማለብ ጀመርኩ:: ነቢዩ ዳንኤልን ከአንበሶች አፍ ያዳነ አምላክ፣ እነ ማርታን ሙት ወንድማቸውን ከመቃብር በማሥነሳት ከሐዘናቸው ያጽናና መድኃኔ ዓለም ለእኔም የዛሬዋን እንደ ሰው ክብር የሰጡኝ አሠሪዬን ጣለልኝ:: ከምኅትተው የሐሳብ ማግ የቅዳሴው መጀመር አባነነኝ:: «አሐዱ...» ሲባል ሙሉ ለሙሉ ሁለንተናዬን ለፈጣሪዬ ሰጥቼ ቆምኩ::

ከቅዳሴ በኋላ ተኣምረ ማርያምን ስማንና ትምህርት ለመከታተል ከቤተ መቅደሱ ወጥተን በደጅ ተኮለኮልን:: መምህሩ በትእምርተ መስቀል አማተበና ትምህርቱን ጀመረ::

የዕለቱ ትምህርት ርእስ፦ «ከድኾች ሰዎች በምሳህ ይቀመጡ፣ ምሳህም እግዚአብሔርን በመፍራት ይሁን::» /ሢራ.9÷16/ ነው:: እማማ ቤት ከገባሁ ጀምሮ የቆጠርኹት ፊደል የቃሉን ምዕራፍና ቁጥር ለመያዝና መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለማመሳከር ረድቶኛል::

መምህሩ ትምህርቱን ቀጥሏል፦ «... የተከበራችሁ ምእመናን ዘርህን እንደ አሸዋ አበዛልሃለሁ የተባለ÷ እንግዳን ባለመሰልቸትና ሰው ከሰው ባለመምረጥ ለመቀበል የተጋ፤ በዚህ ምግባሩም ቅድስት ሥላሴን በቤቱ ማስተናገድ የቻለ ጻድቅ አባታችን ያስተማረን ለኛ የሆነውን መልካም ነገር ሁሉ ከወንድሞቻችን ጋር በቅንነት ተካፍለን እንድናድር ነው::

አባታችን አብርሃም በምሳው እንግዳ ካልተገኘ አይበላም ነበር:: ዛሬ ግን እኛ በተቃራኒው በምሳችን ሰዓት ሰው ከተገኘ አንበላም:: ለምን? ያ እንግዳ ወይም ምንደኛ እስኪሄድ እንጠብቃለን:: አንዳንዶቻችንማ እየበላን ሰው ሲመጣ ገበታውን እንደብቃለን:: ነገር ግን በወንጌል እንደኛ ስስታም ስለሆነው ሰው እንዲህ ተብሎ ተጽፏል:: ሉቃስ 16÷19-20፦

«ቀይ ልብስና ቀጭን የተልባ እግር የለበሰ አንድ ባለጠጋ ሰው ነበረ:: ዕለት ዕለትም እየተመቸው በደስታ ይኖር ነበር:: አልዓዛርም የሚባል አንድ ድኻ በቁስል ተወርሶ በደጁ ተኝቶ ነበር:: ከባዕለ ጸጋውም ማዕድ ከሚወድቀው ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ ነበር:: ውሾች እንኳ መጥተው ቁስሎቹን ይልሱ ነበር:: ድኻውም ሞተ:: መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት:: ባዕለ ጸጋው ደግሞ ሞተና ተቀበረ:: በሲኦልም በስቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ፤ አልዓዛርም በእቅፉ:: እርሱም እየጮኸ፦ አብርሃም አባት ሆይ÷ ማረኝ፤ በዚህ ነበልባል እሠቃያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ ምላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ:: አብርሃም ግን ልጄ ሆይ÷ አንተ በሕይወት ሳለህ መልካም እንደተቀበልኽ አስብ፤ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ:: አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል:: አንተም ትሠቃያለህ:: ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጓል አለ::»

ወዳጆቼ ሆይ÷ ይህ የሰማችሁት የእግዚአብሔር ቃል ነው:: በሰማነው ይፈረድብናል:: ከንፈር መምጠጥና ማዘን ብቻውን ጽድቅ አይሆንም:: እስኪ ለአፍታ እያንዳንዳችን ወደ ጓዳችን÷ ወደ ጐረቤቶቻችን እንሂድ:: እኛ ምሳ እራት ሳይጐድልብን ወጥተን ለመዝናናት÷ ለመስከርና ዳንኪራ ለመምታት እጅ አጠረን ብለን ስናማርር ከጎረቤታችን ግን ደረቅ ቂጣ አሮበት ሆዱ እንቅልፍ የነሳውን ወንድማችንን ማሰብ ያቃተን እኮ ብዙዎች ነን:: በወንጌሉ እንዳነበብኹላችሁ ያ ባዕለ ጸጋ በዓለም በተድላ ሲኖር ደጁ የወደቀውን ነዳይ ዞር ብሎ እንኳ አላየውም:: እግዚአብሔር አምላክ ግን እውነተኛ ፈራጅ ነውና በሲኦል አበጋዝ እንዲገዛ ፈረደበት:: ልብ በሉ÷ በዚህ ሥቃይ ሲኖር ወርቁ አላዳነውም:: ብሩም ዋስ አልሆነውም:: ለዚያ ምስኪን አልዓዛር ግን ለውሾች ከተተወው ፍርፋሪ እንኳ አፉ ላይ አድርጎለት ቢሆን ስለ ድኻው ሰው ምሕረትን ባገኘ ነበር::

«ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል?» /ማቴ.16÷26/ ተብሎ ነው የተጻፈው::

የተወደዳችሁ ምእመናን÷ ለድኾችና ለታናናሾች ምን ያህል ክብር እንዳለን ለማወቅ ሩቅ መሄድ አያስፈልገንም:: መቼም ብዙዎቻችን የቤት ሠራተኛ ቀጥረን ይሆናል:: ስንቶቻችን ነን ፍቅርና ርኅራኄ የባሕርይው የሆነ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዚህች ደኻ ሕይወቱን አሳልፎ እንደ ሰጠ የምናምን? በተለይ እናቶች በጠዋት መጥተን፦ «አቤቱ ማረኝ ... አቤቱ ማረኝ... » ስንል እናረፍዳለን:: ይኼ ያስመሰግናል:: ወዲያው ግን ወደ ቤት ሄደን የቤታችንን ሠራተኛ ከአቅም በላይ እያሠራን፣ በረኀብ እየቀጣን፣ በስድብና በማይበርድ ቁጣ የምናንገበግባት ከሆነ ልፋታችን ገደል አይገባምን? እግዚአብሔር አምላክ እኮ «ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌችን እንፍጠር» ሲል ይህቺን ምስኪን የቤት ሠራተኛንም ጨምሮ ነው:: ወዳጆቼ ሆይ÷ መድኃኔዓለም ያከበረውን ሰው እኛ የምናቃልል ማን ነን? የሚገርማችሁ መናፍቃን በዚህ ከእኛ ተሽለዋል:: ለሐሰት ትምህርታቸው እንኳን በቤታቸው ያለችውን ምስኪን በሰንበት ቀን ይዘዋት ወደ «ፕሮግራማቸው» ይሄዳሉ:: ይልቁንስ እኛ በእውነተኛዋና በቀጥተኛዋ እምነት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የምንኖር ሰዎች ለቤት አገልጋዮቻችን ማሰብ እንዴት ያቅተናል? እስኪ ከዚህ ሁሉ ሰው መሐል፦ «የቤት ሠራተኛዬ ሕይወት በ'ኔ አስተዳደር ሥር ነው:: ነፍሷ ብትጠፋ ያስጠይቀኛል:: ባይሆን በሰንበት ቀን ቃለ እግዚአብሔርን ትስማ» ብሎ ሠራተኛውን ያመጣ አለን?» ሲል ተመሥጬ ከምሰማበት ዓለም መለስ አልኩና እማማን አየኋቸው:: እርሳቸውም እኔን ሲያዩ ዐይኖቻችን ተገጣጠሙ:: በድንጋጤ ዐይኔን ወደ ሌላ አቅጣጫ ሳዞር ከዚህ በፊት የተቀጠርኩበትን ቤት ባለቤት አየኋቸው:: ክፋታቸው ቢጻፍ ሺ መጽሐፍ አይበቃውም:: ትምህርቱን መስማታቸውን ለማረጋገጥ ደግሜ ፊቴን ወደ እርሳቸው አዞርኩ:: ከሌላ ሴት ጋር ወጋቸውን ይሰልቃሉ:: እንዲህ ያለውን ትምህርት ቢሰሙማ የሰው ሰው ባላሠቃዩ አልኩ በልቤ::

«... እንጠንቀቅ÷ ድኻን መበደል ለክርስቲያኖች አይገባም:: በየቤታቸው ሲመለሱ የቀጠሯትን አገልጋይ በመበደል የጉልበቷን ዋጋ ባለመክፈል ስናረክሰው እንገኛለን:: መጽሐፍ ቅዱስ ግን እንዲህ ነው የሚለው፦«የምንደኛውን ደሞዝ የቀማ ሰው ደሙን ማፍሰሱ ነው::» ሢራክ 31÷27:: እንግዲህ ልብ ያለው ልብ ይበል:: እግዚአብሔር አምላክ ልብ ይስጠን:: ስሙም ለዘላለም የተመሰገነ ይሁን:: አሜን::» ብሎ መምህሩ ትምህርቱን ሲፈጽም ሁሉም በአንድነት «ቃለ ሕይወት ያሰማልን» አሉ:: ዕፁብ ድንቅ ÷ እያልኩ ከእማማ ጋር የቤተ ክርስቲያኑን ቅጽር ለቀን ስንወጣ ከኋላችን ድንገት የድሮዋ አሠሪዬ ተቀላቀሉን:: ከእማማ ጋር ትንሽ ተነጋገሩና እኔን ገልመጥ አድርገውኝ ሄዱ:: ምን እያሉብኝ ይሆን? ብዬ በልቤ ከማሰቤ፡ - «ሆ...ሆ... ጉድ እኮ ነው» አሉ እማማ ፊታቸው ልውጥውጥ ብሎ:: «ምነው እማማ?» አልኳቸው እየፈራሁ:: «ሌባ ናት ብለው እያናደዱኝ እኮ ነው::» ሲሉኝ የእትዬን ክፋት ከእማማ ደግነት ጋር እያወዳደርኩ፦ «እግዚአብሔር ሆይ÷ ለኔ ለምንደኛዋ ችግር እንዳልተኛህ ለእትዬም ልብ ስጣቸው::» አልኩ እንደለመደብኝ በልቤ::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# «ኮከብ እማእከለ ከዋክብት ÷ በከዋክብት መካከል ያለ ኮከብ»



*ጤና ይስጥልን የተወደዳችሁ አንባብያን÷ ባለፈው እትማችን ስለ ቅዱስ ፍሬምናጦስ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅና ኮሌጁን ስላቀኑት ታላቅ አባት ልናወጋችሁ ውል አስረን ነበር የተሰነባበትነው:: ከዚያ ጊዜ ወደዚህ ግን ÷ሰኔ 25 ቀን 1997 ዓ.ም. ኮሌጁ ለሦስት ዓመት ያህል በዲፕሎማ መርሐ ግብር ያሠለጠናቸውን 16 ደቀ መዛሙርት ለሁለተኛ ጊዜ እንዲሁም ለአራት ወራት የሠለጠኑ 22 ካህናትን በሰርተፊኬት አስመርቋል:: በማኅበረ ቅዱሳን የመቐለ ንዑስ ማዕከል ባደረሰን ዘገባ በምረቃው ሥነ ሥርዓት ላይ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ፣የክልል ትግራይ ፕሬዝዳንት አቶ ጸጋይ በርሀና ሌሎች ባለሥልጣናት ተገኝተዋል:: የዘገባውን ዝርዝር ከጋዜጣችን /ስምዐ ጽድቅ ÷ መስከረም ወር ÷ 12ኛ ዓመት ቁጥር 12 1998 ዓ.ም/ እትም እንድታነቡ እንጋብዛለን::*

*ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ÷ ኮሌጁ የመጀመሪያ ዙር የዲፕሎማ መርሐ ግብር ደቀ መዛሙርትን ከአንድ ዓመት በፊት ባስመረቀበት ወቅት ባስተላለፉት መልእክት «ይህ ኮሌጅ ዛሬ ለደረሰበት ደረጃ ይበቃ ዘንድ በወቅቱ የትግራይ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ታላቁ አባት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ራእይ ነበር:: ይህ ራእያቸው እውን ይሆን ዘንድ ብፁዕነታቸው ብዙ ደክመዋል:: በመሆኑም «ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር» ነውና የእግዚአብሔር ፈቃዱ ኾኖ የብፁዕነታቸውን ዓላማ በመገንዘብ ቅዱስ ሲኖዶስም ለዚህ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ሥርዓተ ትምህርት እንዲቀረፅለት፣መተዳደሪያ በጀት እንዲመደብለት ፈቅዶ ከዛሬ ሦስት ዓመታት በፊት (1994 ዓ.ም.) እንዲከፈትና የመማር ማስተማሩን ሥራ እንዲጀምር በማድረጉ የታላቁ አባት የብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ራእይ እውን ሊሆን ችሏል::» ማለታቸው ይታወሳል:: ለመኾኑ ባለ ራእዩ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ማን ናቸው? የቅዱስ ፍሬምናጦስ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ኮሌጅ ዛሬ በምን ሁኔታ ላይ ይገኛል? ለወደፊቱስ በምን መልኩ ይቀጥላል? ለእነዚህና መሰል ጥያቄዎች ማብራሪያ ለማግኘት በኮሌጁ ቅጽረ ግቢ እንገኛለን:: ካረፍንበት የመቐለ ዩኒቨርስቲ እንዳየሱስ ካምፓስ ወደ መንፈሳዊ ኮሌጁ ያመራነው በዚህ ዝግጅታችን እያወያዩን አብረውን የሚዘልቁት የኮሌጁ የአስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ሓላፊ ሊቀ ትጉኃን ላእከ ታረቀ በመደቡልን መኪና ነው:: የኮሌጁ ሐዲስ ኪዳን መምህር ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ካሣም የበኩላቸውን ያካፍሉናል:: በአብሮ ቆይታችን ምቾት ከሰጡን ነገሮች ውስጥ መኪናዎን የሚሾፍርልን አቶ የማነ ሥዩም ጣል ያደርጋቸው የነበሩት ማቋረጫ የሌላቸው ቁም ነገር አዘል ቀልዶች የማይዘነጉ ናቸው:: ሁሉም ስላደረጉልን ከፍተኛ ትብብር በሐመር አንባብያን ስም ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርብላቸዋለን:: «ምድላዎትና ኽፃሊ ኢዩ»፤ ዝግጅታችን ይቀጥላል...::*

የሞ ረፉበት ቀን ከተወለዱበት ቀን ጋር ተመሳሳይ ነው:: ነሐሴ 12 ቀን ማታ ለ13 አጥቢያ 1887 ዓ.ም ተወለዱ:: ከ96 ዓመት በኋላ በመልካም ሽምግልና ኖረው እንዳማረባቸው ወደ ፈጣሪያቸው የሄዱት ነሐሴ 12 ቀን ለ13 አጥቢያ ከሌሊቱ 6:00 ነበር:: ገና ሳይፀንሱ ጥንት መካን የነበሩት ወላጅ እናታቸው ያዩላቸው በጎ ሕልም /ራእይ/ ነበር:: ሕልማቸውን የፈቱላቸው የብፁዕ አቡነ አምላክ ገዳም አባት:– «በብርሃን ትምህርቱ የብዙዎችን ምእመናን ልብ የሚያበራ፣በሥራው፣በትሩፋቱ ቤተ ክርስቲያንን የሚጠቅም ይሆናል» ብለዋቸዋል:: እነኾ ሕልሙ እውን ሆኗል፤ ቃሉ ደርሷል÷ ተፈጽሟል:: የቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ የአስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ሓላፊ ሊቀ ትጉኃን ላእከ ታረቀ ይህን ያረጋግጣሉ:: የሥራ ፍሬያቸውንም ከብዙ በጥቂቱ ይዘረዝራሉ:: እንዲህ ሲሉ:-

- የመቐለ የቅዱስ ፍሬምጦስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ ትምህርት ቤትና አዳሪ ቤት
- በአክሱም የቅዱስ ያሬድ መንፈሳዊ ትምህርት ቤትና አዳሪ ቤት/1954 ዓ.ም./
- በዓድዋ የዓዲ ኣቡን ትምህርት ቤት
- በዓድዋ የየሐ ትምህርት ቤት
- በዓድዋ ከተማ ዘመናዊ ትምህርት ቤት
- በምሥራቅ ትግራይ ዞን (በሁለት አውላዕሎ) የውቅሮ፣የአብርሃ ወአጽብሓ እና በዓጋሜ የጉሎ መኸዳ ትምህርት ቤቶች
- በተምቤን የዐብዪ ዓዲ ትምህርት ቤት
- በትግራይ ደቡባዊ ዞን (ራያና አዘቦ) የማይጨው ትምህርት ቤት
- በምዕራብ ትግራይ ዞን (ሽሬ እንዳ ሥላሴ) የሽራሮና የዓዲ አውዓላ ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች
- በመቐለ የደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል፤ በሽራሮና አካባቢው ሦስት አብያተ ክርስቲያናት
- በሽሬ እንዳ ሥላሴ ፣ በማይ ጨው፣ በመቐለ ከተሞች የተለያዩ ሕንጻዎች፣ የእህል ወፍጮዎች ፣ የእርሻ ቦታዎች፣ የእርሻ መኪና፤...

ተቋቁመው በርከት ያሉ የልማት ሥራዎች ተሠርተዋል:: እንደ ሊቀ ትጉኃን ላእከ ገለጻ የእኒህ መንፈሳዊና ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች መሠራት ዋነኛ ዓላማና ተቀዳሚ ተግባር ጥንታዊውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ከዘመናዊው ትምህርት ጋር ለማስፋፋት ነበር:: ለመኾኑ ይህን ሁሉ ትምህርት ቤት የመሥራት፣የማስፋፋት፣ ትምህርትን ለሁሉ የማዳረስ ጽኑ ፍላጎትና ጥረት ባለቤት የመልካም ሥራ አብነት



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ማን ናቸው? ለእናታቸው ወ/ሮ ዓመተ ኢየሱስ ምሕረተ አብ ÷ለአባታቸው ቄስ ገብረ ኢየሱስ ፈቃደ ተስፋ የኾኑ–የብጽአት ልጅ፣ በየግብፃዊ ጳጳስ የተካኑ – ብልሀ ደቀ መዝሙር ፣ በቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ገዳም የመነኮሱ – መስተጋድል፣መምህሮቻቸውን መስለውና አኽለው የወጡ – ሐዋርያዊ ሊቅ፣ ፍትሕ ርትዕ የሚጠነቀቁ – የሕዝብ ልጅ፣ህብተ አንብእ የተሰጣቸው፣ፍቅረ ቤተ ክርስቲያን የሚያቃጥላቸው ኦርቶዶክሳዊና ኢትዮጵያዊ አባት ናቸው– የአክሱምና የትግራይ አውራጃዎች ሁሉ ሊቀ ጳጳስ (1948–1983 ዓ.ም.) ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ።

በረከታቸው ይደረብንና ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ÷በትምህርታቸው፣ በመንፈሳዊ አስተዳደራቸው፣በሥራ ወዳድነታቸውና በትጋታቸው፣ ምእመናንን በማስተባበር ባከናወኗቸው ታላላቅ የልማት ሥራዎች ፣ ለቤተ ክርስቲያን ባላቸው የሌት ተቀን ሐሳብና ራእይ በምእመናን ዘንድ በሰፊው ይታወቃሉ። የቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ የሐዲስ ኪዳን መምህር የኾኑት ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ካሣ –«ሕያው ስም» በሚል ርእስ በ1983 ዓ.ም ባሳተሙት የብፁዕነታቸውን ዜና ሕይወትና ሥራዎች የሚያትት መጽሐፍ እንዳገኘነው የሚከተሉት ብሂሎች ብፁዕነታቸውን ይገልጿቸዋል።

«አባታችን ከሁሉ አብልጠው የሚወዱት ምንድን ነው? ለምን?» ሲል ከአንድ ጋዜጠኛ ጥያቄ ቀረበላቸው። ብፁዕነታቸው ሲመልሱ:– «የመልካም ነገር ምንጭ ትምህርት ስለኾነ ትምህርትን ከሁሉ አብልጬ እወዳለሁ» ብለዋል። አዘውትረው የሚያገኙትን ሰነፍና ምክንያተኛ ወጣት:– «ልጄ ለምን አትማርም?» በማለት ይጠይቁታል። ወጣቱም :– «ምን በልቼ እማራለሁ?» ብሎ ጥያቄያቸውን በጥያቄ ይመልስላቸዋል። «ታድያ ምን በልተህ ትደነቁራለህ?» በማለት ምክንያቱን አፍርሰውበታል። «ከሁሉ አስቀድማችሁ ለማወቅ ፈቃደኞች ኹኑ። ሹመትን እናንተ አትፈልጉት። ደጅ ጠንተው ለምነው የተሾሙት ሹመት የእኔ ነው ብለው የማይኮሩበት የተውሶ ልብስ ነው። ተምራችሁ፣ ዐውቃችሁ ከተገኛችሁ ሹመት ራሱ እናንተን እየፈለገ ካላችሁበት ድረስ ከተፍ ይላል። በራችሁን አንኳኩቶ ወደ ቤታችሁ ይገባል።»

ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ትምህርት ቤት ለመሥራት፣ ለማስፋፋት፣ ትምህርትን ለሁሉ ለማዳረስ የነበራቸው ጠንካራ ዓላማ ካነጋገራቸውና ከሥራቸው ይታወቃል። «ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ከመሥራት ይልቅ ጥቂት ትምህርት ቤቶችን መሥራት ይበልጣል» ይሉ ነበር። ለምን? ሲባሉ:– «በትምህርት የበለጸጉ መምህራን የሚገኙባቸው ጥቂት ትምህርት ቤቶች ብዙ ምሁራንን ብዙ ሊቃውንትን ያስገኛሉ÷ያፈራሉ። ብዙ ሊቃውንት ያስገኛሉ÷ያፈራሉ። እነዚያም ሊቃውንት በበኩላቸው ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን በእምነት በመልካም ምግባር ሊያንጹ ይችላሉ። ምሁራን የማይገኙባቸው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ግን ብዙ ምርት አያሌ ጥቅም ሊሰጥ የሚችል አዝመራ በሚገባ አፍርቶ ሳጨዳ ደርሶ ሳለ የሚያጭደው የሚሰበስበው አጥቶ÷መሬት ላይ ረግፎ ባክኖ የአዕዋፍ የእንስሳት ቀለብ ኾኖ የሚቀር አዝመራን ይመስላል» የሚል ነበር መልሳቸው። ይኸውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «መከሩ ብዙ ነው፤ ሠራተኛው ግን ጥቂት ነው» ያለውን ያስታውሰናል። ማቴ.9÷37–38። በዕለተ ቅዳሜ የቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ትምህርት ቤትን እየተዘዋወሩ በሚጎበኙበት ጊዜ ደንጊያ ሲያነሡ፣ሲያርሙ፣ሲኮተኩቱ አንድ ትልቅ ሰው:– «ምነው አባታችን... ዛሬ እኮ ጌታ እንኳን ያረፈበት ቀን ነው፤ ምነው እርስዎ አያርፉም?» አሏቸው። ብፁዕነታቸውም :– «ጌታ'ኮ ሥራውን ሠርቶ ከጨረሰ በኋላ ነው ያረፈው፤ እኛ ምን ሠርተን እናርፋለን? ለማረፍ'ኮ መሥራት ያስፈልጋል።» ብለው መልሰውላቸዋል። በሌላ ጊዜ ደግሞ ጋዜጠኛው «አባታችን ምን ይመኛሉ?» ሲል ቢጠይቃቸው:– «አገሬ ኢትዮጵያ ሳትከፋፈል በአንድነት ጸንታ፣ በነጻነት፣በልማት ለዘለዓለም እንድትኖር÷ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወንዱም ሴቱም፣ ትልቁም ትንሹም እንዲማር፣አንዱ ከአንዱ ሳይበልጥ ወይም ሳያንስ በሀገሩ ሠርቶ በልቶ ጠግቦ እንዲኖር እመኛለሁ።» ብለው መልሰውለታል።

በኤርትራ ደቡባዊ ዞን ልዩ ስሙ ኩርባርያ በሚባለው ቦታ የተወለዱት አቡነ ዮሐንስ (በቀድሞ ስማቸው ገብረ መስቀል) የስእለት ልጅ በመኾናቸው ሦስት ዓመት ከስድስት ወር ሲኾናቸው ለብፁዕ አቡነ አምላክ ገዳም ተሰጥተዋል። በዚህ ገዳም ውስጥ ንባብ፣ዳዊት፣ግብረ ዲቁና ተምረው ከአንድ ግብፃዊ ጳጳስ ዲቁና ተቀብለዋል። በዲቁናቸው ቤተ ክርስቲያንን በማገልገል፣አበው መነኮሳትን በመርዳት፣መጻሕፍትን በመመልከት እስከ 12 ዓመታቸው ቆይተዋል። የትምህርት አድማሳቸው እየሰፋ ሲሄድ በጎጃም፣በጎንደር፣በትግራይና በሸዋ እየተዘዋወሩ በጥንታዊው ሥርዓተ ትምህርት:– ቅኔ፣ዜማ፣ ቅዳሴ፣ትርጓሜ መጻሕፍት በሚገባ ተምረዋል። በ34 ዓመታቸው ሰኔ ዘጠኝ ቀን 1921 ዓ.ም. በኢየሩሳሌም ቀራንዮ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን መዓርገ ምንኩስና ተቀብለዋል። በነበራቸው የመንፈሳዊ ትምህርት ዕውቀትና ችሎታም:–

- በአዲስ አበባ ቀጨኔ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም በአስተዳዳሪነት (1928–1934 ዓ.ም. )፣
- በሊቀ ሊቃውንት መዓርግ በታዕካ ነገሥት በኣታ ለማርያም ገዳም በአስተዳዳሪነት፣
- የዕጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ (የብፁዕ አቡነ ባስልዮስ) እንደራሴ፣በጠቅላይ ቤተ ክህነት የመንፈሳዊ ጉባኤ ምክትል ሰብሳቢ፣
- የርእሰ አድባራት ወገዳማት ዘኢትዮጵያ አክሱም ጽዮን ንቡረ እድ እና የአውራጃዋ አስተዳዳሪ ኾነው አገልግለዋል።
- በመጨረሻም ቀድሞ የትግራይ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ካረፉ በኋላ ሐምሌ 18 ቀን 1948 ዓ.ም. በመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ እንብሮተ እድ ሁለተኛው የትግራይ ጳጳስ ኾነው ተሾሙ። ሹመቱን በፍጹም ፍርሃትና በታላቅ ትሕትና የተቀበሉት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ጳጳስ ከኾኑ ጀምሮ እስከ ዕለተ ዕረፍታቸው ምእመናን የሚገለገሉባቸውን አብያተ ክርስቲያናት በማሠራት፣ የትምህርትና የልማት ተቋማት በመገንባት ለትውልዱ አስረክበዋል። እንደበታቸው ከማስተማርና ከጸሎት፣ዐይናቸው መጻሕፍትን ከመመልከትና ከማልቀስ፣እጃቸውን ለድኾች ከመዘርጋት፣በኅሊናቸው ከተዘክሮተ እግዚአብሔር ሳይለዩ መዋዕለ ሕይወታቸውን በቁም ነገር አሳልፈውታል።

ለብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ከሰማይ በታች የአቅም ምንጫቸው÷የሀብት መሠረታቸው በመንፈሳዊ አባትነት የሚመሩት ሕዝብ እንዲሁም በትግራይ የሚገኙ ገዳማትና አድባራት ነበሩ። ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ የቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን መንፈሳዊ ትምህርት ቤትን ጥር 14 ቀን 1965 ዓ.ም መርቀው ሲከፍቱ:– «ለመተዳደርያው በጀት (ርዳታ) ይፈቅዱልኛል» የሚል ተስፋ ነበራቸው። ይህንንም በምረቃው ዕለት ባደረጉት ሰፊ ንግግር እንደሚከተለው ገልጠውት ነበር:– «ግርማዊ ሆይ÷ልዑል እግዚአብሔር አባታችን አዳምን÷አካሉን አሣምሮ ውበቱ እንደ አበባ የሚያሸበርቅ፣እንደ ፀሐይ የሚያንጸባርቅ፣ይህ ቀረሽ የማይባል ውብና መልከ መልካም አድርጎ ፈጠረው፤ በኋላ በአፍንጫው የሕይወት እስትንፋስ እፍ አለበት፤ የሚንቀሳቀስም ሕያው ፍጥረት ኾነ። ይህም ትምህርት ቤት አሁን የሚታየው አካሉ÷መልኩና ውበቱ ብቻ ነው። ሕይወት ኖሮት እንዲንቀሳቀስ፣ሕያው ትምህርት ቤት እንዲኾን የግርማዊነትዎን የሕይወት እስትንፋስ ይፈልጋል። ግርማዊነትዎ እፍ እንዲሉበት ይማፀናል።» ነገር ግን እርሳቸው እንዳሰቡት ሳይኾን ቀረ።

ከንጉሡ የተጠበቀው የትምህርት ቤቱ መተዳደሪያ በጀት ሳይፈቀድ መቅረቱ ምን ስሜት እንዳሳደረባቸው ከጋዜጠኛ ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ:– «ከዚህ በፊት ከሠራሁት የበለጠ እንድሠራ፣ሕዝቡን ማስተ ባበር፣ መለመን እንዳለብኝ፣ከሕዝብ የበለጠ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ምንም ኃይል እንደሌለ ተሰማኝ» ብለዋል:: የሕዝቡን አቅም በተግባር የፈተኑት ብፁዕነታቸው ያለ ልግም የሚተጋ ሥራ ወዳድ ታታሪ ሕዝብ መኾኑን ለመግለጽ:- «የትግራይ ሕዝብ ቀኝ እጅ እንጂ ግራ እጅ የለውም፤ ሁለቱም እጆቹ ቀኝ ናቸው» ሲሉ ተደምጠዋል::

ቀደም ሲል እንደ ገለጽነው ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ:- የብፁዕ አቡነ ባስልዮስ እንደራሴና የመንፈሳዊ ጉባኤ ምክትል ፕሬዝዳንት ሳሉ ዘመናዊ ትምህርት ወደ ሀገራችን በእንግድነት የሚገባበት ወቅት ነበር:: ብፁዕነታቸው ስለ እንግዳው ዘመናዊ ትምህርት ያቀርቡት የነበረው ሓሳብ የሚከተለውን ይመስል ነበር:- «ቤተ ክርስቲያናችን የፊደል፣የቃል፣የሥነ ጽሐፍ፣የትምህርት ባለቤት ናት:: ፊደል እያስቀረጠች የሕዝቡን ዐይን ስትገልጥ÷ የአእምሮ ጓዳውን ስትከፍት ኖራለች:: መንፈሳዊ ትምህርት ብቻ ሳይኾን በሥጋው የሚጠቀምበትን ተግባረ እድ ማለት ጽሕፈትን፣ሥዕልን፣ ቅርፃ ቅርፅ ንና የመሳሰለውን ጠቃሚ ጥበብ ሁሉ አስተምራለች:: የሀገሪቱን ታሪክ ሥጋዊውንም መንፈሳዊውንም መዝግባ አቆይታለች:: ስለኾነም ባላት የትምህርት ልምድ መሠረት ከትምህርት ሚኒስቴርም ጎን ተሰልፋ ዘመናዊውንም መንፈሳዊውንም ትምህርት ማካሄድ አለባት:: እንደ ባዕድ ከዳር ኾኖ መመልከቱ የሚያዋጣት አይደለም:: ይልቁንም ቀረብ ብላ ከጊዜው ጋር እየተራመደች የሚሻለውን የሚጠቅመውን በመሥራት፣የሚጎዳውን መጥፎውን በመከላከል የበኩልዋን ድርሻ ልታበረክት ትችላለች:: በቸልተኝነትና አርቆ ባለማሰብ ይህን ሳናደርግ ቀርተን ዕድሉ ከእጃችን ቢያመልጥ ግን ቤተ ክርስቲያን ለነገሩ ባዕድ ትኾናለች፤ ወደ ኋላ ትቀራለች፤ ኋላ ከማንወጣው አዘቅት ውስጥ እንወድቃለን» የሚል ነበር::

ነገር ግን በጊዜው የነበሩ አንዳንድ መኳንንት፣ካህናት ነገሩን ከእምነት ጋር በማያያዝ «ሃይማኖትን ይጎዳል» የሚል ደካማ ምክንያት እያቀረቡ ተቃወሟቸው:: ሓሳባቸው ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ:: እንዳሉትም ዕድሉ አመለጠና ባለቤትዋ ቤተ ክርስቲያን ባዕድ (እንግዳ)÷ እንግዳው ደግሞ ባለቤት ኾነ:: «በሞኝ ቤት እንግዳ ይናኝበት» እንደ ሚባለው በቤትዋ በጓዳዋ እንግዳ ሲናኝበት÷ሲያዝበት በባይተዋርነት መመልከት ግድ ኾነባት::

ብፁዕነታቸው ያቀረቡት ሐሳብ በሀገራችን በአጠቃላይ÷ በቤተ ክህነቱ ደግሞ በተለይ ተቀባይነት ባያገኝም በሀገረ ስብከታቸው ክልል ተግባራዊ ለማድረግ መነሣሣታቸው አልቀረም:: ብፁዕነታቸው ለዚህ ያበቃቸው ተሞክሮ ይኖር እንደ ኾነ ለቅዱስ ፍሬምናጦስ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን መንፈሳዊ ኮሌጅ የአስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ሐላፊ ሊቀ ትጉኃን ላእከ ታረቀ ጥያቄ አቅርበንላቸው ነበር:: ሊቀ ትጉኃን ለጥያቄያችን በሰጡን መልስ:- «ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ለየት ያለ አስተሳሰብ ነበራቸው:: ነገሩ የስጦታም ጉዳይ ነው:: ወደ ውጭ አገርም ሄደው ሲጎበኙ የሚያዩት ነገርም አስተዋፅዖ አለው::...ወደ ግብፅ ሲሄዱ 'ታላቁ የኢትዮጵያ ሐዋርያ' እየተባለ ይነገርላቸው ነበር:: ቅድስናም የነበራቸው ሰው ናቸው:: 'አቡነ ዮሐንስ ጥሩ ነበሩ፤ ነገር ግን መነኮሳትን በከተማ መሰብሰብ ይወዳሉ' ይባል ነበር:: ይህም ወደ ምንኩስና ያደላሉ ለማለት ነው:: ወጣት መነኮሳትን ወደ ትምህርት ቤት አስገብቶ በትምህርትና ዕውቀት የማበልጸግ ከፍ ያለ ዕቅድ ነበራቸው:: አንድን ሰው ሲያገኙ የመጀመሪያ ጥያቄአቸው:- 'ስንተኛ ክፍል ነህ? ምን ትማራለህ?' ነው::...የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት በመሠረቱ ሳይቀየር በዘመናዊ መልኩ ለውጥና መሻሻል እንዲኖር ይሹ ነበር:: ለቅዳሴው፣ለድጓው፣ለመጽሐፍ ትርጓሜው ከፍ ያለ ትኩረት ነበራቸው:: ... ከትምህርት ቤት በፊት ቤተ ክርስቲያን የተሠራ እንደሆን «ማን የሚያገለግላትን ቤተ ክርስቲያን ነው የምትሠሩት? ይሉ ነበር:: የቤተ ክርስቲያን ኃይል ከሌለ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አዳጋች ነው» ብለዋል::

ብፁዕነታቸው ለተነሡበት ዓላማ ይረዳል ብለው ያመኑበትን አንድ ሓሳብ አመጡ:: ይኸውም ከታላላቁ ጥንታውያን ገዳማት ማለት ከርእሰ አድባራት ወገዳማት አክሱም ጽዮንና ከአብርሃ ወአጽብሓ ገዳም የተውጣጡ የትምህርት ፍላጎትና ንቃት ያላቸው አምስት ወጣቶችን መረጡ:: እንትወደ ኾነችው እስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን በመላክ በከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ለአራት ዓመታት እንዲሠለጥኑ አደረጉ:: ከእነዚህም አብዛኞቹ በተማሩበት ትምህርት በቀሰሙት ዕውቀት ቤተ ክርስቲያናቸውንና ሀገራቸውን በከፍተኛ ደረጃ ኾነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ:: እንደ ብፁዕነታቸው አገላለጽ ለኢትዮጵያ ታሪክ ምልእት የኾነላት ቅዱስ ያሬድ:- ሰማያዊ ዜማ ባዜመበት፣ድጓውን በደረሰበት፣ ቅኔውን በቀመረበት ልዩ ሥፍራ (አክሱም - ሙራደ ቃል) «የቅዱስ ያሬድ አዳሪ ትምህርት ቤት» እንዲከፈት አደረጉ:: በማስተማር ሀብታቸው፣ደቀ መዛሙርትን በማፍራትና በመተካት ዕድልና ልዩ ተሰጥዖ ያላቸውን መምህራን በማሰባሰብ የድጓ፣የዝማሬ መዋስዕት፣የቅዳሴው መማሪያና ማስመስከሪያ እንዲኾን አደረጉ:: በ1954 ዓ.ም. የተሠራው የቅዱስ ያሬድ ትምህርት ቤት ብዙ መምህራንንና ሰባክያንን አፍርቷል:: ደቀ መዛሙርቱ ዛሬም በቤተ ክርስቲያኒቱ በልዩ ልዩ ሥራ ተመድበው በትልቅ ሓላፊነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ::

ከዚህ በላይ ግን የብፁዕነታቸው ዘላቂ ዕቅድ÷ ካህናት ዘመናዊውን ትምህርት ከመንፈሳዊው ጋር በማቀናጀት ከፍተኛ ዕውቀት የሚገበዩበት ትምህርት ቤት በትግራይ ማሽከል መቐለ መሥራት ነበር:: ትምህርት ቤቱ በዕቅዱ መሠረት ከተሠራ አገልግሎቱና ጥቅሙ ለመላዋ ትግራይ ከዚያም አልፎ ለኢትዮጵያ እንደሚኾን ምንም ጥርጥር አልነበራቸውም:: ዓላማቸውን ከግቡ ለማድረስ ገንዘብ ያስፈልግ ነበር:: በ1955 ዓ.ም. ይህን አስመልክቶ ለሕዝቡ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ፣እያንዳንዱ ምእመንና በጎ አድራጊ አካል የተቻለውን ያህል አስተዋፅዖ እንዲያደርግ የሚቀሰቅስ አንድ ማኅበር በአብርሃ ወአጽብሓ ስም አቋቋሙ:: «የነገሩ ሁነኛ የጦር አርበኛ» እንዲሉ ብፁዕ አባታችን የሥራው ባለቤት፣የመልካም ተግባር አብነት እንደ መኾናቸው መጠን የሚናገሩትን በተግባር አሳይቶ «እንዲህ አድርጉ» ለማለት አርአያ ለመኾን ሙሉ የወር ደመወዛቸውን በመክፈል አሐዱ ብለው አስተዋፅዖውን ራሳቸው ጀመሩት:: ከዚህ በኋላ ስላለው ሂደት ሊቀ ትጉኃን ላእከ ታረቀ እንዲህ ያስረዳሉ:- «ከ30 ዓመታት በፊት 15 ሄክታር ወይም 150,000 ካሬ ሜትር የሚጠጋ ቦታ ከመንግሥት በብርቱ ጥረትና ድካም ተረከቡ:: በትግራይ የሚገኙ ገዳማትና አድባራት እንዲሁም መላው ሕዝበ ክርስቲያን ባደረጉት አስተዋፅዖ ለማስተማርያ፣ ለመኝታ፣ ለቢሮ፣ ለግምጃ ቤት የሚያገለግሉ፣በጥርብ ደንጊያ የተሠሩ ሕንፃዎች አሠርተው በጥር ወር 1965 ዓ.ም. በግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ አስመረቁ:: በምረቃው ዕለት ብፁዕነታቸው ባሰሙት ንግግር መጨረሻ ላይ:- «ይህ ትምህርት ቤት ለኢትዮጵያና ለቤተ ክርስቲያናችን ታላቅ ታሪክ በሠሩ፣ብዙ በረከት ባበረከቱ በአቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን እንዲሰየምልን ግርማዊትነዎን በትሕትና እለምናለሁ» ብለው ጠይቀው ነበር:: ንጉሡም *«ከሣቴ ብርሃን ሰላማ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት»* ተብሎ እንዲሰየም ፈቅደናል ብለው በሕዝብ ፊት ገለጡ:: ከዚያ ጊዜ አንሥቶ *«ከሣቴ ብርሃን ሰላማ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት»* እየተባለ መጠራት ጀመረ::

ብፁዕ አባታችን የትምህርት ቤቱን ግንባታ በማካሄድ ሂደት ብዙ ነገር ነበር የገጠማቸው:: ከመጀመሪያው ለመነሣት «ኢይከብር ነቢይ በሀገሩ ወፈድፋደስ በሰብእ ቤቱ፤ ነቢይ በሀገሩ አይከብርም፤» እንዲሉ በዋናነት ያስቸገሯቸው የቤተ ክህነት ሰዎች ናቸው:: «ሕንፃ እግዚአብሔርን እያፈረሱ ሕንጻ ሰብእን የሚሠሩ» የሚል መግለጫ ተሰጥቷቸው ነበር:: ይህም ደመወዝ አይሰጡንም፤ ዝም ብለው ነው ሕንጻ የሚያንጹት» ለማለት ነበር::

/ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል /



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ቆስጠንጢኖስ

## ወልደ እሌኒ

/ጌታቸው በቀለ/

የታሪክ ድርሳናት እንደሚያትቱት ቤተ ክርስቲያን እስከ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ከዓላውያን ነገሥታት /ቄሣሮች/ ጋር ስትዋጋ ኖራለች። በተለይ ከ160-312 ዓ.ም ድረስ ባለው «ዘመነ ሰማዕታት» ወይም «የቤተ ክርስቲያን የስደት ዘመን» ቤተ ክርስ ቲያን ብዙውን ቅርሷን አጥታለች። በዚሁ ዘመን የነበሩ ሮማውያን ቄሣሮች በቤተ ክርስቲያን ላይ መከራ ያጸኑባት፣ በደል ይፈጽሙባት ነበር። ቤተ ክርስቲያን ይደርስባት ከነበረው ግፍና መከራ ፋታ ያገኘችው በታላቁ ቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት ነው።

ቆስጠንጢኖስ በ258 ዓ.ም በናይሳን ከተማ ተወለደ። አባቱ ኮንስታንዲዮስ /ቁንስጣ/ እናቱ እሌኒ ይባላሉ። አባቱ አረማዊ እናቱ ክርስቲያን ነበረች። በዚያን ዘመን ክርስትና ገና ስላልተስፋፋ አንዳንድ ሰዎች ይህን የመሰለ ጋብቻ ይፈጽሙ ነበር። (1ቆሮ. 7÷12–16)። ቆስጠንጢኖስ ትውልዱም ነገዱም ሮማዊ ነው። ቆስጠንጢኖስ ማለት ስመ ትርጓሜው ሐመልማል፣ ነበልባል ማለት ነው። መጋቢት 28 ቀን በሚነበበው ስንክሳር፤ ቆስጠንጢኖስ ማለት «ዝንጉርጉር ማለት ነው» ይላል።

ቅድስት እሌኒ ልጇን ቆስጠንጢኖስን ብሉይን፣ሐዲስን፣ ሥርዓተ ሃይማኖትን ቀኖና መጻሕፍትን እያስተማረች አሳደገችው። በልጅነት ዕድሜው በዚያን ዘመን በነበረው ወግና ሥርዓት መሠረት፤ የምሥራቅ ሮምን ክፍል በሚያስተዳድረው በዲዮቅልጥያኖስ ቤተ መንግሥት ውስጥ ጋሻ ጃግሬ ሁኖ የጊዜውን ሞያ፤ ፈረስ ግልቢያ፣ ውኃ ዋና፣ ጦር አወራወር፣ ጋሻ አመካከት እየተማረ አደገ። በወቅቱ የሮም ግዛት በሰሜን ምሥራቅ ግብፅን፣ መካከለኛው ምሥራቅን፣ ታናሽ እስያንና ግሪክን፤ በምዕራብ በኩል ፈረንሳይን እስከ ታላቋ ብሪታንያ ድረስ የያዘ ነበር። የቆስጠንጢኖስ አባት ኮንስታንዲዮስ /ቁንስጣ/ የመክስምያኖስ ቄሣር ሆኖ የሮምን ምዕራብ ክፍል ያስተዳድር ነበር።

የቆስጠንጢኖስን ታሪክ ስናወሳ ሮማውያን ቄሣሮች በክርስቲያኖች ላይ የፈጸሙት ዕልቂት፣ በቤተ ክርስቲያን ላይ የደረሰውን መከራ እንድናስታውስ ግድ ይለናል። ቄሣሮቹ በክርስቲያኖች ላይ ያደረሱት መከራ እጅግ በጣም ዘግናኝና አሰቃቂ ነበር። ሥቃዩን ሁሉ ለመዘርዘር ባይቻልም በቤተ ክርስቲያን ላይ አሳዛኝ መከራ ከፈጸሙት ቄሣሮች መካከል በዓይነትም ሆነ በብዛት ተመሳሳይና ተወዳዳሪ የሌለው ዕልቂት በክርስቲያኖች የተፈጸመው በዲዮቅልጥያኖስ ነው። ለመሆኑ ዲዮቅልጥያኖስስ ማን ነው? ዲዮቅልጥያኖስ በቤተ ክርስቲያንና በክርስቲያኖች ላይ ያደረሰው መከራ ምን ነበር?

ዲዮቅልጥያኖስ ከተራ ቤተሰብ የተወለደ የድልማጥያ ሰው ነው። በልጅነቱ በሮም የወታደር ጦር ትምህርት ቤት ገብቶ፤ በዘመኑ የነበረውን የጦር ስልት ተምሯል። ሀገሩ ከፋርስ መንግሥት ጋር በተዋጋች ጊዜ ባሳየው ጀብዱና የጀግንነት ሞያው፤ በመላው የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ውስጥ ለመታወቅ አብቅቶታል። መልካም ዝናንም አትርፎለታል። በዘመኑ የሮም መንግሥት አስተዳደር ከስፋቱ የተነሣ ወደ መውደቅ አዘንብሎ ያነገንግ ስለነበር፤ ዲዮቅልጥያኖስ የመንግሥቱን ሥልጣን ያዘ። በ285 ዓ.ም አውግስጦስ የሮም ንጉሠ ነገሥት ተባለ።

በ286 ዓ.ም የሮምን ጸጥታ ለመጠበቅ እንዲያመች፣ የአስተዳደር ጉድለት እንዳይፈጠር ዲዮቅልጥያኖስ ምሥራቁን ክፍል ያዘ። ለጓደኛው መክስምያኖስ የምዕራቡን ክፍል እንዲያስተዳድር ሰጠው። መክስምያኖስ በሮም ምዕራብ ክፍል አውግስጦስ ንጉሠ ነገሥት ተባለ። ሁለቱም ነገሥታት ቄሣር በሚያሰኝ የመዓርግ ስም ሁለት እንደራሴዎችን መርጠው ሾሙ። በምሥራቅ የዲዮቅልጥያኖስ አማች ጋሌሪዮስ ቄሣር ተብሎ የዲዮቅልጥያኖስ እንደራሴ ሆነ። በምዕራብ የታላቁ ቆስጠንጢኖስ አባት ኮንስታንዲዮስ ክሎሪን ቄሣር ተብሎ የመክስምያኖስ እንደራሴ ሆነ።

ዲዮቅልጥያኖስ አረማዊ በመሆኑ ክርስቲያኖችን ለመደምሰስና ለማጥፋት ተነሣ። ክርስቲያኖችን የጠላበት ሁለት ምክንያቶች ነበሩት። አንደኛው ምክንያት የፋርስ መንግሥት በ296 ዓ.ም የዲዮቅልጥያኖስን ጦር ድል አደረገ። ዲዮቅልጥያኖስም ስለ ሠራዊቱ ድል መሆን ለማስጠንቆል ወደ ቤተ ጣዖቱ ሄደ፤ ጣዖቱ አጵሎስ /የፀሐይ አምላክን/ ቢጠይቅ «ከተከታዮችህ መካከል በትእምርተ መስቀል የሚያማትቡ ስላሉ ነው» አሉት። በዚህ ተናዶ በክርስቲያኖች ሁሉ ላይ የሞት ቅጣት እንዲፈጸምባቸው፣ ክርስቲያን የሆነ ሁሉ በጦር ሠራዊቱ ውስጥ እንዳይገኝ አዘዘ። ክርስቲያኖችን እያደነ የሚያጠፋ የፀረ ክርስቲያን ድርጅት አቋቋመ። ብዙ ክርስቲያኖችና ቅርሶቻቸው እንዳልነበሩ ሆኑ።

ሁለተኛው ምክንያት ምስሉን አሠርቶ፤ ሮማውያን ለምስሉ እንዲሰግዱና እንዲያመልኩት አዘዘ። ቤተ ክርስቲያን ግን ይህን ትእዛዝ አልተቀበለችውም። ቤተ ክርስቲያን «ፈጣሪ እንጂ ፍጡር አይመለክም» በማለቷ ዲዮቅልጥያኖስ «ተደፈርኩ» ብሎ በሮም ግዛት ውስጥ የሚገኙ ክርስቲያኖች ሁሉ በያሉበት እንዲረሸኑ አዘዘ።

የክርስቲያኖችን ሕዋሳታቸውን እየቆራረጡ ያሠቃዩአቸው ነበር። እንዲያውም የሚቆራርጡትን አካላቸውን እየወሰዱ ለጣዖቶቻቸው ያጤሱት ነበር። ከተመሠረተች ጀምሮ በመከራ ታሪኳ ውስጥ ተመሳሳይና ተወዳዳሪ የሌለው ዕልቂት በቤተ ክርስቲያን ላይ ተፈጸመ። ክርስቲያኖች ይህ ሁሉ ግፍ ሲፈጸምባቸው መከራውን ተሰቅቀው ከእምነታቸው ወደ ኋላ አላሉም። «ጌታ ክርስቶስ ነው፤ ሌላ ጌታ አናውቅም» እያሉ እምነታቸውን በደማቸው አተሙት። ግማሾቹም በዱር በገደል እየተሰደዱ በድብቅ ሃይማኖታቸውን ማስተማር ቀጠሉ።

በክርስቲያኖች ላይ ይህ ሁሉ የጭካኔ ዕልቂት ቢፈጸምባቸውም፤ ሲቆርጡት ከሥሩ እንደሚያቆጠቁጥ ዛፍ ቁጥራቸው በየጊዜው እየጨመረ ሄደ። ዲዮቅልጥያኖስ ክርስቲያኖችን ሞት እንዳላጠቃቸው አይቶ አዲስ የማጥቂያ ዘዴ ዐወጀ። አብያተ ክርስቲያናት እንዲደመሰሱ፡- «አብያተ ክርስቲያናት ይትዐፀዋ፣ አብያተ ጣዖታት ይትረኀዋ»፣ ክርስቲያኖች እርስ በርስ እንዳይገናኙ፣ ስለ ክርስትና ሃይማኖት የሚናገሩ መጻሕፍት ሁሉ እንዲቃጠሉ፣ የቤተ ክርስቲያን ንብረት የሆነ ሁሉ እንዲወረስ፣ ማንኛውም የሮም ዜጋ ክርስቲያን ከሆነ ከመንግሥት ሥራ እንዲወገድ፣ ብሔራዊ መብታቸው እንዲነፈጋቸው፤ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች እንዲታሰሩና እንዲሠቃዩ ክርስቲያኖች ምንም ሕጋዊ ምክንያት ቢኖራቸው እንኳን «በማንም ላይ ክስ ለመመሥረትና ስለ መብታቸውም መከራከር አይችሉም» የሚል ዐዋጅ ዐወጀ። ማኅበረ ቅዱሳን÷ <u>ነገረ ቅዱሳን ቁጥር 3÷</u> ገጽ 40-41/፤ /David Ayerst <u>Records of Christianity</u>, page 132-133/.

ዲዮቅልጥያኖስ ይህን ሁሉ ዕቅድ ቢያወጣ፣ጦሩን ቢያሰልፍ ቤተ ክርስቲያንን ለመደምሰስ ክርስትናን ለማጥፋት የነበረው ሕልም ቅዠት ሆኖ ቀረ። ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ደም የተመሠረተች÷ በሰው ኃይልና ጥበብ የማትፈርስ ናት። የዲዮቅልጥያኖስም ዙፋን እየዘመመ ሄደ። በ305 ዓ.ም መክስምያኖስ ሥልጣኑን በገዛ ፈቃዱ ተወ። በዚሁ ዓመት ግንቦት ወር ከምሥራቅ የሮም ግዛት ዲ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ዮቅልጥያኖስ፣ ከምዕራብ መክስምያኖስ ሥልጣናቸውን ሲለቁ ኮንስታንዲዮስ ልጁን ቆስጠንጢኖስን ከምሥራቅ ጠርቶ እንደራሴው አደረገው:: ቆስጠንጢኖስ የአባቱ እንደራሴ ሆኖ ጥቂት እንደ ቆየ አባቱ ኮንስታንዲዮስ ሞተ:: በዚህ ጊዜ የአባቱ ባለሟሎችና ሕዝቡ በአንድ ድምፅ ተስማምተው ቆስጠንጢኖስ የአባቱን ሥልጣን እንዲወርስ አደረጉ:: አባ ጎርጎርዮስ «የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ» በሚለው መጽሐፍ እንዳሰፈሩት «ቆስጠንጢኖስ በሮም ምዕራብ ክፍል በገላትያ የነገሠው ሐምሌ 25 ቀን 306 ዓ.ም በ18 ዓመቱ ነው::»

ጥቅምት 28 ቀን 306 ዓ.ም. የአውግስጦስ መክስምያኖስ ልጅ ማክሴንዲዮስ በሮም የአባቱ የነበረውን ሥልጣን ያዘ:: ቆስጠንጢኖስ የመክስምያኖስን ሴት ልጅ የማክሴንዲዮስን ታናሽ እኅት አገባ:: ይህንም በማድረጉ ዝምድናና ጥሩ ወዳጅነት ከማክሴንዲዮስ ጋር መሠረቱ :: ጠላት ቢነሣባቸው በአንድነት ለመከላከል የጋራ የጦር ኃይል አቋቋሙ:: በቆስጠንጢኖስና በማክሴንዲዮስ መካከል የነበረው መተማመን፣ የጋራ ጥቅምን በጋራ ኃይል ለመጠበቅ የነበረው ትብብራቸው ብዙ ዕድሜ አልነበረውም፤ በአጭር ተቀጨ::

ለሁለቱ አለመግባባት ምክንያት የሆነው የቆስጠንጢኖስ አማት÷ የማክሴንዲዮስ አባት የቀድሞው አውግስጦስ መክስምያኖስ ነው:: መክስምያኖስ ከሚጦርበት ከልጁ ከማክሴንዲዮስ ተጣልቶ ወደ አማቹ ቆስጠንጢኖስ ሄደ:: እዚያም አርፎ ተቀምጦ በመጦር ፈንታ በቆስጠንጢኖስ መንግሥት ላይ ሲያሤር ተይዞ ታሰረ:: በእስር ቤትም እንዳለ በ310 ዓ.ም ሞተ:: ማክሴንዲዮስ በአባቱ መክስምያኖስ ታስሮ መሞት ምክንያት ተናዶ ከቆስጠንጢኖስ ጋር የነበረውን የሰላምና አብሮ የመሥራት ውል አፈረሰ:: የጦር ኃይሉንም ለይቶ ቆስጠንጢኖስን ለመውጋት ይዘጋጅ ጀመር::

ምሥራቁን የሮም ግዛት ይገዛ የነበረው የዲዮቅልጥያኖስ አማች ጋሌሪዮስ በግንቦት ወር 311 ዓ.ም ሞተ:: የመንግሥቱንም ሥልጣን ሊኒኪዮስ አውግስጦስ፣ ማክሲሚኖስ ዲያስ ቄሣር ተብለው ለሁለት ወረሱ:: ጥቂት እንደ ቆዩ በሥልጣን ምክንያት በሁለቱ መካከል አለመግባባት ተፈጠረ:: በዚህ ጊዜ ሁለቱም ረዳት ለማግኘት ከምዕራቡ ክፍል ገዢዎች ጋር ተጠጉ:: ማክሲሚኖስ ዲያስ የማክሴንዲዮስን ርዳታ ሲጠይቅ÷ ሊኪኒዮስ ደግሞ ቆስጠንጢኖስን የሙጥኝ አለ::

ቆስጠንጢኖስ ምንም እንኳን ማክሲሚኖስ ዲያስን ፊት ለፊት ለመውጋት ፍላጎት ባይኖረውም በነበራቸው በቀል ምክንያት ማክሴንዲዮስን ለማግኘት ሲል ሠራዊቱን ለጦር አሰለፈ:: ማክሲሚኖስ ዲያስ ይረዳኛል ብሎ አምኖ ተጠግቶት የነበረው ማክሴንዲዮስ ሊረዳው እንደማይችል ስለ ተረዳ በእርሱ ላይ የነበረው እምነትና ተስፋ መነመነ::

ቆስጠንጢኖስ በ312 ዓ.ም ክተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት ብሎ በማክሴንዲዮስ ላይ ዘመተበት:: በጉዞ ላይ እንዳለ የእግዚአብሔር መልአክ ለቆስጠንጢኖስ በራእይ ተገልጦ እንዲህ አለው:- «በዚህ ጠላትህን ድል ታደርጋለህ» የሚል በመስቀለኛ ቅርጽ የተጻፈ ጽሑፍ በጠፈረ ሰማይ አየ:: ባየው መስቀል አምሳል እየተመራ ሄዶ ከማክሴንዲዮስ ጋር ጦርነት ገጠመ:: በጦርነቱም የቆስጠንጢኖስ ጦር አይሎ ማክሴንዲዮስን ድል አደረገው:: ማክሴንዲዮስ በጦርነቱ ሞተ:: ወዲያውኑ ቆስጠንጢኖስ የማክሴንዲዮስ ዕጣ የነበረውን ጠቅሎ በመያዝ «አውግስጦስ» ተባለ:: ዐፄ እንደ ማለት ነው::

ቆስጠንጢኖስ ከእናቱ ባገኘው ትምህርት መሠረት ለክርስትና ትምህርት እንግዳ ባይሆንም፤ ወደ ጦር ሜዳ ሲሄድ ትእምርተ መስቀል ባስገኘለት ድል፤ ስለ ክርስትና የበለጠ እንዲመራመርና እንዲያውቅ ክርስቲያኖችንም እንዲወድ አድርጎታል፤ የወርቅ መስቀል አሠርቶ በነገሠበት ዘውድ ላይ አደረገ:: ሠራዊቱም በፈረሱ አንገት፣ በጋሻው እምብርት፣ በጦሩ አንደበት የመስቀል ምልክት እንዲያደርግ ዐወጀ:: የመስቀሉ ምልክት ቀድሞ በታየ ጊዜ ጠላቶቻቸውን ድል ያደርጉ ነበር:: ከዚያን ጊዜ በኋላ የቆስጠንጢኖስ ጦር ሠራዊት የሚለየው በመስቀሉ ነበር:: ሊኪኒዮስ በየካቲት ወር 313 ዓ.ም ተቃራኒውን ማክሲሚኖስ ዲያስን አባሮ ምሥራቁን የሮም ግዛት ለብቻው ያዘ:: ወዲያውም የቆስጠንጢኖስን እኅት አገባና የበለጠ መቀራረብን መሠረተ:: /አባ ጎርጎርዮስ፤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፤ ገጽ 40-45፤ ነገረ ቅዱሳን ቁጥር 3÷ ገጽ 43-44 /::

ከዲዮቅልጥያኖስ ጀምሮ ለአራት ተከፍላ ትገዛ የነበረችው ሮም አሁን በሁለት ነገሥታት ብቻ ትገዛ ጀመር:: እነርሱም በምሥራቅ ሊኪኒዮስ በምዕራብ ቆስጠንጢኖስ ናቸው:: ሊኪኒዮስ ከቆስጠንጢኖስ ጋር ክርስቲያኖችን በሚመለከት በ«ሚላኖ ውል» ተዋውለው ነበር:: የሚላኖው ውል /Edict of Milan/ የሚከተለው ነበር::

1. በታላቁ የሮም ግዛት የሚገኙ ክርስቲያኖች እንደ ማንኛውም ሃይማኖት ተከታዮች፤ ሃይማኖታቸው በሚያዘው ቀኖናና ሕግ አምልኮታቸውን ለመግለጥ ይችላሉ::

2. ባለፉት ዘመናት ይሠራበት የነበረውን ክርስቲያኖችን የሚቃወምና የሚያወግዝ ሕግ ከዛሬ ጀምሮ የተሻረ ነው::

3. ክርስቲያኖች አምልኮታቸውን ወደ ፈጣሪያቸው የሚገልጡበት ቦታ ቢያስፈልጋቸው በነጻ ይሰጣቸዋል:: ያለ አግባብ የተነጠቁት ርስትና ንብረት ቢኖራቸውም ለማስመለስ ወይም በወሰደባቸው ምትክ ካሣ ለመጠየቅ መብት አላቸው:: የሚል ነው:: ውሉን ከተዋዋሉ በኋላ ቆስጠንጢኖስ ወደ ከተማው ገላትያ ተመለሰ::

ሊኪኒዮስና ቆስጠንጢኖስ ውሉን ከተዋዋሉ በኋላ በፍቅር የቆዩበት ጊዜ ብዙ አልነበረም፤ በሁለቱም መካከል አለመግባባት ተፈጥሮ እስከ መዋጋት አደረሳቸው:: በውጊያውም ቆስጠንጢኖስ አሸነፈ:: እንደገና በውል ታረቁ:: ሊኪኒዮስ ለነገር የማያርፍ ሰው ስለነበረ በ312 ዓ.ም የፈረመውን የሚላኖ ውል አፍርሶ በክርስቲያኖች ላይ መከራና ሥቃይ አጸናባቸው::

በክርስቲያኖች ላይ የሚፈጸመው ግፍና በደል እየተባባሰ በመሄዱ ቆስጠንጢኖስ በ323 ዓ.ም ውሉን ያላከበረውን ሊኪኒዮስን በጦር ኃይል ገጥሞ ድል አድርጎ ማረከው:: የተማራኪው ሊኪኒዮስ ሚስት የቆስጠንጢኖስ ታናሽ እኅት ስለነበረች፤ የአማችነት ዝምድና ይዞት በሕይወቱ ላይ አደጋ አላደረሰበትም:: ይልቁንም በክብር ተገልሎ እንዲቀመጥ አደረገው:: ሊኪኒዮስ ግን ባለበት ኾኖ በቆስጠንጢኖስ ላይ ሲያሳድምና ሲያሤር በመገኘቱ በ324 ዓ.ም የሞት ቅጣት ተቀጣ:: እርሱ ከሞተ በኋላ ቆስጠንጢኖስ የምሥራቁን ክፍል ጠቅሎ ያዘ:: ለአርባ ዓመታት ያህል ከአራት ተከፍላ ትገዛ የነበረችው ሮም፤ በአንድ ቆስጠንጢኖስ ሥልጣን ሥር ሆነች:: ቆስጠንጢኖስ የመንግሥቱን ሥልጣን አንድ አድርጎ በያዘ ጊዜ በክርስቲያኖች ላይ ይፈጸም የነበረው ግፍ ተቀነሰ፤ እስረኞች ተፈቱ፤ አብያተ ጣዖታት ተደመሰሱ:: ለቤተ ክርስቲያን ሙሉ የአስተዳደርና ትምህርቷን የማስፋፋት ነጻነት ተሰጣት:: ከ300 የመከራና የስደት ዓመታት በኋላ ቤተ ክርስቲያን በታላቁ ቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት ዕረፍት አገኘች::

### የቆስጠንጢኖስ አስተዋፅዖ ለቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን ከ300 የመከራና የስደት ዘመን በኋላ ዕረፍት ያገኘችው በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት ነው:: ቆስጠንጢኖስ ለቤተ ክርስቲያን ያበረከተው አስተዋፅዖ በርካታ ቢሆንም ዋና ዋናዎቹ:-

1. በ313 ዓ.ም እና በ315 ዓ.ም በወጣው መንግሥታዊ መግለጫ መሠረት ቤተ ክርስቲያን ከግብር ነጻ ናት::
2. ከመንግሥቱ ገቢ ሁሉ ለቤተ ክርስቲያንም የተወሰነ ድርሻ አላት፤ /በዐሥራት፣ በኩራትና ቀዳምያት/
3. ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ የተነሣባት ዕለተ ሰንበት /እሑድ ሰንበት/ በክርስቲያኖች ዘንድ ከትንሣኤ ዕለት ጀምሮ የተከበረች ብትሆንም፤ ከ321 ዓ.ም ጀምሮ ዕለተ እሑድ የክርስቲያኖች የበዓል ቀን እንድ ትሆንና በንጉሡ ነገሥቱም ግዛት ውስጥ ሥራ እንዳይሠራበት ዐወጀ:: /ወደ ገጽ ፳ ዞሯል/




©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

# «ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን ቢ ፈልግ–መልካምን ሥራ ይመኛል»

*/ 1ጢሞ.3÷1/*



ኤጲስ ቆጶስ በመጽሐፈ ዲ. ድስቅልያ እንደ ተነገረው እንደ ጠባቂ ነው:: አስተያየቱና አኗኗሩ በሦስት ወገን ይሁን:: መጀመሪያ ከመመረጡና ከመሾሙ በፊት፣ሁለተኛው የአመራረጡ ሥራ፣ሦስተኛውም ፈጽሞ ከተሾመ በኋላ ያለው ነው:: (ፍ.ነ.ፍ.መ ÷ አንቀጽ 5.ቁ. 80::

ኤጲስ ቆጶስ የቤተ ክርስቲያን የመንጋዋ እረኛ ነው:: በጐቹን በሃይማኖትና በምግባር ለምለም መስክ ላይ ለማሠማራት የሚሾም፤ ከተኩላ መናፍቃን በጐቹን የሚጠብቅ፣ቢሰበሩ ጠግኖ፣ ቢታመሙ ፈውሶ ለድኅነት የሚያበቃ፤ በዚህም የተነሣ ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶሳትን ለመምረጥና ለመሾም ከጾምና ከጸሎት ጋር ብርቱ ጥንቃቄ ታደርጋለች::

*ማንን ትሾማለች?*

1. ያለ ነውርና ያለ በደል ይሁን:: ከሰው ሁሉ በደል የነጻ ይሁን:: (አንቀጽ 5÷84)::
2. ዕድሜው ከ50 ዓመት ያላነሰ ይሁን:: (ቁ.84)
3. ቢቻለውስ ትምህርትን ሁሉና ምክርን የተመላ÷ በቃሉ ነገር ዐዋቂም ይሁን:: (ቁ 84)
4. ሀገረ ስብከቱ ታናሽ ቢሆን በዕድሜው ሽማግሌ ባይገኝ ከወጣቶች መካከል ወይም በጐልምስናው የሽማግሌዎችን ሥራ የሠራው ሰው ከተመሰከረለት ይሾም:: (ቁ.85)
5. ትዕግሥተኛ፣ ሥርዓታዊ፣ የማይቆጣ፣ገንዘብ የማይወድ፣የማይሰክር፣ በዚህ ዓለም ሥራ ነውር የሌለበት:: (ቁ. 87)
6. መነኩሴ የሆነ (ቁ.89)
7. በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ በሕዝብ ምርጫ «ይገባዋል» የተባለለት (ቁ.90)

*ከሹሙት የሚከለከል*

1. ጋኔን ያለበት (ቁ.35)
2. ዝንጉዕ
3. የአካል ጉድለቱ ለአገልግሎት የሚከለክለው (ቁ.96)
4. አማኒ ያይደለ በኋላ የተጠመቀ
5. ክፉ ኑሮ ኖሮ በኋላ የተመለሰ(ቁ.97)
6. በራሱ ፈቃድ አባለ ዘሩን የሰለበ

*<u>ሥርዓተ ሹመት</u>*

1. በሹመቱ ቀን ሰዎች ሁሉ ይገኙ፤
2. ሕዝቡና ካህናቱ «ይደልዎ÷ ይገባዋል» ብለው ይመስክሩለት፤
3. ሥርዓተ ሢመቱ በዕለተ እሑድ ይሁን፤
4. ኤጲስ ቆጶሳቱ ተሰብስበው ይሹሙት (ቁ.3)፤
5. ሃይማኖትን ለማስተማር ሕዝቡን ለመጠበቅ አደራ ይስጡት፤
6. በአንብሮተ እድ ይሹሙት (ቁ.101)
7. ከዚያም ቅዳሴውን ይቀድሱ፤
8. በዚያ ዕለት አስቀድሞ አዲስ የተሾመው ሥጋ ወደሙን ይቀበል፤
9. ሦስት ቀን መንፈሳዊ በዓል ያክብር (ቁ.102)፤

*ከሢመት በኋላ*

1. ለማስተማር ይትጋ
2. ድሆችን የሚጠላ ባለጠጐችን የሚወድ አይሁን
3. በሐሰት አይመስክር
4. ቁጡ አይሁን
5. ሹመትን አይውደድ
6. ሁለት ልብ አይሁን
7. ነገረ ሠሪን የሚሰማ አይሁን
8. ገንዘብ ወዳጅ አይሁን
9. ብልህና አስተዋይ ይሁን::

ኢጲስ ቆጶሳት የእግዚአብሔር ዐይኖች ናቸው:: በነቢዩ ሕዝቅኤል ቃል እንደ ተነገረ (ሕዝ.3÷17–21):: ስለሆነም ምእመናንን ከኃጢአት÷ ከበደል÷ከውድቀት÷ ከጥፋት ለመጠበቅ ይተጋሉ:: ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ:– «የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እና ንተን ጳጳሳት አድርጐ ለሾመባት ለመ ንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ» (የሐዋ.20÷28) እንዳለው መናፍቃን በበዙበት፣በገጠር አብያተ ክርስቲያናት በደኸዩበት ጊዜ የሚሾሙ ኤጲስ ቆጳ ሳት ብዙ ተጋድሎ ይጠብቃቸዋል:: ወጥቶ ወርዶ ማስተማር፣መንጋውን ከተኩላ መለየት፣የቤተ ክርስቲያንን ገቢ ማሳደግ፣የአህጉረ ስብከት ጽ/ ቤቶችን ማደራጀት ከፊታቸው የተዘ ረጋ አገልግሎት ነው::

ከዚህ በፊት የተሾሙት አበው ቤተ ክርስቲያንን ጠብቀው የልማት ሥራዎችን ዘርግተው፣በዳዋ የተዋጡ አብያተ ክርስቲያናትን ፈልገው፣ሕ ዛብን አጥምቀው፣ገዳማትን አጽን ተው፣የካህናት ማሠልጠኛዎችን ዘርግ ተው ለዛሬው ዕድገት እንዳበቁን ሁሉ ዛሬ አዲስ የሚሾሙት አበውም ለ( ለጠ ዕድገት ያበቁናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔ*

*ስንቄን ይዣለኹ*

በእንተ ስለማርያም ኮሮጆዬን ይዤ
ልለምን አይደለም ልማር ልወቅ ብዬ
ጌታዬን ማመስገን ሰዓታት ዜማውን
ውዳሴ ቅዳሴ ቅኔ ማሕሌቱን
ምን እበላ ብዬ መቼ አስባለሁኝ፤
በእንተ ማርያም ስንቄን ይዣለሁኝ
ለአባ ሕርያቆስ ጸጋው ቅዳሴሽ
የአባ ጊዮርጊስ ሰዓታት ዜማሽ
ደ'ሞ ለአባ ኤፍሬም ምግቡ ውዳሴሽ
ይህንን ስሰማ መሰጠኝ ፍቅርሽ
ከመምህር መምህር ለመማር ምሥጢ
በቅሎ ፈረስ አልል አልመኝ ባቡር
ለምለም ሣር ፍራሼ ድንጋይ ነው ትራ
አንቺን ሳመሰግን ትረካለች ነፍሴ
ካ'ንዱ ሀገር ሌላ ሀገር መምህር ፍለጋ
ልማር ልመራመር ድጓ ጾመ ድጓ::

*ወ/ሮ ሙሉ ብርሃን ም*

*አ.*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# የበጎ ፈቃድ አገልግሎት /ምንነቱ፣ ምንጩ፣ መልኮቹ፣ አፈጻጸሙ/

/አበባው ምናዬ/

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሚለው ሐሳብ በሃይማኖትና በተለያዩ የማኅበረሰብ ሳይንስ ዘርፎች ማለትም በሥነ ማኅበረሰብ (Sociololgy)፣ የማኅበራዊ ሥነ ልቡና(Social psychology) እና ሌሎችም ዘርፎች ትኩረት ተሰጥቶት ይገኛል:: ስለዚህም በዚህ የመነሻ ጽሑፍ ከሃይማኖታዊና ከኅብረተሰባዊ ሳይንሳዊ ግንዛቤው አንጻር የሚታይ ይሆናል::

ሀ/የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ምንነት:- የበጎ ፈቃድ አገልግሎት÷ በጎ፣ መልካም፣ ጥሩ የሆነ አገልግሎትን /ገንዘብ፣ ሐሳብ፣ ዕውቀት፣ ንብረት ወዘተ/ በነጻ፣ በፈቃድ፣ በልግሥ፣ በርኅራኄ መስጠትን ወይም ማበርከትን ለመወከል ሰዎች የሚጠቀሙት ጽንሰ ሐሳብ ነው:: በእንግሊዘኛውም:- «Voluntary Service, Charity, Benevolence, Philantropy, Generosity, Kindness» የመሳሰሉት ቃላት ይህንኑ ሐሳብ በመተካት ይገባሉ::

እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ድርጊቱ የፈቃድ ወይም ነጻ መሆኑ እንጂ የሚደረገው ድጋፍ መጠን አይደለም:: እጅግ ውስን ከሆነ የሳንቲም፣ ጉልበት፣ ሐሳብ፣ ንብረት ድጋፍ በእጅጉ የተቀናጀና የተደራጀ የገንዘብ፣ የሞያ፣ የጉልበት እና ሌሎች ድጋፎች ሊደርስ ይችላል::

ብዙ ጊዜ ሰዎች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሲባል የሚታያቸው አንድ ግለሰብ ወይም ማኅበር ለሌሎች የሚያደርገው የገንዘብ ወይም የጉልበት ነጻ ድጋፍ ብቻ ነው:: ነገር ግን በብዙ የኅብረተሰብ ሳይንስ ጸሐፊዎች ትኩረት እየተሰጠው የሚገኘው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለሚሰጠው ግለሰብ፣ ማኅበር ወይም አካል ራሱን እንዲችል፣ ዐቅሙ እንዲጐለብት የሚደረጉ ነጻ ድጋፎች ትኩረትን በመሳብ ላይ ይገኛሉ::

ነጻ በሚለው ቃል አንዳንድ የኅብረተሰብ ሥነ ልቡና ጸሐፊዎች አይስማሙም:: ሰዎች በፈቃደኝነት ያለ ምንም ክፍያ የሚያደርጉት ድጋፍ ወይም እገዛ የሃይማኖት ሰዎች ከሆኑ መንፈሳዊ ትርፍ ለማግኘት፣ ከሃይማኖት ውጭ የሆኑት ደግሞ ድጋፍ ከሚደረግለት ክፍል ምስጋና ለማግኘት ወይም ደግሞ በሁለቱም በኩል ድጋፍ የተደረገለት ክፍል ሲሻሻል በማየት ለሚገኝ እርካታ ሊሆን ይችላል:: ሌሎች የኅብረተሰብ ሥነ ልቡና ጸሐፊዎች ደግሞ ሰዎች የሌሎች ችግር ስለሚሰማቸው ብቻ ለራሳቸው ምንም ጥቅም ሳያስቡ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው::

ቀደም ባሉት ጊዜያት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በአብዛኛው በግለሰቦች የሚፈጸም ነበር:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በጣም በተቀናጀና ሞያዊ በሆነ መልኩ እየተቀየረ መጥቷል::

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በብዙ ሀገሮች የተለያዩ ሰብአዊ ፍላጐቶችን ማሟያ እና የማኅበራዊ ቀውሶች መፍቻ ዓይነተኛ መንገድ በመሆን ላይ ይገኛል::

በተለያዩ ሀገሮች በተለይም በምጣኔ ሀብት ዕድገታቸው ወደ ኋላ በቀሩ ሀገሮች የብዙ ዜጐች ማኅበራዊ ፍላጎቶች በመንግሥት ወይም መንግሥታዊ ባልሆኑ የንግድ ድርጅቶች ብቻ የሚፈታ አይሆንም:: በጣም ብዙ ማኅበራዊ ችግሮች አሉ፤ ከቀያቸው በተለያዩ ምክንያቶች የተፈናቀሉ፣ አሳዳጊ አልባ ሕፃናት፣ ጧሪ የሌላቸው አረጋውያን፣ በተለያየ ምክንያት አካል ጉዳተኛ የሆኑ ዜጐች፣ ምንም ዓይነት የትምህርት፣ የጤና ወዘተ አገልግሎት ማግኘት ያልቻሉ ዜጐች ከላይ የጠቀስናቸውና ሌሎችም የኅብረተሰብ ክፍሎች የተለያዩ መሠረታዊ ፍላጐቶች አሏቸው:: በቂ ምግብ፣ መጠለያ፣ ልብስ፣ የጤና አገልግሎት፣ ጤናማ ስሜት፣ የአእምሮና መንፈስ ማጐልበቻ የትምህርት አገልግሎት ይፈልጋሉ:: ይህ ሁሉ በመደበኛው መንግሥታዊ አገልግሎትና ፍላጎቱ በማያስፈልጋቸው ሰዎች ሊሟላ የሚችል አይደለም:: ስለዚህም የበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ እነዚህን ችግሮች ከማቃለል አንጻር ዓይነተኛ ሚና ይኖረዋል::

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሥራን መጠን አይወስነውም:: ከትንሿ የዐሥር ሳንቲም ድጋፍ እስከ ብዙ ሚሊዮን ርዳታ÷ ከትንሽ የሐሳብ ድጋፍ እስከ ተጠናከረ፣ የተቀናጀና የተደራጀ ሥልጠና ሊደርስ ይችላል::

ለ/ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አመጣጥ /ምንጭ/:- የበጎ ፈቃድ ሥራ ምንጭ እግዚአብሔር ነው:: ያለ ምንም ክፍያ፣ እገዛ ወይም ርዳታ በፈቃዱ፣ በነጻ ፍጥረታትን ሁሉ መልካም መሆናቸውን እያረጋገጠ ከመፍጠር እስከ የዕለት ከዕለት ፍላጎታቸውን በነጻ መስጠት:: የዕውቀት፣ የማስተዋል፣ የጥበብ፣ የጉልበት፣ የሀብት የሁሉ ባለቤት እግዚአብሔር ሰዎች የሚፈልጉትን በሙሉ (ልጅ ለሚፈልጉ ልጅ፣ ማስተዋል ለፈለጉ ማስተዋልን፣ ሀብትን፣ ንብረትን ወዘተ...) እንደ ፍላጎታቸው ይሰጣቸዋል:: አምላካቸውን የተከተሉ ሰዎችም ከአምላካቸው ተምረው ይህንኑ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አበርክተዋል:: አበ ብዙኃን አብርሃም ያለምንም ክፍያ መንገደኞችን በነጻ ማብላቱና ማጠጣቱ አንድ ዋና ማስረጃ ነው::

የክርስትና መመሪያ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስም ሰው የተቸገረ ወገኑን በእንግድነት እየተቀበለ /ገንዘብ፣ ዕውቀት፣ ጉልበት ያለው ለሌለው/ እንዲረዳ እንዲያግዝ ይጠይቃል÷ ያዛልም:: በሐዲስ ኪዳን በመልካም ሥራው የሚታወሰው ሳምራዊም ተጐድቶ፣ ቆስሎ ያየውን ሌዋዊ ያለ ማንም ትእዛዝ ወይም አስገዳጅነት በነጻ ፈቃዱ አንሥቶ ቁስሉን በዘይት ቀብቶ ገንዘብ ለሚረዱት ሌሎች ሰዎች ሰጥቶ÷ ተመልሶ እንደሚረዳው ቃል ገብቶ መሄዱ ሊታወስ የሚገባው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ነው:: እንዲያው ምሳሌ የሚሆነንን አነሣን እንጅ በጠቅላላው በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ አገልግሎቶች በበጎ ፈቃድ የተከናወኑ ናቸው:: አሁንም በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ካህናት፣ ዲያቆናት፣ ምእመናን ብዙ ነገሮችን ያለምንም ክፍያ በበጎ ፈቃዳቸው ይሠራሉ::

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ምንጩ ሃይማኖት ለመሆኑ የሥነ ማኅበረሰብና የማኅበራዊ ደኅንነት ምሁራንም በጣም ይስማሙበታል:: ነገር ግን ምንጩ ሃይማኖታዊ ቢሆንም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሃይማኖታዊ ባልሆኑ ተቋማት የተለያዩ ማኅበራዊ ችግሮችን ለመፍታትና ምጣኔ ሀብታዊ ልማትን ለማጐልበት እየተስፋፋ እንደመጣ ጸሐፊዎች ያስረዳሉ:: በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ሀገሮች እየዞሩ በነጻ ፈቃድ የሚያገለግሉ የሕክምና ቡድኖች፣ የትምህርት አገልግሎት ሰጪዎች፣ የምሕንድስና ባለሞያዎችና ሌሎችም የነጻ ፈቃድ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ::

በሀገራችን የተለያዩ የሞያና ወጣት ማኅበራት ነጻ የሞያና የጉልበት አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው:: የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ባላቸው የክረምት ዕረፍት ጊዜ በየሞያቸው:- በማስተማር፣ በአካባቢ ጥበቃ (ችግኝ በመትከል)፣ በመንፈሳዊ አገልግሎትና በሌሎችም ዘርፎች የበኩላቸውን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በማበርከት ላይ ይገኛሉ::

ሐ/ መንፈሳዊነትና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት:- አንዳንድ ሰዎች የበጎ ፈቃድ ሥራዎች በሃይማኖት ተቋማት ብቻ እንደሚካሄዱ ያስባሉ:: ስለዚህም የበጎ ፈቃድ አገልገሎት መንፈሳዊነት ያላቸውን ልዩነትና አን



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ድነት ማየት ተገቢ ይሆናል።

1. አንድነታቸው:- መንፈሳዊነት በጣም ብዙ ነገሮችን የሚያጠቃልል ነው። የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ማለትም ከፍቅረ ንዋይ የራቀ አገልግሎት የመንፈሳዊነት አንዱ መገለጫ ነው። ስለዚህም ትክክለኛ መንፈሳዊ የሆነ ሰው ለሰዎች ያለምንም ምድራዊ ክፍያ በነጻ ፈቃድ ይረዳል፣ ያግዛል፣ ምክንያቱም የተሻለ፣ የበለጠ፣ ያማረ ክፍያ በሰማያዊ ቤት ስለሚያገኝ። ከላይ እንደ ተገለጸው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ምንጩ መንፈሳዊ በመሆኑ:- በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር፣ በሰንበት ት/ቤቶች፣ በማኅበራትና በግለሰቦች በተናጠልም ይሁን በተቀናጀ መልኩ ይፈጸማል። በገጠር ብዙ አብያተ ክርስቲያናት በምእመናን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሚሠሩ ናቸው። ከጠቀሜታ አንጻርም የሚደረግ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከመንፈሳዊ ፋይዳው ባሻገር የኅሊና ርካታን የሚያስገኝ ሲሆን የመልካም ዜግነት መገለጫም ነው።

2. ልዩነታቸው:- መንፈሳዊ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሚፈጸመው ሰማያዊ መንግሥትን ለመውረስ ነው። ነገር ግን አንዳንድ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች ምንም ሃይማኖታዊ ዝንባሌ በሌላቸው ሰዎች ይፈጸማሉ። ምናልባትም እንዲህ ዓይነት አገልግሎቶች ርካታ ለማግኘት፣ ተወዳጅ ለመሆንና ተቀባይነትን ለማግኘት ሊሆኑ ይችላሉ። ጠቅለል ባለ መልኩ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሃይማኖታዊ /መንፈሳዊ/ መነሻንም ይሁን ዓለማዊ መነሻን መሠረት ቢያደርግ የተለያዩ ማኅበራዊ ችግሮችን በመፍታት ዙሪያ የሚኖረው አስተዋፅዖ የሚናቅ አይደለም።

መ. የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መልኮች:- የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በግለሰቦች ወይም በማኅበራት ሊፈጸም ይችላል።

1. ግለሰባዊ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት:- ግለሰቦች ምክንያታቸው መንፈሳዊም ይሁን ዓለማዊ የተለያዩ የበጎ ፈቃድ ሥራዎችን ያከናወናሉ። ሙሉ ጊዜያቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ገንዘባቸውን ለበጎ ፈቃድ አገልግሎት በማዋል የሚታወቁ አንቱ የሚባሉ ግለሰቦች አሉ። በከተማችን አዲስ አበባ እንደነ ጋሽ አበራ ሞላ ዓይነት ግለሰቦች በምሳሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ። እንዲያው በቀላሉ እዚህ የምናየውን አነሣን እንጂ በመንፈሳዊው በኩል ለዘመናት ሙሉ ሕይወታቸውን ቋጥኝ ፈልፍለው ቤተ ክርስቲያን በማነጽ÷ በቤተ ክርስቲያን የተለያዩ ሞያዊ አገልግሎቶችን የሚያበረክቱ እጅግ በጣም ብዙዎች ናቸው።

2. ማኅበረሰባዊ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት:- በግለሰብ ደረጃ የሚደረጉ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች የማይናቅ አስተዋፅዖ ያላቸውና የሚበረታቱ ተግባራት ቢሆኑም በማኅበር ደረጃ የሚሠሩት የተሻለ ውጤታማ በመሆናቸው እየተስፋፉና እየተጠናከሩ በመምጣት ላይ ናቸው። በመሆኑም በርከት ያሉ የበጎ ፈቃድ ማኅበራት ተቋቁመዋል፤ በመቋቋም ላይ ናቸው። የሕፃናት ወዳጅ ማኅበራት፣ የወጣት ማኅበራት፣ የፀረ - ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ማኅበራት፣ የሞያ ማኅበራት... ወዘተ እነዚህ ማኅበራት ያለምንም ክፍያ የማስተማር፣ በሞያ የማሠልጠን፣ በሽተኞችን የመከባከብ፣ የልማት ሥራዎችንና ሌሎች አገልግሎቶችን በተቀናጀ መልኩ በማከናወን ላይ ይገኛሉ።

ሠ. የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መቼ፣ የት እና ለማን?:- የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እጅግ ብዙ ችግሮችን በመፍታት ረገድ ድርሻ ቢኖረውም:- «መቼ፣ የትና ለማን ሊበረከት፣ ሊሰጥ ይገባል» የሚለውን ግን ብዙ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶችን፣ ማኅበራትንና ግለሰቦችን የሚፈትን ጥያቄ ሆኗል።

ለምሳሌ በአንዳንድ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች አካባቢ በድኾች፣ በአካል ጉዳተኞች፣ ወላጆቻቸውን ባጡ ሕፃናት፣ በአረጋውያን፣ በስደተኞች፣ በጎዳና ተዳዳሪዎች፣ በዝሙት አዳሪዎች... ወዘተ ስም ከሚደረገው ድጋፍ ውስጥ አብዛኛው ድርጅት ሓላፊዎች፣ በጥናታዊ ጽሑፍ አቅራቢዎች እጅ የሚገባው ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል። ስለዚህም ይህ ለተቀደሰ ሥራ እንዲውል የታሰበ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሳልታሰበለት ዓላማ ይውላል። ስለዚህ የበጎ አድራጎት ሥራ በቀጥታ ለተጠቃሚው ግለሰብ፣ ማኅበር ወይም አካል የሚደርስበት ሁኔታ መታየት አለበት። ከዚህም በተጨማሪ ለማን የሚለው ጥያቄ በሚገባ መታየት አለበት። አንዳንድ ጊዜ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ስም አቅሙ ያላቸውን መደገፍ ጥገኝነትን ሲያስከትል ይችላል። ስለዚህ ሰዎች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሲያበረክቱ ቅድሚያ ለማን፣ ለየትኛው ሥራ፣ የትኛው በጣም አስፈላጊ ነው የሚለውን መፈተሽ ይገባቸዋል።

የጊዜ ጉዳይን በተመለከተም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በዚህ ቀን በዚህ ሰዓት ተብሎ የሚወሰኑ ባይሆንም በተገቢው ጊዜ መሆን እንዳለበት ግን አያጠያይቅም። ልንሰጠው የምንፈልገው የበጐ ፈቃድ አገልግሎት የተሻለ ውጤት በሚያስገኝበት ሁኔታ ቢሆን ይመረጣል። ለምሳሌ በገንዘብ የምንደግፍ ከሆነ ሰዎች መንገድ ላይ መጥተው በልመና ሞያ ከመሠማራታቸው በፊት ቤታቸው እያሉ የራሳቸውን ሥራ የሚሠሩበትን መንገድ ማመቻቸትን፣ ሰዎች ጥገኛ እንዳይሆኑ ሊረዳ የሚያስችል ሥልጠና እንዲያገኙ ማገዝ የተሻለና ውጤታማ ይሆናል። ከዚህም ባሻገር የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የሚሰጠው ሰው ትርጉም ያለው በቂ አገልግሎት ሊያሰጠው በሚችለው ጊዜ ሊያደርገው ይገባል። አለበለዚያ ተያይዞ መውደቅን ሊያመጣ ይችላል።

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት የት የሚለውን ጥያቄ በተመለከተም ሰዎች የበጎ ፈቃድ ሥራን በየትኛውም ቦታ ሊያደርጉት ይችላሉ - በቤተ ክርስቲያን ቅጽር በአካባቢያቸው፣ በጉረቤታቸው፣ በሀገራቸው፣ በሌሎች በጎ ፈቃድ አገልግሎት መስጫ ተቋማት /በሆስፒታሎች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በሕፃናት ማሳደጊያዎች... ወዘተ/። በብዙ ቦታዎች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መስጠት የሚቻል ቢሆንም ከሥነ ማኅበረሰብ ምሁራን - አንጻር ግን ሰዎችን ወደ ተሻለ ሁኔታ በፍጥነትና በበቂ ሁኔታ ሊያመጣ በሚችል ቦታ ላይ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መስጠት የተሻለ ወይም የተመረጠ ነው። ለዚህም:- ለምሳሌ ችግርን በዘላቂነት ለመፍታት የክህሎት ሥልጠና ለሚሰጡ ማኅበራት ወይም ድርጅቶች፣ የሥራ ዕድል ለሚፈጥሩ ድርጅቶችና ሌሎችም የተሻለ ሥራ ይሠራባቸዋል ለምንላቸው ማኅበራት ወይም ተቋማት የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን በየመልኩ መስጠት ይቻላል።

4. የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንዲጐለብት ምን መደረግ አለበት?

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ካለው መንፈሳዊ ዋጋ በተጨማሪ ማኅበራዊ ቀውስን በመፍታት በኩል ቀደም ብለን እንደ ጠቀስነው የሚኖረው አስተዋፅዖ የተገነዘቡትና በተለያዩ ቦታዎች በተደጋጋሚ የሚቀርብ ነው። ስለሆነም መጎልበት ይኖርበታል። እንዲጎለብትም የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ማለትም ግለሰቦች፣ ቤተሰብ፣ ማኅበራት፣ መንግሥት፣ ቤተ ክርስቲያን፣ በጠቅላላው ማኅበረሰቡ የጐላ ድርሻ ሊያበረክቱ ይገባቸዋል።

1. በግለሰብ ደረጃ:- ብዙ ነገሮች በመሠረታዊነት የሚጀምሩት ከግለሰብ ነው። ጠንካራ ማኅበራት በአንዴ የሚፈጠሩ አይደለም። ይልቁንም የጠንካራ ግለሰቦች ስብስብ ናቸው። ስለዚህ እያንዳንዱ ምእመን ወይም ዜጋ የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን መንፈሳዊውም ይሁን ማኅበራዊ ፋይዳ ማጤን ይጠበቅበታል። የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለዚህ ወይም ለዚያ የሚባል ሳይሆን ሁሉም የአቅሙን ሊያደርገው የሚችለው ነው። የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለመስጠት ባለሞያ ወይም ሀብታም መሆን የግድ አይደለም። እያንዳንዱ እንደየ ዐቅሙና እንደ የችሎታው ሊያበረክተው የሚገባ እንጅ። አንዱ በገንዘቡ፣ አንዱ በዕውቀቱ፣ ሌላው በጉልበት ሊያከናውነው የሚችለው ነው። ለምሳሌ:- ቤተ ክርስቲያን የራሷ የሰው፣ የንብረት፣ የቦታ፣ የቱሪዝም፣ የቅርስ ወዘተ ሀብት አላት። ስለዚህ ምእመናን ይህን ሀብቷን በተሻለ መልኩ እንድትጠቀምበት የጉልበት፣ የሞያ፣ የዕውቀት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሊያበረክቱ ይችላሉ።

አንዳንድ ሰዎች የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መፈጸም ለሀብታም፤ ወይም ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ የተሰጠ አድርገው ይወስዱታል። ነገር ግን



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

እያንዳንዱ ግለሰብ በሚችለው የተለያዩ የበጎ ፈቃድ ሥራዎችን ማከናወን ይችላል:: ዋናው በምን መንገድ ሀገርን፣ ወገንን ማገዝ እችላለሁ ብሎ ማሰቡ ÷ መነሣሣቱ ነው::

ለምሳሌ:- ገና ትምህርታቸውን ያልጨረሱ ወይም ያልተመረቁ የዩኒቨርስቲና የኮሌጅ ተማሪዎች በተለያዩ መንገዶች የበጎ ፈቃድ ሥራ መሥራት ይችላሉ::

- የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን በክረምት የዕረፍት ጊዜያቸው አሰባስበው በማስተማር የተሻሉ ተወዳዳሪዎች በማድረግ፤
- በአካባቢ ጥበቃ (በችግኝ ተከላ፣ በአካባቢ ጽዳት)፤
- በፀረ - ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ እንቅስቃሴዎች በመሳተፍ (በማስተማር እና ለሕሙማን ድጋፍ በማድረግ)፤
- በግል ሞያቸው:- በግብርና፣ በምሕንድስና፣ በሕክምና ወዘተ ባላቸው ዕውቀት በተቋማት ማገልገል፤

2. በቤተሰብ:- የብዙ ነገሮች መሠረት ቤተሰብ መሆኑን የሥነ ልቡናና የሥነ ማኅበረሰብ ምሁራን ያምኑበታል:: ቤተሰብ ልጆቹን በቅን አስተሳሰብና በበጎ ኅሊና (Positive thin king) ኮትኩቶና ቀርፆ የማሳደግ ሓላፊነት አለበት:: የቅን አስተሳሰብና የበጎ ኅሊና መገለጫ ከሆኑት ነገሮች አንዱ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ነው:: ቤተሰብ ማለትም ወላጆች ለልጆች በጎ ነገርን በማድረግ የበጎ ድርጊት አርአያ መሆን ይጠበቅባቸዋል:: ይህም ለበጎ ፈቃድ አገልግሎት ማደግ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ይኖረዋል::

3. በኅብረተሰብ ደረጃ:- መልካም ማኅበረሰብ ሊፈጠርና ሊዳብር የሚችለው ሰዎች በበጎ ፈቃድ መተጋገዝና መረዳዳት ሲችሉ ነው:: ከዚህ አንጻር በአንድ ሀገር ወይም ማኅበረሰብ ያሉ ተቋማት ማለትም ትምህርት ቤቶች፣ አብያተ ክርስ ቲያናት፣ የመንግሥት አስተዳደር መዋቅሮች፣ መገናኛ ብዙኃን እና ሌሎችም የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን በማስተማር፣ በማስተባበር፣ በማቀናጀት፣ በማበረታታት በመፈጸም የበጎ አድራጎት ሥራ እንዲጎለብት ጉልህ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ::

ሰ. ቤተ ክርስቲያንና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት

በመነሻችን ላይ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ምንጭ ሃይማኖት እንደሆነ ተጠቅሶ ነበር:: ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የእምነቷ አንድ ዋና አካል የሆነውን በበጎ ፈቃድ ብድራትን ባለመሻት ለተቸገሩ፣ ለተራቡ፣ ለተጠሙ፣ ለታረዙ፣ ለተጨነቁ በነጻ መረዳትን ከዚህ ቀደም ታደርገው እንደነበረው ልትቀጥልበት ይገባል:: አርአያ መኾንም ይጠበቅበታል:: ቤተ ክርስቲያን በረጅም ታሪኳ ለበጎ ፈቃድ አገልግሎት አርአያ የሚሆኑ ቅዱሳንና አመች የሆኑ መዋቅሮች አሏት:: አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህልም:-

1ኛ/ ስለ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ለማስተማርም ይሁን አስተባብሮ በቅንጅት ለማሠራት ከየትኛውም ተቋም በበለጠ ምእመናኗን በቅርብ የማግኘት አጋጣሚ አላት::

2ኛ/ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ምሳሌ የሚሆኑ ዝክሮች፣ ሰንበቴ፣ ማኅበሮች ወዘተ በስፋት ይገኛሉ:: እነዚህ የተቀደሱና ጠንካራ ትውፊቶች የተሻለ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ለመስጠት አመች ናቸው:: በገጠሩ አካባቢ አንድ የማኅበር አባል ጉልበቱ ቢደክም፣ የማኅበሩ አባላት ተጋግዘው ያርሱለታል÷ በቀጣይ ሥራዎችም ይረዱታል:: ይህም ወንፈልን መሠረት ያደረገ ሳይሆን በበጎ ፈቃድ የሚደረግ ነው:: ዛሬ የተለያዩ መንግሥታዊ ተቋማት እንኳ ይህንኑ የቤተ ክርስቲያን ሥሪት እንደ ትልቅና ልዩ አጋጣሚ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ:: የዚህ ሀብት ባለቤት የሆነችው ቤተ ክርስተያን ደግሞ የበለጠ ልትጠቀምበት ይገባል::

3ኛ/ በመቋቋምና በመጠናከር ላይ ያሉ በርካታ ሰንበት ት/ቤቶች በአገልጋይነትና በአባልነት የያዙት ግዙፍና ትኩስ ወጣት ኃይል በቤተ ክርስቲያንም ይሁን ከዚያ ውጭ በጣም ብዙ ሥራን በበጎ ፈቃድ ለመሥራት የሚያስችል ነው:: በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከሚገኙ ግቢ ጉባኤያት በየጊዜው እየተመረቁ የሚወጡቱም የተሻለ ሞያዊ ዕውቀት፣ የተሻለ የወጣት አእምሮ የያዘ ዜጋን ያሰባሰበው ማኅበረ ቅዱሳንም ለበጎ ፈቃድ አገልግሎት መዳበርና መስፋፋት ሚናውን አጠናክሮ መጠቀል ይኖርበታል::

4ኛ/ የካህናትና የምእመናን ግንኙነትም ሰዎችን በቀላሉ ለማግኘት፣ ለማስተማር፣ ለማስተባበር ከሚያስችሉ ነገሮች አንዱ ነው::

5ኛ/ ስለ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ለማስተማር የሚያስችሉ ብቁ መጻሕፍት፣ የቅዱሳን ታሪክ፣ ከፍተኛ የሆነ የበጎ አድራጎትና የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ምሳሌዎች ናቸው::

ከላይ የጠቀስናቸው ሁኔታዎች የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን በቀጥታ ለማከናወን፣ ለማስተማርና ለማስተባበር ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራሉ:: በጠቅላላው የጥበብና የበጎ ነገር ሁሉ መገናኛ የሆነች የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በበጎ አድራጎት ሥራና በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ምሳሌ መሆን ይጠበቅባታል:: ለዚህም ስኬታማነት የተቀ ደሱ ክርስቲያናዊ ትውፊቶቿን ከወቅቱ ሁኔታ ጋር አገናዝባ ምቹ ከባቢን በመፍጠር ልጆቿን ማስተባበርና ማነሣሣት ይኖርባታል:: አምላካችን እግዚአብሔር ለበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሁሉ የምንተጋ ያድርገን:: አሜን::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# «ኮከብ እማእከለ...

*/ከገጽ ፳፫ የዞረ/*

/ከገጽ ፳፫ የዞረ/

እርሳቸውም:– «እኔ ደመወዝ እንደማልሰጣችሁ ዐውቃለሁ፤ ግን ለልጅ ልጆቻችሁ ደመወዝ የሚኾን ሥራ ነው እየሠራ'ኹ ያለ'ኹት፤ ይህን በማለቴ እንደምትጠሉኝ እረዳለሁ፤ ነገር ግን ከጊዜ በኋላ ትወዱኛላችሁ» ይሉ ነበር:: ...ወደ ገጠር ወጥተው÷ በግና ፍየል ለምነው÷እዚህ አምጥተው እየሸጡና ወደ ገንዘብ እየለወጡ፣አንድ ሰው ክህነት ሊቀበል ሲመጣ ቢያንስ ለአምስት ወይም ለዐሥር ቀን ሥራ እያሠሩ ነበር የሚሰጡት፤ ዝም ብሎ ክህነት መቀበል የለም:: በአክሱም የአውራጃዋ አስተዳዳሪ ሳሉ ክህነት ሊቀበል ወደ እርሳቸው የሄደ ወደ ሑመራ ሄዶ ለ10 ቀን የሰሊጥ ምርት ላይ ለቤተ ክርስቲያን ይሠራል:: የብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ትልቁ መርሓቸው:– «ሥራ፣ጋብቻ፣ቁርባን» የሚል ነበር:: ክህነት ሊቀበል ከየአውራጃው የሚመጣውን ሁሉ «በል÷ ወደ ከሣቴ ብርሃን ሂድና ለተወሰነ ቀን ድንጋይ በማመላለስ በረከት ተቀበል» ይሉታል:: ታዲያ አንዳንዶች «እኛ ከዚያ ድረስ መጥተን÷ እንዴት እንዲህ ሥራ እንፈታለን::» እያሉ ያማርሯቸው ነበር::

ብፁዕነታቸው በብርቱ ድካም ከመንግሥት የተረከቡት 150000ሜትር ካሬ ቦታ «ያንሰኛል» የሚል ክርክር ነበራቸው:: ራእያቸውን በጥሞና ስታስተውሉት ለሰሜን ኢትዮጵያ ትልቅ የትምህርት ማዕከል የኮነ አንድ ሁለገብ *«የቤተ ክርስቲያን ተቋማት ደሴት»* ለመፍጠር ነበር:: በትንሹ እስከ 500.000 ሜትር ካሬ ቦታ ለማግኘት ይሹ ነበር:: የሚመለከታቸው የበላይ አካላት ትምህርትን ለማስፋፋት የነበረው ግንዛቤና ትብብር አጥጋቢ አልነበረም:: እንዲያውም ግርማዊ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ:– «እኛ የማናውቅ ይህን የሚያህል ሕንፃ እንዴት ሊሠራ ቻለ?» ማለታቸው ይነገራል:: በትምህርት ቤቱ የሕንጻ ምረቃ ዕለት በሥፍራው የነበሩ ሰዎች እንደ ነገሩን:– ጃንሆይ ሕንጻውን መርቀው ወደ ግብዣው ቦታ ሲሄዱ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ «አልገባም» አሉ:: ምክንያታቸው ሲጠየቁ:– እኔ ንጉሥ ባል'ኾን መነኩሴ ነኝ፤ ምንም ነገር አደርግል'ኸለሁ ሳይሉኝ በመ'ኼዳቸው ቅር ብሎኛል:: ሁላችንም ለቤተ ክርስቲያን ልጆች ነን» ማለታችን ይነገራል::

*ይቆየን*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



ይህ ዓምድ በሥርጭቱ ፍጥነትና በጥቃቱ ስፋት አሳሳቢ ደረጃ የደረሰውን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ ማኅበረ ቅዱሳን ከአክሽን ኤይድ ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር የጀመረው ሰፊ ሥራ አካል ሆኖ ከዚህ እትም ጀምሮ የተከፈተ ነው:: ማኅበራችን ይህንን ሥራ ሲጀምር ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ባገኘው መልካም ፈቃድና መመሪያ መሠረት ሲሆን፣ አጠቃላይ የሥራ ሂደቱም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መምሪያ ክትትል እንዲደረግበት ሆኖ ነው::

# የጠባይ ለውጥ እንዴት?

ጸጋዬ ጥላሁን

/ካለፈው የቀጠለ/

3. ኤች. አይ. ቪ/ኤድስ ላይ በተናጠል ማተኮር

ሲተገበሩ የነበሩና በመተግበር ላይ ያሉ አብዛኛዎቹ እንቅስቃሴዎች የሚያተኩሩት በኤች. አይ. ቪ/ኤድስ ምንነት፣ በመተላለፊያ መንገዶች፣ በሽታው በሚያመጣው ችግር እና ተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ነው:: በርግጥ እነዚህ ነገሮች አስፈላጊና ሁሉም ሰው ሊያውቃቸው የሚገቡ ናቸው:: ሆኖም ግን የሚፈለገውን የጠባይ ለውጥ ለ ማምጣት የማይፈለገው ጠባይ /Undesired behaviour/ እና ከሚፈለገው ጠባይ /Desired behaviour/ ጋር የሚያገናኘውን መሠረታዊ የሆኑ አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን፣ የጥሩ ጠባይ መገለጫዎችን፣ ወደ ጥሩ ሥነ ምግባር የሚወስዱ እሴቶቻችንንና ማንነታችንን ለመፈተሽና ለመመርመር የሚያስችሉ ነጥቦችን በብቃት መዳሰስ ያስፈልጋል:: አስፈላጊውን ለውጥ ለ ማምጣት እንቅፋት የሆኑትን ምክንያቶች ማጤንና ማወቅ ተገቢ ነው:: ስለሆነም ሰው መንፈሳዊውም ሆነ ሥጋዊው ሕይወቱ በጠንከረ መሠረት ላይ የተገነባ፣ ራሱንና አገሩን ጠቃሚ፣ ራእይ ያለው ዜጋ እንዲሆን ማስቻል ዘላቂና አስተማማኝ በሆነ መልኩ የታሰበውን የጠባይ ለውጥ ለማምጣት ያስችላል::

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች በመቅረፍ የኤች. አይ. ቪ/ኤድስ ሥርጭትን ለመግታት ብሎም ለማጥፋት የሚሠሩ፣ መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሥራዎችን መሥራታቸው ብቻ ሳይሆን ያመጡት ውጤት ስለሆነ መታየት ያለበት ይህን ጉዳይ «የጠባይ ለውጥ ለምን አልመጣም?» የሚለውን ነገር ልናጤንና ስልታችንን ልንፈትሽ ይገባል:: ዕውቀት የጠባይ ለውጥ እስካልመጣ ድረስ ምንም አይፈይድም:: ሰው የሚማረውን /ዕውቀቱን/ በሥራ ላይ ካልተረጎመው «የተማረ /የተግባር/ ማይም» ይሉታል:: ምንም ማንበብና መጻፍ የማይችል ነው:: ስለዚህ ሰው ስለ ኤች. አይ. ቪ ኤድስ ያውቃል ይባላል:: ዐውቆ ግን ዕውቀቱን ተግባራዊ ካላደረገው ችግር አለ ማለት ነው፤ ይም አልተማረም ማለት ነው:: መማር ማለት እኮ የጠባይ ለውጥ ማምጣት ማለት ነው:: (Learning is any relatively permanent change of behavior as a result of experience and learning.) ይሉታል:: በመሆኑም ሰው የሚፈልገውን የጠባይ ለውጥ እንዲያመጣ ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች በመቅረፍ ሌሎችን መንገዶች በመጠቀም መሥራት ይኖርብናል:: ከቀደምት ጀምሮ በዚህ ዙሪያ ሰዎች የጠባይ ለውጥ እንዲያመጡ ለማድረግ ጉልህ ድርሻ ያለው የምክክር አገልግሎት /Counseling service/ ለሰዎች መስጠት ነው::

## የምክክር አገልግሎት /Counseling service/ የጠባይ ለውጥ ለማምጣት

የሰው ልጅ በዚህ ዓለም በሚኖርበት ጊዜ ብዙ የግልና ማኅበራዊ ችግሮች ይገጥሙታል:: ዓይነቱና መጠኑ ይለያይ እንጂ ችግር የማይገጥመው ሰው የለም:: በእያንዳንዱ የዕድገት ዘመናችን /Developmental stages/ በተፈጥሮአዊና አካባቢያዊ ምክንያቶች /Natural and environmental factors/ የተለያዩ ችግሮች ይገጥሙናል:: አንዳንዱ ችግር ለመሠረታዊ ፍላጎቶች የሚያስፈልጉንን ነገሮች /ምግብ፣ መጠለያና ልብስ/ ማጣት ነው:: አንዳንዱ ደግሞ ስለ ራሱ ደኅንነትና ዋስትና ማጣት ነው:: ሌሎች ደግሞ ተገቢ ማኅበራዊ ግንኙነት ማድረግ ካለመቻል የሚመነጩ ብቸኝነትና የፍቅር ማጣት ችግሮች ናቸው:: እንደዚሁም በአካላዊና ስሜታዊ ዕድገታችን ምክንያት የሚመጡብን ውስጣዊ ስሜቶች ናቸው:: በተጨማሪም የምንፈልገውን ነገር ለማሳካት ስንሮጥ የሚገጥሙን እንቅፋቶች ናቸው:: የችግር ዓይነቶች እጅግ ብዙ ናቸው:: በአጠቃላይ ግን ማኅበራዊ፣ መንፈሳዊ /ሥነ ልቡናዊ/፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ብለን መክፈል እንችላለን::

እነዚህ ችግሮች ደግሞ በወቅቱ መፍትሔ ካላገኙ በሥራችን፣ በአገልግሎታችን፣ በትምህርታችን፣ በ ማኅበራዊ ግንኙነታችን፣ በጤናችን በአጠቃላይ በሕይወታችን ላይ የከፋ ችግር ያስከትሉብናል::

በመሆኑም ለእያንዳንዱ ችግር መፍትሔ ለማግኘት ጉዳዩን ወይም ችግራችንን ተረድቶ መፍትሔ ይሰጠናል ለምንለው ሰው እናማክራለን:: ሌሎች ምሥጢራዊ የሆኑትን ችግሮቻችንን ግን ለማንም ሳንናገር ተሸክመን እንዞራለን:: እነዚህ ችግሮች ደግሞ ውለው አድረው ሌሎች ችግሮችን ይወልዳሉ:: አንዱ ችግር ሌላውን እየወለደ እጅግ የተወሳሰበ ፈተና ይፈጠርብናል::

እነዚህን ችግሮች በተለይም የ ማኅበራዊና ሥነ ልቡናዊ ችግሮችን ለመቅረፍ ከብዙ ዓመታት ጀምሮ የተለያዩ የሞያ ዘርፎች የተለያዩ የመፍትሔ አሳቦችን ሲጠቁሙ ቆይተዋል:: ከእነዚህም ውስጥ ብዙ ምሁራን ይጠቀሙት የነበረውና እየተጠቀሙበት ያለው የሞያ ዘርፍ የምክክር አገልግሎት /Counseling service/ ነው:: ይህ ሞያ በሀገራችን ገና ከሁለት ዐሥርት ዓመታት በላይ ዕ ድሜ ባይኖረውም በአሁኑ ወቅት ግ በአገራችን ውስጥ እየበረከቱ ካሉት የተለያዩ ማኅበራዊና ሥነ ልቡናዊ ችግሮች ምክንያት አገልግሎቱ በመ ፋፋት ላይ ይገኛል:: የአገልግሎቱ ፈላጊዎች ብዙ እንደ ጠቀማቸውና በሚያገኙት አገልግሎት ምክንያት የጠባይ ለውጥ እንዳመጡ ከሚ ጧቸው አስተያየቶችና ከሚያሳዩት ድርጊት አንጻር መገንዘብ ችለናል::

በጥሩ ሥነ ምግባር የታነጹ፣ ለሀገርና ለወገን የሚያስቡ፣ ራእይ ያላቸው፣ በራሳቸው የሚተማመኑ፣ ራ ሳቸውን የሚያውቁ፣ ራሳቸውን የሚ ሆኑ፣ ለሥራ ተነሣሽነት ያላቸው፣ ማንኛውም ሱስ የጸዱ፣ በትዳራቸው፣ በኑሮአቸው፣ በሥራቸው ደስተኛ የሆ ዜጎችን በአጠቃላይ እግዚአብሔ የሰጣቸውን ጸጋ በአግባቡ ተጠቅመ ለራሳቸው፣ ለወገናቸው፣ ለሀገራቸው ለቤተ ክርስቲያናቸው ትርጉም ያለ ሥራ እንዲሠሩ የምክክር አገልግሎ ድርሻ የጎላ ነው::

## ምክክር /Counseling/ ምንድን ነው

በርካታ የምክክር ዓይነቶ አሉ:: ከእነዚህም ውስጥ አንዱ መን ሳዊ የምክክር አገልግሎት /Pastora counseling service/ ነው:: መንፈሳ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የምክክር አገልግሎት ማለት ቃለ እግዚአብሔርን መሠረት በማድረግ ሳይንሳዊ የምክክር ስልቶችን በመጠቀም ተመካካሪውን /Client/ መሆን የሚፈልገውን እንዲሆን ማገዝ ወይም ከአለበት ችግር እንዲላቀቅ መርዳት ማለት ነው:: ለአሁኑ ግን ስለ አጠቃላዩ የምክክር አገልግሎት ምንነት እናያለን:: የምክክር አገልግሎት ከሥነ ልቡና (Psychology) የትምህርት ዘርፎች አንዱ ነው:: ሳይኮሎጂ ስለ ሰው ልጆችና እንስሳት ባሕርይ የሚያጠና የማኅበራዊ ሳይንስ ክፍል ነው:: ምክክር/Counseling/ ለሚለው ቃል የተለያዩ ትርጉሞች በተለያዩ የዘርፉ ባለሞያዎች ተሰጥቷል:: ስለሆነም የተወሰኑትን ብቻ አነሣለሁ:: ምክክር ማለት የሰው ልጆች በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የሚገጥሟቸው የግልና ማኅበራዊ ችግሮች ለመወጣት የሚያደርጉትን ትግል ፈር በማስያዝ ሁለንተናዊ የሆነ የሰብእና እና የጠባይ ለውጥ እንዲያመጡ ሳይንሳዊ የሆኑ መርሖችን በመጠቀም ሰዎች የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ ማገዝ /መርዳት/ ማለት ነው:: በተጨማሪም ምክክር /Counseling/ በአመካካሪው /Counselor/ እና በተመካካሪው /Client/ መካከል የሚደረግ ምሥጢራዊ ግንኙነት ነው:: እንዲሁም ምክክር /Counseling/ ሂደት ሲሆን በዚህ ሂደት ውስጥ አመካካሪው /Counselor/ ሥነ ልቡናዊ ሁኔታዎችን በማመቻቸት አገልግሎት ፈላጊውን /Client/ መለወጥ የሚችልበት፣ ውሳኔዎችን ለመወሰን፣ ችግሮችን ለመፍታት እንዲችልና ሓላፊነት የሚሰማው ራሱን የቻለ የተሻለ ሰውና የተሻለ የኅብረተሰቡ አካል እንዲሆን የሚያግዝ ሞያዊ ግንኙነት ነው::

ከላይ የተሰጡትን ትርጉሞች ስናይ የምክክር አግልግሎት÷ አገልግሎት ፈላጊውን /Client/ ዓላማ እንዲኖረው፣ እግዚአብሔር የሰጠውን የራሱን ዕምቅ ችሎታ እንዲያዳብር፣ ጠንካራና ደካማ ጎኑን እንዲያውቅ፣ መወሰን እንዲችል እና ለችግሩ ራሱ መፍትሔ ፈላጊ /አመንጭ/ እንዲሆን ማስቻል /ማገዝ/ ነው::

የምክክር አገልግሎት የተመካካሪውን /Client/ ችግር መሸከም ሳይሆን አገልግሎት ሰጪው ወይም አመካካሪው /Counselor/ የተመካካሪውን /Client/ ችግር ከነመንሥኤው አጣርቶና ተረድቶ ራሱ ችግሩን ለመፍታት ውሳኔ ላይ እንዲደርስ ማድረግ ነው:: በዚህ ወቅትም አመካካሪውና ተመካካሪው በጋራ በመሆን ለችግሩ ወይም ተመካካሪው /Client/ ለሚፈለገው ነገር የተለያዩ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ያመነጫሉ::

አብዛኛውን ጊዜ በችግሩ ውስጥ ያሉ ሰዎች የሚያዳግታቸው ችግራቸውን ለማቃለል ራሳቸው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ማወቁ ላይ ነው:: በመሆ ኑም በምክክር አገልግሎት ውስጥ የአመ ካካሪው / Counselor/ ዋና ድርሻ ተመካካሪው ወይም አገልግሎት ፈላጊው/Client/ የራሱን ችሎታና አቅም እንዲረዳ፣ የችግሩን መንሥኤ እንዲለይ ማድረግና የመፍትሔ ሐሳቦችን እንዲያመነጭ፣ መፍትሔዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ቁርጠኛ እንዲሆን ማድረግ ነው:: በዚህ አገልግሎት ውስጥ ምንጊዜም ትኩረት መሰጠት ያለበት አመካካሪው በተመካካሪው ላይ ውሳኔ መስጠት ሳይሆን ለችግሩ መፍትሐዎችን በጋራ በመፈለግ ራሱ የችግሩ ባለቤት እንዲወስን ሁኔታዎችን ማመቻቸትና መርዳት ነው:: አመካካሪው የተለያዩ የመፍትሔ /አማራጭ/ መንገዶችን መጠቀም ይኖርበታል::

አንድ ሰው ከውሳኔ ላይ እንዲደርስ ማገዝና ስለ ሰውየው መወሰን በጣም የተለያዩ መሆናቸውን መረዳትና ለይቶ ማወቅ ለምክክር አገልግሎት ሰጪዎች /Counselors/ ሁሉ በጣም ጠቃሚና ወሳኝ ነው::

በአጠቃላይ በምክክር አገልግሎት ተግባርን ውጤታማ ሊያደርገው የሚችለው አገልግሎት ፈላጊው ወይም ተመካካሪው ያለውን ጠንካራና ደካማ ጎኑን የበለጠ እንዲያውቅ በማድረግ ጠንካራ ጎኑን የበለጠ እንዲያጠናክርና ደካማ ጎኑን ደግሞ በሂደት እንዲያሻሽል እንዲሁም ለችግሩ መፍትሔ የመሻትና የመፈለግ ሐሳቡ ከፍ እያለ የመምጣቱ ጉዳይ ነው:: ስለዚህ የአገልግሎት ሰጪውና የአገልግሎት ፈላጊው ግንኙነት ማተኮር ያለበት አገልግሎት ፈላጊው ወይም ተመካካሪው /Client/ ራሱን እንዲያውቅ ማድረግ ላይ ነው:: ሰው ራሱን ካወቀ የሚያስባቸውን ነገሮችና በሌሎች የሚነገሩትን ነገሮች ተግባራዊ ለማድረግ ቆራጥ ይሆናል:: ለምን ቢባል እያንዳንዱን ነገር የሚሠራውና የሚያስበው ከአለው አቅምና ችሎታ ጋር ነውና:: በመሆኑም ነው አንዳንድ የዘርፉ ባለሞያዎች ምክክር /Counselling/ የራስን ማንነት (እኔ ማን ነኝ? ጠንካራ ጎኔ፣ ራሴ የምፈጥራቸው ችግሮች፣ በሌሎች የሚፈጠሩብኝ ችግሮች ምን ምን ናቸው? ፈተናን /ችግርን/ የመቋቋም ልምዴና አቅሜ፣ ራእዩ፣ ፍላጎቴ እስከ ምን ድረስ ነው? ወዘተ.. የሚሉቱን ለማሳየትና ለማወቅ የሚያስችል ሞያዊ ግንኙነት ነው የሚሉት:: እንግዲህ ስለ ምክክር አገልግሎት በመጠኑም ቢሆን አይተናል:: ቁም ነገሩ ተመካካሪው በአገልግሎቱ ተጠቅሞ ተገቢ የሆነ የጠባይ ለውጥ ማምጣቱ ነው:: በተለይም ውጤታማ የሆነ የምክክር አገልግሎት ከተሰጠ ተመካካሪው ለውጥ ሊያመጣ ይችላል:: ተገቢ የሆኑ የጠባይ ለውጥ ከምንላቸው ጥቂቶቹ:-

- የተለያዩ የፈተና መቋቋሚያ ዘዴዎችን ማዳበር /ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት/
- በተለያዩ መንፈሳዊ አገልግሎቶች መሳተፍ
- በዓላማ መጓዝ
- ስለ ሌሎች ማሰብ
- አለመጨነቅ
- ተስፋ አለመቁረጥ
- ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን መፈጸም /በንስሐ፣ በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን መወሰን፣ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን መቀበል/
- ሕይወትን በተረጋጋ መልኩ መምራት /ስሜታዊ አለመሆን/
- ራስን አለማግለል
- ለችግሮች /ለፈተናዎች/ በቀላሉ አለመረታት

እና የመሳሰሉት ለውጦች ከአንድ ተመካካሪ አገልግሎቱን ከአገኘ በኋላ ይጠበቃል:: ስለ አጠቃላይ የምክክር አገልግሎት በአጭሩ ይህን ሲመስል ስለ መንፈሳዊ የምክክር አገልግሎት (pastoral counseling) ደግሞ በሚቀጥለው እትም በዝርዝር ለማየት እንሞክራለን::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

## ስንት ይሆን ኪሎዬ?

በኑሮ መስመር ላይ በሕይወት ጉዳና

ጉዞዬ ከሆነ ውኃ አልባ ደመና

ፍቅር ካልቋጠርኩኝ በልቤ ስልቻ

ዘንግቼ ከወጣሁ የምግባር እንጉቻ

ተስተካክሎ ብቆም ልብስና ሥጋዬ

በነፍስ ሚዛን ላይ ስንት ይሆን ኪሎዬ?

*ተክለ ጽዮን ዘፈ/ገ/ቅ/ጊዮርጊስ*





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# በየጥቂቱ ማደግ

ዲ/ን ያረጋል አበጋዝ

እያንዳንዱ ፍጥረት የራሱ የሆነ ተፈጥሮአዊ የአስተዳደግ ሂደት አለው:: ተክሎች እንደየዘራቸው ተዘርተው የሚበቅሉበት÷ በቅለውም የሚያድጉበትና ፍሬ የሚያፈሩበት የተወሰነ ጊዜ አላቸው:: የሰውም ሕይወት አካላዊም ሆነ መንፈሳዊ ዕድገቱ እንዲሁ ሂደታዊ እንጂ በአንድ ጊዜ የሚፈጸም ቅጽበታዊ አይደለም::

ለሁሉም ነገር አብነትና አርአያ የሆነን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: የባሕርይ አምላክ ሲሆን ከቅድስት ድንግል እመቤታችን በነሳው ሥጋ ሰው ሲሆን የሰውን ሥነ ሕይወታዊ ሂደት (ሕገ ጠባይዐዊ) በሙሉ ጠብቆ አል:: እንደ ማንኛውም ሰው ዘጠኝ ወር በማኅፀን መኖርን እንዲሁም በየጥቂቱ ማደግን ፈጽሞአል:: አምላክ ነኝና ዕለቱን ተወልጄ ዕለቱን ልደግ አላለም:: *«ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር::»* ሉቃ. 2÷52:: ኢየሱስ ክርስቶስ «በጥበብ ያድግ» ነበር ማለቱ እርሱ የባሕርይ አምላክ የጥበብ ባለቤት ሲሆን ነገር ግን ለእኛ መምህራችን ነውና በሁሉም ነገር በተለይም በመንፈሳዊ ጥበብ ማደግ የሚገባው ቀስ በቀስና በሂደት መሆኑን በተግባር ሲያስተምረን ነው:: *«ክርስቶስም ደግሞ ፍለጋውን ትከተሉ ዘንድ ምሳሌ ትቶላችኋል»* እንዳለ ቅዱስ ጴጥሮስ:: 1ጴጥ. 2÷21::

በመንፈሳዊ ሕይወት ዳተኝነት የማያስፈልግ እንደሆነ ሐዋርያው ሲናገር እንዲህ ይላል፡- «በእምነትና *በትዕግሥት የተሰፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድ ትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንዳትሆኑ÷ ተስፋ እስኪሞላ ድረስ እያንዳንዳችሁ ያን ትጋት እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ እንመኛለን::»* ዕብ. 6÷12:: ነገር ግን ዳተኝነት ብቻ ሳይሆን ከመጠን ያለፈ ፍጥነትም እንዲሁ አላስፈላጊ ነው:: አንድን ሰው ካሰበው ለመድረስ እንዳይችል የሚያደርገው ዳተኝነት ብቻ ሳይሆን ከመጠን ያለፈ ፍጥነት (ችኩልነት) ነው:: እንዲያውም ዳተኛ ቢሆንም ጉዞውን እስካላቋረጠ ድረስ ብዙ ጊዜም ቢሆን ወስዶ ካሰበው መድረስ ይችል ይሆናል:: «ሳያቋርጥ የሚጓዝ ቢዘገይም ያሸንፋል» (slow and steady wins the race) የሚባለው ለዚህ ነው:: በጣም የፈጠነ አካሄድ ግን የማሰናከልና ጠልፎ የመጣል ዕድሉ የሰፋ ነው:: አንድ ሰው በመኪና ሲሄድ ሹፌሩ በጣም በከፍተኛ ፍጥነት ያሽከረክር ነበር:: ይህን ጊዜ ሰውዬው «እባክህ ቸኩዬአለሁና ቀስ በል» አሉ ይባላል:: ለዚህ ነው ዳተኞች እንዳይሆኑ የመከረው ሐዋርያ መልሶ ደግሞ:–*«በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ»* ያለው:: ዕብ.12÷2::

ጌታችን በተግባር እንዳስተማረን መንፈሳዊ ሕይወት በትንሹ ተጀምሮ ከዚያም ቀስ በቀስ እያደገና እየጠነከረ የሚሄድ እንጂ በአንድ ጊዜ ተጀምሮ በቅጽበት ፍጹም የሚሆንበት አይደለም:: ቅዱሳን ሐዋርያትን ከተለያየ ሁኔታና ሕይወት ከጠራቸው በኋላ ወዲያውኑ ዕለቱን ወደ ፍጹምነት ደረጃ አልደረሱም:: ብዙ ድክመቶች ነበሩቸው:: እርሱ ስለ ሰማያዊ መንግሥት ሲነግራቸው ስለ ምድራዊ መንግሥት የሚጠይቁበት ጊዜ ነበር:: የሚነግራቸውን ባለማስተዋላቸው፣ ለእርሱ የቀኑና የተቆረቆሩ መስሎአቸው እሳት ከሰማይ ወርዶ እርሱን ያልተቀበሉትን ሰዎች እንዲያጠፋቸው በመጠየቃቸው፣ ስለ ሞቱና መከራው ሲነግራቸው «አትሙትብን» በማለታቸው÷ ስለ እምነት ማነስ ሁሉ ብዙ ጊዜ ተገሥጸዋል:: እነርሱም ከዚህ የተነሣ «ጌታ ሆይ÷ እምነት ጨምርልን» እስከ ማለት ደርሰዋል:: ጌታችንም ብዙ ጊዜ ይገሥጻቸውና ስሕተታቸውን እንዲያስተካክሉ በአባትነቱ ይመክራቸው ነበር፤ ሦስት ዓመት ከእርሱ ጋር ከዋለበት እየዋሉ ካደረበት እያደሩ በቃልም በተግባርም ተምረው እንኳ ፍጹማን መሆን አልቻሉም ነበር:: ጌታችን በሰጣቸው ተስፋ መሠረት መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ ነበር ፍጹማን የሆኑት:: እንግዲህ ሐዋርያት በእንዲህ ዓይነት ሂደትና ውጣ ውረድ ውስጥ ያለፉ ከሆነ ወደ ፍጹምነት ደረጃ መድረስ በአንድ በኩል በራስ ጥረት በዋናነትም በእግዚአብሔር ቸርነት÷ በሂደትና ቀስ በቀስ እንጂ በአንድ ጊዜ በቅጽበት የሚሆን ነገር አይደለም ማለት ነው::

በክርስትና የሕይወት ጉዞ ውስጥ የሕይወትን አካሄድ÷ ስልትና ዘዴ ማወቅ በጣም ወሳኝ ነው:: የጉዞውን ርዝመትና ጠባይ እንዲሁም በሂደቱ ውስጥ ያሉና ሊገጥሙ የሚችሉ ነገሮችን አስቀድሞ ሳያውቁ የሚጀመር ጉዞ መሰናክሎች ሲገጥሙት የመውደቅ ዕድሉ የሰፋ ነው:: ከዚህም አንዱ የአካሄድን ፍጥነት መወሰን ነው:: አንዳንዶች ክርስትና በተወሰነ ጊዜ ተሠርቶ ማለቅ እንዳለበት የሥራ ዕቅድ (ፕሮጀክት) ወዲያውኑ እንደ ጀመሩ አካሄዳቸው ሁሉ የጥድፊያና የችኮላ ይሆናል:: ሰውነቱ ጾምን በሚገባ ሳይለማመድ እስከ ማታ ድረስ በመጾም ይጀምራል:: «የክርስቶስ ክቡር ደም በፈሰሰባት ምድር በጫማ አልሄድም» እስከ ማለት ይደርሳል:: ይህን ዓለም በሙሉ የመጸየፍና የምናኔ ነገር ብቻ ይታሰበዋል:: ሌሎች ሰዎች ኃጢአተኞችና ደካሞች ሆነው ይታዩታል:: አንዳንዶች ሥራቸውን እስከ መተው ደርሰው በየገዳማት መዞርን ብቻ ሥራዬ ብለው ይይዛሉ:: በአጠቃላይ ነገሮችን ሁሉ እንዳይሆን እንዳይሆን አድርገው ይይዟቸዋል:: በየቦታው በመዞር ብቻ በረከትና ጽድቅ የሚገኝ ይመስለዋል:: ከትምህርት ቤት ወደ ትምህርት ቤት እየተዘዋወረ መምህር ሲያማርጥና የተመቸ ሁኔታን ሲፈልግ አንድ ቁም ነገር ሳይማር ጊዜውን የሚያጠፋውን ተማሪ አበው 'እግረ ተማሪ' ይሉታል:: ዛፍ እንኳ ፍሬ የሚያፈራው ከተተከለበት ቦታ ሲኖር ነው:: ነገር ግን በየጊዜው እየተነቀለ የሚተከል ከሆነ ወይ ይደርቃል፤ ባይደርቅ እንኳ ፍሬ ማፍራት አይችልም:: ጊዜውን በዙረት ብቻ የሚጨርስ ሰውም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም:: ቢያፈራም እንኳ በአንድ ቀን በቅላ በአንድ ቀን አብባ በአንድ ቀን ታፈራለች እንደምትባለው ዕፀ ከንቱ÷ ፍሬው ምትሐታዊ ይሆንና ከመታየቱ ወዲያውኑ ይረግፋል:: በእንዲህ ያለ ሕይወት የሚጓዙ ሰዎች የማይመች አካሄድ ውስጥ ይወድቃሉ:: ይህ ዓይነት ሕይወት ብዙ ችግሮችን ሊያስከትል የሚችል አስቸጋሪ አካሄድ ነው:: ከእነዚህም ውስጥ የተወሰኑትን እንመልከት::

1. በሌሎች ላይ መፍረድና መንቀፍ - እርሱ ብቻ በትክክለኛው ክርስቲያናዊ ሕይወት እየተጓዘ እንዳለና ሌሎች ግን ሕይወታቸው የዛለና መንፈሳዊነትን ችላ ያሉ መስሎ ይታየዋል:: ለቤተ ክርስቲያን የሚያስብ÷ የሚቆረቆር እና የአባቶችን ፈለግ የሚከተል እርሱ ብቻ እንደሆነ ያስባል:: እንደ እርሱ ነገሮችን ጥድፍድፍ አድርገው ከመጠን አሳልፈው ያልያዙትን ሁሉ በተጋድሎም በብቃትም ከእርሱ በታች ሆነው ስለሚታዩት በልቡናው ይኮንናቸዋል:: አባቶችም መንፈሳዊነት ቀስ በቀስና በሂደት እንደሆነ ሲነግሩት ጠአይ እነርሱም'ኮ ትተውታል፤ የዚህ ዘመን ነገር ምን ዋጋ አለው!» ይላል:: ይህ ደግሞ ምክረ አበውን እንዳይጠይቅ÷ ቢነግሩትም እንዳይሰማ ያደርገዋል:: በሌሎች ላይ ጣቱን መቀሰሩም ቀናዒነት ይመስለውና ይህንኑ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በማጠናከር ይገፋበታል:: ወደ ውጭ ማየትን ባበዛ መጠን ራሱን መመርመር እየከበደ ውና እየዘነጋው ስለሚሄድ ራሱን እየረሳ ይሄዳል:: በዚህም ሳያውቀው ውስጥ ውስጡን እየተሸረሸረ ይዳከማል::

ጌታችን ሐዋርያትን «የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል» እንዳላቸው ሌሎችን መንቀፍንና መተቸትን ሥራዬ ብለው እግዚአብሔርን እንደሚያስደስት አገልግሎት አድርገው የሚይዙ አሉ:: ይህ ማለት ስሕተት የሆነውን ስሕተት ነው ብሎ መናገርና ጥፋት ሲፈጸም መቃወም ጥፋት አይገባም ማለት አይደለም:: ነገር ግን ሁሉም ነገር በአገባብ ሊሆን ይገባል:: ደግሞም በመንቀፍና በመተቸት ብቻ ችግር አይፈታም፤ ለውጥም አይመጣም:: አንድ ፈላስፋ «ሺሕ ጊዜ ጨለማን ከማውገዝ አንድ ሻማ ማብራት ይበልጣል» እንዳለ የሚችሉትን የራስን አስተዋፅዖ በማድረግ እንጂ በሌሎች ስሕተትና ድካም በማዘንና ያንን በመተቸት ብቻ ምንም ነገር አይገኝም፤ ሌላም ፈላስፋ «በጩኸት ቢሆን አህያ በቀን ብዙ ቤት በሠራች ነበር::» ብሏል::

ችግሮች እንዲፈቱና እንዲወገዱ እግዚአብሔርን በጸሎት መጠየቅ እንዲሁም የራስን አስተዋፅዖ ማድረግ እንጂ የራስን ሕይወት ሳያስተካክሉ በሌሎች ላይ በመፍረድ የሚገለጽ መንፈሳዊ ቅንዓት የለም:: እንዲህ ያሉትን እግዚአብሔር በነቢዩ በዳዊት አፍ በሚከተለው ቃል ይገሥጻቸዋል :-«ኃጢአተኛውን ግን እግዚአብሔር አለው:- ለምን አንተ ሕጌን ትናገራለህ? ኪዳኔንም በአፍህ ለምን ትወስዳለህ? አንተ ተግሣጼን ጠላሁ፥ ቃሎቼንም ወደ ኋላ ጣልህ:: ሌባውንም ባየህ ጊዜ ከእርሱ ጋር ትሮጥ ነበር፤ እድል ፈንታህንም ከአመንዝሮች ጋር አደረግህ:: አፍህ ክፋትን አበዛ፥ አንደበትህም ሽንገላን ተበተበ:: ተቀምጠህ ወንድምህን አማኸው» መዝ. 49÷16-20::

2. ባዕድ ነገሮችን ማምጣት - ያወቀና የበቃ እየመሰለው የሌለና እንግዳ የሆነ ነገርን ያመጣል:: «ከቀደሙት ያገኘነው ነው» በሚል ማስመሰያ ግን እንደ ሠራውና እንደ ደነገገው የማይታወቅ ለእርሱ ግን ጥሩ የሚመስለውን «ሕግና ሥርዓት» ለማምጣት ይሞክራል:: ይህን ከግብዝነትና ከአጋንንት ማታለል የተነሣ የሚያደርገውንም ለቤተ ክርስቲያን ጠቃሚ ነው ብሎ ያስባል:: ይህም ሲያድግና ሲካሄድ ወደ ለየለት የሃይማኖት ሕጸጽ ሊያመራ ይችላል:: ቅዱስ ጳውሎስ ልጁን ጢሞቴዎስን ሲመክረው እንዲህ ያለው ለዚህ ነው:- «መንፈስ ግን በግልጥ በኋለኞች ዘመን አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ፤ ይላል:: በገዛ ኅሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝ ዘው እነዚህ ውሸተኞች መጋባትን ይከለክላሉ፤ አምነውም እውነትን የሚያውቁ ከምስጋና ጋር ይቀበሉ ዘንድ እግዚአብሔር ከፈጠረው መብል እንዲርቁ ያዝዛሉ:: እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ነውና ከምስጋናም ጋር ቢቀበሉት የሚጣል ምንም የለም፤ በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት የተቀደሰ ነውና::» 1ጢሞ.4÷1-5::

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የመንፈስ ልጁን ጢሞቴዎስን እንዳስጠነቀቀው ያወቁና የበቁ እየመሰላቸው በንጽሕና ሰበብ እግዚአብሔር ያከበረውን ጋብቻ የሚያቃልሉና የሚከለክሉ፤ በትሕርምት ሰበብ ደግሞ እግዚአብሔር ከፈጠረው ፍጥረት ሰው ልማድ ካልከለከለው በስተቀር ያልተከለከለውን፤ «እግዚአብሔር ያደረገውን ሁሉ አየ፤ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ» ዘፍ.1÷31፤ እንዲሁም «ሕይወት ያለው ተንቀሳቃሽ ሁሉ መብል ይሁናችሁ፥ ሁሉን እንደለመለመ ቡቃያ ሰጠኋችሁ» /ዘፍ. 9÷3/ ያለውን ቃል በመተውና በመርገጥ ከሥነ ፍጥረት መካከል ርኩስ እንዳለ የሚያስተምሩ መናፍቃን ተነሡ:: ያን ጊዜም ሆነ ዛሬ ዐውቀውትም ሆነ ሳያውቁት የእነርሱን ሓሳብ የሚያራምዱ አሉ:: ይህን ሁሉ ከመጠን ማለፍ የሚያመጣው ችግር ነው:: የቤተ ክርስቲያን አባቶች በዚህ ጉዳይ ላይ ያለውን ትክክለኛ ትምህርት ሲነግሯቸው አልሰማም ብለው የራሳቸውን ፍልስፍና ሲያራምዱ ኖረዋል:: አርዮስም ወደዚያ ታላቅ የክሕደት ገደል ውስጥ የገባው እርሱ ብቻ ትክክል የሆነ ስለመሰለውና በተለይም የተለያዩ አባቶች ሲነግሩት ስላልሰማ ነው::

ጌታችንም ጸሐፍትና ፈሪሳውያንን ይነቅፍ ከነበረበት ምክንያት አንዱ ባዕድ ትምህርቶችን በማስተማራቸው ነበር:: «ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፥ ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው፤ የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል» ብሎ በነቢዩ ኢሳይያስ የተነገረውን ትንቢት ጠቅሶ ነቀፋቸው:: ማቴ.15÷7-9:: እነርሱ በታዘዘው አምላካዊ ሕግ ላይ የራሳቸውን ልማድና ወጋወግ ጨምረውበት ነበር:: ጌታችንም የነቀፈው ይህን ከንቱ የሆነ የረበናት ወግና ሥርዓት ነው:: ክርስቶስን ለመቀበልና በእርሱ ለማመን ዕንቅፋት የሆነባቸው አንዱም ይህ ነበር፤ጌታችን:- «እናንተስ ስለ ወጋችሁ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለ ምን ትተላለፋላችሁ?» (ማቴ.15÷3) ያላቸው ለዚህ ነው:: ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ይልቅ ራራሳቸው ለፈጠሯቸው ወጎች ቅድሚያና ከፍ ያለ ክብደት ይሰጡ ነበር:: ጌታችን ግን ይህን የፈጠራ ወግ ስላላከበረ፤ አለማክበር ብቻ ሳይሆን ስሕተት መሆኑን በግልጥ ስለነገራቸው ጠላት አደረጉት:: «ዓለም እኔ ሥራው ክፉ መሆኑን እመሰክርበታለሁና እኔን ይጠላኛል::» ያለው ለዚህ ነው:: ዮሐ. 7÷7::

ቅዱስ ጳውሎስም አይሁድ የጽድቅ ሕግ ተሰጥቶአቸው ሳለ ወደ ጽድቅ አለመድረሳቸውን «እስራኤል ግን የጽድቅን ሕግ እየተከተሉ ወደ ሕግ አልደ ረሱም» ብሎ ከገለጸ በኋላ ለምን ወደ ጽድቅ እንዳልደረሱ ሲያስረዳ ደግሞ:- «የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውን ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም::» አለ:: ሮሜ 9 ÷ 31/10 ÷ 3::

ማንኛውም ነገር ሥርዓትም ይሁን ትውፊት ተቀባይነት የሚኖረው የመሠረተ እምነት (ዶግማ) ማዕከል ከሆነው ከነገረ ድኅነት ጋር እስካልተጣላ ድረስ ብቻ ነው:: የማንኛውም ነገር መለኪያና መመዘኛም ይህ ነው:: በመሠረተ እምነት ላይ ችግር የማያመጣ ነገር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ያውም በቅዱስ ሲኖዶስ ሊጨመር ይችል ይሆናል:: ከዚህ ውጭ ግን ምንም ዓይነት ስም ቢሰጠውና ብዙ ዘመን ቢያስቆጥር ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ያለ ነገር አትቀበልም:: በባዕድ ነገሮች ቤተ ክርስቲያን እንዳትታወክ ዋናው ነገር መጀመሪያ የቤተ ክርስቲያንን መሠረተ እምነት ከምንጩ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከመምህራን በሚገባ መማር ነው:: ሆኖም ግን ይህንን ሳይማር ያለፈ ሰው በጆሮ ጠገብ የሰማውን፣ በልማድ የያዘውንና የመሰለውን እየተናገረና አስተምራለሁ እያለ መምህራንም ሲነግሩት እንዳይሰማ የራሱን አእምሮ በዐውቃለሁ ባይነት ዘግቶ ያልተማረውንና ቤተ ክርስቲያን የማትለውን «ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ትላለች» እያለ የራራሱን ተከታዮች እያፈራራ ከቤተ ክርስቲያን ጋር በስም እንጂ በተግባር እያለያያቸው ይሄዳል:: ሐዋርያው «የአይሁድን ተረትና ከእውነት ፈቀቅ የሚሉትን ሰዎች ትእዛዝ ሳያዳምጡ በሃይማኖት ጤናሞች እንዲሆኑ በብርቱ ውቀሳቸው» ያለው ለዚህ ነው:: ቲቶ 1÷14:: ከዚህ ሁሉ ለመዳን ጊዜ ወስዶ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን የእምነት ምንጭ የሆኑትን ብሉያትንና ሐዲሳትን እንዲሁም የቅዱሳን ሊቃውንት የእነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅን፣ ቅዱስ አትናቴዎስን፣ ቅዱስ ቄርሎስን፣ ባስልዮስን፣ ጎርጎርዮስንና የመሳሰሉትን ማጥናትና መማር ይጠቅማል፥ ይገባልም::

3. በሌሎች ላይ ሸክምን መጫን - እነርሱ ሳይዘልቁት መሸከም የጀመሩትን ከባድ ሸክም ሌሎችም እንደነርሱ ተሸክመው እንዲንገዳገዱና እንዲወድቁ ለማድረግ ይፈልጋሉ:: አንዳንዶች ገና ጾም እንደ ጀመሩ የጽጌ ጾምን «የዐዋጅ ጾም ነው፤ ለምን ከዐዋጅ ጾም አልገባም? የቀደሙ አባቶች ተሳስተዋል» እስከ ማለት ይደርሳሉ:: ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያ ሲገቡ ገና ከሩቁ ጫማቸውን እንዲያወልቁ ዐዋጅ ነጋሪ ይሆናሉ:: ወደ ቤተ ክርስቲያን አስገቢና አስወጪ በረኛ /ዐጻዌ ኆኅት/ አድርገው ይሾማሉ:: ኮሽ ባለ ቁጥር





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

«ሥርዓት ተፋለሰ» እያሉ በፀጥታና በተመስጦ ሊከታተሉት በሚገባው ሥርዓተ ቅዳሴ ውስጥ ጸብና ክርክር የሚፈጥሩ አሉ:: ራሳቸው ሰዓት ወስነው እስከዚህ ሰዓት ድረስ ያልጾመ÷ ጾሙ ዋጋ የለውም÷ ይላሉ:: በካህናት ሥልጣንና የቀኖና አስተያየት እየተገቡ ሊሰጥ ስለሚገባው የቀኖና ክብደት ይናገራሉ:: አባቶች ካህናት የተነሳሒውን ሕይወትና ልዩ ልዩ ሁኔታዎችን አገናዝበው ቀለል ያለ ቀኖና ሲሰጡ በሥርዓት አፍራሽነትና በግዴለሽነት ይከሳሉ:: «ዛሬ ምን እውነተኛ ካህን አለ?» እያሉ ያዝናሉ:: ሌላም ብዙ ብዙ ያለ የሌለ ነገር ሁሉ ለመጫን ይሞክራሉ::

የሚያሳዝነው ግን ከሩቁ ጫማ ሲያስወልቁ የነበሩ ያን ሁሉ እንደ ማያዋጣ አይተውት እንደገና ወደ ሌላ ጽንፍ ሄደው ከነጫማ ቤተ መቅደስ ይገባ እስከ ማለት የደረሱ አሉ:: ስለ ስምንት «የዐዋጅ አጽዋማት» ሲናገሩ ከነበሩት የጌታን ጾም እንኳ መጾም የከበዳቸው አሉ:: ሌላም ብዙ ሰው ሠራሽ ነገር ሲያስተምሩ የነበሩ ነቢዩ ዳዊት:- «በአምጣነ *ብርሃና ከማሁ ጽልመታ፤ ጨለማዋ በብርሃኗ መጠን ነው»* እንዳለው ጭልጥ ብለው በሌላ ጽንፍ የሚዞሩ ብዙዎች ናቸው:: ሌሎችም እነርሱ በጊዜ ሂደት ተምረውና ተመክረው ቢመለሱ እንኳ እነርሱ ያስተማሯቸው እንደ እነርሱ በዙሪያ መንገድ ደክመው እስኪመለሱ ድረስ ራሳቸውንና ሌላውንም ሲያውኩ ይኖራሉ:: በዚህም በቤተ ክርስቲያን መተሳሰብና መደማመጥ እንዳይኖር÷ ፍቅር እንዲጠፋ÷ መለያየት እንዲስፋፋ ዋና ሠራተኞች ይሆናሉ:: ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱት ተምረው ራሳቸውን ለማስተካከልና ሕይወታቸውን ለመለወጥ ሳይሆን ከራሳቸው አስተሳሰብና ፍላጎት ጋር ብቻ የሚስማማውን እየመረጡ ነገር ግን እየቆዩ÷ የፈጸሙት ስሕተት ሁሉ ትዝ ሲላቸው ወደ ብስጭትና ቀቢጸ ተስፋ ይሄዳሉ::

ክርስትና የክርስቶስ ፍቅር እንደ ተረዳውና እንዳገበረው መጠን ከውስጥ በሚመነጭ ፍቅር የሚመሠረት እንጂ በተጽዕኖ ከውጭ የሚጫን ሸክም አይደለም:: ሐዋርያው:- «የክርስቶስ *ፍቅር ግድ ይለናል»* አለ እንጂ ሌላ ማንም ያስገድደናል አላለም:: በሰዎች ላይ ከባድና አስቸጋሪ ሸክም የሚጭኑ ጸሐፍትንና ፈሪሳውያንን ጌታችን እንዲህ በማለት ገሥጾአቸዋል:- «ከባድና *አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትከሻ ይጭናሉ÷ እነርሱ ግን በጣታቸው እንኳ ሊነኩት አይወዱም::»* ማቴ. 23÷4:: እንዲህ በሌሎች ላይ መጫን ገድልና ትሩፋት መስሎ የሚታያቸው ሰዎች÷ ሁሉን ከሚያውቅና ሁሉን በጊዜው ከሚያደርግ ጌታ ጋር ያሉትን ቅዱሳን ሐዋርያትን የግድ÷ እንዲጾሙ ለማደረግ ወደ ጌታችን ቀርበው:- *«እኛና ፈሪሳውያን ብዙ ጊዜ የምንጾመው÷ ደቀ መዛሙርትህ ግን የማይጾሙት ስለ ምንድነው?»* እስከማለት ደርሰዋል:: ለጾም ከራሱ ከባለቤቱ የበለጠ ተቆርቋሪዎች በመ ምሰል በሌሎች ላይ ለመወሰን ቀረቡ:: ማቴ.9÷14:: አባቶቻችን ሐዋርያትንም እንጀራ ሲበሉ:- «*እጃቸውን አይታጠቡም፤ በሰንበት ቀን እሸት ቆርጠው በሉ*» ወዘተርፈ እያሉ ይከሷቸውና ይነቅፏቸው ነበር::

ጌታችን ከሰው የሚፈልገው ግን ከባድና አስጨናቂ የሆኑ ነገሮችን አይደለም፤ *«እናንተ ደካሞች÷ ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ ÷ እኔም አሳርፋችኋለሁ:: ... ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና»* በማለት የእርሱ ቀንበር ቀላልና የማይጎረብጥ መሆኑን ነገረን:: የተለያዩ ሰዎች መጥተው «ምን እናድርግ?» እያሉ በጠየቁት ጊዜ ዮሐንስ መጥምቅ የነገራቸው በዚያው በአቅማቸው ሊሠሩት የሚችሉትን እንጂ ከባድ የሆኑ ነገሮችን አላዘዛ ቸውም:: ሉቃ.3÷10-14:: ምክንያቱም ገና በመንፈስ ያላደጉ ስለነበሩ ከበድ ያለ ነገር ቢነግራቸው አይችሉትምና:: ጌታችንም:- «ሰዎች *ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፣ ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና»* በማለት ለሁሉም በሚቻልና በማይከብድ ሁኔታ አዘዘ:: ማቴ.7÷12:: ሌሎች ለእኛ ሊያደርጉልን የምንወደውን ነገር እኛም ያንን ለሌሎች ማድረግ እንችላለንና:: ሌሎች እንዲያደርጉልን ከምንፈልገው ነገር እኛ ለሌሎች ማድረግ የማንችለው ካለ ከሌሎች የምንፈልገው እኛ የማንችለውን ነው ማለት ነው:: እኛ የማንችለውን ከሌሎች መጠበቅ ደግሞ ተገቢ አይደለም:: እንዲሁም ራሳችን ከሌሎች የምንፈልገውን ጠንቅቀን እንደ ምናውቅ ሁሉ ሌሎች ከእኛ የሚፈልጉትንም በእኛው ፍላጎት አንጻር በቀላሉ ማወቅ እንችላለን:: ስለዚህ ይህን ማወቅም ሆነ መፈጸም ከባድ አይደለም::

ከበድ ያሉ ነገሮችን ግን ለራሱ ለሰውዬው ውሳኔ ክፍት አድርጎ ነው የተዋቸው:: ለምሳሌ ጌታችን በመዋዕለ ትምህርቱ ስለ ድንግልና ሕይወት ከተናገረ በኋላ:- «ሊቀበለው *የሚችል ይቀበለው»* ነው ያለ:: ማቴ. 19÷12:: እንዲሁም:- *«እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ÷ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ»* በማለት ለእያንዳንዱ የኅሊና ውሳኔ በነጻነት አቀረበ እንጂ እርሱን መከተልና መስቀሉን መሸከም እንደሚጠቅመን እያወቀ የሚያስገድድ (የሚያገብር) ነገር አልተናገረም:: *«እኔን መከተል የሚወድ»* አለ እንጂ በግድ ተከተሉኝ አላለም:: የሚያስገድድ ሰው ከማቅረብ ይልቅ ያሸሻልና:: ለምሳሌ:- ወርቅ ወይም ብር ወይም ሌላ ጥሩ ነገርን «በነጻ ውሰዱ» የሚል ሰው ማስገደድ ለምን ያስፈልገዋል? የስጦታው መልካምነት በራሱ በቂ ነው:: ስጦታ አቅርቦ የሚያስገድድ ግን 'ከስጦታው ጀርባ ምን አለ?' ብሎ ከሚያጠራጥር በቀር ብዙም አይስብም:: በሽተኞችን ሲፈውስ እንኳ «ልትድን ትወዳለህ?» ፣ «ምን ላደርግልህ ትወዳለህ?» እያለ ነው:: ቅዱስ ጳውሎስም በጋብቻ ዙሪያ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖችን በመልእክቱ ከመከረ በኋላ:- «ስለ *ደናግል ግን የጌታ ትእዛዝ የለኝም»* አለ:: 1ቆሮ. 7÷25:: እንዲህ ታላቅና ከበድ ያለ ነገር የሚታዘዝ ሳይሆን በራስ ፍላጎትና ምርጫ ብቻ የሚወሰን ነውና::

በአበው ዜና ሕይወት ላይ የተገለጸ አንድ ታሪክ እዚህ ላይ መጥቀስ ይቻላል:: የግብርና ሥራ እየሠራ ከሚያገኘው የሚተርፈውን እየመወተ የሚኖር ሰው ወደ አንድ ገዳማዊ አባት ሄዶ ሳለ ያ አባት ገበሬውን አኗኗሩን ጠየቀው:: እርሱም ገለጸለት:: ገዳማዊው አባትም አያያዙ መልካም እንደ ኾነና በዚሁ እንዲቀጥል አጽናንቶና መክሮ ላከው:: ይህ ሰው ከተመለሰ በኋላ የዚያ ገዳማዊ አባት ጓደኛ መጥቶ ሲጨዋወቱ÷ ያ ሰው መምጣቱንና መክሮ የሰደደው መሆኑን ሲነግረው አይ ደግም አላደረግኸ፣ እንዲህ ያለውን ሰው እኛን መስለህ ኑር አትለውም ነበር? አለው:: ያም አባት ይህን ይዞ ያ ሰው ሌላ ጊዜ ሲመጣ ያኛው አባት እንደነገረው «እኛን መስለህ ኑር» ቢለው «አይ ÷እንዲያውም ያኛውም ከብዶኛል፤ ሁሉንም እተወዋለሁ» አለው:: በዚህ ጊዜ ይህ አባት እንደገና «ብያዝከው ሕይወት ጸንተህ ኑር» ብሎ መክሮና አጽናንቶ እንዲመለስ አደረገ:: «እኛን መስሎ መኖር አለበት» የሚለውን ምክር እንዲነግረው ያለው አባትም ይህንን ሲሰማ አጥፍቻለሁ ብሎ ተጸጸተ::

ወደ ክርስትና የገቡት አይሁዶች እንኳ ኦሪታዊ ልማዳቸው አልተዋቸው ብሎ ከቤተ አሕዛብ እያመኑ ወደ ክርስትና የሚመጡትን አማንያን «ያንኑ የኦሪቱን ሕግና የሙሴን ትእዛዛት በሙሉ ሊጠብቁ ይገባል» እያሉ ስላስቸገሩ በዚህ ምክንያት የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በኢየሩሳሌም ተደርጓል:: በዚህ ጉባኤም ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ:- *«እንግዲህ አባቶቻችንና እኛ ልንሸከመው ያልቻልነውን ቀንበር በደቀ መዛሙርት ጫንቃ ላይ በመጫን እግዚአብሔርን አሁን ስለ ምን ትፈታተናላችሁ?»* በማለት የጉባኤ መግቢያ ሐሳብ ተናገረ:: ከዚያም ቅዱሳን ሐዋርያት ከተወያዩ በኋላ:- «ለጣዖት *ከታረደው÷ ከደምም÷ ከታነቀ ሥጋ÷ ከዝሙትም ትርቁ ዘንድ ከዚህ ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናልና ከዚህ ሁሉ ራሳችሁን ብትጠብቁ በመልካም ትኖራላችሁ»* ሲሉ በአንድነት ወሰኑ:: የሐዋ. 15÷29::

*/ይቆየን/*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ሥርዓተ ማሕሌት

መ/ር ኃይለ ማርያም ላቀው

«ማሕሌት» የግእዝ ቃል ሲሆን «ሐለየ» ከሚለው ግስ የወጣ ነው:: ከላይ የተጠቀሰውን ግስ መሠረት በማድረግ «ማሕሌት» ዘፈን፣ ምስጋና፣ ወረብ፣ ለዘብ፣ ቅዳሴ፣ ውዳሴ፣ ቅኔ ግጥም፣ ጉማ፣ ተመማ፣ የብዙ ሰው ዜማ በማለት ይብራራል:: /ኪ.ወ.ክ.1948፣ 444/ ስለዚህ ማሕሌት በዜማና በግጥም የሚከወን ምስጋና ማለት ይሆናል::

ለያዝነው ርእስ ተስማሚ የኾነው የቃሉ ፍቺ÷ በሦስቱ የዜማ ስልቶች /ግዕዝ፣ ዕዝል ና አራራይ/ ተከፍሎ÷ በቤተ ክርስቲያን በቅኔ ማሕሌት÷ በዕለተ እሑድና በተለያዩ ክብረ በዓላት÷ በዝማሜ፣ በመቋሚያ፣ በጸናጽል በከበሮ የሚዘመር ለካህናት የኅብረት መዝሙር፣ ምስጋና፣ ወረብ የተሰጠ ስያሜ ነው::

ማሕሌት ከቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ክፍል አንዱ ነው:: በዕለተ እሑድ የሚቆመው መዝሙር ሲባል በየወር በዓላትና በየዓመት በዓላት የሚደረገው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ደግሞ ማሕሌት ይባላል:: በጌታችን በእመቤታችን፣ በጻድቅ፣ በሰማዕት፣ መልአክ ስም በታነፀ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በመደበኛነት በየወሩ የሚከበሩት በዓላት ወርኃዊ በዓላት ይባላሉ:: እንዲሁም ቅዱሳን፣ ጻድቃንና ሰማዕታት የተወለዱበትን፣ የተለያዩ ተኣምራት ያደረጉበትን፣ ሰማዕትነት የተቀበሉበትን፣ ቃል ኪዳን የተቀበሉበትን፣ ያረፉበትን በመዘከር በየዓመቱ የሚከበሩ በዓላት ክብረ በዓላት ይሰኛሉ:: የጌታችን፣ የእመቤታችንንና የሌሎች ቅዱሳንን ክብረ በዓላት መጥቀስ ይቻላል:: በእነዚህ በታወቁ በዓላት የሚዘመሩት መዝሙራት የዓመት በዓላት ቀለማት ይባላሉ:: የዓመት ቀለማት ተብለው በአቋቋም መልክ የሚታወቁት:- ክብረ ቅዱሳንን ያካተቱ÷ ክፍ ባሉት በዓላት የሚዘመሩት ናቸው::

በወርኃዊ በዓላትና በዓመታዊ ክብረ በዓላት ማሕሌት ሲቆም:- «ስቡሕ ወውዱስ ዘሣረረ ኵሎ ዓለመ በኢሐቲ ቃል ዓለምን ሁሉ በአንድ ቃል የፈጠረ ፈጽሞ የተመሰገነ ነው» በማለት ይጀመርና በንዑስ መረግድ እንዲሁም በዐቢይ መረግድ እያመላለሰ ካመሰገነ በኋላ ወደ ሁለተኛው ክፍል ይሄዳል:: ይህ ክፍል «ነግሥ» ይባላል:: ነግሥ በዘወትር የሚደርስ ልዩ ድርሰት ወይም ግጥም ሲሆን እንደ መልክአ መልክአ ሆኖ የቅድስት ሥላሴን፣የእመቤታችንን የቅዱሳንን፣ የመላእክትንና የጻድቃንን ምስጋና የሚናገር ግጥም ነው:: ነግሥ በአብዛኛው ባለ አምስት ስንኝ አርኬዎች አሉት:: ከነግሡ በማስከተል በዓሉ የሚመለከተው የጌታችን የእመቤታችን÷ የጻድቅ÷ የመልአክ÷ የሰማዕት መልክአ /ግጥም/ ይመረገዳል:: በነግሥና በመልክአ መልክእም መካከል እየገባ የሚመረገደው ደግሞ ዚቅ ይባላል:: ዚቅ ከቅዱስ ያሬድ ድርሰት አንዱ እንደ ሆነ ይነገራል::

ቅንብሩ ግን ከቅዱስ ያሬድ የዜማ ድርሰቶች:- ከድጓ፣ ጾመ ድጓ፣ ከመዋስዕት እንዲሁም ከሰዓታትና ከሰባቱ ኪዳናት የተውጣጣ ነው:: ለአንድ መልክእ ከአንድ እስከ ሦስት ዚቅ ይኖረዋል:: ማሕሌት ሲቆም ለዕለቱ በዓል ነክ /ተስማሚ/ የሆነው እየታየ÷ ከነግሥና ከመልክአ መልክእ መካከል እየገባ ይመረገዳል:: በማስከተልም ከማሕሌተ ጽጌ ውስጥ ከ1-3 አርኬ ምሥጢር ያጋጠመው ይመረገዳል:: እንዲሁም ስንክሳር ከተነበበ በኋላ አርኬው በዓሉን ነክ /ተስማሚ/ ሆኖ ሲገኝ ሊመረገድ ይችላል:: ዚቁ በነግሥና በመልክአ መልክእ መሐል እየገባ ከተመረገደ በኋላ ወደ ተከታዩ ክፍል ይገባል:: ይኸውም ምልጣን እስመ ለዓለም ተቃኝቶ÷ አንገርጋሪው ተመርቶ የሚዜመውን÷የሚዘመመውን÷ የሚጸነጸለውን÷ የሚዘመረውን ሂደት ያጠቃልላል:: በሌላ አነጋገር አንገርጋሪው ብቻ ምልጣን ሊባል ይችላል:: በዝርዝር ግን «እስመ ለዓለሙ፣ አንገርጋሪው፣ ሰላሙ» በአንድነት ምልጣን ይሰኛል:: ምልጣን በሥርዓተ ማሕሌት ወቅት በመሪና ተመሪ ይከናወናል:: መሪው መስቀል በመያዝ የሚመራውን÷ ተቀባዩ /ተመሪው/ መሪውን ተከትሎ ዜማን የሚያዜምበት አካሄድ ነው:: በዚህ ክፍል ውስጥ የመቋሚያ አነጣጠቅ÷ የጸናጽሉ አወዳደቅ÷ የቃለ እግዚአብሔር አደማመቅ ጐልቶ ይታያል:: የወር በዓል ከሆነ ሥርዓተ ማሕሌቱ በዚህ ይፈጸማል:: ሰላሙ እንደ ተጸፋ ማብቂያው ይሆናል:: አልፎ አልፎ በክብረ በዓላትም የማሕሌቱ ሥርዓት ከዚህ ላይዘል ይችላል::

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን:- ሥርዓተ ማሕሌቱን አጥብበን ከተመለከትነው በዚህ አኳያ ይጠናቀቃል:: በየክብረ በዓላቱ በዓሉን ለማክበር የሚሰበሰቡ ምእመናን ካህናቱ ቃለ እግዚአብሔሩን በለሰለሰ ዜማ እያዜሙ ሲያደምቁት መደሰታቸውን በእልልታ ይገልጻሉ:: እንግዲህ ከላይ የተመለከትነውን የሥርዓተ ማሕሌት ሂደት መቼ ተጀመረ? በማን ተጀመረ? አሁን ያለበትን ሁኔታ ለመቃኘት እንሞክራለን::

## 1.2 ታሪካዊ ሁኔታ

ጥንታዊትና ሐዋርያዊት የሆነችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቸርነትና በታታሪ ልጆቿ መንፈሳዊ ትጋት ያካበተችው በርካታ ቁሳዊና መንፈሳዊ ሀብት አላት:: ከእነዚህም ውስጥ የሃይማኖት፣ የታሪክ፣ የፍልስፍና፣ የሥነ ጥበብ፣ የዜማና የግጥም መጻሕፍቷ በግንባር ቀደምነት ተጠቃሽ ናቸው:: ከተጠቀሱት የመንፈሳዊ ሥነ ጽሑፍ ፍሬዎቿ መካከል በግጥምና በሰማያዊ ዜማ የምትከውነው የማሕሌት ሥርዓት ጉልህ የሆነውን ሥፍራ ይይዛል:: ስብሐተ እግዚአብሔር የሚደረስበት፣ ታቦተ ሕግ የሚከብርበት፣ ክብረ ቅዱሳን የሚነገርበት፣ ትምህርተ ሃይማኖት የሚሰበክበት በመሆኑ ትኩረት የሚሰጠው የቤተ ክርስቲያን የዜማ ነው:: ማሕሌት ጥልቀት ያለው የዜማ ትምህርት /ዕውቀት/ ባላቸው ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን፣ ካህናት፣ ዲያቆናትና መዘምራን የሚደርስ በመሆኑ የምእመናንን ትኩረት ይስባል::

የማሕሌት መሠረታዊ መገኛው የቅዱሳን መላእክት የኅብረት ምስጋና ነው:: ቅዱሳን መላእክት ከተፈጠሩበት ዕለት÷ ዕለተ እሑድ÷ ጀምረው በሰማያዊ ዜማ ባለማሰለስ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው:- «ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ÷ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር» በማለት ያመሰግናሉ:: /ኢሳ.6÷3/:: ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስም በራእዩ:- «እንደ ብዙ ውኃ ድምፅና እንደ ታላቅ ነጎድጓድ ድምፅ ያለ ከሰማይ ድምፅን ሰማሁ፤ ደርዳሪዎችም በገና እንደሚደረድሩ ያለ ድምፅ ሰማሁ፤ በዙፋኑም ፊት በአራቱም እንስሶችና በሊቃናቱም ፊት አዲስ ማሕሌት ወይም ቅኔ ዘመሩ:: ከምድርም ከተዋጁት ከመቶ አርባ አራቱ ሺህ በቀር ይህን ማሕሌት ወይም ቅኔ ለመማር ለማንም አልተቻለውም::» ይላል::ራእይ.14÷2-4::

ሐዋርያውያን አበው ነገረ ሃይማኖትን በሚያንጸባርቅ ድርሰታቸው በሃይማኖተ አበው፣ በመጽሐፈ ቅዳሴና ኪዳን የማሕሌትን በቅዱሳን መላእክት ዘንድ መጀመር አጠንክረው ይሰብካሉ:: ለምሳሌ አባ ሕርያቆስ:- «ይህን የማርያምን የምስጋናዋን ቃል እንደ ሰማችሁ የሕፃናትን የምስጋና ቃል ይልቁንም ከጣዕሙ ብዛት የተነሣ አጥንትን የሚያለመልም የቅዱሳን መላእ




©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ክትን ማሕሌት /ምስጋና/ እንደዚሁ ያሰማችሁ::» ይላል:: ቅዳሴ ማር ያም ቁ.154:: ይህ የብርሃናውያን መላእክት ማሕሌት ቅድመ እግዚአብሔር ቀርቦ ተቀባይ እንደ ሆነ ሲያጠይቅ በመጽሐፈ ኪዳን «አድሮ ባቸው የሚኖር ሊቃነ መላእክት ያቀረቡትን ማሕሌት» የሚቀበል በማለት ተጽፏል:: /መጽሐፈ ኪዳን:- ገጽ 41÷6/::

እንግዲህ ከላይ ለመዳሰስ እንደ ሞከርነው ሰማያዊ ማሕሌት በዓለመ መላእክት መጀመሩን በተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችና በሐዋርያውያን አበው በጻፉት መንፈሳዊ ሥነ ጽሑፍ ለመረዳት ይቻላል:: በሥነ ፍጥረት ዓለም ቅዱሳን መላእክትን ተከትሎ ፈጣሪውን ለማመስገን የተፈጠረ የሰው ልጅ ነው::

## «ምድራዊ ዜማ ማኅዘኒ» ከክርስቶስ ልደት በፊት እንዴት ተጀመረ?

ከክርስቶስ ልደት በፊት «ምድራዊ ዜማ፣ ማኅዘኒ» ከትካዜና ከሐዘን ጽናት የተነሣ እንደ ተጀመረ ይነገራል:: ይኸውም ከቅትለተ አቤል ወዲህ ቃየን፣ በስደቱ ኅጆ ሠርቶ፥ ልጅ ወልዶ ሲኖር ግፍ የፈጸመ ሰው ይዋል ይደር እንጂ የእጁን ማግኘቱ አይጠቀርምና ከዘሩ የተወለደ ላሜኅ የሚባል ዐይነ ስውር በወንጭፍ ድንጋይ ቃየንን ይገድለዋል:: /ዘፍ.4÷23/:: ቃየን ከተገደለ በኋላ ከልጅ ልጁ የተወለደ ኢዮቤል በቃየን በደል ምክንያት ከሰው ተገልሎ በምድረ በዳ ይኖር ነበር:: በዚያም መከራ ስለ ጸናበት የቃየንን በደል እያስታወሰ መሰንቆ በመምታት፣ በገና በመደርደር ድምፁን በድምፅ እያሰማ የሐዘን እንጉርጉሮ /ማኅዘኒ/ ያሰማ ነበር:: «እርሱም በገናንና መለከትን ለሚይዙ አባት ነበር» እንዲል:: /ዘፍ.4÷16 - 22/:: /ያሬድና ዜማው ገጽ 4/

ከላይ የተመለከተው የታሪክ ማስታወሻ ዜማ መቼ፥ እንዴት፥ በማን እንደ ተጀመረ ዘመናቱን በትክክል ለይቶ ባይነግረንም ቅሉ ዜማ በዘመኑ መኖሩን ለመረዳት የታሪክ መነሻ ይሆነናል:: ከዚህ አንጻር ዜማ ከሰው ልጆች ሕይወት ጋር የቆየ ትስስር ነበረው ለማለት ያስችላል::

በብሉይ ኪዳን ቅዱስ ዳዊት ከልጅነቱ ጀምሮ በገና በመደርደር ስብሐተ እግዚአብሔር በማድረስ ይታወቃል:: ንጉሥ ሳኦል የሚያሰ ቃየው ቁራኛ በሽታ ሲቀሰቀስበት ዳዊት መዝሙሩን እያሣመረ ሲቀኝለት የተቆራኘው ክፉ መንፈስ ቁራኛው ተወግዶ ጤንነቱ ይስተካከል ነበር:: /1ሳሙ.19÷9/:: ቅዱስ ዳዊት፥ በ4397 ዓመተ ዓለም ሲነግሥ በእግዚአብሔር ቤት በቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት ማሕሌት የሚቆሙ /የሚዘምሩ/ ሌዋውያንን ማደራጀቱ ተጽፏል:: /1ኛዜና.16÷4-7/:: ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ቅዱስ ዳዊት 288 መዘምራን ካህናት ነበሩት:: እነዚህ መዘምራን በአራት አለቆች ይመራሉ:: የአለቆቹ ስሞች፣ አሳፍ፣ ቆሬ፣ ኤማንና ኤዶትም ይባላሉ:: /መዝ.87÷49፤ መዝ.87÷48፤ መዝ.60፤ መዝ.88/:: 288ቱ መዘምራን በየአለቆቻቸው በአራት ተከፍለው በበገና፣ በመሰንቆ፣ በከበሮና በቃጭል ዐሥራ ሁለት ዐሥራ ሁለት እየሆኑ በኻያ አራቱ ጊዜያት /ሰዓታት/ በደብተራ ኦሪት እየተሰበሰቡ በንባብ የሚቀርበውን ምስጋና በንባብ፥ በዜማ የሚዘመረውን በዜማ ይዘምሩ ነበር:: ቅዱስ ዳዊት ዘማሪ በመሆኑ ለፍርድ አደባባይ በማይውልበት ቀን ከመዘምራኑ ጋር በአንድነት በበገና ይዘምር ነበር:: 1ኛዜና.6÷31-44:: ነህምያ 12÷28-47::

ከዚህ አንጻር የብሉይ ኪዳን ሥርዓተ ማሕሌት በንጉሥ ዳዊት ዘመን ሥርዓት ተቀርጾለት መጀመሩን ለማረጋገጥ ይቻላል:: በዳዊት ዘመን ፊር ይያዝ እንጂ ከእርሱ በፊት በሌዋውያን ሥርዓቱ ይከናወን እንደ ነበር ማጤን ተገቢ ነው:: አፈጻጸሙ ከላይ ለመግለጽ እንደ ተሞከረው በበገና፣ በመሰንቆ፣ በጸናጽል፣ በከበሮና በቃል በመታጀብ በንባብ የሚቀርበውን በውርድ ንባብ፥ ለዜማ ተስማሚ የሆነውን በዜማ ይዘምሩት ነበር:: በዚህ ረገድ የዜማ ወይም የማሕሌት ሥርዓት ዕድገት ከፍ እያለ በመምጣቱ አሁን ካለበት ደረጃ ለመድረስ ችሏል::

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*


**በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን**
**በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ**
**ማኅበረ ቅዱሳን**

ባሉት ማከፋፈያዎች የሚከተሉትን መንፈሳዊ አገልግሎቶች ያገኛሉ:-

☞ ሐመር መጽሔት
☞ ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ
☞ ቅዱሳት መጻሕፍት
☞ በቴፕ፣ በቪዲዮ፣ በሲዲና በቪሲዲ የተዘጋጁ የመዝሙርና የስብከት ካሴቶች
☞ የካህናት አልባሳት፣ የመዘምራን ዩኒፎርም እና ሌሎች ንዋያተ ቅድሳት
☞ የተለያዩ ቅዱሳት ሥዕሎች፣ ፖስተሮች፣ ፖስት ካርዶች እና የስጦታ ዕቃዎችን በጅምላም ሆነ በችርቻሮ ያገኛሉ:: ይጎብኙን !!

ቅርንጫፎቻችን:-

| | |
|---|---|
| አዲስ አበባ 22 86 01 /ቅ/ማርያምቅርንጫፍ/ | ሆሳዕና ቅርንጫፍ /06/ 55 17 28 |
| 56 67 88 /ንዋያተ ቅድሳት ማምረቻና ማከፋፈያ/ | ደሴ ቅርንጫፍ /03/ 11 75 45 |
| 13 81 30 /ቅ/ራጉኤል ቅርንጫፍ/ | ወልድያ ቅርንጫፍ /03/ 31 22 57 |
| 56 34 45 /ቅ/ጊዮርጊስ ቅርንጫፍ/ | ጅማ ቅርንጫፍ /07/ 11 86 34 |
| መቀሌ ቅርንጫፍ /04/ 40 97 61 | ናዝሬት ቅርንጫፍ /02/ 12 33 77 |
| ጎንደር ቅርንጫፍ /08/ 20 44 44 | አሰላ ቅርንጫፍ /02/ 31 27 64 |
| ባሕር ዳር ቅርንጫፍ /08/ 11 62 40 | ድሬዳዋ ቅርንጫፍ /05/ 12 04 93 |
| ደ/ማርቆስ ቅርንጫፍ /08/ 71 39 61 | አርባ ምንጭ ቅርንጫፍ /06/ 81 15 97 |
| ፍቼ ቅርንጫፍ 35 11 99 | አዋሳ ቅርንጫፍ /06/ 21 02 87 |
| አሶሳ ቅርንጫፍ /07/ 75 12 22 | ሻሸመኔ ቅርንጫፍ /06/ 10 47 95 |
| ነቀምት ቅርጫፍ /07/ 61 43 22 | |

**የቃሉን ወተት አሁኑኑ ይመገቡ!!**





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «ዘመን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጠው የመኖሪያ ፈቃድ÷ የሥራ መድረክ ነው፡፡»

## «እስመ የአክለክሙ ዘኀለፈ መዋዕል፤ ያለፈው ዘመን ይበቃችኋል፡፡» /፩ጴጥ.፬÷፫/

/መሪጌታ ተስፋ ሚካኤል ታከለ/

ቅዱስ ጴጥሮስ በቃሉ ለሚያምኑ÷ በሞተ እስጢፋኖስ ለተበተኑ ምእመናን ያለፈውን ዘመን መጥፎ ሕይወታቸውን አስወግደው÷ እግዚአብሔር የደላቸውን ዘመን ለመልካም ሥራ አውለው÷ የስሙ ቀዳሾች የመንግሥቱ ወራሾች እንዲሆኑ፡- «የአሕዛብን ፈቃድ የደረጋችሁበት ያለፈ ዘመን ይበቃችኋል» /፩ጴጥ.፬÷፫/ በማለት ጻፈላቸው፡፡

◆ **ምክንያተ ጽሕፈት፡-** ከክርስትና ውጪ በጣዖት አምልኮ የነበሩ ወገኖች ከአሕዛባዊ ሕይወት ተጠርተው÷ እውነተኛውን ቃል ከቅዱሳን ሐዋርያት ተምረው ከማመናቸውም በላይ ያላቸውን ሁሉ ለማኅበረ ምእመናኑ በመስጠት «ስምንት ሺሕ ማኅበረ እስጢፋኖስ» ከሚሰኙት ምእመናን ጋር በእስጢፋኖስ ትምህርት እየተጽናኑ መንፈሳዊ ሕይወት ይዘው ይኖሩ መካሪያቸው÷ አጽናኛቸው ቅዱስ እስጢፋኖስ ግን በሰማዕትነት ዐረፈ፡፡ ግብ.ሐዋ.፮÷፯፡፡

በዚህም ምክንያት ምእመናኑ ተበተኑ፡፡ መበተናቸውም ጥበበ እግዚአብሔር ነበር፡፡ ምክንያቱም ስምንት ሺሕ ማኅበረ እስጢፋኖስ በኅብረት ቢኖሩ ሃይማኖት ባሉበት አካባቢ ይጸናል እንጂ አይሰፋም፡፡ ስለሆነም ሃይማኖት እንዲሰፋ÷ ክሕደት እንዲጠፋ የሚፈልግ እግዚአብሔር ከቅዱሳን ሐዋርያት የተማሩትን ሃይማኖተ ወንጌል በተግባር ለዓለም እንዲገልጡ በዓለም በተናቸው፡፡ እነርሱ ግን «ታጥቦ በጭቃ» እንዲሉ ከተቀደሱ በኋላ ለመርከስ÷ ለሌላው አርአያና ምሳሌ መሆን ሲገባቸው በአሕዛብ ባሕል ተዋጡ፤ አርአያ ክርስትናቸውንም ዘነጉ፡፡

በዚህ ምክንያት ቅዱስ ጴጥሮስ፡ - «ከማመናችሁ በፊት አሕዛባዊ ሥራ ትሠሩበት የነበረው ያለፈው ዘመናችሁ ይበቃል» በማለት ወደፊት ያለ ዘመናቸውን ለጽድቅ ሥራ እንዲጠቀሙበት መከሯቸዋል፡፡ ዘመን ምንድን ነው? ዘመን ማለት አምላካችን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች /ለፍጥረታት/ የሰጠው የመኖሪያ ፈቃድ ነው፡፡ ይልቁንም ዘመን የሰው ልጆች ወጥተው ወርደው መልካም ሥራን በመሥራት ሰማያዊ ህብትን የሚያከማቹበት እግዚአብሔር ያዘጋጀው የሥራ መድረክ ነው፡፡ ማቴ.፮÷፳፡፡ ስለዚህ ቅዱስ ጴጥሮስ የአሕዛብን ሥራ በሠሩበት ባለፈ ዘመናቸው እንዲጸጸቱና እግዚአብሔር ለመልካም ሥራ ያዘጋጀላቸውን አዲሱን ዓመት ክርስቲያናዊ /መልካም ሥራ/ እንዲሠሩበት፡- «የአሕዛብን ፈቃድ የሠራችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃችኋል፡፡» በማለት ጻፈላቸው፡፡

### ◆ የአሕዛብ ፈቃዳቸው ምንድን ነው?

የአሕዛብ ፈቃዳቸው ሥጋን ብቻ ደስ የሚያሰኙ ተግባራትን መፈጸም ነው፡፡ አሕዛብ በተሰጣቸው ዘመን መልካም ሥራ ሠርተው ሰማያዊና ዘለዓለማዊ ድልብ ከማከማቸት ይልቅ ፈራሽ በስባሽ ሥጋቸውን ያለ ልክ በመብላት በመጠጣት ማስደሰትን ይመርጣሉ፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ፡- «የአሕዛብን ፈቃድ የደረጋችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃል» ብሎ የአሕዛብ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ ከቅዱስ ጴጥሮስ ቃል እንደምንረዳው መስከር፣ መዳራት፣ መዝፈን፣ ያለ ልክም መብላት፣ መጠጣት፣ የአሕዛብ ፈቃድ /ሥራ/ መሆኑን ነው፡፡ በአርባና በሰማንያ ቀን ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና የተሰጣችሁ ምእመናን ሆይ÷ ይህ ቃል በቅዱስ ጴጥሮስ ዘመን ለነበሩ ምእመናን ለምክር የተጻፈላቸው ነው፡፡ ኾኖም በቅዱስ ጴጥሮስ የእምነት ምስክርነት ላይ ለተመሠረትንና በቃሉ ለምናምን ምእመናን ሁሉ ለምክርና ለተግሣጽ ይሆነን ዘንድ ተጽፎ ከእኛ ዘመን ደርሷል፡፡ «የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ÷ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ይጠቅማል፡፡» እንዲል፡፡ ፪ጢሞ.፬÷፲፮፡፡ ዛሬም ይህ ቃል በዚህ ዘመን ለምንገኝ ምእመናን፡- «ከመንፈሳዊ ሕይወት ርቃችሁ አሕዛባዊ ሥራን የሠራችሁበት÷ ለአገር፣ ለወገን፣ ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅም ሥራን ለመሥራት ያልተጋችሁበትን ክፉ የኑሮ ልማድ ትታችሁ÷ ከአሕዛባዊ ግብር ርቃችሁ÷ ለአገር፣ ለወገን፣ ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅም ሥራን ለመሥራት ተዘጋጁ፤» ሲለን መሆኑን ልናስተውል ይገባናል፡፡ መልካም ሥራን ይሠራ ዘንድ ግእዛነ አእምሮ የተሰጠውና ዘመናት የሚፈራረቁለት የሰው ልጅ÷ በትሑት ሰብእና በሰከነ ኅሊና ሆኖ፡- «ያለፈው ዘመን ይበቃችኋል» የሚለውን የቅዱስ ጴጥሮስን ቃል ቢመረምረው ሕይወቱን ለማስተካከልና አዲሱን ዘመን÷ ዘመነ ማርቆስን/1998 ዓ.ም/÷ እንዴት ባለ አቀባበል እንደሚቀበለው ከአእምሮው መልስ ለማግኘት አይቸገርም፡፡

ስለዚህ አዲሱን ዘመን ለመቀበል በጉጉት የሚጠባበቅ ምእመን መለስ ብሎ ያሳለፈውን ዘመን መመልከት ይኖርበታል፡፡ «ፈጣሪዬ የሥራ ዘመን ስጥቶኝ ነበር፤ ባለፈው ዘመን ምን ሠራሁ? ሕይወቴስ ምን ይመስል ነበር? በአዲሱ ዘመንስ ምን መሥራት አለብኝ? የወደፊት ሕይወቴስ ምን መምሰል አለበት?» ብሎ መመርመር ይኖርበታል፡፡

### ◆ ራስን እንዴት መመርመር ይቻላል?

ሀ. ከራስ አንጻር፡- ከራስ አንጻር መመርመር ማለት: - «ባለፈው ዓመት እኔ ምን ነበርሁ? ክርስቲያን ወይስ አሕዛብ? እሠራው የነበረ ሥራስ በግብር አሕዛባዊ ወይስ በግብር ክርስቲያናዊ? ንጹሕ ወይስ ዘማዊ? ሌባ ወይስ መጽዋች? ጾማዊ ወይስ ሆድ አምላኩ? ወ.ዘ.ተ ...» ብሎ ራስን መፈተሽ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም ከእግዚአብሔር ጋር በእምነት የሚኖዝ ምእመን ራሱን መመርመር እንዳለበት ሲያስረዳ: - «በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ» /፪ቆሮ.፲፫÷፭/ ብሏል፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስም ራሱን በመመርመሩ ከፈጣሪው እንዳይለይና የተሰጠውን ዘመን ተጠቅሞ በንስሐ ራሱን አስተካክሎ ከፈጣሪው ጋር አዲስ ሕይወትን /ዘመንን/ እንዲኖር አድርጎታል፡፡ የቅዱስ ጴጥሮስ ራሱን የመመርመሩን ታሪክ ስናይ ክርስቶስ ፈቃዱ ሆኖ አይሁድ በያዙት ጊዜ መከራ ከመፍራቱ የተነሣ «ክርስቶስን አላውቀውም» እስከ ማለት ድረስ ነበር፡፡ ነገር ግን «ባለፈ ጊዜ /ከመከራው በፊት/ ከሁሉ ይልቅ እኔ እወደው ነበር፡፡ ከሁሉ አስቀድሜ እኔ ልካደውን?» ብሎ በተሰጠው የንስሐ ዘመን በልቅሶ ፈጣሪውን ጠየቀ፤ «ጴጥሮስም÷ ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ፤ ያለው የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ትዝ አለው፤ ወደ ውጪም ወጥቶ መራራ ልቅሶን አለቀሰ፡፡» ማቴ.፳፮÷፸፭፡፡ ያለፈ ዘመን ሕይወቱን እያሰበ ማዘኑን÷





©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ማልቀሱን የተመለከተ እግዚአብሔርም ቅዱስ ጴጥሮስን ለአዲስ ፍቅር ጠራው፣ እንዲህ ብሎ «አ ስምዖን ወልደ ዮና ታፈቅረኒኑ ፈድፋደ እምእሉ፤ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ÷ ከነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን?» ዮሐ.፳፩÷፲፭:: ቅዱስ ጴጥሮስም ጥፋቱን ከማመን ጋር የወደፊት ዘመኑን ከእርሱ ጋር የሚኖርና የሚወደው፣ የማይክደው መሆኑን ቃል ገብቷል:: «ወአንተ ተአምር ከመ አነ አፈቅረከ፤ እንደምወድህ አንተ ታውቃለህ» /ዮሐ.፳፩÷፲፭/ ብሎ ፍጡር ፈጣሪውን የሚወደው ወዶ፣ ፈቅዶ እንጂ ተገዶ አለመሆኑን ከቃሉ እንማራለን:: አምላካችን እግዚአብሔር «አምላከ ኩርህ»÷ በግድ የሚገዛ አምላክ አይደለምና:: ስለሆነም የሰው ልጅ የውዴታ ግዴታ ቢኖረውም:- የማመን ያለማመን÷ ፈጣሪውን የመውደድ ያለመውደድ÷ ፈጣሪው የሰጠውን ዘመን በአግባቡ የመጠቀም ያለመጠቀም ነጻ ፈቃድ አለው:: በዘመኑ ያልተጠቀመ ይሁዳ በተሰጠው ዘመን ተጠቅሞ ከፈጣሪው ጋር ሳይፋቀር፣ መልካምን ሳይሠራ አሟሟቱ የከፋው በነጻ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ የጊዜ አጠቃቀም ችግር ስለነበረበት ነው:: ያሳለፈው ዘመኑ ትዝ ያለው ቅዱስ ጴጥሮስ ግን በቀደመ ዘመን የነበረበትን ፈጣሪውን የመካድ÷ ሰውን የመፍራት ጉድለቱን አስወግዶ÷ ይፈራ የነበረው ያለምንም ፍርሃት ስለ እምነቱ የሚመሰክር፣ ይክድ የነበረው እርሱ ጠንካራ አማኒ ከመሆን አልፎ በአንድ ቀን ሁለት ሺሕ ሦስት ሺሕ ሰው የሚያሳምን ሆኗል:: 'ዘመኑን ተለወጠ' የምንለው እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ የሰው ልጅ ካለፈ ሕይወቱ ተምሮ የሥነ ልቡና፣ የምግባር ለውጥ፣ የእምነት ጥንካሬ ሲያሳይ ብቻ ነው::

ስለዚህ በቅዱስ ጴጥሮስ የእምነት ምስክርነት መሠረትነት ላይ የተመሠረተ ምእመን ባለፈው ዘመን የሚዘፍን፣ የሚደንስ ከሆነ ለሚመጣው አዲስ ዘመን:- መዘመር፣ ማስቀደስ፤ የማይጾም፣ የማይጸልይ ከሆነ ከእንግዲህ ወዲህ ደግሞ መጸለይ አለብኝ፤ በትምህርቱ ደካማ የነበረው ከእንግዲህ ወዲህ ፈጣሪዬ የሰጠኝን ጊዜ በሚገባ ተጠቅሜ ጥሩ ውጤት ማምጣት አለብኝ፤ ያጨስ ይቅም የነበረም ያጨስኩበት፣ የቃምሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃኛል፤ ንስሐ ገብቼ ለሥጋ ወደሙ መብቃት አለብኝ፤ በማለት ቁርጥ ውሳኔ መወሰን ይኖርበታል::

አዲሱን ዘመን በጉጉት የሚጠባበቅ የሰው ልጅ ከላይ የተዘረዘሩትንና የመሳሰሉትን ነገሮች አስተውሎ ሥነ ልቡናዊ ለውጥ የማያመጣ ከሆነ በዘመኑ መለወጥ ምናልባትም የዕድሜ ጭማሪ አግኝቶ ይሆናል እንጂ ዘመኑ አልተለወጠለትም:: አዲሱ ዘመንም ለእርሱ አሮጌ እንጂ አዲስ አይደለም:: ምክንያቱም ለመንፈሳዊም ሆነ ለሥጋዊ ሕይወቱ አዲስ ነገር አላከለበትምና:: ስለዚህ የዘመኑን መለወጥ ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ ያለፈ ዘመን ስንፍናውን /ክፉ ምግባሩን/ አርቆ መልካም የሆኑ ምግባር መንፈሳዊንና ምግባር ሥጋዊን ለመሥራት አስቀድሞ አእምሮውን ማሳመንና ይህን የተቀደሰ ዓላማ ከግብ ለማድረስ ታላቅ ትጋትና የልብ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልገዋል::

ለ. <u>ከቤተ ሰብእ አንጻር</u>፡- ቤተ ሰብእ ስንል በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ አባላትን ማለታችን ነው:: በዘመናችን በአንዳንድ ቤተሰቦች ውስጥ በእምነት፣ በምግባር መለያየት÷ በሐሳብ አለመግባባት፣ መናናቅ፣ መነታረክ ጐልቶ ይታያል:: ይህ ዓይነቱ ቤተሰብ÷ ክርስቲያናዊ ሕይወቱን እንደሚገባው መምራትና እግዚአብሔርን ማስደሰቱ ቀርቶ የሚኖርባትንም ቤት ጸንታ እንድትቀጥል ለማድረግ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ይደርሳል:: መምህራችን ክርስቶስም መለያየት የሚያመጣውን ችግር ባስተማረበት ትምህርቱ :- «ኩላ መንግሥት እንተ ትትናፈቅ በበይናቲሃ ትማስን ወኩላ ሀገር ወኢመሂ ቤት እንተ ትትናፈቅ በበይናቲሃ ኢትቀውም፤ እርስ በርሷ የምትለያይ መንግሥት ትጠፋለች፤ እርስ በርሷ የምትለያይ ከተማ ወይም ቤትም አትቆምም::» ብሏል:: ማቴ.፲፪፥፳፭:: በክርስቶስ ትምህርት የሚመራ ምእመን መለያየት የሚያመጣውን ችግር ከቃሉ ተገንዝቦ ባለፈው ዘመን የቤተሰቦቼ ሕይወት እንዴት ነበር? ብሎ የቤተሰቦቹን ሕይወት ሊመረምርና የጐደለውን ሊያስተካክል ይገባል:: የሚጠቅም፣ የሚያስደስት ነውን? ብሎ የቤተሰቦቹን ሕይወት ሊመረምርና የጐደለውን ሊያስተካክል ይገባል:: ንጉሥ ሕዝቅያስ: - «ቤትህን አስተካክል» የተባለው ለዚህ ነው:: ከሕገ እግዚአብሔር ወጥተው በዝሙት ባሕር የተዋጡ፣ ሰውን የሚገላምጡ፣ ወደ መናፍቃን ጉባኤ የሚሮጡ፣ ፈሪሃ እግዚአብሔርን ያጡ ልጆች /ቤተሰቦች/ እያሉን:- «እንዲህ ብንላቸው ይከፋቸዋል፤ ከእነርሱም የምናገኘው ሥጋዊ ጥቅም ይቀርብናል» በማለት ያለፈው ዘመን አሕዛባዊ ምግባራቸውን እንዲያስተካክሉ ካላደረግን እንደ ካህኑ ኤሊ በልጆቻችን ከመጠየቅ አንድንም:: ካህኑ ኤሊ ልጆቹ ፈሪሃ እግዚአብሔር አጥተው ከመንፈሳዊ ሕይወት ወጥተው እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ተግባር እየፈጸሙ እያየ ዝም በማለቱ እግዚአብሔርም ተቆጥቶታል፣ አሟሟቱም የከፋ ሁኖአል:: «ከእኔ ይልቅ ልጆችህን ለምን አከበርኽ? እነሆ ለቤትህ ሽማግሌ እንዳይገኝ ክንድህን÷ የአባትህንም ቤት ክንድ የምሰብርበት ጊዜ ይመጣል::» ብሎታል:: ፩ኛሳሙ.፪፥፳፱:: ከዚህ በኋላም «ሙት ይዞ ይሞታል» እንዲሉ በሥነ ምግባራቸው የሞቱ የኤሊ ልጆች የምግባራቸው ብልሹነት የቤተሰቡንም ሕይወት የተመሳቀለ፣ የተናጋ አድርጎታል:: ፩ሳሙ.፬፥፲፪-፳:: ዛሬም በዓለማችን ጎልቶ እየታየ ያለው ችግር ይህ ነው:: ስለዚህ እግዚአብሔርን የሚያመልክ፣ የሚያከብር ምእመን አዲስ ዘመን ሲመጣ ለዘመን መለወጫ የሚሆን የተለያዩ ዘመናዊና የፋሽን ልብሶችን ከመግዛትና ቀይ ዶሮ÷ ዳንግሌ በግ እያለ ከመበደል ይልቅ የቤተሰቦቼ ያለፈ ዘመን ሕይወታቸው ምን ይመስል ነበር? ስለ ሃይማኖታቸው፣ ስለ አገራቸው፣ ስለ ወገናቸው ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል? የሚመጣው አዲስ ዘመን ሕይወታቸውስ ምን መምሰል አለበት? የሚለውን ሊያተኩርበት ይገባል::

ሐ. <u>ከጎረቤት አንጻር</u>፡- ጎረቤት ስንል በምንኖርበት አካባቢ ያለውን ኅብረተሰብ ማለታችን ነው:: ክርስቲያን÷ ስንዴ በእንክርዳድ መካከል እንደሚኖር በሕዝቡም፣ በአሕዛቡም መካከል ይኖራል:: ማቴ.፲፫፥፳፱:: በሕዝቡ መካከል በሚኖርበት ጊዜ ግን እርሱም ሆኑ ቤተሰቦቹ ባለፈው ዓመት ከጎረቤቶቹ ጋር የነበራቸውን ሕይወት ሊያስተውለው ይገባል:: ጎረቤቶቼን አሳዝኛቸው ይሆንን? ወይስ አስደስቻቸው ይሆን? በድለናቸው ይሆንን ወይስ ጠቅመናቸው ይሆን? ወዘተ በማለት ያደረግንላቸውንና ያደረግንባቸውን ለይተን ማወቅ ይኖርብናል፤ በሚቀጥለው ዘመን ለማስተካከል ይረዳናልና:: ክርስቲያን በሌላው መበደሉ ክብር ይሆንለታል እንጅ ሌላውን ማሳዘኑ፣ መበደሉ ኃጢአት ይሆንበታል:: «ሲነቅፏችሁና ሲያሳድዷችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ፤ ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ::» እንዲል ማቴ.5፥11:: ስለዚህ ቃለ እግዚአብሔርን መመሪያው ያደረገ ምእመን ባለፈው ዘመን ከጎረቤቱ ጋር የነበረው መቀራረብ የከፋ ከሆነ ለሚቀጥለው ዘመን መልካምና ለጎረቤቱ አርአያ በሚሆን መልካም ሥራ እርሱም ቤተሰቡም አርአያ እንዲሆን መጣር ይገባዋል:: ይህ ከሆነ እርሱ ከመመስገን አልፎ ፈጣሪውን፣ ሃይማኖቱን፣ ያጠመቀችውን ቤተ ክርስቲያንን ያስመሰግናል:: «መልካም ሥራችሁን አይተው በሰማይ ያለውን የሰማይ አባታችሁን እንዲያከብሩት ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ» ተብለን የታዘዝነውም ለዚህ ነው:: ማቴ.5፥16:: ብርሃን የተባለው መልካም ሥራ መሆኑን ልብ ይሏል:: ቅዱስ ጴጥሮስም:- «ኑሮአችሁ በአሕዛብ መካከል መልካም ይሁን» ማለቱ ኑሯችን ለጐረቤቶቻችን የሚያሳዝን፣




©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የሚያስናክል፣ ፍቅር የሌለበት መሆን የለበትም ሲለን ነው። 1ጴጥ.2፥12። ስለዚህ ባለፈው ዘመን ከጎረቤቶቻችን ጋር ሰላምና ፍቅር ያልነበረን ሁሉ የሚቀጥለው ዘመናችን /በአዲስ ዓመት/ በንስሐ አባቶቻችን አማካይነት ያለፈውን ማሩኝ፣ ይቅር በሉኝ በማለት የወደፊት ሕይወታችንን በፍቅር መቀጠል ይጠበቅብናል። ፍቅር የሌለበት እምነት ከንቱ ነውና። «ተራሮችን እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ።» እንዳለ። 1ኛቆሮ.13፥3።

መ. <u>ከሥራ ባልደረቦች አንጻር:</u> - የሥራ ባልደረቦች በአንድ መሶብ /ማዕድ/ እንደ ሚመገቡ ሰዎች ናቸው። ማንኛውም ሰው ባለፈው ዘመን የማይገባ ሥራ ሠርቼ የሥራ ባልደረቦቼን አስቀይሜ ይሆንን? ወይስ በመጀመሪያ ደካማ ጎኑን እንዲያስተካክል ሳልመክረው በማይገባ ገምግሜ ከሥራው ያፈናቀልኹት ሰው ይኖር ይሆንን? ብሎ ያለፈ ዘመን ሕይወቱን መፈተሽ ይኖርበታል። ማንኛውም ሰው እንደ ነቢዩ ዳንኤል 'የሥራ ባልደረቦች' በሰው ላይ ሰበብ /በደል/ ፈላጊ መሆን የለበትም። «አለቆችና መሳፍንቱ በዳንኤል ላይ ሰበብ ይፈልጉ ነበር» እንዲል። ዳን.6፥4። ይህ ዓይነቱ ምግባር ለአሕዛብ እንጂ ለክርስቲያን ፈጽሞ የማይገባ ተግባር ነው። በሃይማኖት የተመሠረተ ማንኛውም አካል ግን በሰው ሰበብ መፈለግ የለበትም። ይልቁንም ሓላፊነቱን ከመወጣት አንጻር ብቻ ሳይሆን ለሀገር ለወገን ዕድገት በማሰብና ትሩፋት በመሥራት ሰበብ /በደል/ እንዳይገኝበት ሆኖ መገኘት አለበት፣ የእምነት ሰዎች ቅዱሳን ሰበብ /በደል/ ቢፈልግባቸውም አልተገኘባቸውምና። «ዳንኤልም የታመነ ነበርና በእርሱ ላይ ሰበብና በደል ያገኙበት ዘንድ አልቻሉም።» /ዳን.6፥4/ እንዲል።

ስለዚህ በስመ ክርስቶስ የተጠራን ሁላችንም የሥራ ባልደረቦቻችንን ሳናስቀይም አርአያ በመሆን ከጉቦኝነታቸው፥ ሕዝብና መንግሥት የጣለባቸውን የሥራ ሓላፊነት ካለመወጣት /ከሥነ ምግባር ጉድለት/ እንዲላቀቁ መምከር፥ ማስተማር፥ ባይሰሙን ስንኳን ሁለት ሦስት ኋደኛ ይዘን ልንደክምላቸው ይገባል። በሰማይ ዋጋ አለውና። ማቴ.18፥15።

<u>ከአገር አንጻር</u>:- አገር ማለት አብልታ፥ አጠጥታ፥ ንጹሕ አየሯን መግባ ያሳደገች /እናት/ ማለት ናት። የዚህ ሁሉ ባለውለታ የሰው ልጅ፥ እንዲህ አድርጋ ላሳደገችኝ እናት አገሬ ባለፈው ዘመን ምን አደረግኹላት? ወደፊትስ ምን ማድረግ አለብኝ? ብሎ ማሰብና የሚጠበቅበትን ማድረግ ይገባዋል። በተለይም በአሁኑ ሰዓት በአስከፊ ድህነትና ኋላ ቀርነት ተይዛ የድረሱልኝ ድምጿን ለምታሰማን ለአገራችን ኢትዮጵያ አቤት ብለን ከችግርና ከችጋር የምትላቀቅበትን መፍትሔ የምንፈልግበት ጊዜ ነው። ይሁንና በዘመኑ የወለደችን ልጆቿ ግን በተቃራኒው ንጹሕ አየሯን መግባ ደክማ ከችግሬ ያላቀቁኛል ብላ ተስፋ ስትጥልብን «እርሷ ምን አደረገችልኝ፤» ከዚህች ድኻ አገር ማን ባላቀቀንና በተገላገልናት» ሲሉ የሚደመጡ ብዙዎች ናቸው። ይህም ለነገዋ ኢትዮጵያ ዕድገት የተሻለ አስተዋፅዖ ለማድረግ ከሆነ መልካም ነው። ራስን ከመውደድ አገሪቱን ከመጥላት አንጻር ከሆነ ግን በደል መሆኑን ማስተዋል ይኖርብናል፤ የእምነት ሰዎች ለአገር አሳቢዎች ናቸውና። ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት:- «እመሰ ረሳእኩኪ ኢየሩሳሌም ለትርስአኒ የማንየ፤ ኢየሩሳሌም ሆይ፥ ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ» በማለት ላሳደገችው ለኢየሩሳሌም ቃል ኪዳን ገብቷል። መዝ.136፥5።

ስለዚህ አምላከ ዳዊት ብሎ ፈጣሪውን የሚጣራ ምእመንም: - «ለአገር ለወገን ዕድገት ሳናስብና ሳንጨነቅ የተኛንበት ያለፈው ዘመን ይበቃናል። በአዲሱ ዘመን አገራችን ኢትዮጵያ ከችግርና ከችጋር የምትላቀቅበትን ሥራ ለመሥራት ታጥቀን የምንነሣበት፥ ለአገሪቱ ችግር እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መፍትሔ የምንፈልግበት ዘመን ሊሆን ይገባል» ብሎ ከራሱ ጋር ቃል ኪዳን መግባት ይኖርበታል።

ረ. <u>ከቤተ ክርስቲያን አንጻር:</u> - ማንኛውም ምእምን በአርባና በሰማንያ ቀኑ ከተጠመቀ ጊዜ ጀምሮ የቤተ ክርስቲያን ልጅ ነው። ስለሆነም የተጠመቀ ሁሉ «እክሕደከ ሰይጣን በቅድመ ዛቲ እምየ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን» በማለት የቤተ ክርስቲያን ልጅ መሆኑን ዘወትር ይመሰክራል። በዚህ ብቻ የሚያበቃ ግን አይደለም። ቤተ ክርስቲያን ልጇ እንደ መሆኑ መጠን ከእርሱ የምትጠብቀው ነገር አለ። ይኸውም አካሉን ንጹሕ መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ከማቅረብ ጋር ዕጣኑን፣ ዘቢቡን፣ መብራቱን ዓሥራቱን በኩራቱን ወ.ዘ.ተ እንዲያበረክትላት ትፈልጋለች። ይህን ያደርግ ዘንድ ዘመን የተሰጠው ምእመን:- «ቤተ ክርስቲያን ከእኔ ምን ትፈልጋለች? እኔስ ባለፈው ዘመኔ ምን አድርጌያለሁ? በሚመጣውስ ዘመን ምን ማድረግ አለብኝ?» ብሎ ራሱን መፈተሽ አለበት።

በገጠሪቱ የአገራችን ክፍል: - የካህን፣ የመሥዋዕት፣ የንዋያተ ቅድሳት እጦት ከመኖሩ የተነሣ የማይቀድሱ የማይወድሱ አብያተ ክርስቲያናት ብዙ ናቸው። በአካባቢያችን ያሉ አብያተ ክርስቲያናት የተሟሉ መሆናቸውን ብቻ ሳንመለከት የድረሱልኝ ጥሪዋን ለምታሰማን ለእናታችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንደየጸጋችን ማሰብ ይኖርብናል። እነ ቅዱስ ጳውሎስ የተሰጣቸውን ዘመን በሚገባ የተጠቀሙበት ለቤተ ክርስቲያን በማሰብ ነበርና። 2ኛቆሮ.11፥28። «ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው» እንዲል። ከእኛ ከልጆቿ ሌላ የቤተ ክርስቲያንን ጉድለቷን /ችግሯን/ የሚሞላ የለም።

በሌላ በኩል ከቤተ ክርስቲያን አንጻር ስንል የቤተ ክርስቲያን ዓላማ እንደ እናትነቷ ልጆቿ በሥጋም በነፍስም እንዲድኑ ነው። ዋነኛው የማዳኛ መሣሪያዋ /መድኃኒቷ/ ደግሞ ንስሐ ነው። ስለዚህ ባለፈው ዘመን የንስሐ ጥሪዋን ከመስማት አንጻር የነበረንን ድርሻ መለስ ብለን ማስተዋል ይኖርብናል። ቤተ ክርስቲያን እንደ እናትነቷ ልጆቿ ይድኑ ዘንድ በየቅዳሴው፣ በየስብከቱ ዘወትር:- «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» ሳትል ያለፈችበት ጊዜ የለም። የዘመናት ባለቤት እግዚአብሔርም ከዘመን ወደ ዘመን የሚያሸጋግረን ጥሪዋን አክብረን ለንስሐ እንድንበቃ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሲያስረዳ:- «የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱንም ባዕለ ጠግነት ትንቃለህን?» በማለት ግልጽ በሆነ ቃል አስተምሯል። ሮሜ.2፥3። በተሰጠው ጸጋ /ዘመን/ መጠቀም ደግሞ የሰው ልጅ ድርሻ ነው። ስለዚህ የሰው ልጅ ቢያንስ ግዕዛን ከሌሉት ከገብረ ጉንዳን፣ ከዕፀዋት ማነስ የለበትም። ገብረ ጉንዳን ክረምት ከመምጣቱ በፊት የተሰጣትን ዘመን /በጋ/ ተጠቅማ ያለምንም አዛዥ ምግቧን ታዘጋጃለች። በክረምትም አትቸገርም። ዕፀዋትም በጊዜው አለምልመው፣ በጊዜው አብበው፣ በጊዜው አፍርተው ይገኛሉ። የሰው ልጅም የዘመን አጠቃቀምን ከእነርሱ ሊማርና በሥነ ምግባር ሊያለመልም፥ የንስሐ ፍሬን ሊያፈራ ይገባዋል። ዘመናችንን ሳንጠቀምበት ያለ ፍሬ መጠራት ይመጣልና። «ከቅጠልም ብቻ በቀር ምንም አላገኘባትምና:- ለዘለዓለሙ ፍሬ አይገኝብሽ አላት። በለሲቱም ያን ጊዜውን ደረቀች።» እንዲል። ማቴ.፳፩፥፲፱።

የሚመጣውን ዘመን፥ ዘመነ ማርቆስን፥ አሕዛባዊ ምግባራትን አስወግደን፣ ራሳችንን አስተካክለን ለአገር፣ ለወገን፣ ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅም ሥራ የምንሠራበትና ንስሐ ገብተን፣ ሥጋወደሙን ተቀብለን ዘለዓለማዊውን ሕይወት የምንወርስበት ዘመን ያደርግልን ዘንድ የእግዚአብሔር ቸርነት፥ የእመቤታችን አማላጅነት፥ የቅዱሳን ሁሉ ጸሎትና ተራዳኢነት አይለየን። አሜን።



©ማኅበረ ቅዱሳን
www.eotcmk.org

*ውድ አንባብያን ባለፈው ትምህርታችን የግስ ለውጥ ሂደትን በግስ አርእስት መሠረትነት ሕጋውያን አንቀጾች ከሓላፊ /ቀዳማይ/ ወደ ካልአይ /የአሁን እና መጻኢ/ ዘንድ፣ ትእዛዝ እና ንዑስ አንቀጽ እንዴት በዐሥሩ መራሕያን እንደሚረባ ተመልክተናል። ዛሬ ደግሞ የግሶችን ሂደት በሁለተኛው ዐቢይ አንቀጽ በካልአይ አንቀጽ በዝርዝር እንግራለን።*

*መ/ር ደሳለኝ ቀለብ*

2. ካልአይ /ሁለተኛ/ አንቀጽ፡- ይህ አንቀጽ የአሁን /Present/ እና የመጻኢ /Future/ አንቀጾችን የጊዜ ለውጥ ሂደትን ይይዛል። ለዚህም ከአማርኛ የግስ እርባታ ጋር እያገናኘን እንመለከታለን።

## <u>የአማርኛ የግስ እርባታ መንገድ</u>

| ንዑስ አንቀጽ | ሓላፊ /ቀዳማይ/ | ካልአይ | ሣልሳይ | |
|---|---|---|---|---|
| 1. መብላት | በላ | ይበላል | ይብላ | ይበላ ዘንድ |
| 2. መናገር | ተናገረ | ይናገራል | ይናገር | ይናገር ዘንድ |
| 3. መዋሸት | ዋሸ | ይዋሻል | ይዋሽ | ይዋሽ ዘንድ |
| 4. መሞት | ሞተ | ይሞታል | ይሙት | ይሞት ዘንድ |
| 5. መርገጥ | ረገጠ | ይረግጣል | ይርገጥ | ይረገጥ ዘንድ |
| 6. መቀመጥ | ተቀመጥ | ይቀመጣል | ይቀመጥ | ይቀመጥ ዘንድ |
| 7. መሄድ | ሄደ | ይሄዳል | ይሂድ | ይሄድ ዘንድ |
| 8. ማስተባበር | አስተባበረ | ያስተባብራል | ያስተባብር | ያስተባብር ዘንድ |

እዚህ ላይ፡- በላ፣ ተናገረ፣ ዋሸ፣ ሞተ፣ ረገጠ፣ ተቀመጠ፣ ሄደ፣ አስተባበረ ለአማርኛው የሕጋውያን ግሶች /Regular verbs/ ቤት፣ አርእስት ናቸው። ስለሆነም የሚከተሉት ግሶች ቤቶች እነማን እንደ ሆኑ ለመለየት እንሞክራለን።

| ሓላፊ | ቤቱ | ካልአይ | ትእዛዝ/ ዘንድ | ንዑስ አንቀጽ |
|---|---|---|---|---|
| ቀዳ | በላ | ይቀዳል | ይቅዳ/ይቀዳ ዘንድ | መቅዳት |
| ተዋረደ | ተናገረ | ይናገራል | ይናገር/ይናገር ዘንድ | መናገር |
| ዋኘ | ዋኘ | ይዋኛል | ይዋኝ/ይዋኝ ዘንድ | መዋኘት |
| ጮኸ | ሞተ | ይጮኻል | ይጨኽ/ይጮኽ ዘንድ | መጮኽ |
| ወደቀ | ረገጠ | ይወድቃል | ይውደቅ/ይወድቅ ዘንድ | መውደቅ |
| ተከደነ | ተቀመጠ | ይከድናል | ይክደን/ይከድን ዘንድ | መክደን |
| አስተናገደ | አስተባበረ | ያስተባብራል | ያስተባብር/ያስተባብር ዘንድ | ማስተባበር |

## የግእዝ ግስ እርባታ መንገድ

| ሓላፊ | ካልአይ | ትእዛዝ/ ዘንድ | ንዑስ አንቀጽ |
|---|---|---|---|
| ቆመ-ቆመ | ይቀውም-ይቆማል | ይቁም-ይቆም ዘንድ /ይቁም | ቀዊም/ቀዊሞት |
| ሤመ/ሾመ/ | ይሠይም | ይሢም | ሥዩም/ሠይሞት |
| ቀተለ /ገደለ/ | ይቀትል | ይቅትል | ቀቲል/ቀቲሎት |
| ባረከ/ባረከ/ | ይባርክ | ይባርክ | ባርኮ/ባርኮት |
| ደንገፀ/ደነገጠ/ | ይደነግፅ | ይደንግፅ | ደንግፆ /ደንግፆት |
| ማህረከ/ማረከ/ | ይማህርክ | ይማህርክ | ማህርኮ/ማህርኮት |
| ብህለ /አለ/ | ይብህል | ይብሃል | ብሂል/ብሂሎት |
| ገብረ/ሠራ/ይገብር | ይገብር | ይግበር | ገቢር /ገቢሮት |
| ዴገነ/ተከተለ/ | ይዴግን | ይዴግን | ዴግኖ/ዴግኖት |
| ኖለወ/ጠበቀ/ | ይኖሉ | ይኖሉ | ኖልዎ/ኖልዎት |
| ቀደሰ/አመሰገነ | ይቄድስ | ይቀድስ | ቀድሶ/ቀድሶት |

### አንዳንድ የአማርኛውና የግእዙ አርእስት ሂደት ተመሳሳይነት

| <u>ሐላፊ</u> | <u>ትእዛዝ</u> | <u>ሐላፊ</u> | <u>ትእዛዝ</u> |
|---|---|---|---|
| ቆመ | ይቁም | ሞተ | ይሙት |
| ሤመ | ይሢም | ሄደ | ይሂድ |

የሚከተሉት ግሶች እንዴት ወደ ካልአይ ይለወጣሉ። ይህም የሚታወቀው በቤት ነው።

| ሐላፊ | ቤቱ | ካልአይ |
|---|---|---|
| ሞተ | ቆመ | ይመውት |
| ጌሠ | ሤመ | ይገይስ |
| ነጸረ | ቀደሰ | ይኔጽር |
| ተንበለ | ደንገፀ | ይተነብል |

*ይቀጥላል*



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# «የሁሉ ዐይን አንተን ተስፋ ያደርጋል»

## «ያነሥእሙ እግዚአብሔር ለእለ ወድቁ ዐይነ ኵሉ ነፍስ ይሴፎ ኪያከ አንተ ትሁቦሙሲሳዮሙ በበጊዜሁ» /መዝ.144፥15/

እግዚአብሔር በመከራ የተያዙትን ከመከራ ያድናቸዋል። በወርኀ ዘር በገበሬው እጅ በእርሻው የወደቁትን አዝርዕት ዝናምን ጠልን በማውረድ ከወደቁበት ያነሣቸዋል። ልምላሜን፣ አካልን፣ ቅጠልን.... በመስጠት ያስውባቸዋል። የተበታተኑትን ዘሮች በአጫጁ እጅ ይሰበስባቸዋል፤ በአንድ አውድማ፣ አይበት፣ አቆማዳ፣ ሪቅ፣ ጐተራ ያከማቻቸዋል። የሁሉም ሰውነት አንተን ተስፋ ያደርጋል። «በየጊዜው ምግባቸውን ትሰጣቸዋለህና፤ በዘር ጊዜ ዘሩን፥ በመከር ጊዜ መከሩን ትሰጣቸዋለህና» ብለው የሰው ሁሉ ሰውነት አንተን ተስፋ ያደርጋል።

በመግቦ ኩላዊት ያለ ብዑለ ጸጋ እግዚአብሔር ፍጥረትን በዘጠኝ ወራት፦ ሐጋይ፣ መፀውና ጸደይ፥ በሦስት ወራት ክረምት ብርሃናትን አመላልሶ፣ ነፋሳትን አንፍሶ፣ ውኆችን አፍስሶ፣ ፍጥረቱን በፍጥረቱ መግቦ፣ መካነ ፍጥረቱን በሥነ ፍጥረት አስውቦ፣ በሥጋዊ ደማዊ፣ በነባቢ ነፍስ በከበረ ፍጥረት ሁሉ ይመሰገናል። መዝ.150፥6። አነሰና ይብዛ፣ በዝቶአልና ይነስ፣ ረዝሞአልና ይጠር፣ አጥሮአልና ይርዘም፤ ባለማለት በቁርጥ ቃል ማንኛውንም ፍጥረት የፈጠረ እግዚአብሔር፦ «እስከ ዝየ ብጽሒ ወኢትትአጸዊ እምወሰንኪ ዳዕሙ ይከወስ ማዕበልኪ» ብሎ ውቅያኖስን ከከንፈሩ ብቅ፣ ዝቅ እንዳይል አድርጎ ፈጠረ። እጀ ሰፊ ነውና እጁን ዘርግቶ አራቱን ባሕርያት፣ አራቱን አንሥሣት ያጠግባል፥ይመግባል። ሰውን፣ አራዊትን፣ እንስሳትን፣ ነፍሳትን /ራእ.4፥7/ ከሥርዓቱ ያልወጣውን ፍጥረት ፈጣሪው ቸል ሳይለው መፍቅደ ነፍሱን በየጊዜው እየሰጠ ደስ የሚያሰኘው እርሱ ነውና። ባለቤቱም በደገኛው ሕገ ወንጌሉ፦ «ስለዚህ እላችኋለሁ፦ ለነፍሳችሁ በምትበሉትና በምትጠጡት ወይም ስለ ሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ» በማለት በማንኛውም የሰው ፈቃድ እርሱ አሳቢ ሰጪ እንደ ሆነ ነግሮናል። ማቴ.6፥25። እግዚአብሔር በተናገረው ነገር ሁሉ የታመነ ነው። የተናገረውን ነገር አያስቀርም። መዝ.144፥14። ወላዋይ፣ ተጠራጣሪ የሰው ልብ ከሃይማኖቱ ግብ ፈቀቅ በማለቱ የተሰጠውን እያጣ የቀረበለት ጸጋ እንዲዘገይበት ያደርገዋል። «አሳባችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ አድርጉ» ማለት እርሱ ያስብልናል በሉ በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ነግሮናል። /1ጴጥ.5፥7/። የሰው ልጅ ወደዚህ ዓለም በራሱ ፈቃድ ሳይሆን በፈጣሪው ፈቃድ መጥቶአል። በሰውነት ባሕርይውም እጅግ ብዙ የሆኑ ፈቃዳት አሉት። ታድያ ፈቃዱን ዐውቆ የፈጠረው ፈቃዱን ላያሟላለት አልፈጠረውም /አላመጣውም/። የሰው ችኩል ባሕርዩ ወደ አልተፈቀደለት ምኞት ሲገፋው ይኖራል። ከሰው የሚጠበቀው በንጽሐ ጠባይዕ ጸንቶ ፈቃዱን ሁሉ ለፈጣሪው መስጠት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በፊል.4፥6፦ «በምንም በምን አታስቡ። ነገር ግን በየጊዜአቱ ሁሉ ጸልዩ፤ ለምኑ፤ ስትለምኑም ለእግዚአብሔር አንድ ነገር ገልጻችሁ ንገሩት» በማለት በማያሻማ ቃል ነግሮናል። ይኸውም ገልጠን የነገርነው ፈቃድ ሲፈጸምልን ሃይማኖታችን እንዲጸና ነው።

ዓለም ያለ ፕሮግራራም አልተፈጠረም። ዓመታት፣ አውራኀ፣ ሳምንታት፣ ዕለታትና ሰዓታት ያለ ተግባር አይመላለሱም። እያንዳንዷ ቅጽበት /ሰከንድ/ የእርሷ የሆነ ሥራ አላት። ዓመት 12 ወሮች ያሉት ሲሆን እኒህም 12 ወሮች በአራት ክፍል ይከፈልና 3.3 ወራት /90 ቀናት/ ይሆናል። እነዚህም ጸደይ፣ ክረምት፣ መፀው፣ ሐጋይ ይባላሉ። እነዚህ አራቱ ክፍላተ ዘመን በየራሳቸው የሥራ ግሥጋሴ ሲኖራቸው የሚገለገልባቸው በደመ ነፍስና በነባቢት ነፍስ የከበረ ፍጡር ነው።

ከአራቱ ክፍላተ ዘመን አንዱን፥ ወርኀ ክረምትን፥ እንውሰድና እንደ ወርኀ ክረምት ሰማይ በደመናው፣ መሬት በጉተናው ግርማ ሞገስ ያገኙበት፣ ጅረቶች እንደ ቃና ዘገሊላ ጋኖች ወኃ የተሞሉበት፣ ተራራሮች በደን ጉፈሬ የተዋቡበት፣ ሜዳው አረንጓዴ ምንጣፍን ዘርግቶ ተንከባለሉብኝ ያሰኘበት በአጠቃላይ መሬት ሥነ ገጹ ተሟጦ፣ ደም ግባቱ ተጨልጦ፣ ሐመልማል ጠጉሩ ተመላልጦ የታየበት ወቅት ነው። ገበሬው የተበጠረ፣ የተንጠረጠረ ዘር ዘርቶ በየመልኩ ታድሶ የሚበቅልበት፥ እንደ ትንሣኤ ዘጉባኤ የሰው አካል እየአካሉ ከመቃብሩ ብቅ የሚልበት ወርኃ - ትንሣኤ - ዘር ነው።1መቃ.8፥22፤ 3ኛ መቃ.10፥2።


መምህራን ይህን ወቅት ዝናም፣ አፍላግ፣ ነጎድጓድ፣ መብረቅ፣ እጉለ ቋአት፣ ዐይነ ኵሉ፣ ፍሬ ወዘተ በማለት ከፋፍለው ይመድቡታል። ይህንም የሚያደርጉት ፍጥረታት የሚሠለጥኑበትን ጊዜ እያዩ ነው። «ሁሉ ዐይን /ተስፋ/ አንተን ያምናል፣ በአንተ ይታመናል፤ አንተን ተስፋ ያደርጋል» ይላል። ከፍጥረታት ሁሉ በላይ የሆነ ሰው ነው። ከሰማይ በታች ከመሬት በላይ ያለውን ሁሉ ይገዛ፣ ይነዳ ዘንድ ከፈጣሪው ተለግሦአል። የፈጣሪውን ትእዛዝ ጠብቆ፣ ከክፉ ምኞት ርቆ፣ ከጠላቱ /ከሰይጣን/ ወጥመድ ተጠንቅቆ እንዲኖር ሕግ በልቡና በመጽሐፍ ተሰጥቶታል። የፈተና አጻራሽ፣ የመከራ እልፍኝ ሰው መሆኑ ይታወቃል። ሊረታ የማይፈልግ የማይደክም ጽኑዕ ጠላት አለበትና፤ ያ ዕሩቅና ወዱቅ ጠላቱ የሰውን ልጅ የሚፈትነው ግዙፍ በሆነ አካል ዝቅ ሲል በደመ ነፍስ በተፈጠሩ እንስሳት ለምሳሌ፦ እባብ፥ ከፍ ብሎም በነባቢት ነፍስ በከበሩ ሰዎች እያደረ ነው። በራእየ ዮሐንስ 12፥3፦ «እነሆ ታላቅ ቀይ ዘንዶ ሰባት ራሶች እና ዐሥር ቀንዶች ነበሩት። በራሶቹም ላይ ሰባት ዘውዶች ነበሩ። በጅራቱም የሰማይን ከዋክብት ሲሶ እየሳበ ወደ ምድር ጣላቸው» ይላል። ቀይ ዘንዶው ጠላት ሰይጣን፥ ሰባት ራሶች ባለዘውዶች ገዥዎቻችን፥ ቀንድ ሥልጣናቸው፣ ጅራት ዓለምን /ምእመናንን/ የሚያስትበት /የሚጥልበት/ ተንኮሉ ነው። በዚህ ጊዜ የሃይማኖት ሰዎች አብዝተው አጥብቀው ይጸልዩ ዘንድ ታዝዘዋል። መዝ.78፥6-8። የገዥዎች አረመኔነት ሲጠነክር፣ ሰዎች በወገኖቻቸው ላይ በጣም ሲከፉ «ዐይነ ኵሉ ነፍስ ይሴፎ 'ኪያከ» እንደ ተባለው ወደ እግዚአብሔር በጽኑዕ ተስፋ መቅረብ ነው። መዝ.26፥10።

መቼም ዓለም የማታስተናግደው አምባገነን፣ የማታበቅለው ኃጢአት ፣የማታመርተው ወንጀል የላትም። ሆኖም የሰላም ተስፋ የሚገኘው ከእግዚአብሔር ብቻ ነው። በሰላም ስም ጦርነት፣ በነጻነት /በስምምነት/ ስም ብጥብጥ፣ በእንወዳችኋላን ስም ጥላቻ፣ በአንድነት መፈክር ስም የመለያየት /መከፋፈል/ የዓለም ገጸ በረከት ሆኖአል። በተለይም በዚህ መጨረሻ ዘመን በምንገኝ ትውልድ ላይ የመከራ ቋያ /ነበልባል/ ሲፋፋም ይታያል። ሰው ለሰው የማሰብ ተስፋው ጨልሟል። በተለይ ሕዝበ ክርስቲያኑ በማንኛውም ፈተና ተስፋ ሳይቆርጥ፣ ፍርሃትን አስወግዶ፣ የመለያየት ኮረብታን ንዶ፣ የጥላቻን አጥር ተራምዶ፣ ሁሉም ነገር የማይሣነው እግዚአብሔርን መማፀን ይኖርበታል። በየዘመናቱ የሰው ጠላት ሰይጣን እያነሣሣቸው በሰው ልጅ የመከራ ዶፍ ያዘንሙ የነበሩ አረመኔ ወንበዴዎችን እግዚአብሔር በጽኑዕ ሥልጣኑ በሚያስደንቅ ኃይሉ ያደቃቸው እንደነበር ቅዱስ መጽሐፍን ማገላበጥ ያስፈልጋል። ፍርሃትም የሃይማኖት ጉድለት በመሆኑ ከምንፈራው ነገር ነጻ አያወጣንም፤ መፍራት፥ መፈራት የሚገባውን እግዚአብሔርን ነው። ከሁሉም የሚከፋው ተስፋ መቁረጥ፣ ከእምነት ራእይ ወደ ኋላ ማፈግፈግ የመሳሰሉት ጉድለቶች ናቸው። «የሰው ሁሉ ተስፋ ወደ እርሱ ነው፤ እሱን ተስፋ ያደርጋል፤ የተጠቁትንም እግዚአብሔር ያስነሣቸዋል» ተብሎአልና። መዝ.144፥16።

የኢትዮጵያን ሕዝብ ጸሎት እግዚአብሔር ይስማ። አሜን።

መ/ር ደጉ ዓለም ካሣ
ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ
የሐዲስ ኪዳን መምህር

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



መንፈሳዊ መጻሕፍትን ያንብቡ!!
አናቅጸ ሲኦል
አዘጋጅ መምህር ብርሃኑ ጎበና
420 ጥያቄዎችና መልሶቻቸው
አዘጋጅ:- ዲ/ን ቢላ መገርሣ
ያንብቡም እራስዎንና
ቤተሰብዎንም
ከመናፍቃን
ይጠብቁ!!
ትምህርተ ሃይማኖትና
ክርስቲያናዊ ሕይወት
ወደ ምስራቅ ተመልከቱ!!
አዲስ የስብከት ቪዲዮ ካሴት
መጻሕፍቱንና ካሴቱን
በሁሉም የሐመር
መጽሔትና
ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ
ማከፋፈያዎች ውስጥ
ያገኟቸዋል።
ዜና መጻሕፍት
የዲያብሎስ ውጊያዎች
አዘጋጅ:- አቡነ ሺኖዳ
ትርጉም:- አያሌው ዘኢየሱስ
የተሰፋ ሕይወት
አዘጋጅ:- አቡነ ሺኖዳ
ትርጉም:- አያሌው ዘኢየሱስ
እናታችን ጽዮን
አዘጋጅ:- ያዕቆብ ሰንደቁ
መጻሕፍቱን በሁሉም የሐመር መጽሔትና ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ማከፋፈያዎች ውስጥ ያገኟቸዋል!
ወይም 09-63 63 93 ☎ 20 04 38 ይደውሉ E-mail: yakobzz@yahoo.com P.O. Box 12437 ይጻፉ
ዋጋ ብር 3.50
ሜጋ ማተሚያ ድርጅት

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፣እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡